## የመጽሐፍ ስጦታ

ከ________________________

ለ________________________

ይህን መጽሐፍ ለማከፋፈል የምትፈልጉ ጌልገላ መንፈሳዊ መዝሙር ቤት ወይም

በስልክ ቁጥር

0111 11 30 06
0111 55 97 16
ሞባይል 0911 60 80 54 ይጠይቁ።

# ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ

*የ፲፱ ጥንታውያን ገዳማት*
*እና*
*አድባራት ታሪክ*

## ክፍል ፩

በ
**ዘመድኩን በቀለ**

የካቲት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የመጀመሪያው ዕትም የካቲት 1992 ዓ. ም.

ሁለተኛው ዕትም የካቲት 1993 ዓ. ም.

ሦስተኛው ዕትም ታኅሣሥ 1995 ዓ. ም.

አራተኛው ዕትም ታኅሣሥ 2000 ዓ. ም.

## ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ በእኔ አእምሮ የማይሆነውን እንዲሆን አድርጐ ስፈጸመልኝ እና ሁሉን ሳደረገልኝ ስልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

፩/ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰባኬ ወንጌል እና የቅኔ መምህር የሆኑት ንቡረዕድ ክፍለ ዮሐንስ ሙሉ ጊዜያቸውን በመስጠት ጽሑፌን በማረም እና በማስተካከል ስረዱኝ መንፈሳዊ አባቴ።

፪/ ስመጽሐፉ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ስኅትመት እስኪቀርብ ድረስ የእጅ ጽሑፌን ወደ ኮምፒዩተር በመስወጥ በአጠቃላይ ሬዲዮስ በማድረግ ከብዙ የገንዘብ ወጪ ሳዳነችኝ ስመንፈሳዊ እኅቴ ስወ/ት ፍቅርተ ገ/ሕይወት ( ፍቅርተ ሥሳሴ ) ።

፫/ ይህ መጽሐፍ በጥራት እንዲወጣ ሳደረጉልኝ እና በኅትመቱ ሥራ መልካም ትብብር ሳደረጉልኝ ስአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ሠራተኞች በሙሉ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባስሁ።

እግዚአብሔር ብድሩን በመንግሥተ ሰማያት ይክፈልልኝ አሜን።

## መታሰቢያነቷ

ለሰ ለንዱት ሃይማኖታቸው ሲሉ ሙሉ ሕይወታቸውን በመሰጠት በእግዚሰብሔር ፈቃደ በየገዳማቱና በየዋሻው ሆነው ለቤተክርስቲያን አንድነት ለሀገር ለወገን ለሳምና ደህንነት ለሚጸልዩ ለባቶች ትሁንልኝ::


© ዘመድኩን በቀለ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

all Rights Riserved in law


## ማ ሳ ሰ ቢ ያ

*ይህን መጽሐፍ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በእንግሊዝኛ እና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ለሰተርጉሚ ለሰንባብያን የማቀርብ መሆኔን ለመግለጽ እወዳለሁ::*

© ዘመድኩን በቀለ

# ማውጫ

## አርእስት


| | ገጽ |
|---|---|
| መቅደም | ፩ |
| መግቢያ | ፲፫ |
| የዮዲት ጉዲት ታሪክ | ፲፮ |
| እንጦጦና አዲስ ለበባ | ፴ |
| እንጣጦ ማርያም | ፴፫ |
| እንጦጦና ራጉኤል | ፴፮ |


## ወሎ


| | |
|---|---|
| ግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም | ፶፩ |
| ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም | ፶፱ |
| የቅዱስ ላልይበላ ታሪክ | ፷ |
| ቤተ መድኃኔ ዓለም | ፷፮ |
| ቤተ ማርያም | ፷፱ |
| ቤተ መስቀል | ፸፮ |
| ቤተ ደናግል | ፸፰ |
| ቤተ ደብረ ሲና | ፹ |
| ቤተ ጉልጉታ | ፹፫ |
| ቤተ ሚካኤል | ፹፭ |
| የሥላሴ ቤተ መቅደስ | ፹፮ |
| የአዳም መካነ መቃብር | ፹፱ |
| ቤተ ለማኑኤል | ፺ |

ቤተ መርቆርዮስ ........................................ ፸፫
ቤተአባ ሊባኖስ ........................................ ፹፬
ቤተልሔም ........................................ ፺፩
ቤተ ገብርኤል ወሩፋኤል ........................................ ፺፫
ቤተ ጊዮርጊስ ........................................ ፺፮
ገነተ ማርያም ........................................ ፻፲፩
ነአኩቶ ለአብ ........................................ ፻፲፫
አሸተን ማርያም ........................................ ፻፲፯
ብልባላ ጊዮርጊስ ........................................ ፻፳፪
ይምርሐነ ክርስቶስ ........................................ ፻፳፮


## ትግራይ


አብርሀ ወአጽብሐ ........................................ ፻፴፩
ሚካኤል ዐብይ ዓዲ ........................................ ፻፴፬
ደብረ ማርያም ቆርቆር ........................................ ፻፴፮
አቡነ ይምዓታ ........................................ ፻፴፱
ደብረ ጽዮን አቡነ አብርሀም ........................................ ፻፵፩
ደብረ ዳሞ ........................................ ፻፵፬
አባ ጰንጠሌዎን ........................................ ፻፵፮
ማኅበረ ዶጌ ........................................ ፻፵፱
አክሱም ጽዮን ........................................ ፻፶፪


## ጐንደር


ዙር አምባ ........................................ ፪፻፬
ዋሻ እንድርያስ ........................................ ፪፻፲
ወይን ዋሻ ተ/ሃይማኖት ........................................ ፪፻፲፪


## የጣና ሐይቅ ገዳማት


የጣና ሐይቅ ........................................ ፪፻፲፫
ደብረ ማርያም ........................................ ፪፻፲፯
ክብራን ገብርኤል ........................................ ፪፻፲፱
ብራ ኪዳነምሕረት ........................................ ፪፻፳፪
መሀል ዘጌ ጊዮርጊስ ........................................ ፪፻፳፭
አቡነ በትረ ማርያም ........................................ ፪፻፳፰
ኢዝዋ ማርያም ........................................ ፪፻፴፪
ደጋ እስጢፋኖስ ........................................ ፪፻፴፬
ይጋንዳ ተ/ሃይማኖት ........................................ ፪፻፴፮
ናርጋ ሥላሴ ........................................ ፪፻፴፰
ደብረ ሲና ማርያም ........................................ ፪፻፵
ማንዳባ መድኃኔ ዓለም ........................................ ፪፻፵፫
ጣና ቂርቆስ ........................................ ፪፻፵፮
ክርስቶስ ሠምራ ገዳም ........................................ ፪፻፶
ረማ መድኃኔ ዓለም ........................................ ፪፻፶፪


## ጐጃም


መርጦ ለማርያም ........................................ ፪፻፶፬
ደብረ ወርቅ ማርያም........................................ ፪፻፶፱

## ልዩ ምስጋና

ይህ አራተኛው ዕትም ታትሞ ለምዕመናን እንዲዳረስ ያደረጉት አሁን በሀገረ አሜሪካን የሚገኙት እና ሐዋርያዊ አገልግሎት በመስጠት ቅድስት አናት ቤተክርስትያንን በማገልገል ላይ የሚገኙት አንደበተ ርቱዑ ሰባኬ ወንጌል አባ ወልደ ትንሳኤ አያልነህ አና የመንፈስ ልጆቻቸው ናቸው:: አናም እኔም በኢትዮጵያዊው የጨዋነት ደንብ አራሴን ዝቅ በማድረግ እግዚአብሔር ይስጥልኝ አላለሁ:: ባላችሁበት በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ድንግል ትጠብቃችሁ::

ወስብሀት ለእግዚአብሔር



# **መቅድም**

መቅድም ማለት እንደ እኔ አገላለጽ ለአንድ መጽሐፍ እንደ በረኛ ( ዘበኛ ) ሆኖ የሚያገለግልና በውስጠኛው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ ስላለው አጠቃላይ ይዘት የምንረዳበት ሥፍራ ነው:: የአንድን መጽሐፍ መቅድም ሳያነቡ ሌላውን ጽሑፍ ወደ ውስጥ ዘልቆ ማንበብ በራሱ ዘበኛን ሳያናግሩ ወደማያውቁት ግቢ ወይም አዳራሽ እንደ መግባት ያለ ነው:: በመቅድም ላይ ብዙ ነገር ይገለጻል:: ከመጽሐፉ ርዕስ አንስቶ ተራ በተራ በመጽሐፉ ውስጥ እስከሚገኙ አጠቃላይ ሁኔታዎች በሙሉ ይገለጻሉ:: እኔም ከመጽሐፉ ርዕስ አነሳና በአጠቃላይ ለማለት የምፈልገውን ሁሉ በዚሁ ቦታ ላይ እንደሚከተለው አቀርባለሁ::

የመጽሐፉን ርዕስ « <u>ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ</u> » የሚል ስያሜ ነው የሰጠሁት:: <u>መካን</u> ማለት የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ቦታ / ሥፍራ / ማለት ነው:: ለዚህ <u>ቦታ ( ሥፍራ )</u> ላልነው ቃል በዚህ መጽሐፍ ርዕስ መሠረት ለማለት ወይም ለመግለጽ የተፈለገው እነዚህ « ቦታዎች » የተለዩ ( የተቀደሱ ) መሆናቸውን ነው:: እነዚህ ቅዱሳን መካናት ደግሞ ቅድስናን ያገኙት «<u>ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት</u>» እንዲሉ በዕለተ ዓርብ ጌታ ሲሰቀል ዑራኤል መልአክ በብርሃን ጽዋ ክቡር ደሙን ተቀብሎ በብርሃን መነሳንስ በዓለም ላይ ረጨው:: በዚያን ጊዜ የደሙ ነጠብጣብ ያረፈበት ሥፍራ ሁሉ ቤተክርስቲያን እንደተሠራበት የቤተክርስቲያን መምህራንና

ቅዱሳት መጻሕፍቶቻችን ያስረዱን እና እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትውፊት መሠረት ያስተማሩን እውነታ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር ናት፡፡ ይህች ሀገር ምሥራቃዊት ፣ የገነት ነፋስ የሚነፍስባት መዓዛ ቅዱሳን የሆነች ምድር ናት፡፡ ኢትዮጵያ በእምነታቸው ጽኑዓን ሆነው በተጋድሎአቸው ብዛት ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ፍጹምነት የተነሳ ቅዱስ የተሰኙ አባቶችን ያፈራች ቅድስት ሀገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ የእነ ንግሥት ሳባ ፣ ቀደማዊ ምኒሊክ ፣ አብርሀ ወአጽብሐ ፣ ቅዱስ ላልይበላ ( ላሊበላ ) ፣ ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት፣ የእነ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ እና ቅዱስ ያሬድ የመሳሰሉት ሀገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ ከአብራኳ የተገኙ ልጆቿ ብቻ ሳይሆኑ ከውጪ ዓለም የመጡ መንፈሳውያን ጥምር በክብር ላይ ክብርን የተቀበሉባት፣ ቅዱሳንም የተሰኙባት ሀገር ናት፡፡ ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ከግብጽ ደቡብ ከቆላው አገር ከንኂሳ፣ ተስዓቱ ቅዱሳን ከሶሪያና ከታናሽ እስያ መጥተው በቅድስና የታወቁባት ምድር ናት፡፡ እነዚህ ቅዱሳን በሀገራችን በኢትዮጵያ በተለያዩ ክፍለ ሀገሮችና ከሀገራችን ውጪም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በሚገኙበት ክፍለ ዓለማት ሁሉ መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ በስማቸው



ቤተክርስቲያን ታንጾላቸው ጽላትም ተቀርጾላቸው ለዘላለም ስማቸው ሲጠራ ይኖራል፡፡

ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት መጀመሪያ በሕገ ልቦና በመቀጠልም በሕገ ኦሪት እግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረች ሀገር መሆኗ የሚታወቅ ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ ደግሞ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ ፲፣፱ ላይ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ የተናገረችው ኃይለ ቃል እራሱ በቂ ምሥክር ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያ የሚለው ቃልም በብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ይህም በእግዚአብሔር በማመኗ የተሰጣት ክብር ነው፡፡

ኢትዮጵያ በሐዲስ ኪዳንም ቢሆን ሌሎች ዓለማት ክርስቶስን ሳያውቁት ክርስትናንም ሳይቀበሉ ጌታ ሳያስተምርባት ሐዋርያትም ሳይሰብኩባት የማንኛውም ቅዱስ ደምም ሳይፈስባት ወልድ ዋህድ ብላ በማመን ክርስትናን የተቀበለች ቀዳማዊት ሀገር ናት፡፡ እንዲያውም ጌታ « **ሳያዩኝ የሚያምኑኝ ብፁዓን ናቸው** » የሚለው አምላካዊ ቃል የተፈጸመባት ሀገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ በዙሪያዋ ያሉ አጎራባች ሀገሮች የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ምክንያት <u>**የክርስቲያን ደሴት**</u> በመባልም ትታወቃለች፡፡ በኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የነበሩ አበው የኦሪትን ሥርዓት እየፈጸሙ የብሉይ ኪዳንን እምነት ከሥርዓተ አምልኮቱና ከማዕረገ ክህነቱ ጋር ጠንቅቀው በማወቅ ኢትዮጵያ በአንድ አምላክ የምታምን ሀገር መሆኗን በማስተማር

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፱፻፹፪ ዓመተ ዓለም እስከ ፴፬ ዓመተ ምሕረት ድረስ ቆይተዋል። በ፴፬ ዓመተ ምሕረት በኢትዮጵያዊው ጀንደረባ አማካኝነት የክርስትና እምነት ከሥርዓተ ጥምቀቱ እና ከወንጌል ትምህርቱ ጋር ወደ ሀገራችን ገብቶ ነበር። ነገር ግን በወቅቱ በኢትዮጵያ ጳጳስ ባለመኖሩ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሳይፈጸም እስከ ፫፻፴፬ ዓ.ም ድረስ ቆይቶ ነበር። በኋላ ላይ ግን በ፫፻፴፬ ዓ.ም በኢትዮጵያ ነግሦ በነበረው በኢዛና ዘመነ መንግሥት በጢሮሳዊው ፍሬምናጦስ አማካኝነት በንጉሡ መልካም ፈቃድ ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ ተልኮ ከሃያኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ከቅዱስ አትናቲዎስ ዘንድ ማዕረገ ጵጵስናን ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል።

ጳጳሱ ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሰ የክርስትናን እምነት በመላ ሀገሪቱ በመስበክ ቀሪዎቹን ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን፣ ሥርዓተ ቁርባንንና ሌሎችንም ምስጢራት በሚገባ እያስተማረ ሥርዓተ ቤተክርስቲያናት እንዲፈጸሙ አድርጓል። ከዚያን ግዜ ጀምሮም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ክርስትና ሆነ። በተለይ በዚሁ ዘመን በጳጳሱ ፍሬምናጦስ አማካኝነት ምኵራባት ወደ ቤተክርስቲያንነት ተለወጡ። የጳጳሱም ስም ከሳቴ ብርሃን ሰላማ ተባለ። ለምሳሌ በትግራይ የምትገኘዋ የአክሱም ጽዮን ፣ አሁን በጣና ውስጥ የሚገኘው የቅዱስ ቂርቆስ ገዳም ፣ ጉጃም የምትገኘዋ የመርጡ ለማርያም ገዳም ፣ የመሳሰሉት በሙሉ ሥርዓተ ኦሪት



ይፈጽምባቸው የነበሩ ሥፍራዎች እንደነበሩ እስከ ዛሬ ድረስ በየገዳማቱ የሚገኙት ጽሑፋዊ መረጃዎችና በዓይን የሚታዩት የኦሪት ሥርዓት መፈጸሚያ ቁሳቁሶች በቂ ምሥክሮች ናቸው።

በኢትዮጵያ ክርስትና ከተሰበከበት ዘመን አንስቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለክርስትና እምነት መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት በኢትዮጵያ ነግሠው የነበሩ ነገሥታትም ናቸው። ነገሥታቱ ከልጅነታቸው ጀምሮ ከፊደል ገበታ እስከ ቅኔና ድጓ ፣ ጾመ ድጓ ድረስ በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት በመከታተል ስለሚያድጉ ቤተክርስቲያንን እና ክርስትናን በሚገባ ያውቁ ነበር። አንዳንዶቹም ዓለምን በመናቅ መንግሥታቸውን ለሌላ በማውረስ ወደ ምናኔ በመግባት እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ገዳማዊ በመሆን የዘላለም ሕይወትን መውረሳቸውን ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍቶቻችን ያስተምሩናል ሐቅ ነው። እናም ነገሥታቱ ክርስትናውን በመስበክ ረገድ ከማንም በላይ ሐዋርያዊ ሥራን ፈጽመዋል። ከዚህም በላይ ደግሞ የአምልኮ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው አብያተ ክርስቲያናትን አንጸዋል።

ለምሳሌ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነግሠው የነበሩት ወንድማማቾቹ የአክሱም ነገሥታት አብርሀ እና አጽብሐ ታላቁንና በወርቅ ተለብጦ ተሠርቶ የነበረውን እና በዮዲት ጉዲት የፈረሰውን የአክሱም ጽዮንን ቤተክርስቲያን እና በተጨማሪም በትግራይ ውስጥ የሚገኙ ከቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍለው የተሠሩ

ስብዮተ ክርስቲያናትን በማነጽ፤ አፄ ካሌብ አብያተ ክርስቲያናትን ከማነጽ ባሻገር በዐረቡ ዓለም ይገኙ ለነበሩ ክርስቲያኖች እየደረሰባቸው ከነበረው አደጋ በመታደግ፤ አፄ ላሊበላ እስከዛሬ ድረስ የዓለምን ሕዝብ አስደንቀው የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ፤ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ቋንቋ በማስተርጐም ለክርስትናውም ሆነ ለሥነጽሑፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ እነዚህን እንደ ምሳሌ አድርገን አነሳናቸው እንጂ ሌሎቹም ነገሥታት በዘመናቸው ብዙ ክርስትናውን የሚመለከት ሥራ ሠርተው አልፈዋል፡፡

ታዲያ አሁን እንዲህ አምሯ እና ጸንታ መላውን ዓለም በማስደነቅ ላይ የምትገኘዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ይህን ያህል ረጅም ዘመን ተጉዛ አሁን ካለንበት ዘመን የደረሰችው ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ ብዙ ከባድና አስቸጋሪ የፈተና ጊዜዎችን በማሳለፍ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ እንዲያውም ለማስታወስ ያህል፡፡

በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን **<u>ዮዲት ጉዲት</u>** ፣ ፲፮ኛው ክፍለ ዘመንም **<u>ግራኝ መሐመድ</u>** በቤተክርስቲያን ላይ ያደረሱት ጉዳት እስከ ዛሬ ድረስ ጠባሳው ያልሻረ ከባድ ጥፋት ነው በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ጥለው ያለፉት፡፡ ከዚህም በኋላ **<u>በአፄ ሱስንዮስ</u>** ዘመነ መንግሥት የካቶሊክ ሃይማኖትን ለማስፋፋት በሚል ሰበብ ንጉሡን በማሳሳት ካቶሊካውያኑ በፈጠሩት



ስሕተት በወቅቱ ለወጣው « **<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ትፍረስ የሮም ካቶሊክ ትንገሥ</u>** » ለሚለው አዋጅ እንገዛም ያሉ የብዙ ሺህ ኦርቶዶክሳውያን ደም ፈሶ ነበር፡፡ እንዲያውም ጐንደር ውስጥ **<u>ደንቀዝ</u>** በተባለ ቦታ ብቻ በአንድ ቀን የስምንት ሺህ ንፁሕ ካህናትና ምዕመናን ደም ነው በከንቱ የፈሰሰው፡፡ ከዚያም በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቷ ቀላል የማይባሉ ፈተናዎችን በማሳለፍ ነው አሁን ያለንበት ዘመን የደረሰችው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ግን ሐዋርያዊ ጉዞዋን አላቋረጠችም፡፡ በአሁኑ ጊዜም በሀገር ውስጥ [illegible] አህጉረ ስብከት ሲኖራት በውጭ ሀገርም በኢየሩሳሌም፣ በካሪቢያን ሀገሮች ፣በላቲን አሜሪካ ፣በካናዳ ፣በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ ፣በአፍሪካ እና በሌሎች ክፍለ ዓለማት አህጉረ ስብከቶች አሏት ፡፡

ቤተክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ ስላሏት ምዕመናኖች ብዛት ለማወቅ ባደረግኩት ጥናት መሠረት ሁለት መረጃዎችን አግኝቻለሁ፡፡ ከቤተክህነት ያገኘሁት አንድ የጽሑፍ መረጃ [illegible] ሚሊዮን ያህል ምዕመናን እንዳሏት የሚጠቁም ሲሆን ከዚህ ሌላም በ[illegible] ዓ.ም. በሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ በኩል ተዘጋጅቶ የቀረበው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ሆነው በሰበካ ጉባኤው የተመዘገቡ ምዕመናን ቁጥር [illegible] ሚሊዮን [illegible] እንደሆነ ነው የሰበካ ጉባኤው ስታትስቲካዊው መረጃ የሚቀጥመው በሌላ በኩል ደግሞ በ[illegible] ዓ.ም በኢትዮጵያ

በተደረገው የሕዝብ እና የቤት ቆጠራ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባስሥልጣን መረጃ ደግሞ ፷፮ ሚሊዮን ፯፻፶፯፻፲ ፲፻፰ እንደሆነ ነው የሚጠቀመው፡፡ በሴሳ በኩል ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. የተሾሙትን ሊቃነ ጳጳሳት ጨምሮ ከ፴ በላይ ሊቃነ ጳጳሳት ያሏት ሲሆን ፩፻፵ አገልጋይ ካህናት ፴፪ የሰበካ ጉባኤ አብያተ ክርስትያናትም አሉዋት፡፡

በተለይ በመዲናችን በአዲስ አበባ ብቻ ከ፳፩ በላይ አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸው እራሱ የቤተክርስቲያኒቱ ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ ምን ያህል እድገት እያሳየ መምጣቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ነገር ግን አዲሶቹን አብያተ ክርስትያናትን በማነጽ ላይ መሆናችን የሚያበረታታና የሚያስመሰግን ቢሆንም በዚህ መሀል ግን ቤተክርስቲያኒቱ ካሏት ከ፯፳፱ በላይ የኢጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ከ፩፻ በላይ የሚሆኑት ጥንታውያን ገዳማት ናቸው፡፡ እነዚህ ጥንታዊያን ገዳማት ደግሞ በአሁኑ ወቅት በውስጣቸው ካቀፉአቸው አገልጋዮችና ቅርሶች ጋር ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው ነው፡፡ ገዳማቱ ባለፉት ሺህ ዘመናት ውስጥ ብዙ መንፈሳውያን አባቶች የጸለዩባቸው እና መንፈሳዊ ተጋድሎን የፈጸሙባቸውም ናቸው፡፡ እንዲያውም እነዚህ ገዳማት የትላንቱን ታሪክ ዛሬ ላይ ላስን ትውልዶች መረጃ በመስጠት ረገድ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡

ለምሳሌ በሥርዓተ ኦሪት የነበሩት አባቶች ይጠቀሙባቸው የነበሩ ንዋያተ ቅድሳት ፣ የመጀመሪያው የከሳቴ ብርሃን ሰላማ



ትርጉም የሆነው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ፣ የቅዱስ ያሬድ ከሐር የተሠራ ካባው ፣ የመጀመሪያው በእጁ የጻፈው የድጓ መጽሐፍ፣ **በጣና ቂርቆስ ገዳም**፤ የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ከሰማይ የወረደላት ጽዋ ፣ አክሊል ፣ በሕይወት ዘመኗ ከእጇ የማይለየው በትረ መስቀሏ፣ በዓይን የሚታየው እስከሬኗ፣ **በፎገራ ደብረ ጓንጉት ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ገዳም** ፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በረድነታቸው ወቅት ይጠቀሙበት የነበረ የድንጋይ ወፍጮ፣ የወፕ ማማስያ እስከ ድስቱ **በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም** ፤ የቤተክርስቲያን ጠላት የነበረው የግራኝ መሐመድ የክብር ካባ በክፋት ታሪክነቱ እንኳን **በመርጡ ለማርያም**፤ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቀኝ እጁ ያረፈበት ግማደ መስቀል **በግሸን ደብረ ከርቤ** እና በሌሎቹ ገዳማትና አድባራት ውስጥ የሚገኙ ቅርሶች በቂ ምሥክሮች ናቸው፡፡

ነገር ግን እነዚህን እና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያልጠቀስኳቸው የቤተክርስቲያን ቅርሶች በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነው የሚገኙት፡፡ በጥቂቱም ቢሆን በውስጠኛው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ የአንዳንዶቹን ገዳማት ቅርሶች በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚገኙ ለመግለጽ ሞክሬያለሁ ፡፡

ታዲያ እኔ ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ ምንአስባትም ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ የቤተክርስቲያን ልጆች በግልም ይሁን በህብረት

አቅማቸው የፈቀደውን ሥራ ሠርተው እንዲያስፉ ለመጠቀምም ሞክሬአለሁ።

ይህ መጽሐፌ ቁጥር አንድ ሲሆን ከዚህ በኋላ በተከታታይ በማሳትማቸው መጻሕፍቶቼ ውስጥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያልተከተቱትን ደብረ ሊባኖስን ፣ ዝቋላ አቦን ፣ አሰቦት ሥላሴን ፣ ዋልድባን፣ ኮምቶ ሥላሴን ፣ኢቲሳ ተክለሃይማኖትን፣ ምድረከብድ አቦን ወ.ዘ.ተ በሙሉ እግዚአብሔር እንደፈቀደ አዘጋጅቼ የማቀርብ መሆኔን ለገልጽ እወዳለሁ። ይህም ማለት መጽሐፉ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለመግለጽም ጭምር ነው።

በሌላ በኩል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉት ታሪኮች በሙሉ ከዮዲት ጉዲት ታሪክ እንስቶ አጠቃላይ የአብያተ ክርስቲያነናቱ ታሪኮች በሙሉ ዋቢ የተጠቀስባቸው ናቸው። በተለይ የዮዲት ጉዲት ታሪክ አብዛኛዎቻችን ከምናውቀው ታሪክ ለየት ያለ በመሆኑ የዚህች ሴት ታሪክ ከተጻፈበት መጽሐፍ ከአክሱም ክብረ ነገሥት ከግእዝ ወደ ዐማርኛ ተገልብጦ ከተጻፈው መጽሐፍ የተገኘ ሙሉ ታሪክ ስለሆነ ይህን ዋቢ ያደረግኩትን መጽሐፍ ማንበቡ ይበልጥ ይጠቅማል ባይ ነኝ። የዚህችን ሴት ታሪክም አስቀድሞ እንዲቀርብ የተፈለገበት ዋናው ምክንያቲ በአብዛኛው እስከ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የነበሩ አስደናቂ ቤተመቅደሶች በሙሉ ማለት ይቻላል በዚህች አደገኛ ሴት ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው። በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙት አብዛኛዎቹ ገዳማት በጉዳም



ከምትገኘው የመርጦ ለማርያም ገዳም እንስቶ እስከ ታሳቂ አክሱም ጽዮን ድረስ ሄደን ያየን እንደሆነ የፈረሱ ህንጻ ቤተክርስቲያናትን ፣ የወደቁ ሐውልቶችን የተቃጠሉ እና ጉዳት የደረሰባቸውን ንዋየ ቅድሳትን በምናይ ጊዜ ምን ሆነው ነው? ብለን ከህናቱን ለምንጠይቀው ጥያቄ የሚሰጠን መልስ በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሳይ በተነሳችው በዮዲት ጉዲት አማካኝነት እንደወደሙ ነው የሚያስረዱን። ታዲያ እንባቢ ይህች ሴት ማን እንደሆነች በምን ምክንያት ተነስታ ይህንን ሁሉ ጥፋት ልታደርስ እንደቻለች ጥያቄ ማንሳቱ አይቀርም። በዚሁ ምክንያት እኔም በየገዳማቱ ብዙ የታሪክ መዛግብትን ተመልክቻለሁ። ሆኖም ግን የዚህችን ሴት ሙሉ ታሪክ ሳላገኝ ከቆየሁ በኋላ ይህን ጉዳይ ለዶ/ር ቀኝ. ሰሎሞን አበበ አማከርኳቸው። እሳቸውም ከሌሎቹ መጻሕፍት በተሻለ መልኩ የተጻፈ ነው ብለው ይህን በመቀጠል የምታነቡትን የዮዲትን ሙሉ ታሪክ የተጻፈበትን መጽሐፍ ሰጡኝ። እኔም ታሪኩ ለምጽፈው መጽሐፍ ይጠቅመኛል ብዬ ስለአመንኩኝ ሳልጨምር ሳልቀንስ እንዳለ አቅርቤዋለሁ። ሌላው በሳሊበላ ገዳማት ላይም መጠነኛ የሆነ የትርጉም ሥራ እና የራሴም ምልከታ የታከለበት ነው።

በመጨረሻም ለመግለጽ የምፈልገው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉት ገዳማት ታሪኮች በሙሉ እነዚህ ብቻ ናቸው ፤ በቃ ከዚህ ሌላ ገዳሙ ወይም ደብሩ ቀሪ ታሪክ የለውም፤ ማለት ሳይሆን ገዳማቱን ለሚጐበኝ እና የገዳማቱን ታሪክ ማወቅ

ስሚፈልግ ሰው መሪ ሆኖ ከገዳማቱና አድባራቱ ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ሆኖ የሚጠቅም መጽሐፍ እንጂ የገዳማቱን አጠቃላይ ታሪክ የያዘ አይደለም::

በተረፈ ይህን መጽሐፍ የምታነቡ በሙሉ የጎደለውን አሟልታችሁ የጠመመውን አቅንታችሁ ስሕተት ነው የምትሉትን በቀና ልቦና አርማችሁ እንድታነቡት በትህትና እየጠየኩኝ ለምትሰጡኝ አስተያየት በመሳቁ. 21938 ወይም በስልክ ቁጥር

0911 608054

0111 113006

0111 559716

ብትደውሉልኝ ለቀጣዩ ሥራዬ ደረዳኛል ብዬ አምናለሁ::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር::

አዘጋጅ ዘመድኩን በቀለ



## መግቢያ

መጽሐፍን ያህል ትልቅ ነገር መጻፍ ይቅርና እንድያው ለወዳጅ ዘመድ እንኳን የምንጽፋትን ደብዳቤ አቀናብሮ ቃላትን መርጦ መጻፍ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ሁላችንም የምናውቀው ሐቅ ነው:: እኔ ይህንን ስለገዳማት ታሪክ የያዘውን መጽሐፌን ስመጻፍ ሳስብ እንዲህ ፍጻሜ አግኝቶ ለአንባብያን ይቀርባል የሚል ፍጹም እምነት አልነበረኝም:: ከዕለታት በአንደኛው ቀን ግን እንዲህ ሆነ:: ወሩን ባላስታውሰውም በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በዕለተ እሁድ ከቀኑ በአምስት ሰዓት ሳይ መርካቶ በሚገኘው ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ በየ፲፭ ቀኑ ይሰጥ የነበረውን መንፈሳዊ ትምህርት ለመከታተል ወደ እዚህ ቅዱስ ሥፍራ ማስታወሻዬንና መቅረጸ ድምጼን ይዤ ሔድኩኝ:: ከስብከተ ወንጌሉ በፊት የሚሰጡት መዝሙሮች ቀረቡ:: መዘምራኑም መዝሙሮቻቸውን አቅርበው እንደረጨረሱ የዕለቱ መምህር ወደ መድረኩ ቀረበና ትምህርቱን መስጠት ጀመረ:: በዕለቱ ትምህርት ትንቢተ ነህምያ ምዕራፍ አንድን በሚገባ አስተማረ:: ስለ እየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ፣ ስለ ኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት፣ በጥንት ዘመን እና በአሁኑ ዘመን ስላላቸው ይዞታ፣ ኢትዮጵያ ስላሏት ገዳማትና አድባራት አስደናቂነትና አሁን ግን እየደረሰባቸው ስላለው ዘረፋ ብዙ ችግሮች ሳግ በተናነቀው ድምጽ አስተማረና በመጨረሻም በተለይ ወጣቱ ትውልድ የኦርቶዶክሳዊነቱንና የኢትዮጵያዊነቱ አሻራ

የሆኑትን እነዚህን ገዳማትና አድባራት እንዲመለከታቸውና ለችግራቸውም አስቸኳይ መፍትሔ ይሰጣቸው ዘንድ ስመናን ባዘለ የማሳሰቢያ ቃል ጥሪ አደረገ ዲ.ዳንኤል ክብረት።

እኔም ከስብከቱ ኃይል የተነሳ በውስጤ ሳልሞት እነዚህን የተባሉትን ቅዱሳን ገዳማት በመጐብኘት የአባቶቼን ድንቅ ሥራ ዓይቼ በረከትንም መቀበል እንዳለብኝ ወስኜ በዚሁ ዓመተ ምሕረት የልደትን በዓል ለማክበር ወደ ቅዱስ ላልይበላ ሂጄ ወደ ፲፮ የሚጠጉ ገዳማትን ዓይቼ ተመለስኩ። ነገር ግን ከሐይቅ እስጢፋኖስ ፣ ከገነተማርያም፣ ነአኩቶ ለአብ አብያተ ክርስቲያናት በስተቀር የሌሎቹን ገዳማት ታሪክ አብራርቶ የሚነግረኝ በማጣቴ ምክንያት ሳልችገር አልቀረሁም። ይህ ደግሞ በአብዛኛው በተለይ በገጠር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚታይ ችግር ነው። በዚህ ጉዞዬ ላይ በመጠኑም ቢሆን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካቶ የምታገኙትን ስለ ቅዱስ ላልይበላ ታሪክ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን የቅዱስ ላልይበላ ገዳም ጉብኝት አስመልክቶ የተጻፈ ጽሑፍ አንድ መንፈሳዊ አባት በዚያው በደብረ ሮሀ ያሉ ታሪኩን እንድገለብጠው ለስሰጡኝ፣ እሱንና በዓይኔ ለሳአየሁት የዚህን ጉዞዬን አጠቃላይ ይዘት በጽሑፍ በማቀነባበር በቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን መድረክ ላይ ለምዕመናን አነበብኩላቸው። ይህን የሰሙ ምዕመናንም ያነበብኩትን ጽሑፍ አባዝቼ እንድሰጣቸው አጥብቀው ይጠይቁኝ ነበር። እኔም ቀይ ሌሎችንም ገዳማት ጨምሬ ይሻላል አያልኩ



ብዙ ጊዜ ቆየሁ። በቆይታ ጊዜዬም ውስጥ በእግዚአብሔር ፍቃድ በተመሠረተው የኢያቄም ወሐና መንፈሳዊ የጉዞ ማኅበር አማካኝነት በወሎ፣ በትግራይ፣ በጐንደር፣ በጐጃም፣ በጣና ሐይቅ ላይ የሚገኙ ገዳማትን ሸዋን ጨምሮ ከሁሉም ክፍለ ሀገሮች በከፊል ከአንድም ሦስት ጊዜ እየደጋገምኩ የማየት እድሉ አጋጠመኝ። በዚህም ወቅት በደረስኩበት ገዳም ሁሉ ስለ ገዳሙ የተጻፉትን ጽሑፎች በመሰብሰብ፣ በመቅረጸ ድምጽም ከአበው ቃላቸውን በመቅረጽ፣ መረጃዎቼንና ለጽሑፌ ይጠቅሙኛል ያልኳቸውን በሙሉ ከያሉበት ሰበሰብ፣ በሥነ ጽሑፍና በታሪክ እውቀት ያላቸውንም ሳማክር ብዙ ቆየሁኝ እና በመጨረሻ ላይ እጄ ላይ ያለውን የእጅ ጽሑፌን በኮምፒዩተር በማጻፍ ለኅትመት በማዘጋጀት በእግዚአብሔር ቸርነት በድንግል ማርያም ምልጃና ጸሎት ለዚህ በቅቶልኛል።

**እግዚአብሔር ይመስገን አሜን።**

**አዘጋጅ፡- ዘመድኩን በቀለ**

## ዮዲት ( ጉዲት )

ዮዲት በአባቷ የአክሱም ንጉሥ የውድም አስፈሬ ልጅ ስትሆን በእናቷ በዓድዋ አውራጃ የሐሐይስ ወረዳ ተወላጅ ናት:: በልጅነቷ አባቷና እናትዋ ሰለ ሞቱባት ልጓሰ ማውታ ሁና ካንድ ዘመድ ወደ አንድ ዘመድ እየተዘዋወረች ስታድግ የ፲፮ ዓመት ልጃገረድ በሆነች ጊዜ በተወለደችበት ሀገር ከሀብታም ተቀጥራ ሰመቀመጥ ስለ አሳፈራት ከዚህ ዘወር ብዬ ወደ አባቴ ሀገር አክሱም ሔጄ ታቦተ ጽዮንን ተማፅኜ እቀመጣለሁ ብላ ወደ አክሱም ሒዳ ሠርታ የምትኖርበትን የሀብታም ቤት ስትፈልግ በጣም የማረችና የተዋበች እንደ ፀሐይ የምታበራ ቆንጆ ስለነበረች ሕዝብ ቊንጅናዋን እየተመለከተ አንድ ነገር አሳት እንጂ ከሀብታም ተቀጥራ ሠርታ ለትቀመጥ የመጣች ምንም አትመስልም እያለ ይመልሳታል:: እርሷም በዚህ ምክንያት ተስንክላ ከአክሱም ጽዮን ደጅ ሰላም ተቀምጣ ወይም ወድቃ ታቦተ ጽዮንን ተማፀነች:: ሕዝቡ ሲገባ ሲወጣ መልኳን እየተመለከተ በቊንጅናዋ እየተደነቀ ብቻ ምንም ሳይጥልላት አልፎአት ሲኼድ አንድ የ፳፪ ዓመት ጉልማሳ ዲያቆን ለተልእኮ ወደ አክሱም ቤተ ክርስቲያን ሲገባ አትኩሮ ባያት ጊዜ በልቡ ተመኛት::

ከዚህ በኋላ ለአመክንዮ ምክንያት ለኃጢአት እንዳለው ዳዊት በዝሙት ሰለ ተነደፈ ለቸርነት አስመስሎ ከቤቱ እህል ውኃ እያመጣ ይሰጣት ጀመር:: እንዲህ እያደረገ ሲረዳት አንድ ቀን



በሩካቢ እንዲያውቃት በግልፅ ቢጠይቃት ፊት ነስታ አዋርዳ መለሰችው:: እርሱም ሲሰጣት የነበረውን እህል ውኃ ብከለከላት ጊዜ በረኃብ ተጎዳች:: ርኃብ ክፉ ነውና ያስለመዳትን እህል ውኃ እንዲሰግሳት ዲያቆኑን ለመነችው :: እርሱም ሰፈቃደ ስጋው ሲል እንደ ልማዱ የተሰናዳ ምግብ እያመጣ ሲሰጣት ቀይቶ ዝሙት ለመፈፀም ለመናት:: እርሷም በቁጣ ተነስታ ምንም አጥቼ እዚህ ብወድቅ በአባቴ የአክሱም ነገስታት ዘር ነኝ ለምን አንተ አንድ ተራ ዲያቆን እኔን ለመድፈር አሰብህ ብላ በኃይለ ቃል ብትገሥፀው ዲያቆኑ በሐፀ ዝሙት ሰለተነደፈ « **እምነ መንግሥት የዓቢ ክህነት** » ይላል መጽሐፉ ሲል መለሰላትና ምግቡንም እንዲነሣት ቁርጥ ነገራት:: ዮዲትም በዚህ በደረሰባት ችግርና ፈተና አያዘነች እየተከዘች እንግዲያስ የነገስታት ዘር ሁኜ በከንቱ ከምትደፍረኝ ለነገስታት ልጆች የሚገባ ወርቅ ጫማ አጫምተህ አለመህ ውሰደኝ አለችው:: እርሱም ፍላጐቱ ሞልቶለት እሺ ብሎ እግሯን ለክቶ ፈጥኖ ኼዶ አክሱም ቤተክርስቲያን ውስጥ ገብቶ አብርሀ ወአጽብሐ ነገሥት የሰጡትን ወርቅ መጋረጃ በእግሯ ልክ ለክቶ በስለት አዙሮ ቀዶ ማዘቢያውን ወርቅ አስናድቶ አምጥቶ አጫምቶ ሌላውንም አልማት አለም በስውር ወደ ቤቱ ወሰዳት:: ወዲያውም አረከሳት:: ( ወርቅ መጋረጃ ያለው ወርቅ ምንፃፍ ነው የሚሉ አሉ::)

በነገታው ለብሐተ ነግህ የሚቆሙ ካህናት መጥተው ገበዘ አክሱም ቤተክርስቲያን ውስጥ ገብተው ወርቅ መጋረጃውን

ቢመስከቱ በሰው እግር ልክ ከሁለት ተቀድዶ ባየት ጊዜ ደንግጠው ለብሐተ ነግሁን ትተው ደውል ( መረዋሕ ) ደውለው ሕዝቡን ሰብስበው አሳዩት። ወዲያው በንጉሥ ድግናዝን ትዕዛዝ አንድ ሰው ሳይቀር በገበዘ አክሱም አደባባይ ተሰብስቦ እያንዳንዱ ሲመረመርና እግሩ ሲለካ የዮዲት ጉዲት እግር ልክ ሆኖ ተገኘ። በዚህ ተገዳ ከንጉሡ ፊት ቀርባ ብትመረመር ከሳይ የገለፅነውን ሁሉ ተንትና ባስረዳቻቸው ጊዜ ዲያቆኑን ጠቁሚ ተብላ በአሽከር ተይዛ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል እየዞረች አስተውላ ስትመለከት ይኸ ነው ብላ ዲያቆኑን አስያዘችው። ዲያቆኑም ከፍርድ ዳኞች ቀርቦ ሲጠየቅ ዮዲት የተናገረችውን ሁሉ አመነ። በተናገሩት ይረቱ ፣ በሳሉት ሰይፍ ይመቱ እንዲሉ ባመነው ቃል ሲቀጣ ሲገባው ካህናተ አይሁድ ሰቅሉ ሰቅሉ ብለው ለቄሣር አመልክተው ኃጢአት የሌለውን በአፉ ያልበደለውን በእጁ ያልገደለውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስቅለው ነፍስ ገዳዩን ባርባንን ከሞት ቅጣት እንዳዳኑት የአክሱም ካህናት ሐጢአት የፈፀመው የእነሱ ልጅ የኾነው ዲያቆን ( የ፲፪ ) የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ ስለ ሆነ ሕፃን ነውና ሲቀጣ አይገባውም። እንዲያውም ያሳሳተችውና ወርቅ መጋረጃ ቀድዳ ጫማ ያደረገች ዘማ ዮዲትን ቅጣስን ብለው በንጉሥ ድግናዝን ላይ ጮሁበት።

ንጉሡም ዲያቆኑ የ፳፪ ዓመት ወጣት መሆኑን እያየ ያመነውን ኃጢአት እያወቀ ጲላጦስ በከመ ሕግከሙ ኰንንዎ ብሎ ጌታን ገርፎ አሳልፎ ለካህናተ አይሁድ እንደ ሰጠው ዮዲትን



አስገርፎ እንደታያችሁ ፍረዱባት ብሎ አሳልፎ ለካህናቱ ሰጣት። ካህናቱም በፍርድ አንጉ ተቀምጠው።

፩ኛ. ሁለቱ ጡቶቿን ትቆረጥ

፪ኛ. ከኢትዮጵያ ትባረር።

ብለው ፈረዱባት ከዚህ በኋላ ዕድለ ቢስ ዮዲት ከንጉሡ ፊት ቀርባ ቋንጃ ቆራጭ ቀርቦ ለብሷን ገፎ ሁለት ጡቶቿን በሰይፍ ቆረጣትና በደምዋ እየታጠበች በሰቃይ ወደቀች።

ከዚያ ወዲህ ወደ ገበዘ አክሱም ቤተክርስቲያን ማንም ሴት እንዳትገባ በውግዘትና በአዋጅ ለሰፀና እስከ ዘላለም ሕግ ሆኖ ቀረ።

መከረኛይቱ ቀን የፈረሰባት በደል የፀናባት ፍርድ የጉደሰባት ግፍ የደረሰባት ዮዲትን እንደገና የንጉሡ አሽከሮች አየገፉ እያጣደፉ ከአክሱም አውጥተው እንደከብት እየነዱ ከኢትዮጵያ ድንበር አሳልፈው ግብጽ በረኻ ጥለው ለአራዊት ሰጥተዋት መጡ።

ዮዲትም « **ወሰኩኒ ዲበ ጸልዕየ ቍስለ** » እንዳለው ከመከራዋ በላይ ቀን ዋዕየ ፀሐየ፣ ሌሊት በብርድና በውርጭ እየተሰቃየች በለቅሶ ስትኖር አምላክ ነደያን ወተሰፋ ቅቡጻን እግዚአብሔር አንድ ግብጻዊ እንዲጉበኛት አደረገ ግብጻዊው ሰውዬም ዮዲትን በአስከፊ ሰቃይ ስትሰቃይና እንደበቷ በውኃ ጥማት በምግብ እጦት ደርቆ አገኛት። ወዲያው ከየት መጣሽ ብሎ በአረብኛ ቋንቋ አሳዝኖ ጠየቃት።

ዮዲትም ከላይ እንደተገለፀው የደረሰባትን ግፍ በመሉ አያንዳንዱን ዘርዝራ በዓረብኛ ቋንቋ ነገረችው ግብጻዊው ሰውየም በዚህ አያዘነ ዮዲትን አቅፎ ደግፎ አያዘገመ ወስዶ ለግብጽ ንጉሥ አስረከበው።

ንጉሡም በ ፱ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው የአክሱም ንጉሥ አርማህ ዳዊት ከግብጽ ለመጡለት እስላሞች ያደረገላቸውን ችሮታና ውለታ በማሰብ ዮዲትን በርኅራኄ ተቀብሎ የደረሰባትን መከራ ተመልክቶ ሲደነግፅ ወዲያው ዮዲት እንባዋን እያፈሰሰች የአክሱም ካህናት ያደረሱባትን ጥካኔ የግፍ ሰቃይ አንድ ባንድ ነገረችው። እርሱም በጣም አዘነና ሐኪሞች አስመጥቶ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ እያሳከመ አዳናት።

መልኳን ቅላቷን ቁንጅናዋ ሁሉ በቤተ መንግሥቱ ከሚቀመጡ ወይዛዝርት በላይ ሆኖ በማየቱ በእልፍኙ ውስጥ ዓመት ያህል በጥሩ እንክብካቤ ካስቀመጣት በኋላ በሚስትነት እንዲያገባት ለመናት። እርሷም ወደ ኢትዮጵያ አብረን ሄደን የአክሱምን ንጉሥ ወግተህ አሸንፈህ ካህናቱን ካላጠፋህልኝ አታገባኝም ብላ መለሰችለት። እርሱም የኢትዮጵያን ንጉሥ መውጋት የማይቻለው መሆኑን ተገንዝቦ ቀን እንጠብቅ እንጂ ዛሬ አይቻልም አላትና ሳያገባት ተጠብቃ ስትኖር ከሀገሬ ኢትዮጵያ በግፍ አስወጥቶ ያባረራት የአክሱም ንጉሥ ድግናዣን የግዛቱን ሰፋት አያለሁ ብሎ ሠራዊቱን አስከትቶ ከአክሱም ተነስቶ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አዜብ ወደ ተባለው ሲጓዝ ሀገሩን ሁሉ አልፎ



አሸዋ የበዛበት ዋዕይ ፀሐይ የፀናበት ነፋስ የማይነፍስበት አህል ውኃ ፈፅሞ የማይገኝበት ወባና ንዳድ ያለበት አልም ያለ ቆላ ቦታ ደረሰ።

በዚህ ጊዜ በፀሐይ ቃጠሎ በአሸዋ ተውጦ በወባና በንዳድ በረኃብና በጥማት አንድ ሳይተርፍ ከሠራዊቱ ጋር ጠፍቶ ቀረ።

ጥፋቱ በሁሉ ለለ ተሰማ አክሱም ላይ መንግሥቱን እንደራሴ አድርጉ የተወው ልጁ ግዳዣን ነገሠ። እርሱም ፲ ወር እንደ ነገሠ ታሞ ሞተ። ወዲያውም የ፲፮ ዓመት ልጁ አንበሳ ውድምን መሳፍንቱ መኳንንቱ አንግሰው በአባቱ ዙፋን አስቀመጡት ። አባቱ ንጉሥንም በአክሱም መቃብረ ነገሥት ቀበሩት።

በቀለኛይቱም ዮዲት የድግናዣንን ሞትና ሕፃኑ አንበሳ ውድም መንገሡን አረጋግጣ ሰምታ በተረዳች ጊዜ ንጉሡን እንዲዘምት ገፋፋችው። እርሱም ሰራዊቱን ሰብስቦ መሣሪያውን አስይዞ እርሷ ዮዲት እየመራች ቀይ ባህርን ተሻግረው በአዱሊስ አድርገው መሻሎኪያ በሚባል በር ዘልቀው ወደ አክሱም ስትመራቸው መምጣትዋ በአክሱም ለለ ተሰማ የአክሱም ካህናት መጻሕፍቶቻቸውን ንዋየ ቅድሳታቸውን ታቦተ ጽዮንን ታቦተ ማርያምን ይዘው ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሸሽተው ዝዋይ ደሴት ገብተው ተሸሸጉ፡

ግማሾቹም ካህናት ብዙ የቤተክርስቲያን ቅርስና አንቲካ ወርቅና ዕንቁ የእብ፡ ሐኪም በዕንቁና ወርቅ አልማዝ በብዙ

ኅብረ መልክዕ የተሠራ ዙፋን ዕንቁ ፅዋዕና ሞብርሌ የቤተ መንግሥት ሽልማት የፈረስና የበቅሎ ሙሉ ወርቅ፣ መጣብር ወርቅ፣ ስንደቅ ዓላማ፣ ወርቅ ነጋሪት ወርቅ ከበሮ፣ ወርቅ ጸናጽል ብዙ ወርቅ መቋሚያ ፤ ወርቅ ዳታን ፤ ወርቅ መነሳንስ ይዘው ጣና ደሴት ገብተው ተቀመጡ::

መሳፍንቱ መኳንንቱም ዮዲትን ወግተው ለመመለስ የሰራዊቷንና የመሳሪያዋን ብዛት አስቀድመው በዜና ስለ ሰሙና ስለ ፈሩ ሕፃኑ ንጉሥ አንበሳ ውደምን ይዘው ወደ መንዝ መጥተው በዙሪያው ባለ ተራራና ዋሻ ውስጥ ገብተው ተቀመጡ:: ዮዲትም ሰተት ብላ አክሱም ከተማ ገብታ ከሸሸት የተረፉ ሽማግሎችና ደካሞች አካለስንኩሎችን ሕሙማን ካሕናት ሁሉ በአመጣቻቸው አለሳም አጅ በሰይፍ አስፈጃቻቸው::

በዚሁ ቀጥላ አብርሃ ወአጽብሐ ነገሥት በወርቅና በዕንቁ በከበረ አብነ በረድ ያሠሩት አሥራ ሁለት ቤተ መቅደስ ያለው የአክሱም ማርያም ቤተክርስቲያንን ለማፍረስና በእሳት ለማቃጠል የማይቻሳት ቢሆን የምታቃጥልበትን መንገድ ለማግኘት ከሰሜን አውራጃ ጌዳዎን የተባለውን ብረት ቀጥቃጭ አስጠርታ አመጣችውና ጉዳዩን አማከረችው:: እርሱም ቤተክርስቲያኑ የሚቃጠልበትን ምክር ከመከራት በኋላ ጓዙንና መሳሪያውን ብረት ቀጥቃጩን ሁሉ ለማምጣት ተመልሶ ሀገሩ ሄደ:: ከዚያ ወናፍና መዶሻውን መሠርሰሪያ ብረቱን በየዓይነቱ ብረታብረት ይዞ ወደ አክሱም መጣ::



ዮዲትም እርሱ እንደመከራት ከየሀገሩ ፍልጥ ዕንጨትና ደረቅ ጥፍጥፍ ኩበት በአጋሰስና በአህያ ፣ በሰው ጉልበት እያስጫነች በአዋጅ አክሱም ሰይ አስበሰበች::

በብረት ቀጥቃጩ ጌዳዎን ምክር በቤተክርስትያኑ ውስጥ ፍልጥ ዕንጨትና ኩበቱ እየተደረደረ እስከ ጣራው ሞላ:: መልሶ እንዲሁ በውጩ ፍልጥ ዕንጨትና ኩበት እየተዛነቀ በዙሪያው ሁሉ ከሥሩ ጀምሮ እስከ ወርቅ ጉልላቱ እየተደረደረ ተሸፈነ:: ከዚያ ጌዳዎን እንዳዘዛቸው ብረት ቀጥቃጮቹ ወናፍታቸውንና መሳሪያ ብረታቸውን መቆስቆሻ ረዥም ብረት እሳትን ይዘው መጥተው መጀመሪያ በውስጡ በአራቱ መዓዘን እሳት ለኮሱበትና አራት አራት ሆነው በአሥራ ሁለቱ ቤተ መቅደስ በአራቱ መዓዘን ወናፍት እየነፉ እሳቱን በዚሁም ላይ ነፋሱ ሲነፍስበት እሳቱ እየተብላላ ሲጋጋም ዝግባውና ጥዱ እየተቀጣጠለ፣ አብነ በረዱ እየተፈረካከሰ ተቀጣጠለ:: እንደገና ከዚያ ወጥተው በውጩ በየአራት መአዘኑ እሳት ለኩሰው ወናፍት ሲነፋበት እሳቱ እየተፈረካከሰ ፣ ወርቁና ዕንቁ እንደ ሠም እየቀለጠ፤ እየፈሰሰ ፤ ግንቡ እየፈራረሰ ፤ በየዓመቱ የሚዘንበው የክረምት ዝናብ እሳቱን ሳያጠፋው ሁለት ዓመት ተመንፈቅ እየነደደ ቆየ:: የቀለጠው ወርቅና ዕንቁም እንደ ጉርፍ እየጐረፈ እስከ ማኸል ከተማው ደርሶ በየአለበት እንደ ድንጋይ ሆነ:: ቤተክርስቲያኑም ከሰልና ሐመድ ሆነ:: በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያና በሌላ ዓለማት ሳሉ ክርስቲያኖች የማያልፍ ውድቀትና ኀዘን ወደቀባቸው::

ዮዲት ግን በተበደለችበት በደል የልቧን ፈፅማ የአክሱም
ነገስታት ዘር ሰለ ሆነች ያመጠችውን ግብፃዊ ንጉሥ በበታቿ
አድርጋ በወርኃ ክረምት በ፱፻፷፪ ዓመተ ምሕረት በኢትዮጵያ ሳይ
በጉልበቷ ነግሣ በአክሱም መንበረ መንግሥት ተቀመጠች
(አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በ፰፻፵፪ እና ፰፻፹፪ ዓመተ ምህረት
ነገሠች ብለዋል )።

ቤተክርስቲያኑን ሳቃጠሉ ጎዳዎንና ግብረ አበሮቹም
ከአክሱም ከተማ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ባለው ሜዳ ሐፀቦን አልፎ
ከመቃብረ ተበን በላይ የሚገኘውን ዓዲ ሰየ ሞረር የተባለውን
አፈ ሜዳ በርሰትነት ሰጥታ በባለሚልነት አስቀመጠቻቸው እነሱም
ብረታ ብረት እየሠሩበት ተቀመጡ ( ይሠሩበት በነበረ ቦታም
የእሳቱ መንደጃ ከሰል መሰሉ እስከ ዛሬ ይታያል )።

ዮዲት ርኅራኄ በሌሰው አጨካከንዋ ካህናትና
ክርስቲያኖች በመፍጀትዋ ቤተክርስቲያን በማቃጠሏ ሃይማኖት
በማጥፋቷ በትግራይ <u>ጉዲት</u>፣ በጠለጠል ( **እዳል** ) <u>ጋዕዋ</u> ፣
በአማራ <u>እሳቶ</u> ተባለች። ጉዲትና ጋዕዋ ፣ ጨካኝ ፣ጉደኛ ፣
አብረተኛ፣ መርዘኛ ፣አረመኔ ማለት ነው። አንድ ምሥጢር ነው።
እሳቶ ማለት ደግሞ ቤተክርስቲያንን ያቃጠሰች እሳተ ነበልባ
ነፍሰ በላ እሳተ መዓት ማለት ነው። ሕዝቡን ሁሉ እንደ ሠም
አቅልጣ እንደ ገል ቀጥቅጣ አሠቃየቻቸው። በዘመንዋ ሁሉ
ረሃብና መከራ መቅሰፍት በዛ።



ዮዲት አንድ ተቃዋሚ አንድ ተቃራኒ ሳይኖራት መንግሥቷን አጽንታ ስትኖር ኃይሉ የሚባል አንድ ቀጣፊ ዋሽ ከጉዲት ፊት ቀርቦ የቀድሞዎቹ የአክሱም ነገሥታት ወርቅና ንብረት በትልቁ ሐውልት ሥር ተቀብሮ ይገኛል ብሎ ዋሻት። እንዲህ መዋሸቱም ገንዘብ የምትሰጠውና የምትሾመው መስሎት ነው። እርሷ ጉዲትም እውነት መስሏት የዋሻሳትን መሬ አድርጋ ቆፋሪ ሰዎች አስመጥታ የሐውልቱን ሥር ብታስቆፍረው ምንም አልተገኘም። ያን ጊዜ ሰውየውን አስገደለችው።

ከዚህ በኋላ የተቆፈረው መሬት በዝናብና በጐርፍ እየተሸረሸረ ሰለ ተናደ ትልቁ ሐውልት ተሻካሚ አጥቶ ከሥሩ ተነቅሎ ወድቆ ተሰበረ። ሐውልቱ ሲወድቅ ከተማው ኹሉ ተንቀጠቀጠ ብዙ ቤትም ፈረሰ። በጉዲት ዘመነ መንግሥት የዓለም ሕዝብ ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሁሉ መመኪያ በሆነ በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ቃጠሎ በከባድ ኃዘን ሳለ እንደገና በሐውልቱ ውድቀት እስከ ልጅ ልጅ የማይረሳና የማይጠፋ ኃዘንና ትካዜ ጸናበት የወደቀው ትልቁ ሐውልት ቁመቱ ፴፫ ሜትር + ፴ ሣንቲ ሜትር ነው። በክንደ ሲከነዳ ግን ስልሳ ሰባት ክንድ ተኩል እንደ ነበረ በአክሱም ታሪክ ተጽፏል። ጉዲት ሠራዊቷን አስከትታ በውስጠ አዋቂ መሬ እየተመራች ከአክሱም ተነሥታ አንበሳ ውድምን ለማጥፋት ወደ አማራ ሀገር ስትገሰግስ መንዝ ደረሰች። ከዚያ በአንድ ባለገር መሬ ዙሪያውን ሁሉ ስትፈልገው የበረኻው አቀማመጥ ገደልና ተራራ የበዛበት ጥንቅ

ቦታ ስለ ሆነ አንበሳ ውድም ከተሸሸገበት ዋሻ ደርሳ ሳታውቅ ተመለሰች፡፡ አንበሳ ውድም በዋሻው ውስጥ ሁና መሪው ጉዲትን እየመራ ሲመጣበት ስለ አየው **<u>መርሐ ቤትየ</u>** ብሎ በግዕዝ ተናገረ፡፡ ከዚያ ወዲህ ሲጠሩ መርሐ ቤትየ እየተባለ ሲጠራ በቀን ብዛት መርሐ ቤቴ ተባለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድግናዝን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ሲሰቃይ ከዚያም የባሰ በጉዲት ዘመን በረኃብና በበሽታ አለቀ እንደ ቅጠልም ረገፈ፡፡

ጉዲትም ከነገሠች ከ፱፻፷፮ ዓመተ ምሕረት ጀምራ ፵ ዘመን ሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያንን አስጨነቀችው፡፡

በመጨረሻ ዘመነ መንግሥቷ ሠራዊቷን ሰብስባ ወደ ጉልብሻ ወረዳ መጥታ አጻ አብርሀ ወአጽብሐ ቤተክርስቲያን ወረደች፡፡ ከዚያ ሕዝቡን እያስገደደች እንጨትና ኩበት አሰብስባ በሕንፃው ውስጥ እያስደረደረች እሳት አስለቀቀችበት፡፡ በዚህ ጊዜ ብረት ሠሪዎቹ ወናፍት እየነፉ እሳቱን አቀጣጠሉት፡፡

ሕንፃው በጢስ ታፍኖ እንደ ጥቀርሻ ጠቆረ፣ እሳቱም ከለስ ሕንፃው አልፈርስ ቢል ሐውልቶቹን በመዶሻ አስመታቻቸው ግን አልተሰበሩም አንዳንዱ ተሸርፈዋል፡፡

ያን ጊዜ እግዚአብሔር የሠራችውን በደል ሁሉ ቆጥሮ ሕንፃ ሰናፃርን በነፋስ በታትኖ እንዳጠፋው ጉዲትን በነፋስ አውሎ እንደ ወረቀት አንጠልጥሎ ከአጻ አብርሀ ወአጽብሐ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሰማይ ሰማየን እያጥመለመለ ወስዶ ሩቅ ቦታ ኮረብታ ላይ ጣላትና ፍርክስክስ ብላ ሞተች፡፡ በዚያ ጊዜ ያያት



ክርስቲያናዊ አልል አያለ ለእግዚአብሔር ምስጋና እያቀረበ እርሷን እስይ እስይ እያሉ በወደቀችበት ኮረብታ ቀበሯት፡፡ በመቃብሯ ላይም ለመታሰቢያ እንዲሆን ኮረት ድንጋይ ቆለሉበት ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ በእግዚአብሔር ተአምር በመቃብሯ ላይ እስከዛሬ ድረስ እንደ እሸን ( **ቁርጺጽ** ) ፈልቶበት ነፋስ ሕማም ሲነፍስበት ይኖራል፡፡ ቦታውም መቃብረ ጉዲት ዓዲነፋስ እየተባለ ተጠራ፡፡ ከዚያ ላይ ሰው ይሁን እንስሳ ሳያውቅ ቢወጣ ቁርጺጽ በመዥገር ተነድፎ በነፋሱ ተገርፎ ወዲያው ይሞታል፡፡

የጉዲት ሞት በሁሉ በተሰማ ጊዜ በኢትዮጵያ ትልቅ ደስታ ኾነ፡፡ በስደት የነበሩ የአክሱም ካህናትም ታቦተ ጽዮንንና ታቦተ ማርያምን ተሸክመው ከሞሳጉደል ንዋየ ቅድሳታቸውንና መጻሕፍታቸውን ይዘው በማኅሌት እየተመሩ ወደ ጥንት ሀገራቸው አክሱም ተመለሱ፡፡ በዦሮ የሰሙትን በዓይናቸው የተቃጠለውን ወርቃማ ቤተክርስቲያን የወደቀውን ሐውልት ባዩ ጊዜ እርስ በርሳቸው በዋይታ ሲዘሉ ሲናጩ ለነበቱ፡፡ ዋይ ወዮ እኛ እንሙት ተባባሉ፡፡

ከዚህ ላይ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ስለ ጉዲት ትውልድና መንግሥት ሲያትቱ በሰሜን አውራጃ ይኖር የነበረ ጌዲዎን የተባለ ፈላሻ ዮዲት የተባለች ሴት ልጅ ወለደ፡፡ እሷም ዘርአ ጽዮን የተባሉ የላስታ ባላባት አግብታ ላስታ ኪዳ ቡግና በተባለ ወረዳ ስትቀመጥ በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ ድግናዝን ለሰሞተ ልጁ ግዳዝን ነገሡና በ፲ ወሩ ሞተ ሰርሉም

አንበሳ ውድም የተባለ ገና ሕፃን ልጅ ነበረው እርሱን ቢያነግሡት መንግሥቱን ለመጠበቅ የማይችል ስለሆነ የአንበሳ ውድምን ሕፃንነት ዓይታ በስሜን ላስታ አውራጃ የሚኖሩትን አይሁዶች ሁሉ ሰብስባ በ፰፻፵፪ ዓመተ ምሕረት ነገሠች። ከዚያ አንበሳ ውድምን አባርራ የክርስትያን ሃይማኖትን አጥፍታ የአይሁድን ሃይማኖት ለማቆም ስለ አሰበች የአክሱም ቤተክርስቲያንን አቃጠለች ብለው ዋዜማ ባሉት መጽሐፋቸው በ፳፱ ገጽ ጽፈዋል። ስመሆኑ ምንም አንበሳ ውድም ሕፃን ቢሆን የደረጀ መንግሥትና ጀግኖች ሠራዊት ያሉበትን የአክሱም መንግሥት አጥፍታ እንዴት ተራ ሴት ዮዲት የስሜንና የላስታ አውራጃ አይሁዶች ሰብስባ ነገሠች ከዚያ አንበሳ ውድምን አባርራ የክርስቲያን ሃይማኖት አጥፍታ የአይሁድ ሃይማኖት ለማቆም ስለ አሰበች የአክሱም ቤተ ክርስቲያን አቃጠለች ማለታቸው እውነት ይመስላል? ይላሉ መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ግን ከፍብሎ ስለ ዮዲት ታሪክ ከዋናው ከአክሱም ክብረ ነገሥት ከግዕዙ በአማርኛ ተርጉመው ማቅረባቸውን መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሲቅ በሚባለው መጽሐፋቸው የጻፉትን እኔም በውስጡ ያገኘሁትን የዮዲት ጉዲትን ታሪክ እንዳለ ለማቅረብ ችያለሁ።

* በዮዲት ዘመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ።
* ቅዱሳት መጻሕፍት ተቃነጸሉ፣ ወደ ውጥም ተዘረፉ።



* ብዙ ክርስትያኖች በግፍ ተገደሉ።
* ብዙ ቅርሶች ጠፉ የሃይማኖትና ጥበብ የፍልስፍና የምርምር ሊቃውንት እየታደኑ ታረዱ።
* እንስሳው በበሽታ አህሉ በቀጠና ጠፋ ሕዝቡም በርኃብ አለቀ።
* ሃይማኖተ ክርስቲያን መነመነ የእስላም እምነት ሰፈነ።
* ይህ ሁሉ መከራና መዓት ለኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ነው።

ማሳሰቢያ:- ይህን ለመረዳት የሚፈልግ ሰው የዮዲትን ታሪክ የያዘውን <u>የአክሱም ግእዝ ክብረ ነገሥት</u> ይመልከት።

## እንጦጦ እና አዲስ አበባ

<u>አዲስ አበባ</u> ⇨ ይህች ከተማ አንድ ምዕተ ዓመትን ያሳለፈች ከተማ ናት። ከተማዋ በአሁኑ ወቅት ማለትም በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የ፻፲፭ ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ ስትሆን። ይህን ያህል ረጅም ዕድሜን ያስቆጠረችው አዲስ አበባ ከተማ በአሁኑ ጊዜ ፪ሚሊዮን ፩፻፲፪ሺ፯፻፴፯ ህዝብ እንደሚኖርባት በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን አማካኝነት በተደረገው የህዝብና የቤት ቆጠራ መሠረት የታወቀ ነው። በዚሁ መረጃ መሠረት የባለሥልጣን መሥሪያቤቱ አጠቃላይ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ቁጥር ፩ሚሊዮን ፯፻፵፱ሺ፯፻፳፯ መሆኑን አረጋግጧል። አዲስ አበባ በ፶፬ሺ ሔክታር መሬት ላይ ተንሰራፍታ በ፪ሺ፬፻፶ ሜትር ከፍታ ላይ የምትገኝ ከተማ ናት።

ስለ አዲስ አበባ ከተማ አመሠራረት ለማወቅ ስንፈልግ ታሪክ የግድ ወደ ኋላ መልሶ እንጦጦ ተራራ ላይ ነው የሚያደርሰን። እንጦጦ እንደሌሎቹ ቀደምት የኢትዮጵያ መዲናዎች በ፲፰፻፸፩ ዓ.ም በተራራ ላይ የተመሠረተ ከተማ ነው። **የቀድሞዎቹ ነገሥታት ራሳቸውንና ሕዝባቸውን ከጠላት ለመከላከል ሲሉ ተራራማ የሆኑ ሥፍራዎችን ለከተማነት ይመርጡ እንደነበር ይታወቃል። በዚሁ ምክንያት የተነሳ ይመስላል የእንጦጦ ተራራም ለከተማነት የታጨው።**



የእንጦጦ ተራራ በአባይ ወንዝና በአዋሽ ሸለቆ መካከል በ፫ሺ፪፻ ሜትር የባሕር ወለል ከፍታ ላይ ይገኛል። ከተማዋም ለትቆረቆር ( እንጦጦ ማለት ነው። ) ከ፳ሺ ያላነሰ ሕዝብ ይኖርባት እንደ ነበር ይነገራል።

ነገር ግን

- ለማገዶ የሚሆን እንጨት ያለመኖር።
- ለመጠጥ የሚውል የውኃ ምንጭ በአካባቢው ያለመኖር።
- ወደ ከተማዋ ለመዝለቅ ዳገቱ ያስከተለው ችግር።
- በክረምት ወራት የቆፈኑና የነፋሻው ቀዝቃዛ አየር ክብደት።

« ለሰላሙ ወቅት የማትስማማ ከታማ » ለለ አደረጋት በአዲስ ዓለም ከተማ እንድትተካ ታስቦ ነበር።

ነገር ግን ከእንጦጦ ግርጌ የሚገኘው የፍንፍኔ ፍልውኃ ከብዙ በሽታዎች ፈዋሽ መሆኑ በመታወቁ በተለይ በቀዝቃዛው የክረምት ወቅት በአገሬው ሕዝብ ይዘወተር ነበር። ይህንኑ በመገንዘብ እቴጌ ጣይቱ ፍልውኃው አጠገብ መኖሪያ ቤት ለመሥራት አሰቡ። ለስጉዳዩም ንጉሡን በማማከር የቤት መሥሪያ ቦታ አስፈቀዱ። ቤቱን ሠርተው ትንሽ ጊዜ እንደቆየም በሥፍራው <u>**ሚሞሳ**</u> በመባል የሚታወቅ አበባ ዛፍ አብቦና ፈክቶ በማየታቸው አዲሷን ከተማ <u>**አዲስ አበባ**</u> ብለው ሰየሟት። ቀስ በቀስም ዋና ከተማው ወደ ረባዳማው ቦታ በመዘዋወሩ የመገናኛ እና የውኃ አገልግሎት ችግርም በመቃለሉ የአየር ንብረቱም

ከእንጦጦ ይልቅ ተስማሚ ሆና በመገኘቱ የማእከላዊ መንግሥት፣ የመንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ፣ የኤምባሲዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የንግድ ተቋሞች በሚገባ ተደራጅተው ተቋቋሙ።

የአዲስ አበባ ከተማ በይፋ የተመሠረተችው ኅዳር ፲፯ ቀን ፲፰፻፸፱ ዓ.ም ሲሆን። አጼ ምኒልክ ቤተ መንግሥታቸውን የሠሩት ጥር ፳፰ ቀን በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም ነው።

ስዚህ ነው እንግዲህ እንጦጦ ለመዲናችን መነሻ ሆና በማገልገልዋ ታሪካዊ ናት ብለን ያልነው። ለመዲናችን መቆርቆር ምክንያት የሆነች ተራራ ስዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ቅዱሳን መካናት መጻፍ ስጀመርኩት ጽሑፍ ሲረዱኝ የሚችሉ አሁን እስከ አስንበት ዘመን ድረስ ግርማ ሞገሳቸውን እንደያዙ በተራራው ላይ ጉላ ብለው በመታየት ከአካባቢው መልከዓ ምድራዊ ውበት ጋር ተስማምተው የታነጹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሀብት የሆኑ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ።

<u>እነሱም</u>:- **እንጦጦ ማርያም እና እንጦጦ ራጉኤል ናቸው።**



## <u>እንጦጦ ማርያም</u>

ከዋና ከተማዋ አዲስ አበባ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ፲.፫ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። ቤተ ክርስቲያኗ የተቆረቆረችው ፲፰፻፸፮ ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ ነው። አጼ ምኒሊክ በ፲፰፻፸፮ መቃኞውን አስመርቀው ከሦስት ዓመት በኋላ ደግሞ በ፲፰፻፹ ሁለተኛውን ቤተክርስቲያን አስመረቁ። ይህ አሁን የምናየው ግሩም ህንጻ ቤተክርስቲያን የታነጸው ግን በንግሥት ዘውዲቱ በ፲፱፻፲፫ ዓ.ም የተመረቀ ነው። የሕንፃዎቹ ግንባታ ከአዲስ አበባ ከተማ አመሠራረትና በአጠቃላይም ከዘመናዊ የከተማ ባህል ዕድገት ጋር የተያያዙ ናቸው። አጼ ምኒልክ ከአንኮበር ወደ እንጦጦ ተጉዘው ዋና ከተማቸውን ከቆረቆሩ በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት ሥፍራው የባህል የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ማዕከል ሆና መቆየቱ ይታወቃል።

የእንጦጦ ማርያም ጽላት ንጉሥ ተክለሃይማኖት በእምባቦ ጦርነት ሲሸነፉ ከጉጃም በምርኮ የመጣች መሆኗ ይነገራል። በምርኮ የተገኘችው ይህች ጽላት በመቃኞ ለዓመታት ቆይታለች። መቃኞዋም ክብ ሆጣሪያ ቅርጽ ያላት አነስተኛ ቆርቆር ቤት ሆና ከደወል ቤቱ ፊት ለፊት ትገኛለች። በአሁኑ ጊዜ ግን ስዐቃቢቶች መኖሪያ ቤት በመሆን ታገለግላለች። እቴጌ ጣይቱ ከጉንደር በመጡ ዘጠኝ አናጢዎች የቤተክርስቲያኑን ግንባታ ያስጀምሩታል። ሥራውም በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሲጠናቀቅ በ፲፱፻፺፰

የቀንድ ከብቶች ታርደው በታላቅ ድግስ ታቦትዋ « <u>እንጦጦ ርዕሰ አድባራት መንበረ ፀሐይ ማርያም</u> » በመባል በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም ነግሣለች:: በ፲፰፻፹፪ ዓ.ም አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለመባል የበቁትም በዚችው በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ በተካሄደ ሥነ-ሥርዓት ነበር::

በ፲፰፻፺፮ ዓ.ም እቴጌ ጣይቱ ዘመናዊ የሕንጻ ሠራተኞችን ከአውሮፖ አስመጥተው ቤተክርስቲያኗን ያሳደሷት ሲሆን በ፲፱፻፲፫ ዓ.ም የሕንጻውን ግድግዳ በግንበና ጣርያውን በቆርቆሮ የቀየሩት ግን ንግሥት ዘውዲቱ ናቸው:: ከአፄ ምኒልክ ሕልፈት በኋላ በተነሳው የፖለቲካ ውዝግብ ምክንያት እቴጌ ጣይቱ በዝችው ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በቁም እስር ቆይተው በ፲፱፻፲ ዓ.ም አርፈዋል:: የቤተክርስቲያኗ የውስጥ ግድግዳ በዘመኑ የኢትዮጵያ የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች በአለቃ ሕሩይና በዕምዓዕሳፍ ድንቅ ሥዕሎች የተዋቡ ናቸው:: እንዲሁም የሕንፃው ጣሪ ዲዛይንና ውቅር በጣም ማራኪ ነው:: በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም አገራችንን ጠላት በወረረበት ወቅት ሕንፃው ምንም ዓይነት አደጋ አልገጠመውም:: ጽላቱም በቀሳውስቱ በመሠወሩ በወራሪው ኃይል እጅ አልወደቀም::

ከቤተክርስቲያኗ በስተጀርባ በመቶ ሜትር ርቀት ላይ የአፄ ምኒልክ የግብር አዳራሽ ይገኛል:: የአዳራሹ የውስጥ ክፍል ለግብር የተዘጋጀ ምግብ መቆያ የነበረና ለዩት ያለ ሲሆን የተለያየ የማዕድ ቤት ዕቃዎችን ለማንጠልጠል እንዲያስችሉ



በግድግድጋው ላይ የተቸነከሩ ቀንዳች ይታያሉ:: ለንጉሡ ማረፊያ ለዩት ያለ ክፍልም አለው:: ሕንጻው በጭቃና በድንጋይ የተገነባና ውፍረቱ እጅግ ቢያንስ ፹ ሳ.ሜ እንደሆነ ይገመታል:: በአቅራቢያው በግምት ከስባ ካሬ ስኩየር ሜትር ስፋት ላይ በእንቁላል ቅርጽ በጭቃና በድንጋይ የተገነባና ምድር ቤት ያለው የአፄ ምኒልክ እልፍኝ ይገኛል:: የእልፍኙ ጣሪያ በጥርብ የጥድ እንጨት የተዋቀረና እንደ አዳራሹ ሁሉ በጠፍር የተማገረ ሲሆን ተመልካችን የሚማርክ ውበት አለው:: ወደ እልፍኙ የሚያስገባ እና ከሕንጻው ውጫዊ ግድግዳ ጋራ የታያየዘ ደረጃም ተዘጋጅቶለታል:: በሰሜንና በደቡብ በኩልም ተካፋች መስኮቶች አሉት:: በሁለቱም አቅጣጫ ማራኪ የመልክአ ምድር አቀማመጥንና ከፊል የአዲስ አበባን ከተማ ለመቃኘት ይቻላል::

በዚሁ አካባቢ ንጉሡ ከቤተክርስቲያን መልስም ዛቲ ይቀምሱበት የነበረና ሸራ ቤት በመባል ይታወቅ የነበረው ቤት ይገኛል:: ሸራ ቤት የተባለውም ጣራው በሸራ ተሸፍኖ የነበረ በመሆኑ እንደነበር ይገመታል:: እቴጌ ጣይቱ በ፲፱፻፲ ዓ.ም እንዳረፉ እስከረፉናቸው በዚሁ በሸራው ቤት ውስጥ ቆይቶ በንግሥት ዘውዲቱ አማካኝነት ወደ ባዕታ ቤተክርስቲያን ምድር ቤት ተዛውሯል:: በአሁኑ ወቅት እነዚህ ታሪካዊ ቤቶች በቤተክርስቲያኑ አገልግሎት ለተሠማሩ መነኮሳት በመኖሪያነት ያገለግላሉ:: ሆኖም አዳራሹና እልፍኙ ጥገናና እንክብካቤ ተደርጐላቸው በቅርስነት ቢጠበቁ መልካም እንደሆኑ ለመግለጽ እወዳለሁ::

በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን መግቢያ በር አጠገብ በዘመናዊ መልክ የተደራጀ ሙዝየም አለ። ሙዝየሙ በወቅቱ የነበሩ ነገሥታት የተገለገሉባቸው የንግሥ ልብሶችና፣ ዘውዶችን፣ ባለወርቅ ፈርጥ ዣንጥላ፣ ኮርቻ አፄ ምኒልክ ከአንኮበር ጀምረው ይገለገሉበት የነበረ የጠፍር አልጋና ከንጉሡና ከንግሥቲቱ ለቤተክርስቲያኑ የተባረከቱትን በርካት ዕቃዎች ያካትታል። አፄ ምኒልክ በ፲፰፻፹ ዓ.ም አስደጉሰው የሰጡት ያሬዳዊ መጽሐፍ የንግሥቲቱ ደንገጡሮች ከአክርማ ያዘጋጁት ውበት የተሳበሰ ባለፈርጥ መሶበ ወርቅ ፣ ፲፰፻፮ ዓመት እድሜ ያስቆጠረ ከአንድ ወጥ እንጨት የተሠራ መስቀል፣ ፲፰ ዓመት ያሰው የእመቤታችን ሥዕል፣ በ፲፰፻፺፫ ዓ.ም በኢጣሊያ መንግሥት የተበረከተ የድንግል ማርያም ቅርጽ ፣ ስቀሳውስት ጥምጣም ማስተካከያ በአቴጌ ጣይቱ የተበረከተ ያማረ መስታወት፣ በጀርመን አገር የተሰራ እንዚራ (አኮርዲዮን) የንግሥቲቱ ካባ፣ ከሶሪያና ከፋርስ የመጡ የሐር ምንጣፎች የንጉሡ ጋሻና ጦር በወርቅ የተጠለፈ ሆኖ ንጉሡ ወደ አድዋ ሲዘምቱ የያዙትና ከራስጌ የእመቤታችን ከግርጌ ግራና ቀኝ የጣይቱና የምኒልክ እንዲሁም በመሐል የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስል የሚታይበት አርማ በአድዋ ጦርነት ስዘመቻ ጥሪ የተገለገሉበት ነጋሪት እና ሌሎች ማራኪ ዕቃዎች በሚዝየሙ ውስጥ ይገኛሉ።

በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም በአፄ ዳዊት አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ የመጣውና ዛሬ በግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም በክብር ተቀምጦ



ያለው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቀኝ እጁ ያረፈበት ግማደ መስቀል ከመናገሸ ቀጥሎ በእንጦጦ ተራራ ላይ ማረፉንም አንዳንድ ጽሑፋዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ሌላው ደግሞ በእንጦጦ መንበረ ፀሐይ ጥንትም የነበረ ነገር ግን ግዜውን ጠብቆ ሕሙማንን በመፈወስ ላይ የሚገኝ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ ጸበልም ይገኛል። ጸበሉ ከቤተክርስቲያኒቷ ራቅ ብሎ የሚገኝ ሲሆን በእግር ከ፲፭ - ፳ ደቂቃ ያህል ይወስዳል። የእንጦጦ መንበረ ፀሐይን ጉብኝታችንን አበቃን። በዚሁ መስመር ወደ እንጦጦ ራጉኤል እንሄድና የቤተክርስቲያኑን ታሪካዊ አመሠራረት እናያለን።

**የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን አሜን።**

## እንጦጦ ራጉኤል

የእንጦጦ ማርያምን የጉብኝት መስመር እንዳጠናቀቁ የጉጃምን መንገድ በሚያገናኘው መስመር አንድ ኪ.ሜ ተኩል ያህል እንደተጓዙ በኪነ ጥበባዊ ውበቱ የተደነቀውንና በድንቅ ሁኔታ የተሠራውን በመልአኩ በቅዱስ ራጉኤል ስም የታነጸውን ቤተክርስቲያን ያገኛሉ።

የዚህ ውብ ቤተክርስቲያን ግንባታ የተጀመረው በ፲፰፻፸፯ ዓ.ም በወርሐ ጥር በአፄ ምኒልክ ነው። የዚህ ድንቅ ቤተክርስቲያን ሥራ ሲጀምር አቡነ ማቴዎስ በሥርዓተ ክህነት ሆነው እያጠኑ ንጉሡም በሥርዓተ መንግሥት ቆመው መዝሙረ ዳዊትን፣ ውዳሴ ማርያምን፣ አራቱን ወንጌል ደግመው በየማዕዘኑ ፬፻ እግዚኦታ አድርሰው ፣ ጳጳሱም አራት ድንጋዮች ባርከው በአራት ማዕዘን የመሠረት ድንጋይ አኖሩ ተብሎ በጸሐፌ ትዕዛዝ ገ/ሥላሴ ተዘክሮስታል።

ለግንባታ የሚሆን ድንጋይ በመንኮራኩር የጥድ እንጨቶች በሠረገላ እየቀረቡ ቅኔ ማኅሌት ቅድስቱም መቅደሱም ስምንት ስምንት ማዕዘን ሆኖ የተሠራ ሕንጻ ነው። በድንጋይ መጥረቡ ሥራ ላይ ንጉሡ እራሳቸው ሲካፈሉ ንግሥቲቱም በትጋት ሥራውን ተከታትለዋል። የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሕንጻው ከመገንባቱ በፊት ጽላቱ በግቢው ውስጥ በሚገኘው ዋሻ



በዘመኑ በቀን ከ ፫፻፹ በላይ ካህናት አገልግሎት ያበረክቱ ነበር ይባላል። ዋሻው ሦስት ክፍሎች አሉት የመጀመሪያው ክፍል መቅደስ በስተግራ የሚገኘው ክፍል ኪዳን ማድረሻና ከመቀደሻው ጋር የተያያዘው ክፍል በግድግዳ ተፈልፍሎ ገበ እንዲል ተደርጎ ለጽላቱ ማስቀመጫ የተዘጋጀው ሥፍራ ሦስተኛው ነው። የቤተክርስቲያኑ ሥራ እስከ ተጠናቀቀ ድረስ የቅዱስ ራጉኤል ጽላት በዚህ ክፍል ውስጥ መቆየቱ ዋሻውን ታሪካዊ ያደርገዋል።

የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ባለሦስት ፎቅ ሕንጻ ሲሆን ከሕንጻው ውጫዊ አካል ጋር ተያይዞ የተሠራ ደረጃ ወደ አንደኛው ፎቅና ወደ ሚቀጥለው ለመዝለቅ ያስችላል። የቤተክርስቲያኑ የውስጥ ጣሪያ በሰማያዊና በብርቱካንማ ቀለም ደምቆ የክርስቶስን ልደትና ሕይወት በሥዕል ያሳያል። ሌሎችም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በግድግዳዎች ላይ የተሣሉ እጅግ ማራኪ ሥዕሎች ይታያሉ። የምድር ቤቱ ውጫዊ አካል የተዋበና ግማሽ ክብ ያላቸው በርካታ በር መሳይ ምስሶዎችን ይዟል። ድምድማቱ በድንጋይ ፣ በኖራ ተገንብቶ ጉልላቱ ስለ አረፈበት ሕንጻውን ውበት አላብሶታል። በርካታ አገር ጎብኝዎች ይህን ቅዱስ ሥፍራ ያደንቁታል። በዘመኑ ብዙ ሊቃውንት ቅኔና ዜማን ብሉይንና ሐዲስን ይማሩበት እንደነበረም ተዘግቧል። ዛሬ ግን ያሁሉ በነበር ተተክቷል።

አንደ አንጦጦ ማርያም ያስ የክብር ዕቃዎች ማስቀመጫ ሚዝየም ባይኖርም ቤተክርስቲያኑ ውስጥ በ፲፰፻፷፰ ዓ.ም በመቅደላ ሳይ አፄ ቴዎድሮስ ድል ከሆኑ በኋላ በእንግሊዝ ወታደሮች የተዘረፉት መጽሐፍት ሲመለሱ በዚሁ ቤተክርስትያን እንዲቀመጡ ተደርጓል:: አቴጌ ጣይቱ ያበረከቱት የወርቅ ከበሮ፣ ንጉሥ ሚካኤል የሰጡት የወርቅ መስቀል ፣ ራስ ጉበና ዳጨው ያበረከቱትና አሥራ ሦስት የአንበሳ ምስሎች የተሰበጡበት ጋሻና ጦር፣ ራስ ተፈሪ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ወቅት ያደርጉት የነበረው ራስ ወርቅ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ይገኛል:: ከዚሁ ቤተክርስቲያን ሰሜናዊ ክፍል የአባይ ሸለቆ ጦርዝ እንደሚጀምር ይጠቀሳል:: አንጦጦ ተራራ ሳይ ያሉትን የእነዚህ ሁለት አብያተክርስትያናት ታሪካዊ አመሠራረት በአጭሩ ይህን ይመስላል::

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር::**



## ግሸን
## ደብረ ከርቤ ማርያም

ግሸን ከደሴ ከተማ ፹፪ ኪሎ ሜትር ርቀት ሳይ በወሎ ክፍለ ሀገር በአንባሰል ወረዳ ውስጥ በሐይቅና በመቅደላ በደላንታና በየጁ መካከል በበሽሎ ወንዝ አዋሳኝ ከፍተኛ በሆነ ተራራ ሳይ የምትገኝ ገዳም ናት:: የበሽሎን ወንዝ ተሻግረው ለማይ ጥግ የደረሱ የሚመስሉትን ተራሮች ወጥተው በስተመጨረሻ መግቢያዋ አንድ በር የሆነ እና ከተራራው አናት ሳይ በሚገኝ ሥፍራ ሳይ በአመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስም የታነጸ እና ግማደ መስቀሉ የሚገኝበት የእግዚአብሐር አብ አብያተ ክርስቲያናትን ያገኛሉ:: በተለይ በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም __አቡነ ሚካኤል ጳጳስ ዘጎንደር__ ከዚህም ጋር « __መንፈሳዊ መናኝ__ » በመባል የሚታወቁት ደገኛ አባት ባሠሩት ከቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሆነው የተራራውን ተፈጥሮአዊ አቀማማጥ ሲመለከቱ አንድ ጥሩ ዐናጢ ከጥሩ እንጨት ባማረ ጌጥ ጠርቦ የሠራውን ግሩም የእጅ መስቀል ይመስሳል:: የዚህን አምባ የመሬት አቀማመጥ ዓይተው ስለቦታው ታሪክ የገዳሟን አበውና የታሪክ መዛግብቶችን ሲያገላብጡ ከነገረ መስቀሉ ታሪክ ጋር በተያያዘ መልኩ ከብዙ በጥቂቱ ይህን ይመስለ ታሪክ ያገኛሉ::

ግሸን ይህን የአሁኑን መጠሪያ ስም ከማግኘቷ በፊት በተለያዩ መጠሪያ ስሞች ትታወቅ ነበር:: መጀመሪያ በአፄ ደልነዓድ ዘመነ መንግሥት በ፲፰፻፷፯ ዓ.ም ሐይቅ ደብረ

እስጢፋኖስ ሲመሠረት፣ ሐይቅ ደብረ ነገድጓድ ተብሉ ሲሰየም ግሽንም በሐይቅ ግዛት ውስጥ ስለሆነች ስሟ «ደብረ ነገድጓድ ተባለች:: ይህን መጠሪያ ስሟን እንደያዘች እስከ አስራ አንደኛ ክፍለ ዘመን ድረስ ቆየች:: በ፲፩ኛው ክፍለ ዘመን ሳ በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው ጻድቁ ንጉሥ ላሊበላ ከቋጥኝ ድንጋ ፈልፍሎ የሠራው ቤተ መቅደስ በእግዚአብሔር አብ ስም ይጠራ ስለነበር ግሸንም «ደብረ እግዚአብሔር» ተብላ መጠራ ጀመረች:: ነገር ግን በዚህ ስም በመጠራት ብዙም ሳትቆይ ስሟ ተለውጦ « ደብረ ነገሥት » ተባለች ደብረ ነገሥ የተባለችውም ነገሥታቱ ይማጸኑባት፣ የክብርና የማዕረግ ዕቃዎች ያስቀምጡባት ፤ የነገሥታቱ የመሳፍንቱ ልጆችም የቤ መንግሥት አስተዳደር የሚማሩባት ሥፍራ ስለ ነበረች ነው::

እንደገና ደግሞ በ፲፪፻፺፮ ዓ.ም ኢትዮጵያዊው ፈላስ እየተባሉ በሚጠሩት በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ግማ መስቀሉ መጥቶ በዚህ ቅዱስ ሥፍራ ሲያርፍ ደብረ ነገሥ መባሏ ቀርቶ « ደብረ ከርቤ » ተባለች:: የደብር አስተዳዳሪዋም የማዕረግ ስም መምህረ እስራኤል ዘደብረ ከርቤ ይባል ነበር:: አፄ ዘርዓያዕቆብ ግማደ መስቀሉን አሽክመው እየገሰገሉ ከብዙ ድካምና ፍለጋ በኋላ ወደ ተራራ በመምጣታቸው « ገሠገሠ » ከሚለው ቃል በግእዝ « ጌሠ » የሚል ትርጓሜ ያለው በመሆኑ ከጌሠ በጊዜ ብዛት ግሸን የሚል ቃል በመፈጠሩ ግሸን የሚለውን ስያሜ ሲሰጣት ችሏል ::



ግሸን ማርያም የሚለውን ስያሜዋ ይህን ይምሰል እንጂ የቦታው መገኘት የቆየ ታሪክ አለው:: አፄ ዘርዓያዕቆብ ግማደ መስቀሉን ይዘው ከመምጣታቸው ፱፻፩፮ ዓመት በፊት ቅዱስ ላሊበላም ደብረ እግዚአብሔርን ከመመስረቱ ፩፻፹፫ ዓመት በፊት እነ አባ ኢየሱስ ሞአም ሐይቅ ደብረ ነገድጓድን ከመመስረታቸው ፫፻፵፱ዓመት አስቀድሞ በአንድ ደገኛ አባት ነው ግሸን ተገኝታ የተመሠረተችው:: ታሪኩ እንዲህ ነው::

በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ሮማውያን ባደረሱት የጭካኔ አገዛዝ የተነሳ ከሀገራቸው ተማረው የተሰደዱ በርካታ እስራኤላውያን በኢትዮጵያ ጥላ ሥር በጥገኝነት ትተዳደር በነበረችው የመን ውስጥ ይኖሩ በነበረበት ግዜ አረማዊያኑ ክሳባና ከሒማርያት ወገን በሆኑት እስራኤላውያን ላይ ጥቃት እንደፈጸሙባቸው ለአፄ ካሌብ ስለ ተነገራቸው በኤርትራ ባሕራቸው የሚንሳፈፉ መርከቦቻቸውን ይዘው ወደ የመን በመጓዝ በክርስቲያኖች ላይ ጥቃት የሰነዘሩትን አረማውያንን በማጥፋት የመንን የኢትዮጵያ ግዛት አድርገው በመጠቅለል አብርሀ የሚባል አስተዳዳሪ (ገዥ) መድበው ከበርካታ ጭፍሮች ጋር ትተውት ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ:: ከዚህም የተነሳ የመን ከ፬፻ - ፭፻ ዓ.ም ለአንድ መቶ ዓመታት ያህል በኢትዮጵያውያኖች ሥር ልትተዳደር ችላለች:: በየመን ነዋሪ ከሆኑት አንዱ እና ለአፄ ካሌብ እንደ ነፍስ አባት ሆነው የሚያገለግሉት አባ ፍቃደ ክርስቶስ የሚባሉ መንፈሳዊ መናኝ በየመን በሀገረ ናግራን ተራራ ላይ ይኖሩ

ስለነበር በናግራን ተራራ ላይ የሚገኙ ሁለት ጽላቶችን ኢትዮጵያ
ወስደው እንዲያኖሩ ከፈጣሪያቸው በጸሉት እንደተገለጸላቸው
ለንስሐ ልጃቸው አፄ ካሌብ በመናገራቸው ንጉሡም ፈቅደው አባ
ፍቃደ ክርስቶስም ሁለቱን ጽላቶች አሸክመው በሽሎ ወንዝን
ተሻግረው አቀበቱን ወጥተው ወደ መስቀለኛው አምባ ጥግ
ሲደርሱ ወደ አምባው ጫፍ ለመውጣት ሰርጥ ሲፈልጉ
የአምባውን ዙሪያ በገደሉ ላይ ንብ ሰፍሮ የማሩ ሰፈፍ ጨረቃ
መስሎ በማየታቸው የአካባቢውን እና የእግዚአብሔርን የተፈጥሮ
ስጦታ ሲያደንቁ ይህስ **አምባ አሰል** ነው በማለት ተናገሩ
ይባላል:: አሰል የሚለው ቃል በዐረብኛ ማር ማለት ሲሆን ሙሉ
ትርጉሙም **የማር አምባ** ማለት ነው:: ከዚያን ግዜ ጀምሮ
እስካሁን እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የግሸን ማርያም አካባቢ
ወረዳ አምባሰል ተብሎ እየተጠራ ይገኛል:: እንግዲህ እኚህ አባቶ
ናቸው የአራዊት መፈንጫ የነበረውን ተራራ በ፭፻፲፯ ዓ.ም
ወጥተው በተራራው ላይ መጠነኛ ጐጆ በመቀለስ ሁለቱን ጽላቶች
ያስቀመጡት:: ሁለቱ ጽላቶችም ታቦተ እግዚአብሔር አብና ታቦተ
ቅድስት ድንግል ማርያም ናቸው:: የአምባው መገኘት ይህን
የሚመስል ሆኖ ላለ የመስቀሉ አመጣጥ ታሪክ ደግሞ ከዚህ
እንደሚከተለው ቀርቧል::

በይሁዳ ንጉሥ ሄሮድስ በኢትዮጵያም ነግሦ በነበረው
በባዚን ዘመነ መንግሥት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል አብሣሪነት ከእመቤታችን ከቅድስት



ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በፍጹም
ተዋሕዶ በቤተልሔም ተወለደ:: ከዚያም በግእዘ ሕፃናት እያደገ
ሄደ ፴ ዓመት ሲሆነውም በባሕረ ዮርዳኖስ ተጠመቀ በገዳም
ተቀመጠ ተራበ፣ተጠማ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ
የመጀመሪያውን ተአምራቱን በቃና ዘገሊላ ፈጽሞ፣ ሙት
እያስነሳ ጐባጣ እያቀና ፣ ሽባ እየተረተረ፣ ዕውር እያበራ፣
ሕብስት አበርክቶ እየመገበ በምድረ እስራኤል በገጠር በከተማ
በምኩራብ በገበያ እየተዘዋወረ ሦስት ዓመት እንዳስተማረ
አይሁድ በቅንአት ተነስተው በሐሰት ከሰው በሐሰት መስክረው
በሰሰተ አርብ በቀራኒዮ አደባባይ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ
ሰቀሉት:: ከመስቀላቸው በፊት ግን እያንዳንዳቸው የአይሁድ
ጭፍሮች ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ጅራፍ ገርፈው
ሳዶር ፣ አላዶር ፣ ዳናት ፣ አዴራ፣ ሮዳስ በተባሉ አምስት
ቅንዋት ( ችንካር ) ቸንክረው ሰቅለውታል:: ስለእነዚህ አምስት
ቅንዋተ መስቀል (ችንካሮች) ከተነሳ አይቀር መሪጌታ ልሳነ ወርቅ
ገብረጊዮርጊስ **ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ቢቅ**
በሚል አርዕስት ለኅትመት ባበቁት መጽሐፋቸው በምዕራፍ አንድ
ክፍል አርባ አምስት ላይ ስለአምስቱ ቅንዋት ታሪክ እንዲህ
ብለው አብራርተውታል የቱ ችንካርም በየትኛው የክርስቶስ አካል
ላይ እንዳረፈ ግልጥልጥ አድርገው ጽፈዋል :: እኔም ከያዝኩት
የመስቀል ታሪክ ጋር የሚጣጣም መስሎ ስላገኘሁት እንዳለ
አቅርቤዋለሁ::

« አይሁድ ጌታ ኢየሱስን ሲሰቅሉት በሰውነቱ ቅርጽ አንድ ረጅም ግንድ መሬት ላይ ዘርግተው አንደገና ከእርሱ አጠር ያለ ሌላ ግንድ አምጥተው ግራና ቀኝ አስተሳስፈው በምስማር አስምረው ጌታ ኢየሱስን በላይ አስተኝተው እጁን እግሩን ወጥረው አላዶር በተባለ ችንካር / ቀኖት / ቀኝ እጁን፣ ዳናት በተባሌ ችንካር ግራ እጁን ፣ አዴራ በተበለ ችንካር ሁለት እግሮቹን ደርበው አጥብቀው ከቸነከሩት በኋላ ሌላ ከአምስቱ ቅንዋት ( ችንካር ) በመጀመሪያ የሚጠራውን ሳዶር የተባለ ብረት እንደ ዝናር የሚታጠፍ ላይና ታቹ እንደ መጋዝ ጥርስ ያለው አምጥተው ሰውነቱ እንዳይንቀሳቀስ ከልቡ በታች በሸንጡ መካከል ከመስቀሉ ጋር አስታጥቀው እንደጨረሱ መሬቱን አጥልቀው ቆፍረው እንደ ሙቀጫ የተፈለፈለ ግንድ ከጉድጓዱ ላይ ከተው ደቅድቀው ከሙቀጫው ላይ ጌታ ኢየሱስ የተሰቀለበትን መስቀል አቁመው ተክሰው ባስታጠቁት ባለ ጥርስ ብረት ሰውነቱን እየተወጋ በቸነከሩት ቀኖት ( ችንካር ) ሲሰቃይ እንደ ት ፊደል ራሱን ወደ ቀኝ ትክሻው ዘንበል አደረገ፡፡ አምስተኛው ቀኖት ሮዳስ የተባለ ጌታ ኢየሱስ ሲሰቀል የሚሰቅሉበት ግንድ ረጅምና አጭር ስለነበር ረዣሙን አቁመው አጭሩን አጋድመው አስተሳስፈው የቸነከሩበት ነው ብሰው ጽፈዋል፡፡

ስለ አምስቱ ቅንዋት ይህን ያህል ካልን ወደ ጀምርነው የመስቀል ታሪክ እንግባ፡፡ መስቀል ማለት እንደ * ተ * ፊደል ቅርጽ ያለው ነው፡፡ በዚህ የእንጨት መስቀል ላይ ቤተ እስራኤላውያን ዓለምና በውስጧ የሚገኘውን ፍጥረት ፈጥሮ የሚገዛውን አምላክ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በእነዚያ ከላይ በተገለጹት ቅንዋት በቀራንዮ አደባባይ ላይ ሰቅለውታል፡፡ በሰቀሉት ግዜም ከመከራው ጽናት የተነሳ ደሙ ወርዶ የተሰቀለበትን መስቀል አልብሶት ስለነበር ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ ተሰቅሎበት የነበረው የእንጨት መስቀል ሌት ተቀን በሙሉ ሳያቋርጥ እንደፀሐይ ሲያበራ በተጨማሪም አጋንንት ሲያባርር ፣ ድውይ ሲፈውስ፣ ሙት ሲያስነሳ አይሁድ ቀንተው በዓዋጅ ትልቅ ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር የቤት ጥራጊና ሐመድ፣ አየተደፋበት የቆሸሸ መከማቻ እንዲሆን ስለተወሰነ አዋጁ ከታወጀበት ቀን አንስቶ ፫፻ ዘመን ድረስ ተቀብሮ ከቆየ በኋላ በ፫፻፳፮ ዓ.ም የቆስጠንጢኖስ እናት እሌኒ ንግሥት የተባለችው ደግ ሴት የክርስቶስን መስቀል ከተቀበረበት ሥፍራ ለማውጣት ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ አደረገች፡፡ እዚያም እንደደረሰች መስቀሉ ያለበትን ቦታ ለማወቅ ስለተቸገረች በአዋጅ እንጨት አሰብስባ እንጨቱን አስነድዳ በላዩ ላይ ዕጣን ስትጨምርበት መስቀሉ ያለበትን ቦታ ለለ ጠቆማት በዚሁ የዕጣን ጢስ ምልክት የክርስቶስን መስቀል መለከረም ፲፯ ቀን ቁፋሮውን አስጀምራ በብዙ ድካምና ከባድ ወጪ መጋቢት ፲ ቀን አገኝታዋለች፡፡ ወዲያው ታላቅ ቤተ መቅደስ ጐልጐታ ላይ አሠርታ በክብር አስቀመጠችው ፡ መስቀሉም እንደቀድሞው ተአምራት መሥራት

መቀጠሉ ተስማ፡፡ በዘመኑ ከነበሩት ኃያላን ነገሥታት መካከ
የፋርሱ ንጉሥ ሆሱኮስ መስቀሉን ማርኮ በኃይሉ ወደ ሀገሩ ወ
ፋርስ ወስዶ ያስቀምጠዋል፡፡ በመስቀሉ መማረክ ያዘኑ
የኢየሩሳሌም ምዕመናን የሮማውን ንጉሥ ሕርቃልን ዕርዳ
በመጠየቅ ተዋግተው በክብር ወደ ነበረበት እስመለሱ
ኢየሩሳሌም ተቀምጦም ብዙ ዘመን ኖረ፡፡ በዚህ መሐል እንደገ
ኃያላን መንግሥታት ይህን መስቀል እኔ እወስዳለሁ እ
እወስዳለሁ እያሉ ጠብ ይፈጥራሉ፡፡

የጠቡን መክረር የተመለከቱ የኢየሩሳሌም
የቁስጥንጥንያ፣ የእንጾኪያ፣ የኤፌሶን፣ የአርመንያ ፣ የግሪክ
የእስክንድርያ ፣ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት የሃይማኖት መሪዎች ጠ
ለማብረድ መስቀሉን እና ሌሎችን የክብር ዕቃዎች በ
እንዲከፋፈሉ ያደርጋሉ፡፡ በወጣው ዕጣ መሠረት የጌታችን የቀ
እጁ ያረፈበት ግማደ መስቀል ለአፍሪካ ሰለደረሳት ከሌሎ
የክብር ዕቃዎች ጋር ወደ ግብጽ መጥቶ የእስክንድርያ
ፓትሪያርክ ተቀብለው በክብር ያስቀምጡታል፡፡

ይህ ግማደ መስቀልም በእስክንድሪያ ለብዙ ዘመና
ሲኖር ከጊዜ በኋላ በግብጽ ያሉ እስላሞች ቁጥራቸው እየበ
በመምጣቱ ኃይላቸውም የዚያኑ ያህል እየበረከተ በመሄ
በእስክንድሪያ በሚኖሩት ክርስቲያኖች ላይ የመከራና የስቃ
ቀንበር ስለአጸኑባቸው ከዚህ ስቃይ ይታደጋቸው ዘንድ በዘመኑ



ኃያል ለነበሩት ለኢትዮጵያው ንጉሥ ለአፄ ዳዊት እንዲህ የሚል ጦማር ( ደብዳቤ ) ይልኩላቸዋል፡፡

« ንጉሥ ሆይ በዚህ በግብጽ ያሉ እስላሞች መከራ አጽንተውብናል እና ኃይልህን አንስተህ አስታግስልን » ብለው ይጠይቁታል በወቅቱ በዚህ መከራ ውስጥ ሁለት ግብጻውያን ጳጳሳት ማለትም አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል የሚባሉ ንዑዳን ክቡራን ጳጳሳት በመታሰራቸው እነዚህ ክርስቲያኖች ለሰደረሰባቸው መከራ መፍትሔ እንዲፈልጉላቸው ለአፄ ዳዊት መልእክት ላኩባቸው፡፡

አፄ ዳዊትም ይህን መልዕክት እንደሰሙ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ መኳንንት ፣ ባሕታዊያንና ካህናት ይዘው በዛሬይቱ መቋድሾ ላይ ጉባኤ ያደርጋሉ፡፡ መቋድሾ በፊት የእመቤታችንና የመድኃኔ ዓለም ቤተመቅደስ ስለነበረባት **<u>መቃ ድስ</u>** ትባል ነበር፡፡ በኋላ አፄ ዳዊትም ሆኑ ጉባኤው በአንድነት ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡

**<u>ውሳኔውም</u>** ፡- ፩ኛ. ሁለቱ ጳጳሳት በአስቸኳይ እንዲፈቱ ፣

፪ኛ. በክርስቲያኖች ላይ የሚደረገው የግፍ አገዛዝ እንዲቆም ፣

፫ኛ. የክርስቶስ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣበትን መንገድ ወስነው ጉባኤው በደስታ ይበተናል፡፡ በዚህ ጊዜ ከንጉሡና ከተወለኑት በቀር ሌሎች ጀግኖች ለአደን በዚያው በሶማሊያ ወደ ጫካ እንደገቡ የአንበሳ መንጋ መጥቶ ግማሹን

በልቶ ግማሹን አቆሰለ:: ከሞት የተረፋትንና የሞቱትን በሙሉ ንጉሡና የቀረው ሠራዊት አምጥተው **ቀብሬደሀር** ላይ ቀበሩአቸው:: ቀብሬደሀር ማለት **ከቀብር መልስ** ማለት ነው:: በዚህም ከተማ ቤተክርስቲያን ሠርተው ወደመሀል ሀገር ጉዞ አደረጉ::

ከዚያም ዳግማዊ አፄ ዳዊት ለመንፈሳዊው ሃይማኖት ቀንተው የክርስቶስ ፍቅር አስገድዷቸው ቁጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ ሠራዊት አስከትለው ወደ ግብጽ ዘመቱ:: በዚህን ግዜ የግብጽ ኃያላን የአፄ ዳዊትን መምጣት የሠራዊታቸውን ብዛት እንደ ሰሙ ንጉሡ ያረፋበት ሰናር (ሱዳን) ካርቱም ድረስ መጡ:: ከዚያም ንጉሡ ሰናር (ሱዳን) ካርቱም ላይ ሁነው መልዕክተኞች ላኩ የመልዕክቱም ፍሬ ነገር ሁለቱ ጳጳሳት እንዲፈቱ፣ እስላሞቹ ከክርስቲያኖቹ ጋር እንዲታረቁ የሚል ነበር:: እነሱም ወዲያው ከክርስቲያኖቹ ታርቀው ሁለቱ ጳጳሳትንም ፈትተው ወርቅና ብር ጨምረው ለአፄ ዳዊት ቢልኩም ፤ አፄ ዳዊት ግን የተፈቱትን ሁለት ጳጳሳት አርሳቸው ዘንድ በማቆየት ከግብጽ መንግሥት የተላከላቸውን የገንዘብና የወርቅ ገፀበረከት በመልዕክተኞቻቸው አስይዘው መልሰው በመላክ ጳጳሳቱን በመፍታታቸው ከክርስቲያኖቹም በመታረቃቸው አመሰግነው የተላከውንም ወርቅና ብር መልሰው በሀገራቸው በኢትዮጵያ ረሀብና ችነፈር በመግባቱ ይህንን መከራ ሲያስወግድላቸው የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረውን መስቀል ቢያገኙ መሆኑን በመግለጻቸው



ይህ ባይሆን ግን ይዘው በመጡት ጦር ወረው በምርኮ እንደሚወስዱት በቁርጠኝነት በመግለጻቸው ግማደ መስቀሉን ከብዙ ንዋየ ቅድሳት ጋር ንጉሡ የነበሩበት ድረስ መስከረም ወር በታላቅ ክብር ካርቱም ገባ:: በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ታላቅ ብርሃን ሦስት ቀን ሙሉ ሲበራ ሰነበተ::

ግማደ መስቀሉም ወደ መካከለኛው ኢትዮጵያ ሳይደርስ አፄ ዳዊት ከበቅሎአቸው ላይ ወድቀው እዚያው ሰናር ( ሱዳን ) ላይ ይሞታሉ:: አፄ ዳዊት አንድ ወንድና አንድ ሴት ልጅ ነበራቸው ወንዱ ልጃቸው መናኝ ሆኖ ያለበት ሳይታወቅ ይኖር በነበረበት ወቅት በማረፋቸው በቦታቸው ሴት ልጃቸው ንግሥት እሌኒ ተብለው እንዲነግሡ ተደረገ:: ሕዝቡ ግን ወንድ ልጅ እንዳላቸው እየታወቀና ይሙት ይኑር ቁርጡ ሳይታወቅ እንዴት በዙፋኑ ላይ ሴት ትቀመጣለች ብለው ውስጥ ውስጡን በማጉረምረም ወንድ ልጃቸውን ቢያፈላልጉም ሲገኝ አልቻለም::

በዚህ መሃል አክሱም ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሃይማኖት በዓል ይከበር ነበርና ከመላው የአፄ ግዛት አማኞች ሁሉ በመጉረፋቸው አክሱም ጽዮን በሕዝበ ክርስቲያን ተሞልታ ሁሉም በየጥጋጥጉ እንጨት እያነደዱ ይሞቁ በነበረበት ሰዓት አንድ መናኝ **እርጥብ እንጨት እየቀሰቀሰ ይሞቅ ኑሮ ተቀጣጥሉ የፍንዳታ ድምፅ ሲሰማ ዩጃን** ልጅ ብሉ በመፎከሩ በአጠገቡ የነበሩ ሰዎች ተጠቃቅሰውና ተጠራርተው ከበቡት::

የአካባቢው ሰው አንተ ማነህና ነው የጃን ( **የጃንሆይ**
ልጅ ብለህ የፎከርከው ብለው ሰለ አዋከቡት ዘርዓ ያዕቆብ
የሚባለው የአፄ ዳዊት ልጅ መሆኑን በመግለፁ ሕዝብ አስገድ
ዘርዓያዕቆብን በዙፋኑ በማስቀመጥ የዘርዓያዕቆብን የምንኩስ
ቆብ በንግሥት አህቱ በእሴኒ ሳይ በመጫን ዘርዓያዕቆብን ስመ
መንግሥቱ ቆስጠንጢኖስ ተብሎ እንዲነግሥ ተደረገ።

አፄ ዘርዓያዕቆብም እንደነገሱ ወደ ሰናር (ሱዳን) ሂደው
ግማደ መስቀሉን እና ሴሎችንም ንዋየ ቅድሳት አምጥተው
በመናገሽ ከተማቸው በደብረ ብርሃን ሳይ ቤተ መቅደስ ሠርተው
ሰማስቀመጥ ሲደክሙ በህልማቸው « አንብር መስቀልየ በዲብ
መስቀል » ማለትም መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ አስቀምጥ
ተብለው ከእግዚአብሔር ይታዘዛሉ። ንጉሡም መስቀለኛ ቦታ
እየፈለጉ በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ መስቀለኛ ቦታ በመፈለግ
እና በማስፈለግ ከብዙ ቦታ አስቀምጡት።

ለምሳሌ በሸዋ በደርሄ ማርያም፣ በመናገሽ አምባ፣
በጨጨሆ፣ በእንጦጦ፣ በደብረብርሃን፣ በአንኮበር፣ ወ.ዘ.ተ
ተራራማ ቦታዎች አሳርፈውት ነበር። ነገር ግን የመጨረሻውን ቦታ
ያሳገኙት በመሆኑ በራዕይ እየደጋገመ መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ
ሳይ አስቀምጥ እያለ ይነግራቸው ሰለነበር ይህን ቦታ ለማግኘት
ሲፈልጉ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለባት ቀን ሱባዔ ገቡ። በዚያም
አሁን መስቀሉ ያለበት የግሸን አምባ አስታያቸው መስቀሉን
ይዘው ባለ አምስት ድርብርብ የሆነው መስቀለኛ ተራራ ሳይ



መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም በራዕይ የተነገረኝ ሥፍራ
ይህ ነው በማለት ተራራውን ሰባት ጊዜ ከዞሩ በኋላ ግማደ
መስቀሉን በመሸከም የአዳል ሜዳ በሚባለው በኩል ያለውን
ገደል እየተንጠላጠሉ ከነመስቀላቸው በመውጣት ከተራራው አናት
ሳይ እንደደረሱ ቀደም ሲል የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት በጥሩ
ሁኔታ አሳንጸው እንዳበቁ ግማደ መስቀሉን በእግዚአብሔር አብ
ቤተክርስቲያን ውስጥ በከፍተኛ ጥንቃቄና ብልሃት በተዘጋጀ ቦታ
ሳይ ጉድጓድ አስቆፍረው በማስገባት ግማደ መስቀሉን በብረት
ሳጥን ውስጥ ከከተቱት በኋላ በተለያዩ ሳጥኖች ውስጥ ደራርበው
በመክተት በግንብ በተሠራ ጉድጓድ ውስጥ ማደና ማደ ብረት
በማስተካከልና በወፍራም ሰንሰለቶች በመጥለፍ በአየር ሳይ እንደ
አልጋ በመወጠር ሳጥኖቹን በሰንሰለቶች በመጥለፍ በአየር ሳይ
እንዲቆም ከተደረገ በኋላ የጉድጓዱ ግንብ ጣራ ተበጅቶለት
ግማደ መስቀሉ ከጉድጓዱ መሀካል ሁኖ ዙሪያውን ራቅ ብሎ ቤት
በመሥራት እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን በአፄ ዘርዓያዕቆብ
የእመቤታችን ቤተ መቅደስ ደግሞ በንግሥት ( **እማሆይ** ) እሴኒ
እንዲታነጽ ተደረገ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፬ ከዞረ
፳፻፫ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ባለማቋረጥ በየዓመቱ
በዓሉ በልዩ ሁኔታ እየተከበረ ይገኛል። የግሸንን እዚህ ሳይ
አናበቃና ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ታሪክ እናመራለን።

**የመስቀሉ በረከት ይደርብን አሜን።**

## ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም

ከአዲስ አበባ ተነስተው ወደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲያቀኑ በ፩፻፭ኛው ኪ.ሜ ላይ ጥንታዊቷን ደሴ ከተማን ያገኛሉ። በዚህች ከተማ ውስጥ ያሉትን ጥንታውያን እና በድንቅ አሠራራቸው የሚታወቁትን እነ ደሴ መድኃኔ ዓለምን ወ.ዘ.ተ አየጐበኙ ከቆዩ በኋላ የደሴን ከተማ ለቀው የመቀሌን መንገድ ይዘው ከደሴ ከተማ በ፴ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ሐይቅ ከተማን ያገኛሉ። በመቀጠል ከከተማዋ በስተሰሜን አቅጣጫ የሚገኘውን መንገድ ይዘው ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ሕሊናን በሚማርክ የተፈጥሮ አቀማመጥ ውበት የተሳበሰውን የሐይቅ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያንን ያገኙታል።

ሐይቁ ፴፭ ስኴር ኪሎ ሜትር አጠቃላይ ስፋት ፯ ኪሎ ሜትር ርዝመት ፣ ፭ ኪሎ ሜትር ወርድ ፣ ፳፻ ሜትር ከፍተኛ ጥልቀት ያለው ሲሆን የሐይቁ ከፍታ ከባህር ወለል በላይ ፪፻፹ ሜትር ነው።

የሐይቅ ደብረ እስጢፋኖስ ተካዩ በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጨረሻው የአክሱም ንጉሥ የነበሩት አፄ ድል ነዓድ ናቸው። የተመሠረተውም በአቡነ ሰላማ ዘአዜብ ሁለተኛ ነው። አቡነ ሰላማ በድንገት ከሐይቁ በስተ ምሥራቅ በኩል __ድማሞ__ በሚባል ተራራ እንዳረፉ ስለደሴቷ ታሪክ ይሰማሉ። እኚህ አባት ሕዝቡን ካስተማሩ በኋላ ወደ አክሱም ሒደው በዘመኑ ለነበረው ንጉሥ ለአፄ ድልነዓድ ለአንተ ለመንበረ መንግሥትህ፣ለእኔም



ለመንበረ ክህነቴ ትሆን ዘንድ የምትገባን ቦታ አለች እና እንሂድ ብለው ይዘውት ይመጣሉ። እንደደረሱም ከአክሱም ይዘውት የመጡትን ታቦተ እግዚአብሔር አብን አርፈውበት በነበረው በድማሞ ተራራ ላይ አስቀምጠው ሕንጻ ቤተክርስቲያኑን አሠርተው ቅዳሴ ቤቱን አክብረው ወደ ደሴቲቱ ይገባሉ። የዚህ ቅዱስ አስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ከመሠራቱ አስቀድሞ __ባሉጥ__ በሚባል ትልቅ ዛፍ ሥር ሕዝቡ የሳም ሥጋና ወተት እየገበረ የሚሰግዱለት ዘንዶ ስለነበር ይህንን ዘንዶ አባ ሰላማ ሁለተኛ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በማለት በመስቀላቸው አማትበው እንደጠፋትም ገድሉ ይተርካል። ቀጥሎ በደሴቷ ውስጥ በ፲፱፻፶ ዓ.ም አንዲት ቤተክርስቲያን በጥሩ ሕንጻ መሥራት ጀመሩ...። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥራው ተፈጽሞ በማን ታቦት ይሁየም። በመላእክት ወይም በጻድቃን ወይስ በማርያም እያሉ ሲጠያየቁ መስከረም ፲፭ ቀን __ቶራ__ የተባለች ሚዳቋ የምትመስል አውሬ «**ምጽ ገበታ**» እየተባለ በሚጠራው የደሴቱ ሰሜን ምዕራብ ጫፍ ላይ ስትጮህ ይሰማሉ። አቡነ ሰላማ የአውሬዋን ጥሪ በመንፈስ ተረድተው ከተከታዮቻቸው ጋር ሲሄዱ አውሬዋ ጽላት ተጭና ያገኟታል። ጽላቱንም ከጀርባዋ ሲፈቱ አውሬዋ ከህዝቡ ተሰወረች። ጽላቱ ላይ ያለውንም ጽሑፍ ሲያነቡ « __ዝውእቱ ታቦተ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት ምስለ ታቦተ ካልዑ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘለውጽዕዎ ኅቡዓን እም ኢየሩሳሌም__ » የሚል ጽሑፍ ያገኛሉ። አብሮም ሁለት ጽላት አለ። ይህ ቀንም እስከ አሁን ድረስ በታላቅ

ድምቀት ይከበራል። ወዲያው ታቦተ ጊዮርጊስን በሐይቁ በስተ ሰሜን ተከለው ጸሎተ እስጢፋኖስን ግን ዛሬ ገዳሙ ካለበት ከደሴቱ ላይ አኖሩት።

የአባ ኢየሱስ ሞአ ገድል ስለ እስጢፋኖስ ገዳም አተካከል ይህን ያህል ካመለከተ በኋላ የዚሁ ገዳም አበ ምኔት (መምህር) ስለነበሩት ስለ አባ ኢየሱስ ሞአ ሲጽፍ እንዲህ ይላል። በዚህች ሀገር ዘ-ክርስቶስ የሚባል ከሚስቱ ከእግዚእ ክብራ ጋር በማይምነት ሲኖሩ.......... ኢየሱስ ሞአ፣ ገብረ ጽዮንና ሰቡሐ አምላክ የሚባሉ ልጆች እንደወለዱ ... ከነዚህ መካከል ኢየሱስ ሞአ ግንቦት ፳፮ ቀን ረቡዕ ፲፪፻፮ ከተወለዱ በኋላ አየተማሩ እንዳደጉ... ቀጥሎ ወደ ደብረ ዳሞ ይምደስ ምሕረት ከሚባለው ጋር ሄደው ከገዳሙ መምህር <u>አባ ዮሐኒ</u> ዘንድ ምንኩስናን ተቀብለው ፯ ዓመት እንደኖሩ ከዚያ ወደ ደብረ ሐይቅ ተመልሰው ያገሩ ተወላጅ <u>ኄር አምላክ</u> ወደ ደሴቱ ውስጥ መርቶ እንዳስገባቸው በዚያም ሲኖሩ ነዋሪዎቹ ትጋታቸውንና ትህትናቸውን ስለተመለከቱ በዘመኑ ወደ ነበረው ወደ ዛጉዌ ንጉሥ ልከው መምህራቸው ይሆኑ ዘንድ እንዳስፈቀዱላቸው ገድላቸው ያመለክታል።

ስለ ገዳሙ መሥራችና አመሠራረት ይህን ያህል ግንዛቤ ካገኘን ዘንድ ገዳሙ የሚገኝበት ሐይቅም ግኝቱን በተመለከተ የሰማሁትንና ያነበብኩትን ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ። አሁን ገዳሙን ከቦ የምናየው ሐይቅ ጥንት በዚህ ሁኔታ



አልነበረም። ሐይቁ ከባሕር ወለል በላይ ፪፻፴ ሜትር ከፍታ አለው። ታሪኩ እንዲህ ነው። በዚያች ሀገር አንዲት ባለጸጋ ሴት ትኖር ነበር። ይህችም ሴት አንዲት አገልጋይ ነበረቻት። አገልጋይዋም እህልን የምትፈጭ ነበረች። እመቤቲቱም ለዚህች አገልጋይ ትፈጭላት ዘንድ ብዙ እህል ትሰጣታለች። ገረዲቱም ምንም እንኳን እህሉን ከእመቤቷ ብትቀበልም ቀን ብዙ አድካሚ ሥራ ስትሠራ በመዋሏ ደክሟት ሳለ ነበር « ወላዲተ አምላክ እኔ ደክሞኛል አንቺ ፍጭልኝ » ብላ ትተኛለች ጧት ከመኝታዋ ተነስታ እህሉን ለመፍጨት ወደ አስቀመጠችበት ቦታ ብትሄድ ያላሰበችው ነገር ይገጥማታል። እህሉም ዱቄት ሁኖ ታገኘዋለች ። ገረዲቱም ወላዲተ አምላክ ያደረገችላትን በማሰብ ድንግል ማርያምን እያመሰገነች በተአምራት የተፈጨውን ዱቄት ለእመቤቷ ተስረከባለች። ቆይታ እመቤቲቷ ይህን ነገር በሰማች ጊዜ ገረዲቱን አስጠርታ ይህን እህል አንቺ ስላልፈጨሽው ስትፈጪው እኔም ሆንኩ ማናችንም ስላላየንሽና ስላለማንሽ ደሞዝሽን አልከፍልሽም ትላታለች። ገረዲቱም « የቀጠርሽኝ እሁሉን እንድፈጭልሽ ነው »። እህሉ ደግሞ ተፈጭቶ አስረክቤሻለሁ። ስለዚህ ደሞዜን ልትከፍይኝ ይገባል ትላለች። በዚህ ሁኔታ አለመግባባቱ እያየለ በመምጣቱ ነገሩ ወደ ሽማግሌ ዘንድ ይደርሳል። ሽማግሌዎችም ለባለጸጋዋ ሴት በማድላት « **ስትፈጪ ስላልታየሽ ሊከፈልሽ አይገባም** » ብለው በገረዲቱ ይፈርዱባታል። እርሷም ፍርዱ ትክክል ያለመሆኑን እንዳወቀች

ጉዳዩን እረኞች እንዲያዩሳት በመጠየቋ እረኞች ዘንድ ይዛት ትሄዳለች እረኞችም ነገሩን ካደመጡ በኋላ « የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጥው » ነውና ዱቄቱ ተፈጥቶ እስከ ቀረበልሽ ድረስ ደሞዟን ለትከፍያት ይገባል ብለው ይፈርዱባታል፡፡ ይህ ነገር በተፈጸመ ማታውኑ ያልታሰበ ዝናብ መጥቶ ፍርዱን አዛብተው የፈረዱባት ሽማግሌዎች ያሉበት ስፈርና አካባቢው በሙሉ ሰጠመ፡፡ ከመሬቱም ውኃ መነጨ ዙሪያውም ውኃ ሆነ፡፡ ነገር ግን ዛሬ ገዳም ሆኖ የምናየው አካባቢ እረኞች የነበሩበት ሥፍራ በመሆኑ ሳይሰጥም ቀረ ይሰናል ገድለ አባ ኢዮሱስ ሞአ፡፡

ይህ ቅዱስ ሥፍራ ከትውልድ ትውልድ ከዘመን ዘመን የሚቀዩ የማይለወጡ የማይሻሩ መንፈሳዊያን አባቶቻችን ያቆዩልን ቅርሶችንም ይዞ ይገኛል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

* እነ አጺ ድልነዓድ ያርፉበት የነበረ ቤት፣
* ጻድቁ አባት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለመመንኮስ በገዳሙ በቆዩበት ወቅት ለመነኮሳቱ ምግብ ይፈጩበት የነበረው ወፍጮ፣
* ጻድቁ እህሉን ሲፈጩ ይሸከሙት የነበረ ወደ ፲ ኪ.ግ የሚመዝን ከዕብነ በረድ የተሠራ መስቀል፣
* [illegible] ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረ አና ለወፕ ማጠራቀሚያነት ይገለገሉበት የነበረ ጋንና ማማሰያዎች



* አቡነ ተክለሃይማኖት በጸሉት ግዜ አንገታቸውን የሚያስደግፉበት የእንጨት ባላ አንደተተከለ፣
* በአይጥና በብል ምክንያት ሲጠፉ የተቃረቡ ውድ የብራና መጻሕፍቶች ወለሉን ሲሾ የሚያደረገው በመጥፋቱ መሬት ላይ ለሌን ተነጥፎላቸው የተቀመጡ ቅርሶች፣
* ከዛሬ ፩፻ ዓመት ምሕረት በፊት በሐይቅ ውስጥ የነበረና አሁን ድረስ ያለ በባሕር አንበሳት ቅርፊት ( ሼል ) ተሸፍኖ የተገኘ አንበራ፡፡

በአጠቃላይ በዚሁ ቅዱስ ቦታ ያለው የሱማ፣ የብርቱካን፣ የማንጐ ወ.ዘ.ተ በአረንጓዴ ዕጽዋት የተሸፈነ መሬት ከሐይቁ ውበት ጋር ተዳምሮ ምድራዊ ገነት የመሰለ ሥፍራ በመሆኑ ማንኛውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አምነት ተከታይ ሊያየውና የአባቶችን በረከት ሊቀበልበት የሚገባ ቅዱስ ሥፍራ ነው፡፡

**የሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ ረድኤት በረከት አይለየን**

**አሜን**

## የቅዱስ ባልደበባል ታሪክ

ቅዱስ ባልደበባል ታህሣሥ ፳፬ ፲፱፻፲፪ ዓ.ም ከዛን ስዩምና ከወ/ሮ ኪሪወርና ተወለደ። ኪሪወሪና ማለትም በአገውኛ ቋንቋ ቤተክርስቲያን ማለት ነው።

በዚህም ምክንያት ደራሲው « **ዘመሐረተከ ጥበብ እረፍተ እማዳማ ቤተ ክርስቲያን ለእምከ ለማ** » ብሎ ጽፎለታል።

ቅዱስ ባልደበባል ከመወለዱ በፊት የነበሩት ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶች ቅዱስነቱን በትንቢት አነደ ገለጹት ታውቋል። ባልደበባል ማለትም « **ንብ** » ሲበላው ማለት ነው። ይኸውም ቅዱስ ባልደበባል በተወለደ ጊዜ ሰዎች በሳዩ ላይ ንቦች ሠፍረውበት እንደማር ሲልሱት አይተው ያወጡለት ስም ነው «**ባል**» ማለት በአገውኛ ቋንቋ **ንብ** ማለት ነው። **ደበባል** ሲጨመርበት **ባልደበባል** የሚል ቃል ( ስም ) አስገኝቶለታል ስለዚህ ትክክለኛ ስሙ ባልደበባል ነው።

ባልደበባል ቡግና እየተባለ በሚጠራው በአባቱ በዛን ሥዩም ቤተ መንግሥት ውስጥ ለነገሥታት ልጆች የሚሰጥ መንግሥታዊ የአስተዳደር ሥርዓትና የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እየተማረ አደገ። ነገር ግን ቅዱስ ባልደበባል ከህፃንነቱ ጊዜ ጀምሮ የነበረው የክርስትና እምነት እጅግ ጸኑ ስለ ነበር እንደ ጓደኞቹ የነገሥታት ልጆች በምቾትና በቅንጦት መኖርን የማይወድ ዘወትር ከቤተ ክርስቲያን የማይለይ እንደ ነበር ይነገርለታል።



በጾምና በጸሎት ጸንቶ የኖረ ቅዱስና ጻድቅ መሆኑንም ገድሉና ታሪክ ነገሥት ይመሰክሩለታል።

ባልደበባል በ፳፪ ዓመቱ ወንድሙ አፄ ገብረማርያም እንደተመቀኘውና አንድ ቀን በነገረ ሰሪዎች ምክንያት ከሦስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ እንዳሰገረፈው ዜና ገድለ ባልደበባል ይገልጻል። ነገር ግን እስራኤላውያን ኤርምያስን በገረፉት ጊዜ ከአጠገቡ በነበረው ድንጋይ ላይ ጅራፉ እያረፈ ከጥፋት እንደ ሰወረው ሕይወቱም ከሞት እንደ ተጠበቀ ሁሉ ቅዱስ ባልደበባልም አፄ ገብረማርያም ከሦስት እስከ ዘጠኝ ባሰገረፈው ወቅት እግዚአብሔር እንደ ሠወረው እንረዳለን። እዚህ ላይ አንድ ሰው ስድስት ሰዓት ተገርፎ በሕይወት መገኘት እግዚአብሔር በወዳጆቹ ላይ የሚገልጸውን ገቢረ ተአምር የሚያመለክት የመስተጋድላን ክርስቲያን ሃይማኖት የሚያጸና ስለሆነ የእግዚአብሔርን ኃይል ለጹብ ድንቅ ብሎ በአንክሮ ከመቀበልና ከማድነቅ በቀር ሌላ አስተያየት ሊሰጠው የማይቻል ነው።

አፄ ገብረማርያም ወንድሙን ካስገረፈው በኋላ የሞተ መስሎት አውጥተው እንዲጥሉት አዘዘ። ቅዱስ ባልደበባል ግን እግዚአብሔር ከግርፋትና ከጥፋት ከልሎታልና እንኳንስ ሊሞት ግርፋቱም አልተሰማውም። ስለዚህም ከጊዜያት በኋላ አፄ ገብረማርያም የወንድሙን የባልደበባልን በሕይወት መኖር ሰማ። ይሁን እንጂ እውነት አልመሰለውምና አስጠርቶ መጥቶ ፊቱ በቆመ ጊዜ እጅግ ተደነቀ። ከባድ ኀዘንም ተሰማው። እግዚአብሔርንም

በድያለሁ የማይገባ ሥራ ሠርቻለሁ ብሎ ቅዱስ ላልይበላን በሕዝቡ መካከል ከዛሬ ጀምሮ መንግሥት ላንተ ይገባል በግፌ አስገርፌሃለሁና ይቅር በለኝ በማለት ከጫማው ወድቆ ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ መንግሥቱን አስረክቦ መንና ለመሄድ ወሰነ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት ቅዱስ ላልይበላም ለይቅርታው ይቅር ብየሀለሁ ነገር ግን « እስመ ለእግዚአብሔር መንግሥት » እንዳለ ነቢይ መንግሥት የእግዚአብሔር ገንዘብ ናትና መንግሥትህን የምቀበለው ከእግዚአብሔር እንጂ ከአንተ አይደለም አንተም በዙፋንህ መቀየት አለብህ እኔም መልሰም ሆነ ፈቃድ ከእግዚአብሔር እስካገኝ ድረስ በትዕግስት እጠባበቃለሁ ብሎ የአጼ ገብረማርያምን ጫማ ስሞ በፍቅር ተሰናብቶ ወጣ፡፡

በዚህ ጊዜ ሕዝቡ መንግሥትን ያህል ነገር እንደቀላል ነገር ቆጥሮ አልነግሥም አንተ በመንግሥትህ ቆይ ብሎ ትቶ መሄዱ እንዴት የእግዚአብሔር መንፈስ ቢያድርበት ነው? በማለት በችሎት ተቀምጦ ሁኔታውን በግብር ሲከታተል የነበረው ሁሉ አያለቀሰ ቅዱስ ላልይበላን ተከትሎ ወጣ፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱስ ላልይበላ ዘመዶቹና ቤተሰቦቹ ሳይሰሙ ወደ እየሩሳሌም ለመሄድ ከአገሩ ተነሳ፡፡ ከዚያም በአክሱም ቤተ መቅደስ ለሰባት ቀን ያህል በጸሎት ቆይቶ እግዚአብሔርን ጠይቆ በሱዳን ምድር አቋርጦ ወደ ግብጽ ሀገር ሔደ፡፡ ግብጽም ብዙ ክርስቲያኖችን አገኝ ከነርሱ ጋርም ተዋወቀ፡፡ በምን ሰይነት ኑሮ እንደሚኖሩ እየጠየቀና እያጠና ከቆየ ከአደረ በኋላ ከእግዚአብሔር የታዘዘ



መልአክ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ አንተ ወደ እየሩሳሌም ለመሄድ አልተፈቀደልህም ይልቁንስ እነዚህ በግብጽ ምድር የተበተኑት በጐቹን ወደ መጣህበት ወደ ኢትዮጵያ ይዘህ ተመለስ ብሎ ስለነገረው በግብጽ ያሉትን ክርስቲያኖች ሰብስቦ በጊዜው የነበረው የግብጽ መንግሥት እንዴት አድርጐ እንደሚያስተዳድራቸው ጠየቃቸው፡፡ ክርስቲያኖቹም መልሰው የእግዚአብሔርንም መሥዋዕት ከመሠዋት ተከልክለው የሚኖሩ መሆናቸውን በኀዘን በለቀቀን ገለጹለት፡፡

ቅዱስ ላልይበላ በፈቃደ እምላክ ስልሳ ሺህ ክርስቲያኖችን ይዞ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡ ሆኖም ቅዱስ ላልይበላልና ክርስቲያኖቹ በዚህ ጉዞ ላይ ብዙ ችግርና መከራ ቢደርስባቸውም እግዚአብሔር ኃይላቸውና ረድኤታቸው ስለሆነ በሰላም ወደ ምድረ ኢትዮጵያ እንደገቡ እንገነዘባለን፡፡

አጼ ገብረማርያም ወንድሙ ቅዱስ ላልይበላ ሕዝበ ክርስትያንን ይዞ የኢትዮጵያን ምድር እንደረገጠ በሰማ ጊዜ በክብር የሚቀበለው ቁጥር ስፍር የሌለው ሠራዊት አሠልፎ ወደ ቤተመንግሥቱ እንዲመጣ ላከለት፡፡ ቅዱስ ላልይበላም ይህን መልእክት በሰማ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደደረሰ አውቆ ልዋል ልደር ሳይል ወደ ቡግና ቤተመንግሥት መጥቶ ከወንድሙ ከአጼ ገብረማርያም ጋር ተገናኘ፡፡ ወዲያው ንጉሱ አጼ ገብረማርያምም ወንድሙ ቅዱስ ላልይበላን ባየው ግዜ በፍቅር እንባ ተቀበለውና ሕዝቡን ሰብስቦ አሁን የእግዚአብሔር ፈቃድ

ደርሷል መንግሥት ለዚህ ሰው ይገባል ብሉ ዙፋኑን ለቅዱስ ሳልይበላል አስረክቦና ተሰናብቶ ዛሬ **<u>ቅዱስ ሀርቤ</u>** እየተባለ ወደሚጠራው ገዳም ሄደ። በዚያም ዘግቶና በጾም በጸሎት በቀናና ሰውነቱን ለእግዚአብሔር አስገዝቶ በክብር አርፎአል።

ቅዱስ ላልይበላል ከዚያን ቀን ጀምሮ መንግሥቱን ተቀብሉ ሕዝቡን በሰላም በሃይማኖት ይመራ ጀመር። ቅዱስ ላልይበላል በዘመነ መንግሥቱ ሁሉ እንደ ሌሎች ነገሥታት ርስት ጉስት ፈፅሞ እንዳልነበረው ታውቆአል። ከሕዝቡም በንጉሥነቱ ምክንያት የሚቀበለው ግብርም ይሁን ሌላ ምንም አልነበረውም።

ቅዱስ ላልይበላል ንጉሥ ነኝ ብሉ ሥልጣኑን ጨብጦ አስተዳደሩን ጨቁና አልያዘም። ሥልጣኑን ለሕዝቡ ሰጥቶ በሕዝቡ ይመራ እንደ ነበር ታሪክ ነገሥት ይመሰክራል። ከሁሉ የሚያስደስተው፣ የሚያስቀናውና የሚያስደንቀው ደግሞ ለዕለት ምግቡ እንኳ ከችሉት ሲመለስ በሰውር ለሌን እየሠራ ያንንም ለታማኝ አሽከሩ ሰጥቶ እየሸጠ ከዚያው ገንዘብ ጥሬም ሆነ ቁራሽ እንጀራ ለቁመተ ሥጋ ያህል ይቀምስ ነበር እንጂ እንደሌሉቹ ነገሥታት ጮማ በመቁረጥ፣ ጠጅ በማማረጥ ልብሰ መንግሥት ለብሶ በመሽሞንሞን አልኖረም። በዘመኑም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያስተምሩ የቅዱሳት መጻሕፍት መምህራን በብዛት ይገኙ ስለ ነበርና እነርሱም ተግተው ያስተምሩ ስለነበር ኃጢአት የሚሠራ አንድም እንዳልነበር ተገልጿአል።



ሕዝቡም የቅዱስ ላልይበላልን የሃይማኖት ፅናትና ደግነት አያየ ይህን ሃይማኖታዊ ንጉሥ ዕድሜውን አርዝምልን እያሉ ይጸልዩለት እንደ ነበር ተረጋግጧአል። የቅዱስ ላልይበላል ደግነትና ሃይማኖት ጽኑነትን የሚያስረዱ አሁን የምናያቸውና የአለም ተረሰቶች ሲጎበኙአቸው የሚኖሩ ዐሥሩ ቤተ መቅደሶች በመሳእከት ተራዳኢነት አንጾና ሠርቶ ለትውልደ ትውልድ እንዲተሳሰፍ አድርጓአል።

ቅዱስ ላልይበላል መዋዕለ ዘመኑን በሰላምና በጽኑ እምነት ከአሳለፈ በኋላ ሰኔ ፲፪ ቀን ፲፩፻፸፪ ዓ.ም በነገሡ በ፵ ዘመኑ እግዚአብሔር ለመረጣቸው ለዘለዓለም ደስታና ዕረፍት እንደተፈቀደላቸው ዓለም ሳይፈጠር ያዘጋጃትን መንግሥተ ሰማያት እንዲወርሰ ጠርቶታል።

**የቅዱሱ ረድኤት በረከት አይለየን አሜን!**

ከዚህ በመቀጠል የቅዱሱን የጥበብ ሥራዎች አንድ በአንድ ለማየት እንሞክራለን።

## ቤተ መድኃኔ ዓለም

ደብረ ሮሀ ( ላሊበላ ) ከተማ ገብተው ቅዱስ ላልይበላ ያነጻቸውን ዓሥራ አንዱን ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ለመጎብኘት ሲነሱ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚያገኙት ይህን በስፋቱ እና በአሠራር ጥበቡ የሚስተካከለው የሌለ ግሩም ቤተ መቅደስ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኑ ተዋቅሮ የተሠራው ደመቅ ካለ ድንጋይ ሲሆን ከዚሁ ዓለት ላይ ተጠርበው የወጡት ጠንካራ ምለሶዎችም የቤተክርስቲያኑን የጣሪያ ክፍል ክብደት በመደገፍ ቆመው ይታያሉ፡፡ ነገር ግን በውጭ በኩል ቆመው የጣሪያውን ክፍል ደግፈው ከያዙት ምሰሶዎች መካከል አንዳንዶቹ ተሰባብረው በመውደቃቸው ምክንያት በእነዚህ በወደቁት ምሰሶዎች ምትክ አዳዲስ በሲምንቶ የተያያዙ ምሰሶዎች ቆመው ይታያሉ፡፡ በአጠቃላይ ከውስጥም ከውጭም ቤተ መድኃኔ ዓለምን ደግፈው የሚገኙት ምለሶዎች ብዛት ፸፪ ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል በውጭ በኩል ፴፬ ዓምዶች ( ምሰሶዎች ) ሲገኙ በውስጠኛው ክፍል ደግሞ ፴፰ ዓምዶች ይገኛሉ፡፡

የቤተመድኃኔ ዓለም ኪነ ጥበባዊ የህንፃ ሥራ ከውጭ ሆነን ስንመለከተው ጣሪያው አሞራ ክንፍ አያልን ከምንጠራው የቤት አሠራር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን በዚሁ በላይኛው በውጭ በኩል ባለው የጣሪያ ክፍል ላይ በበር ቅርጽ ተዋቅሮ የተሠራ ቅርጽ ይታያል፡፡ ይህ የላይኛው የጣሪያ ክፍል ከዕድሜ ብዛት በደረሰበት መጠነኛ ጉዳት ምክንያት መጠነኛ እድሳት



ስለተደረገለት የቀድሞ ይዘቱን እንዲይዝ አድርጎታል፡፡

<u>የቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታ</u> ፡- የቤተ መድኃኔ ዓለምን ውስጣዊ ይዘት ስንመለከት በጥንቃቄ የተከናወነ እና እጅግ ልዩ ጥበባዊ ሥራ የታከለበት ቅዱስ ሥፍራ ነው፡፡ የቤተክርስቲያኑ የውስጠኛ ክፍል በ፴፰ ዓምዶች ( ምሰሶዎች ) የተደገፈ ሲሆን ይህ ግዙፍ እና ሰፊ ክፍል በውስጡ አምስት የቅኔ ማኅሌት መተላለፊያ ክፍሎች ሲኖሩት የእነዚህ ክፍሎች የጣሪያው ክፍል ልሙጥ ነው፡፡

በየክፍሉቹ ውስጥ ያሉት ምሰሶዎች አሠራራቸው በሙሉ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያላቸው ሲሆን በመጠን አንድ ወጥ ይሆኑና በስተመጨረሻ ላይ የመስቀል ቅርጽን ይይዛሉ፡፡ ታዲያ እነዚህን ምሰሶዎች ልዩ የሚያደርጋቸው ከታች ጀምረው እስከ ላይ ድረስ በአንድ ዓይነት ስፋት መዝለቃቸው ነው፡፡

በቤተ መድኃኔ ዓለም ውስጥ ከምናያቸው አንዳንድ ቅርጻ ቅርጾች በስተቀር እንደ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ብዙም ጌጣጌጦች እና የቅብ ሥራዎች አይታዩም፡፡ የቤተክርስቲያኑ መስኮቶች ለብርሃን ማስገቢያነት የሚያገለግሉ እና በመስቀል ቅርጽ ተቀርጸው ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተሠሩ ናቸው፡፡ በእነዚህ መስኮቶች ላይ በኖራ መሰል ማጣበቂያነት የተጣበቁ ማራኪ ቀለም ያላቸው መስታወቶች ይታያሉ፡፡

አሁን በቅርቡ ተሰርቆ የተመለሰው እና «<u>አፍር አይገባ</u>» በመባል የሚታወቀው ከሰማይ የወረደው ድንቅ መስቀልም የሚቀመጠው በዚሁ በቤተ መድኃኔ ዓለም ውስጥ ነው። ቤተ መድኃኔ ዓለም በ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በተነሳው በግራኝ መሐመድ አማካኝነት መጠነኛ ጥቃት የተፈጸመበት ነው።



ቤተ መድኃኒዓለም



## <u>ቤተ ማርያም</u>

በራሱ ስፊ ግቢ ውስጥ ያለውን የቤተ መድኃኔ ዓለምን የጉብኝት መስመር እንደጨረሱ ቀጣዩ የጉብኝትዎ ምዕራፍ የሚሆነው ከዚሁ ግዙፍ ግቢ ቀጥሎ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስም የታነጸ ቤተክርስቲያን ነው። ወደዚህ ቤተክርስቲያን ለመድረስ ከቤተ መድኃኔ ዓለም በስተ ምዕራብ በኩል የሚገኘውን አጭር የዋሻ ውስጥ መንገድ ማለፍ የግድ ይሆናል።

ቤተ ማርያም በአራቱም አቅጣጫዎች በአብያተ ክርስቲያናት የተከበበች ናት። የሚያዋስኗትም በስተ ምሥራቅ ቤተ መድኃኔ ዓለም በስተ ምዕራብ ቤተ ጐልጐታ ፣ በስተ ደቡብ ቤተ ደናግል እና በስተ ሰሜን ቤተ መስቀል ናቸው። ቤተ ማርያም በአካባቢው ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ስብስብ መካከል ልዩ ቦታ የሚሰጣት ቅዱስ ሥፍራ ናት። ስለ እውነት ከሆነ ቤተ ማርያምን ከሕንጻ ቤተ ክርስትያኗ አወቃቀር ጀምሮ ስንመለከት ቅዱስ ላሊበላ ካነጻቸው ሕንጻዎች መካከል መጀመሪያ ያነጻት እርሷን ነው ተብሎ የሚተረከው እና ቅዱሱ ከሁሉም ካነጻቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል በይበልጥ ይወዳት ነበር የሚባለውን የታሪክ መዛግብቶችን ምሥክርነት ያጠናክርልናል። እንደውም ንጉሥ ላሊበላ ከዚህች ቅድስት ሥፍራ ዘወትር ሳይገባ አይውልም ነበር። አሁንም ቢሆን ይህች ቤተክርስቲያን በእኛ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምዕመናን ዘንድ በጣም ተወዳጅ ነች።

በበዓላት ቀን የቤተ ማርያም ቅጥር ግቢ ከየክፍላተ አህጉሩ በሚመጡ ምዕመናንና ካህናት ትጨናነቃለች፡፡

ቤተ መድኃኔ ዓለምን ተሳልመው የሚመለሱ እንግዶች ወደ ቤተ ማርያም እንደቀረቡ የርህራሄ እና የሠላማዊ መንፈስ ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ በቤተ ማርያም የሚገኙት መንፈሳዊ ቅርሶች እንኳ ከአመቤታችን እውነተኛ የአምላክ እናትነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው፡፡

የቤተ ማርያም ወለሉ በምዕራብ አቅጣጫ ከሚገኘው መግቢያው አንስቶ ለተመለከተው ከጥንታውያኑ ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት አሠራር ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሁለት የቅኔ ማኅሌት መቋሚያ ሥፍራዎች ሲገኙ በቤተክርስቲያኑ ምዕራብ ሰሜን እና ደቡብ መግቢያ ያሉት በሮች በአብዛኛው የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የማይታዩ ልዩ ልዩ ፈጠራዎች ታክለውባቸዋል፡፡ በምሥራቃዊው የቤተክርስቲያኑ ግድግዳ አካባቢ የመጠመቂያ ገንዳ አለ፡፡ ገንዳው በአሁኑ ወቅት ባዶውን ሲገኝ ሌላኛው የውኃ ገንዳ ውስጥ ያለው ውኃ ( ጸበል ) ከተለያዩ ደዌዎች የመፈወስ ኃይል አለው፡፡ በተለይ መካን የሆኑ እናቶች ወደዚህ ሥፍራ በመምጣት ቅድስና የተላበሰችውን የእግዚአብሔር ወልድን እናት ወላዲተ አምላክን ሲማጸኑአት በጥንቀታቸውና በሐዘናቸው ፈጥና በመድረስ በጸበሏ የእናቶችን ማኅፀን ዘር እንዲቋጥር እንደሚያደርግ ይመሰክርለታል፡፡ ይህንን ዕድል ለማግኘት ሲሉ እናቶች በጸበሉ ዙሪያ ይሰለፋሉ፡፡ ካህናቱ ደግሞ



በደቡብ ጠርዝ ላይ ቆመው ሥርዓተ ጸሎት ያደርሱና ሥርዓቱ ይፈጸማል፡፡

ቤተ ማርያም ሕንጻ ቤተክርስቲያኑ ፲፫ X ፱.፪ X ፲.፭ ማትር በሆነ ርዝማኔ ላይ ይገኛል፡፡

## የቤተክርስቲያኑ የውጭ ገጽታ ፡-

ቤተ ክርስቲያኑ ከጣሪያው በስተቀር በቀላል የመስቀል ቅርጾች የተጌጠ ነው፡፡ በግድግዳዎቹ ዙሪያ አግድም የተቀመጡት ቅርጾች ልዩ ውበት አላቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ስሙጥ የሆኑት የመግቢያ በሮች የተለየ መስህብ አላቸው፡፡ ከውጭ የሚገኙት የቤተክርስቲያኒቱ ቅርጻ ቅርጾች አብዛኛዋቹ ወድመዋል፡፡ በመካከለኛው ምሰሶዎች ላይ የጥንታውያኑ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መስቀሎች ተቀርጸው ይታያሉ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ የሚያስደስተው እና የሚያስደንቀው ነገር ቢኖር በውጭው ግድግዳ በምዕራቡ ገጽ ላይ ጦር የያዙ የሁለት ፈረሰኞች ምስል ጉብተኛነት ባለው አቀራረጽ ስልት ተቀርጸው ማየቱ ነው፡፡ ሁለቱ ፈረሰኞች እየተዋጉ የሚያሳየው አንድ ክንፍ ካለውና ምንነቱ ካልታወቀ እሳት ከሚተፋ ፍጡር ጋር የሚያደርጉትን ፍልሚያ የሚያሳይ ምስል ነው፡፡ ቀደም ብሎ በሚገኘው ፈረስ ቀኝ ታፋ ላይ የአሞራ ( የንስር ) ሥዕል አለበት፡፡ ሁለቱ ፈረሰኞች በቀኝ እጃቸው ጦራቸውን ሰብቀው አውሬውን ሲፋለሙት ከፈረሰኞቹ ራስ ላይ ያሉትን ዝርግ ነገሮች

በተለያዩ መንገዶች ሲተረጉሟዋቸው ይታያሉ፡፡ በተለይ ሁለት ወገኖች እንዲህ ይላሉ፡፡ አንደኛው ወገን ይህ ከብ ቅርጽ የፀሐይ ምልክት እንዲሆን ታስቦ የተሣለ ነው ሲል ሁለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ ክብ ቅርጾቹ በፈረሰኞቹ የሚያዙ ጋሻዎች ናቸው ይላሉ፡፡ ይሁንና ቦታው ለጋሻ መቀመጫ እና ለፈረሰኛ ጥሩ ውጤት የሚሰጥ እንደሚሆን ነው የሚታመነው፡፡ ነገር ግን ከሁለቱ ግምት ሰጪዎች ውጪ ያሉም ሦስተኛ ወገኖችም በሁለቱ ወገኖች ሐሳብ ሳይስማሙ ይቀሩና የለም ይህ ክብ ቅርጽ ለፈረሶቹ የተሠራ ጌጥ ነው ብለው አጥብቀው ያስረዳሉ፡፡ ሌላው በቤተክርስቲያኒቱ ዙሪያ ያሉት የመስቀል ዓይነቶች ከላቲኖች ፣ ከግሪኮች ወ.ዘ.ተ መስቀል አሠራር ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

## የቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታ ፡-

ቤተ ማርያም ባለ አንድ ፎቅ ህንጻ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ ቤተመቅደሷ ሦስት ደጃፎች ያሏት ሲሆን ለእያንዳንዱ ደጃፎች ደግሞ ሁለት ሁለት ዓምዶች አሏቸው፡፡ የዓምዶቹ ስድስት መሆን የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ ናቸው፡፡ የእነዚህ ዓምዶች (ምሰሶዎች) ቁመታቸው ፪ ሜትር ከ፺፩ ሳንቲ ሜትር ወርዳቸውም ፴፮ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡ የሦስቱ ዳጆፎች ቁመታቸው ፩ ሜትር ከ፳፭ ሳንቲ ሜትር ሲሆን ወርዳቸው ደግሞ ፸፮ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡ ቤተክርስቲያኗ በውስጧ በተለያዩ መንፈሳዊ ጌጣጌጦች ማሸብረቋ በተለይ የጉብኝን ዓይን ለቅጽበትም ቢሆን እንኳን



ያፈዝዛል፡፡ ለቅጽበትም ቢሆን እንኳን ያፈዝዛል፡፡ ውስጡ ምንም እንኳን ሁለት ጣሪያዎች ያሉት ቅኔ ማኅሌት ቤቶች ቢኖሩትም የዋሻ ቅርጽ ባለው ግርዶሽ ተለያይቶ ይገኛል፡፡ ቅኔ ማኅሌቱ በመስኮት ቅርጽ ከተሠሩ ጌጣጌጦች ተውበው ይታያሉ፡፡ እነዚህን ድንቅ ሥራዎች አንገቱን ቀና አድርጐ ላያቸው ልዩ እርካታን ይሰጣሉ፡፡ ውስጣዊው የበር ገጽታዎች ከአክሱማውያኑ የጥበብ ሥራዎች ጋር ተቀራራቢነት አላቸው፡፡

ወደ ላይኛው ፎቅ የሚያስገባውን የጃፍ የምናገኘው በመቅደሱ ውስጥ ሲሆን ቀመቱም ፩ ሜትር ከ፸፯ ሴንቲ ሜትር ነው፡፡ እዚህ በውስጠኛው ክፍል ውስጥ ያሉት ደጃፎች እያንዳንዳቸው አንዳንድ አርከን አላቸው፡፡ በመንበሩ ግራና ቀኝ ሁለት ደጃፎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ደጃፎች መካከል በስተ ሰሜን በኩል የሚገኘው ደጃፍ የታቦተ ዮሐንስ መጥምቅ መግቢያ ነው፡፡ የዚህም መግቢያ ቁመት ፩ ሜትር ከ ፶፫ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡ በመቅደሱ ውስጥኛ ክፍል ፯ ዓምዶች ያሉ ሲሆን የእነዚህ ዓምዶች ቁመታቸው ፪ ሜትር ከ ፸ ሳንቲ ሜትር ወርዳቸው ፺፩ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡

ወደ ቤተክርስቲያኗ የውስጥ ክፍል እየቀረቡ በሄዱ ቁጥር አንድ በጨርቅ የተሸፈነ አምድ ( ምሰሶ ) ያገኛሉ የዓምዱ ቁመት ፯ ሜትር ከ ፶፭ ሳንቲ ሜትር ሲሆን ወርዱም ፺፭ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡ ይህ ምሰሶ በጨርቅ የተሸፈነው በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ሲቀ ካህናት ዜና በተባሉ የደብሩ አስተዳዳሪ

አማካኝነት ነው። ይህ አምድ ያእምነት አንድነት መግለጫ እንደሆነ የሃይማኖት አባቶቻችን ይናገራሉ። ቅዱሱ ንጉሥ ሳሲበሳ በዘመኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾለት ከዘመነ ፍጥረት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያለውን የዓለማችንን እጣ ፈንታ አንድ በአንድ በዚህ ዓምድ ላይ ተጽፈው ይገኛሉ። የምሰሶዋ በጨርቅ የመጋረድ ምስጢርም የሰው ልጅ በእግዚአብሔር የተሰጠውን እውነታ ለመሸከም ደካማ እንደሆነ ለማሳየት ሲባል ነው እየተባለ ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ አባቶች ሲመሰክሩ ቆይተው አሁን ድረስ ምሥክርነቱ እንደጸናና እንደተጠበቀ ይገኛል። የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሐዲስ ኪዳን ክፍል የተወሰዱ ሥዕላዊ መግለጫዎች በግድግዳዎች ላይ ተስፈው ይታያሉ። ቅድስት ኤልሳቤጥን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለትጐበኛት በመጣች ግዜ ሁለቱ ተቃቅፈው ሰላምታ ሲለዋወጡ ፣ እመቤታችን ጌታን የመፅነሷን ዜና ከመልአኩ በሰማች ጊዜ ፣ በኢትዮጵያውያን የአሣሣል ጥበብ በትልልቅና በጥቋቁር ዓይኖች መልአኩን በመገረም ስትመለከተው፣ ይህ ሥዕል እመቤታችን ከፍተኛ ክብርና ትህትና እንዳላት ያመለክታል።

ሴላው ቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሚገኘው ሥዕልም እመቤታችን ወደ ግብጽ ያደረገችውን ስደት ያመለክታል። በሥዕሉ ላይ እመቤታችን በአህያ ጀርባ ተቀምጣ ትታያለች። የቴምር ዛፎች በደረቁ መሬት ላይ ተንዠርገው በለምላሚያቸው



እመቤታችንን ሲቀበሉአት ፣ ሳምራዊቷ ውኃ ቀጂ ሴት ከጉድጓድ ውኃ ለትቀዳ ስትጣጣር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከውኃው እንድታጠጣው በጠየቃት ጊዜ በመካከላቸው የነበረውን የቃላት ልውውጥ የሚያመለክት ሥዕል ፣ ፴፰ ዓመት ሙሉ የአልጋ ቁራኛ የነበረው መጻጉ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውስ አግኝቶ እንዲሄድ ሲያዘው ይተኛበት የነበረውን ድንክ አልጋ ተሸክሞ ሲጓዝ የሚያሳይ ሥዕል ፣ ለእነዚያ የሚበላ ምግብ ሳልነበራቸው መድኃኔ ዓለም ጥቂት አሣዎችንና ዳቦዎችን ባርኮ ሲሰጣቸው የሚያሳየው ድንቅ ሥዕል በቤተ መቅደሱ ቀኝ በኩል ከጣሪያው ሥር ይታያል። በወቅቱ እነዚህን ውብ ሥዕሎች የሣላቸው ጠቢብ በሬዎችና አውራ ዶሮዎች እርስ በርሳቸው ሲፋለሙ የሚያሳይ ምስል ለማስቀመጥ ሞክሯል። እነዚህ ሁሉ ቅዱሳት ሥዕሎች ከቤተክርስያኒቱ መቆርቆር በኋላ የተሣሉ ናቸው። ሥዕሎቹ የተሣሉት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ባደረጉት በአፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመን ( ፲፬፻፴፬-፲፬፻፷፰ እ.አ.አ ) እንደ ተሣሉ ብዙዎቹ ይስማሙበታል።

## ቤተ መስቀል

ቤተ መስቀል የሚገኘው ከቤተ ማርያም በስሜናዊው አቅጣጫ በኩል ባለው ግድግዳ ውስጥ ነው። ቤተ መስቀል ፲፩ ሜትር ከፍታ እና ፫.፮ ሜትር ስፋት ያለው ሆኖ በአራት ምሰሶዎች ረደፍ አማካኝነት የቅኔ ማኅሌቱ ከሁለት ቦታ ተከፍሎ እናገኘዋለን። ለቤተመቅደሱ መግቢያና መውጫ ሆኖ የሚያገለግለው በደቡብ በኩል ያለው በር ብቻ ነው። ከዚህ በር በተጨማሪ በቤተክርስቱያኑ ውስጠኛ ክፍል ወደ ዕቃ ቤት የሚወስድ በር አለው። ቤተ መስቀልም ብርሃን የሚያገኘው በሁለት መስኮቶች አማካኝነት ነው። አንደኛው መስኮት በግሪክ የመስቀል ቅርጽ የተሠራ ሲሆን ሌላኛው ( የመቅደሱ ) መስኮት ሲከፈት የማልታዎች አይነት መስቀል ቅረጽ ይታይበታል። በዚህ ቤተ መቅደስ እንደ ሌሎቹ የቅዱስ ላልይበላል ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ጥበቦች የሚታዩበት ሥፍራ ነው። ይህን ቤተመቅደስ ከውጭ በኩል ሆነን ስንመለከተው በግማሽ ክብ ጨረቃ መልክ የተቀረጹ ዓስር ቅርጾች እናገኛለን የእነዚህ ቅርጾች ዓስር የመሆናቸው ምሳሌ የሚያመለክተው።

፩/ ለሲቀ ነብያት ሙሴ የተሰጠውን ዓሰሩን ቃላተ ኦሪትን ለማሰብ።

፪/ በደብረ ሮሀ የተሠሩትን ዓሰሩን አብያተክርስቲያናት ለማመልከት።



፫/ እሌኒ ንግሥት የክርስቶስን መስቀል ፈልጋ ያገኘችው በመጋቢት ወር በ፲ኛው ቀን በመሆኑ ነው።

ቤተ መቅደሱ ምንም እንኳን ጠባብና ትንሽ ቢሆንም በተለያዩ እና ረጅም ዕድሜን ባስቆጠሩ መንፈሳዊ ሥዕሎች ያሸበረቀ ነው። በተለይ በበዓላት ቀን ከቤተ መቅደሱ አቅራቢያ ከሚገኙት ምሰሶዎች ብዙም ሳይርቁ የሚቆሙት ካህናት የሚለብሱትን የወርቅ ዘርፍ ያላቸውን የቅዳሴ ልብስ እና የሚያብለጨልጩ ጃንጥላዎችን ፣ ጸናጽሉችን እና ከበሮዎች ለተመለከታቸው መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያድሱ አባቶቻችን በእምነት ያገኙትን መንፈሳዊ ጥበብ የምናደንቅበት ቅዱስ ሥፍራ ነው።

## ቤተ ደናግል

ከቤተ ማርያም ደቡባዊ አቅጣጫ ላይ ወጣ ብሎ የሚገ
እና ፳.፮ ሜትር ከፍታ ፲.፮ ስፋት ያለው አነስተኛ ቤተ መቅደ
ነው። ቤተ መቅደሱ መታሰቢያነቱ በ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመ
በሮም ነግሦ የነበረው በጁሊያን / JULIAN / ዘመን ለክርስት
እምነታቸው ሲሉ በአደባባይ ለተሰየፉት ደናግላን ነው።

የእነዚህን ሰማዕታት ታሪክ ስንመለከት ደናግሎ
ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የሰጡ ክርስትናው የገባቸውና በተጋደ
በጾም በጸሎትና በትህርምት በኤዲሳ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው
ኤዲሳ የሚለው ቃል በአረብኛ አል-ራሃ ወይም ሮሀ የሚለው
ትርጉም የያዘ ነው። ሮሀን ዛሬ ድረስ ቃሉን ይጠቀሙበታል
እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ቢኖር ሮሀ የሚባለው
በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ሥፍራ ስያሜውን ያገኘ
ከጥንታዊቷ ኤዲሳ ከተማ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ማረጋገጡ ነው

ንጉሥ ጁሊያን በኤዲሳ አቅራቢያ ሲያልፍ የደናግሉ
መኖሪያ ይመለከት እና በውስጡ ያሉትን ማናቸውንም ሰዎ
እንዲገደሉ አንጋቾቹን ያዛል። አንጋቾቹም እንደ ታዘዙት በጭ
ደናግሉን በሰይፍ ለየፉአቸው። ደናግሉም እንደ አባቶቻቸው እን
ሰማዕታት የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጁ። ለዚህም ሲባል
በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን ቅዱስ ላልይበላ ቤተመቅደሶቹ
ሲያንጽ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተፈጸመውን ታሪክ እ
ለደናግሉቹ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ይህን ቤተመቅደስ አነጸ።



በዚህ ቤተመቅደስ በስተ ደቡብ አቅጣጫ ከግድግዳው አጠገብ በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም ያረፉትና የመሀሉና የሰሜን ኢትዮጵያ ገዢ የነበሩት የራስ ካሳ ዳርጌ መታሰቢያ ይገኛል። ራስ ካሳ ከጣሊያን ወረራ በፊት የነበሩ የ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን ሰው ነበሩ።

በአጠቃላይ ቤተ ደናግል ውስጥ ሆነን ታሪኩን ስናዳምጥ ኢትዮጵያ ከጥንታዊው የክርስትና ዓለም ጋር የነበራትን ግንኙነት የሚያውቁበት ቅዱስ ሥፍራ መሆኗን ነው።

በመጨረሻም የቤተ መስቀልን የቤተ ማርያምን የቤተ ደናግልን የጉብኝት መስመር አጠናቅቀው እንደጨረሱ በስተደቡብ በቤተ ደናግል አጠገብ ያለውን የመውጫ በር ይዘው እንዲሄዱ በስተግራ በኩል ከቤተ ደናግል ጋር የተያያዘ የአመቤታችን ቤተመቅደስ ንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ ዕቃ ቤት ያገኛሉ። ከዕቃቤቱ መጨረሻ ላይ የምትገኘውም በታ የሕሙማን ማጥመቂያ ሥፍራ ናት።

አሁን ይህን የመጠመቂያ ሥፍራ አልፈው እንደጨረሱ በበሩ በኩል ሲወጡ ሦስት ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚወስዱ መንገዶችን ያገኛሉ። በስተግራ በኩል ያለው መንገድ ወደ ቤተ መድኃኔ ዓለም ፣ ፊት ለፊት ያለው መንገድ ወደ ዋናው የመኪና መንገድ የሚወስድ ሲሆን በስተቀኝ በኩል ያለውን መንገድ ይዘን ስንሄድ ቤተ ደብረ ሲናን እናገኛለን። እናም አሁን ይህን መንገድ ይዘን ወደ ቤተ ደብረሲና እናምራ።

## ቤተ ደብረ ሲና

በቤተ ደብረ ሲና ቤተመቅደስ ውስጥ በርካታ ክፍሎች ይገኛሉ። ግማሽ ጉናቸው በመጋረጃ ብቻ ተሰይቶ አንድ ራሱን የቻለ መቅደስ ሆነው እንዲያገለግሉ የተደረጉ ክፍሎችም አሉ። በዋናነት ግን ቤተመቅደሱ የሚታወቀው ቤተ ደብረሲና ወይም ቤተ ጉልጉታ በመባል ነው። ቤተ ሚካኤል የምንለው መንበረ ታቦት ግን በቤተ ጉልጉታ ውስጥ የሚገኝ ነው። በመሆኑም በዚህ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከሚገኙት ታቦታት መካከል ታቦተ ሥላሴ፣ ታቦተ እየሱስ ፣ ታቦተ ኪዳነምህረት ፣ ታቦተ ቅዱስ ሚካኤል ፣ ታቦተ ቅዱስ ላሊበላ የሚገኙ ሲሆን በምድረ እስራኤል ከሚገኙ ቅዱሳን ሥፍራዎችም መካከል ጌታ የተወለደበት ቤተልሔምን እየተመሳሰለ ያስተማረባት ገሊላ እና ያደገባት ናዝሬትን የሚወክሉ ቅዱሳን ሥፍራዎች ይገኛሉ። እናም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በሙሉም ባይሆን በጥቂቱ ከዚህ በታች እስከ አዳም መካ መቃብር ድረስ ያሉትን የተቀደሱ ሥፍራዎችን እናያለን። በመጀመሪያም ቤተ ደብረ ሲናን እንመለከታለን።

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በመንትዮቹ የጉልጉታ እና የደብረ ሲና አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በርካታ ቅዱሳን ቦታዎች በመኖራቸው የተነሳ በማንኛውም ሰው ዘንድ የተወለ መደናገሮችን መፍጠሩ አይቀርም። ከዚህም የተነሳ አብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት የሚመሳሰሉ ስለሚመስሉ ቤተ ደብረሲና



ሚካኤል የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው። ነገር ግን ቤተ ካኤል በቤተ ደብረ ሲና ውስጥ ያለ እና የራሱ የሆነ መንበረ ት ያለው ቤተ መቅደስ ሲሆን ቤተ ደብረ ሲናም እራሱን ለና ፬.፭ X ፭.፭ ሜትር ስፋት ፣ ፫ ሜትር ከፍታ ያለው ቤተ ቅደስ ነው። ቤተ መቅደሱ በሦስቱም አቅጣጫዎች ከዓለት ልፍሉ የተዋቀረ ነው።

### ተክርስቲያኑ ውጫዊው ገጽታ

በቤተክርስቲያኑ ውጫዊ ክፍል በኩል ሁለት ቅስት ቸው መስኮቶች አሉት በደቡባዊው ግድግዳ የታችኛው ክፍል በቢ ያሉት መስኮቶችም የቁልፍ ቀዳዳ በሚመስል እና ውበት ው ቅርጽ የተፈለፈሉ ናቸው። በየበሩ እና በየመስኮቶቹ ውስጥ ት የነበሩት እና ወደ ውጭ ወጣ ወጣ ብለው የሚታዩት ንጨት ፍሬሞች ዛሬ እንዳሉም ስለማይቆጠር የሉም ቢባል ሳል።

### ተክርስቲያኑ ውስጣዊው ገጽታ

የቤተ ደብረ ሲናን ውስጣዊ ገጽታ ስንመለከተው ንደሌሎቹ ፍልፍል አብያተክርስትያናት ለዓይን የሚከብዱ ሮችን አናይበትም። በምሰሶዎች አማካኝነትም የምዕመናኑ ሉት ማድረጊያ ቦታዎች ቅኔ ማኅሌቱን ጨምሮ አምስት ፍራዎች በአምስት መስመሮች ተሰይተዋል። የቤተክርስቲያኑ ሚዎች ከግድግዳው ጋር በቅስት መልክ የተሠሩ ናቸው። እዚህ

ሳይ ቋሚ ምስሶዎቹ በጥንቃቄና ውበት በተሳበሰ መልኩ የተለያዩ ዓይነት ቅርጽ ያሰቸው መስቀሎች ተሥለውባቸው ይታያሉ እነዚህን ሥዕሎች የሣሉ ሠዓሊያን ከሣሉዋቸው ሥዕሎች ለመረዳት እንደሚቻለው ሠዓሊያኑ እንኳ ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የሰጡ መሆናቸውን ነው፡፡

በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ ቅርሶች መካከልም ካህናቱ ለዘመናት እያወጡ ሲያሳዩ የኖሩት አንድ በተለያዩ ህብረ ቀለማት ያሸበረቀ መሐረብ ያሳይዎታል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የጥበብ ውጤቶች እንኳን በዚያን ዘመን ይቅርና በአሁኑ ቴክኖሎጂ በበለጸገበት ዘመን እንኳን ለመሥራት አዳጋች መሆኑን እንረዳለን፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም አስደናቂ ነገሮችን በቤተ ደብረ ሲና ውስጥ ሲጉበኙ ይቆዩና ወደ ሌሳኛው የጉብኝት ምዕራፍ ይሸጋገራሉ፡፡



## ቤተ ጎልጎታ

ቤተ ጎልጎታን የምናገኘው የደብረሲናን ቤተክርስቲያን ነታን ብዙም ሳንርቅ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ስንዞር የደብረ ሲና ንትያ ሆና እናገኛታለን፡፡ ቤተ ጎልጎታ አንድ ግድግዳ ብቻ ላት ናት፡፡ ይህንኑም ግድግዳ በቤተክርስቲያኑ ምዕራብ ገጽ ኩል እናገኘዋለን፡፡ ካህናቱ በቤተ ጎልጎታ ውስጥ ሦስት ታቦታት ማሪቸውን ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት አንዳንድ ምዕመናን ተ ጎልጎታ በየትኛው ታቦት ስም እንደ ታነጸች ሳያውቁ ርተው ግርታ ሲፈጥርባቸው ይስተዋሳል፡፡

ጎልጎታ የሚለው ቃሉ የአረማይክ ሲሆን ትርጉሙም ራስ ቅል ማለት ነው፡፡ ቦታው ከኢየሩሳሌም ቅጥር ውጭ መንገድ አጠገብ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ የዓለምን ኃጢአት ሰወገደው አማናዊው በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበታል አዳምና የሔዋን የእዳ ደብዳቤ የተቀደደው በእግዚአብሔር እና ሰው መካከል የነበረው የጥል ግድግዳም የተወገደው በዚህ ጎልጎታ ሳይ ነው፡፡ ስዚህም ነው ቅዱስ ላሊበላ በምድረ እስራኤል ያለውን ጎልጎታን አናስብ ዘንድ በምድረ ኢትዮጵያም ጎልጎታን ያዘጋጀልን፡፡

### የቤተክርስቲያኑ ውጫዊ ገጽታ

የቤተ ጎልጎታን በውጭ በኩል ያለውን ገጽታ ስንመለከት ግድግዳው ልስሳሴ ባለው እና እንደ ሌሎቹ ሕንጻ ቤተክርስቲያናት

ባልሆነ መጠነኛ ውበት የተገጠ ነው። ቤተክርስቲያኑን በደቡ
አቅጣጫ በኩል ግድግዳ አጠገብ ሆነን ስናየው በድንቅ አቀራረ
የታነጹ መስኮቶችን እንመለከታለን። እነዚህ በድንቅ አቀራረ
የተቀረጹ ሁለት መስኮቶች ብርሃን እንዲሰጡ ተደርገው
የታነጹት። በስተ ግራ በኩል ባለው በአንደኛው መስኮት የሚገ
ብርሃን በቤተ ጐልጐታ ውስጥ ለሚገኘው « **ስሊዮሉስ ቤት**
(**መቅደስ**) ሲሆን በሁለተኛው በስተቀኝ በኩል የሚገባው ብር
ደግሞ « **ስሥላሴ ቤት** » ( **መቅደስ** ) ብርሃናቸ
ያስተላልፋሉ።

## ውስጣዊው የቤተክርስቲያኑ ገጽታ

ወደ ቤተ ጐልጐታ ውስጠኛው ክፍል ስንገባ በሦስ
በሦስት ምሰሶዎች አማካኝነት የተደገፉ ሁለት የቅኔ ማኅሌቶ
እናገኛለን። በቤተክርስቲያኑ ውስጠኛው ክፍል በስተ ምሥራ
በኩል ባለው መቅደስ ውስጥ «**የኢየሱስ ቤት**» በስሜን በክ
ደግሞ « **የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር** » ተብለው የተለየ
ቦታዎችን እናገኛለን። እነዚህ ቦታዎች ብዙም ባይሆን በጥቂ
ተውበው እናያቸዋለን።



## ቤተ ሚካኤል

ይህ ቤተመቅደስ ወደ ሚገኝበት ክፍል ሴቶች አይገቡም በቤተመቅደሱ ውስጥ ሁለት መናብርት አሉ። በስተ ቀኝ በኩል ያለው የታቦተ ቅዱስ ሚካኤል ሲሆን በስተ ግራ ያለው ደግሞ የታቦተ ቅዱስ ላሊበላ ነው። በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ ከሌሎች ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት በተለየ መልኩ በዚያው በቤተመቅደሱ ዙሪያ የተቀረጹ አስደናቂ ምስሎችን እናያለን። በግራ ስድስት በቀኝ ስድስት በድምር ዓስራ ሁለት የሆኑ እና አስራ ሁለቱን ቅዱሳን ሐዋርያት የሚወክሉ ቅርጾች ይታያሉ። ከዚህም ሌላ ቅዱስ ላሊበላ ከተቀበረበት መንበር አጠገብ የጌታችን እና መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግንዘት የሚያመለክት የአንድ መልአክ ሐውልት ተቀርጾ እናያለን። ከዚህ ሐውልት ግርጌ የአንድ መልአክ ሐውልት አለ። በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ ያሉት ዓምዶች / ምሰሶዎች / በአያንዳንዱ ላይ ባለ አራት ማዕዘን ቅርጽ መስቀል ተቀርጾባቸዋል። የቤተመቅደሱ ከፍተኛ ቁመት ፬ ሚትር ከ፹፱ ሳንቲ ሜትር ነው። በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ ግሩም የሆኑ መስቀሎች እና ንዋየ ቅዱሳት ይገኛሉ። በተለይ ቅዱሱ ንጉሥ ላሊበላ በጸሎት ግዜ ይደገፍበት የነበረ የመስቀል መቋሚያው የቅዱሱ አስከሬን ያረፈበት መካነ መቃብር የሚገኘው በዚሁ ቤተመቅደስ ውስጥ ነው። በቤተ ሚካኤል ውስጥ በሚገኘው የቅዱስ ላሊበላ መንበር ከሚገኝበት በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ላይ በሚገኘው በር በኩል ወደ ውስጥ ሲገባ የቅድስት ሥላሴን ቤተ መቅደስ እናገኛለን።

## የሥላሴ ቤተ መቅደስ

ይህን በአጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ ስም የታነጸውን ቤተ መቅደስ የምናገኘው የጕልጕታን ቤተ መቅደስ ዋና በር አልፈን በምሥራቅ በኩል ወደ « **ቤተ ሲዖሉስ** » በሚያመራው ሥፍራ ላይ ነው፡፡ ወደ እዚህ ቤተክርስቲያን የሚገባው ቀደም ሲል በምዕራብ በኩል የአዳም መካነ መቃብርን ተሻግሮ ነበር፡፡ አሁን ግን ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚገባው በደቡብ በኩል ወደ ቤተ ማርያም ቤተክርስቲያን በሚያስኬደው መንገድ በኩል ሆኖአል፡፡ በአጠገቡ ያለው ወደ መጀመሪያው ቤተክርስቲያን የሚያመራው በር ወደ ደብረ ሲና ወይም ቤተ ሚካኤል ያደርሰናል፡፡ ይህ ቤተመቅደስ በቅዱስ ላልይበላ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከሚገኙት ቤተ መቅደሶች መካከል ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚታይበት ነው፡፡ ቦታውም ለአይታ ብዙም አይፈቀድም፡፡ ውስጡን ገብተን ያየን እንደሆነ የቤተ መቅደሱ ግድግዳ ሁለት ሦስተኛው በመጋረጃ የተሸፈነ ነው፡፡ ይህ ቦታ ከቅድስናው የተነሳ ለካህናቱ እንኳን ዘወትር ግልጽ አይደለም፡፡ የመላለሚያ ሥፍራው በአጠቃላይ ከዓለት የተሠራ ነው፡፡ የታችኛው ምሰሶ ጣሪያውን ደግፎ በመያዝ ያገለግላል፡፡ በውስጠኛው ማለት ከመንበሩ አጠገብ በስተግራና በስተቀኝ በኩል « **ክርስቶስ** » እና « **ጸራቅሊጦስ** » የሚል ጽሑፍ ይታያል፡፡



የቅድስት ሥላሴ መንበረ ታቦት ያለበት ቤተመቅደስ የውስጠኛው ክፍል ህንጻ ርዝመት ፪ ሜትር ከ፹፭ ሳንቲ ሜትር ሲሆን ወርዱም ፩ ሜትር ከ፷ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡ የቤተመቅደሱ መግቢያ በር በቀስተ ደመና መስክ የተሠራ ደጃፍ ያለው ሲሆን የዚህም ደጃፍ ቁመት ፪ ሜትር ከ፹፯ ሳንቲ ሜትር ሆኖ ወርዱ ደግሞ ፩፻ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡ ከመናብርቱ ፊት ለፊት ቤተ ማርያም ውስጥ እንዳየነው ዓይነት በጥንግ ድርብ የተሸፈነ የብርሃን ዓምድም ይገኛል፡፡ የዓምዱም ቁመት ፩ ሜትር ከ፹፯ ሳንቲ ሜትር ሲሆን ወርዱ ፶፯ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡ ከእዚህ ዓምድ ፊት ለፊት ፫ የድንጋይ መናብርት ይገኛሉ፡፡ እነዚህም የድንጋይ መናብርት የእግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔር ወልድ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ታቦታት መቀመጫ ናቸው፡፡ የመናብርቱም ርዝመት ቁመታቸው የአያንዳንዱ ፴፯ ሳንቲ ሜትር ሲሆን ወርዳቸውም ፺፯ ሳንቲ ሜትር ነው፡፡

በ፲፩ኛው ክፍለ ዘመን የተሣሉትና ከመንበሩ በስተጀርባ ያሉት ቅዱሳን ሥዕሎች ግን ውድመት ገጥሟቸዋል፡፡ ነገር ግን የሚያስደንቀው በዘመኑ የነበሩ ሠዓሊያን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፉ ታሪኮችን ወደ ሥዕል ለመገልበጥ የሚያደርጉት ሙከራ ነው፡፡ በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥም ይህን ሙከራ አድርገዋል፡፡ በተለይ በትንቢተ ዳንኤል በምዕራፍ ፯፥፱ ላይ የምናነበውን ታሪክ ሙሉ በሙሉ ወደ ሥዕላዊ መግለጫ ለመቀየር ያደረጉት ሙከራ በእጅጉ የሚያስደንቅ ነው፡፡

ሌላው መካከለኛው የመቅደሱ ክፍል ውስጥ በሚገኘው መንበር አካባቢ የምናየው አራት ክንፍ ያላቸው ኪሩቤሎች ድንቅ ጥበብ ነው፡፡ እነርሱም አርባእቱ እንስሳ ተብለው የሚታወቁትና የሥላሴን ዙፋን ተሸክመው የሚኖሩት የአርባእቱ እንስሳ ምስል ነው፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**



## የአዳም መካነ መቃብር

ይህን የአዳም መካነ መቃብር ምሳሌ የሆነውን ቅዱስ ሥፍራ የሚያገኙት በቤተ ጉልጉታ ምዕራባዊ አቅጣጫ ሲመለከቱ አንድ ትልቅ እና አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ድንጋይ ቆሞ ያያሉ፡፡ ይህ ድንጋይ ነው እንግዲህ የአዳም መካነ መቃብር ምሳሌ፡፡ ድንጋዩን ቀርበው ሲመለከቱት ውስጡ የተቦረቦረ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን አባታችን አዳም የተቀበረው በምድረ እስራኤል በማዕከለ ምድር በቀራንዮ አደባባይ እንደሆነና እንዲያውም ክርስቶስ መድኃኒታችን የተሰቀለው በመስቀሉም ስር ተሥሎ የምናየው የራስ ቅል ወይም የአፅም ምልክት ሥዕል የአዳም እንደሆነ ነው የምታስተምረው፡፡ ነገር ግን በቅዱስ ላልይበላ የሚገኘው የአዳም መካነ መቃብር የቀራንዮው ምሳሌ ነው፡፡

ይህ የአዳም መቃብር የተባለ ቦታ በመሬት ላይ ያለ ወለሉ በምዕራብ በኩል ባለው ቦታ ላይ ለምናገኛቸው አብያተ ክርስያቲያናት እንደ መግቢያ በርነት ያገለግላል፡፡ የወለሉ የላይኛው ክፍልም ደግሞ ለባህታውያን፣ ለመናንያን መጠለያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ለመካነ መቃብሩ በደበልጥ ውበት የሰጠው ደግሞ በመስቀል ቅርጽ ተቦርቡሮ የሚታየው ሥፍራ ነው፡፡ ከመካነ መቃብሩ በስተምሥራቅ በኩል አንድ ለፊ ቀዳዳ አለ፡፡ ይሀ ቀዳዳ

አገልግሎት አለው፡፡ አገልግሎቱም የፀሐይ ብርሃን ወደ ውስጠኛው ክፍል ዘልቆ እንዲገባ ይረዳል፡፡ ከበሩ ከፍ ብለው እስከ ሥላሴ ቤተ መቅደስ ድረስ የተቀቡ ምስሎች ተሰቅለው ይታያሉ፡፡ በግድግዳው ላይ በመስቀል አምሳያ የተቀረጹት የመቋሚያ እና መጻሕፍትን የያዙ የቅዱሳን ምስል መኖርም ለቦታው ውበት አጎናጽፎት እናገኛለን፡፡



## ቤተ አማኑኤል

ቤተ አማኑኤል ፲፰ X ፲፪ X ፲፪ ሜትር በሆነ ድንጋይ ተጠርበው የአክሱምን ሐውልት በሚመስሉ ቅርጾች ዓይነት የምድር ቤትና ፎቅ መስኮቶች ተበጅተውለት የታነጸ ቤተመቅደስ ነው፡፡ ይህ ቤተክርስቲያን በአካባቢው ካሉት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ትክክለኛ ይዘቱን ይዞ ይገኛል፡፡ በተለይ የታሪክ ተመራማሪዎችና የኪነጥበብ ሰዎች በቅዱስ ላሊበላ ቤተመቅደሶች ውስጥ ሲዘዋወሩ እንደ ቤተ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ህሊናን የሚጫን አያገኙም፡፡ ውስጡ አራት ዓምዶች ያሉበት አዳራሽ ወይም ሰፊ ክፍል ሲሆን ወደ ሰገነቱ የሚያወጣው ደረጃም ከዚያው ከዓለቱ ተጠርቦ የተሠራ ነው፡፡

### ውጫዊው የቤተክርስቲያኑ ገጽታ

ቤተ አማኑኤል ገና ወደ ቅጥር ግቢው እንደገባን የተዋበ እና በሚያብረቀርቅ ደማቅ ቀይ ቀለም ያለውን ቤተመቅደስ እናያለን፡፡ ቤተክርስቲያኑ ተፈልፍሎ የተሠራው ከቀይ ሸክላ ዓለታማ ድንጋይ ውጤት ነው፡፡ የቤተክርስቲያኑ ግድግዳዎች የተሠሩት ወደ ጉን እና ወደ ላይ በተመሳጠሩ ሥራዎች ነው፡፡ በሦስቱም መግቢያ በሮች አካባቢ ቆመው በአትኩሮት ሲመለከቱትጋደል የሚል እይታ ይታይበታል፡፡ በሦስት የቀለት ቅርጽ የተዋቀሩ መስኮቶች ይታያሉ፡፡ በእነዚህ መስኮቶች ከሰረኛው እና ከላይኛው ክፍላቸው ላይ የተቀረጹት መስቀሎች የግሪኮች መስቀል ዓይነት ነው፡፡

የበሮቹም ሳንቃዎች በወፍራሙ ተጠርበው በዓስቱ በር መድረክና ጉበን ተሹሰው የገቡ ናቸው። ይህም ከቅዱሱ የአሠራር ጥበብ የተነሳ እነዚህ በሮች ለምንት መቶ ዓመታት ያህል ሲቆዩ ምንም ዓይነት የመናወጥ እና የመንቀሳቀስ መለክን እስከ አሁን ድረስ አሳሳዩም። ግሩም ድንቅ ነገር።

## የቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታ

በውስጠኛው የቤተመቅደሱ ክፍል ግድግዳውን ተገን ያደረጉ መስኮቶች እና በሮች የውስጠኛውን ክፍል እንዲያንጸባርቁ ተደርገው ነው የተሠሩት። በውስጠኛው የቤተክርስቲያኑ ክፍል አራት የተስተካከሉ አራት ደግሞ በሦስት ማዕዘን ቅርጽ የተሠሩ ምሰሶዎች ይገኛሉ። በደቡባዊው የመቅደሱ ወለል አካባቢ በአጉራባች ከሚገኘው ከቤተ መርቆሬዎስ ጋር የሚያገናኝ ዋሻ አለ። የቤተክርስቲያኑ ውጫዊ ክፍል ላይ ለፀሐይ ብርሃን ተብሎ የተቀረጸ ቀዳዳ አለ። በቤተክርስቲያኑ አንዳንድ ክፍሎች ውስጥ የመነኮሳትና ወደ ሥፍራው የሚመጡ ምዕመናን መቃብሮች ይገኙበታል። በእነዚህ መቃብሮች ውስጥ የተቀበሩት ክርስቲያኖች « **በተቀደሰው ከተማ** » በመቆየት ያረፉ ክርስቲያኖች ናቸው። በዚሁ የቤተክርስቲያኑ ውጫዊ ክፍል በኩል ውስጥ ለውስጥ ከቤተ መርቆሬዎስ ቤተክርስቲያን ጋር የሚያገናኝ መንገድ ያገኛሉ። በአጠቃላይ የዚህን ቤተመቅደስ ሕንጻ ሥራ ሲመለከቱ ውስጡ ቢያድሩ ሁሉ ጊዜ ድንቅ ነው።



## ቤተ መርቆሬዎስ

የቤተ መርቆሬዎስ ቤተ መቅደስ ቅዱስ ሳልደበሳል ካነጻቸው ዓስራ አንዱ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ ነው። ቤተመርቆሬዎስ በወቅቱ በምን አይነት ቀለም ተውቦ እንደነበር ለማወቅ በአሁኑ ወቅት ትንሽ ያስቸግራል። ቤተመቅደሱ በሰማዕቱ ስም ከመሰየሙ በፊት የፍትህ አገልግሎት ይሠራበት እንደ ነበር በቅርቡ የተገኙ አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከእነዚህ መረጃዎች መካከልም በታችኛው የሕንጻው ክፍል ውስጥ የተገኙ የእግር ብረቶች በቂ ምሥክሮች ናቸው። ምናልባት ይህ ህንጻ በዚያን ዘመን የነበሩ መኳንንቶች የሕንጻውን የተወሰነ ክፍል ለዚሁ አገልግሎት ይጠቀሙበት ነበር የሚለውን ግምት ያጉላዋል። ያም ሆነ ይህ ሕንጻው በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የዋለ ነው። የቤተ መቅደሱን ውስጣዊ ይዞታ ስንመለከት እንደተቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ቁጥራቸው የበዛ እና ውብ የሆኑ ጥበባዊ ሥራዎች ባይታይበትም በመጠኑም ቢሆን ድንቅ የሆኑ ሥራዎችን እናያለን።

ይህ ቤተ መቅደስ ለረጅም ግዜ በመፍረሱ ምክንያት ታቦተ መርቆሬዎስ እስከ ንዋየ ቅዱሳቱ በቤተ አማኑኤል ውስጥ ተደብሎ የኖረ ነው። ነገር ግን የሰማዕቱ ቅዱስ ማርቆሬዎስ ታቦት እና ንዋየ ቅድሳቱ ወደ ነበሩበት ቤተመቅደስ የተመለሱት በ[illegible] ዓ.ም በአካባቢው ሕዝብ እና ካህናት ገንዘብ ጊዜያዊ መጠለያ ተሠርቶለት ነው። በቤተ መቅደሱ በመቅደሱ እና

በማኅሌቱ ውስጥ ፲፩ ዓምዶች ( ምሰሶዎች ) አሉት፡፡ ከዚህም ሌላ ፯ ከመቅደሱ ውጪ ጣሪያቸው ፈርሶ የቆሙ ፩ የወደቀ ፪ ስምልክት ያህል መሠረታቸው የቀሩ ፫ ዓምዶች አሉ፡፡

በሥዕል ደረጃ ከምሰሶዎቹ ዝቅ ብሎ ስድስት ነገሥታት ወይም መኳንንት በእጆቻቸው የሚያምሩ መስቀሎችን ይዘው የሚያሳይ ሥዕል እናያለን፡፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ተወዳጅነት ያላቸው የቀለም አጣጣል ሥራዎችም ይታያሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንዲያውም እድል አግኝተው በአዲስ አበባ ብሔራዊ ሙዝየም ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የቅብ ዓይነቶች እስከ ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ድረስ በጎንደር በነበረው ሥርወ መንግሥት ዘንድ ተወዳጆች የነበሩ ናቸው፡፡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ከምናገኛቸው ቅዱሳን ሥዕላት መካከል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇ መድኃኔ ዓለምን እንደታቀፈች፣ የጌታ ሕማማቱ የእሾህ አክሊል በራሱ ላይ እንደደፋለት፣ እና ሌሎችም የቅዱሳን ምስሎች ይገኙበታል፡፡ የታሪክ ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ እነዚህ የሥዕል ጥበባት የፈለቁት ከ፲፯ኛው እስከ ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ሕንፃ ቤተክርስቲያኑ በስሙ ተሰይሞ ስለምናገኘው ሰማዕት ታሪክ በጥቂቱ ገድለ ሰማዕታት በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰበካ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ልዩ እትም በአለቃ ነቢዩ ልዑል የሐንስ ተዘጋጅታ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ለንባብ ከበቃችው እና ባለ ፻፲ ገጽ



ከሆነች አነስተኛ መጽሐፍ ላይ ያገኘሁትን ታሪክ በማሳጠር ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

ቅዱስ መርቆሬዎስ የመጀመሪያ ስሙ **ፒሉፓዴር** ይባል ነበር፡፡ ፒሉፓዴር ቃሉ ላቲን ሲሆን ትርጉሙም ታማኝ ሐቀኛ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ መርቆሬዎስ የተወለደው ጣዖት ከሚያመልኩ አረማውያን ቤተሰቦች በ፪፻፳፭ ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ በ፪ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ደግሞ የክርስትና እምነት እየተስፋፋ ስለመጣ ቤተሰቦቹ ክርስቲያኖች ይሆናሉ፡፡ ቅዱሱም ካደገ በኋላ አምኖ ተጠመቀ፡፡ ስመ ጥምቀቱም **መርቆሬዎስ** ተባለ፡፡ መርቆሬዎስ ማለትም የእየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ማለት ስለሆነ ቋሚ መጠሪያ ስሙ ሆነ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእንግሊዞች የተጻፈው ገድለ ቅዱሳን ( ባዮግራፊ ኦፍ ሴንትስ ) ዜግነቱ ኢጣሊያዊ ሲሆን ስሙም **መርኩርዮ** እንደሆነ የአባቱ ስም **ሉሬዮ** የእናቱ ስምም **ክርስቲና** እንደሚባል ገልጿል፡፡

ሌላው በሀገራችን ህዳር ፳፭ የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር ደግሞ የአባቱ ስም **ኖኅ** የእናቱ ስምም **ታቦት** የራሱ ስምም **መርቆሬዎስ** እንደሚባል ይገልጻል፡፡

በዚያን ዘመን ውትድርና የተወደደና የተከበረ ስለነበር ቅዱስ መርቆሬዎስም **ዳክዮስ** ለተባለ ንጉሥ ወታደር ሆነ፡፡ ዕለት በዕለትም በሚያሳየው ወታደራዊ ሥነ ሥርዓትና በሚፈጽመው ጀብዱ ከሌሎቹ ወታደሮች ይልቅ በንጉሡ ዘንድ ተወዳጅነትንና ባለሟልነትን አገኘ፡፡ ዳክዮስ ጠላቱን ድል አድርጎ በተመለሰ ቁጥር

ድል ያስገኘለት እግዚአብሔርን በመዘንጋት ድል አስገኝዎቹ ጣዖታት እየመሰሉት ከጦርነት መልስ ለጣዖታት መሥዋዕት ያቀርብ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ዳክዮስ መርቆሬዎስን አስከትሎ ዘመተና ጠላቱን ድል አድርጐ ይመለሳል። ንጉሡም እንደልማዱ ለጣዖታት ከስግደትና ከጸሎት ጋር የምስጋና መሥዋዕት አቀረበ። ከደስታው ብዛት የተነሣም ብዙ እንስሳትን በየአይነቱ እየመረጠ ሠዋ።

ቅዱስ መርቆሬዎስም ይህን በማየቱ አዘነ። የንጉሡንም አረማዊነት በሚገባ ተረዳ። በዚህም የተነሳ ንጉሡ ወደ አዘጋጀው ግብዣ ሳይሄድ ይቀራል። የመርቆሬዎስን ወደ ምሣ ግብዣ ያለመምጣት ያዩ ወታደሮችም ወደ ንጉሡ ቀርበው ንጉሥ ሆይ እኛ ትእዛዝህን አክብረን ሳቆምከው ጣዖት ሰግደን በጠራኸን የምሣ ግብዣ ላይም ስንገኝ ታማኝ ባለሟልህ መርቆሬዎስ ግን ትዕዛዝህን በመናቅና አንተንም ባለ ማክበር በዚህ ታላቅ ግብዣ ላይ አልተገኘም። እንዲያውም አንተ የምታመልካቸውን ጣዖታት የሚያመልክ አይመስለንምና አስተያየት ስጥበት ብለው ነገሩት።

ንጉሡ ዳክዮስም በቅዱስ መርቆሬዎስ ላይ የቀረበውን ክስ ካዳመጠ በኋላ ቅዱስ መርቆሬዎስን አስጠርቶ ስለምን ለጣዖት እንዳልሰገደ መሥዋዕትም እንዳላቀረበ እንዲሁም ወደ ግብር ለምን እንዳልወጣ ጠየቀው።



መርቆሬዎስም የንጉሡን ንግግር በጥሞና ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ ሳይፈራና ሳይደነገጥ በድፍረት እንዲህ አለው። ንጉሥ ሆይ ! እንኳንስ እኔ ለጣዖታትህ ልሰግድና መሥዋዕት ሳቀርብ አንተም እንዲህ በማድረግህ አዝናለሁ ብሎ መለሰለት ፤ ነገር ግን እኔ እግዚአብሔርን አመልካለሁ። ለእርሱም እሰግዳለሁ። እንዲያውም እኔ ከዛሬ ጀምሮ የአንተ ባለሟል አልሆንም ብሎ መሣሪያውንና ትጥቁን ፈትቶ ተቀበለኝ ብሎ ወረወረለት። ንጉሡ ዳክዮስም የዚህን ታማኝና የክርስቶስ ወታደር ንግግር ካደመጠ በኋላ ጥፍሮቹን ጠርቶ በግርፋት እና በእስራት እንዲያሰቃዩት አዘዘ።

ቅዱስ መርቆሬዎስም በእስር ቤት ሲሰቃይ ሳለ የሮም ዜጋ ሆኖ በመታሰሩና በመሰቃየቱ ይህን ጉዳይ የሮም ነገሥታት የሰሙ እንደሆን ኃይላቸውን አንስተው ያጠፉናል፤ እኛም እነሱን ማቋቋም ስለማይቻለን ግዛታችን ሰፊ ነውና በጽኑ እስራትና በግዞት እንዲሰቃይ ወደ <u>ቂሣርያ</u> እንላከው ሲሉ ተማከሩ። ንጉሡ ዳክዮስና አማካሪዎቹ በዚሁ ኃሳብ በመስማማታቸው ታማኙ ሰማዕት ወደዚችው አገር ተላከ ።

ቂሣሪያ ክርስቶስ በምድር ሳለ በእስራኤል አገር ሮማዊ የአገር አስተዳደር ዋና መቀመጫ ናት። አብዛኛውን ጊዜ የአገር አስተዳዳሪው በቂሣሪያ እየኖረ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣ ነበር። በዚህ ምክንያት ቅዱስ ጳውሎስ በቂሣሪያ በሁለት አገር አስተዳዳሪዎች ፊት ቀርቦአል የሐዋ. ሥራ

፳፫፡፳፬ ፣ ፳፬፡፲ ፣፲፡፳፭ ፣ ፮ ቅዱስ ጳውሎስ በዚህችው በቂሣሪያ ለሁለት ዓመት ታስሯል የሐዋ ፳፬፡፳፯፡፡ ከተማዋ የሮሚን ንጉሥ ቄሣርን ለማክበር በንጉሥ ሄርዶስ የተሠራች ናት፡፡ በዘመኗ እስከ መቶ ሺህ ህዝብ ይኖርባት ነበር፡፡ በዚህችው ከተማ የወንጌል ሰባኪው ፊሊጶስ ( የሐዋ.ሥራ ፳፩፡፰፤ ፳፩፡፱ ) የመቶ አለቃው ቆርኖሊዎስ እኒህ ሁሉ በቂሣሪያ ይኖሩ ነበር፡፡

ቅዱስ መርቆሬዎስ በቂሣሪያ እስር ቤት መከራውን እና ሥቃዩን እየተቀበለ በእስር ቤቱ ውስጥ የሚገኙትን እስረኞችንም ወንጌል እያስተማረ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና እምነት እየለወጠ ስላስቸገራቸው ኅዳር ፳፭ ቀን ፫፻፲ ዓ.ም በሰይፍ ተከልሎ በሰማዕትነት አርፏል፡፡

ይህ ከላይ መንፈሳዊ ተጋድሎ የፈጸመውን ታላቅ ሰማዕት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለመታሰቢያ ይሆነው ዘንድ ቤተክርስቲያን በስሙ አሳንጻ ስሙን ለዘላለም ስታነሳ ትኖራለች፡፡

**የሰማዕቱ ረድኤትና በረከት ይደርብን አሜን !**



## ቤተ አባ ሊባኖስ

ቤተ አባ ሊባኖስ የሚቆጠረው ከአስራ አንዱ የቅዱስ ላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ጋር ቢሆንም ቤተ መቅደሱን ግን ያነጸችው የቅዱስ ላሊበላ ባለቤት ቅድስት **መስቀል ክብሬ** ናት፡፡ ቅድስት መስቀል ክብሬ አንድ ቀን ሌሊት በሕልሟ ቤተክርስቲያኑን በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት እንደምታንጸው ስለተመለከተች ከዚህ የተነሳ እሷም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በገዳም የምንኩስና ሕይወታቸው ታዋቂ ለሆኑት ለአባ ሊባኖስ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ይህን ድንቅ ቤተክርስቲያን አንጻለች፡፡

### የቤተክርስቲያኑ ውጫዊ ገጽታ

ቤተክርስቲያኑን ከደቡብ አቅጣጫ ሁነው እየቀረቡ ሲመጡ ጨለምለም ባለ ዋሻ የተከበበውን ግድግዳ ያገኛሉ፡፡ በዚህ ግድግዳ ላይ የሚታዩ አንዳንድ የጥበብ ሥራዎች የጥንቱን የአክሱማውያንን የጥበብ ውጤት በገሀድ ያዩበታል፡፡ የቤተክርስቲያኑ የላይኛው ክፍል እንዳለ አፈር ዩለበሰ መሬት ሆኖ መቅደሱ ዙሪያውን ከዓለት እንደ ዋሻ ተፈልፍሎ በሚያምር ቅርጽ ታንጾ ይገኛል፡፡ በዚሁም አሠራሩ ቤተክርስቲያኑ በዋሻ ውስጥ ለሚታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ግሩም ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የቤተክርስቲያኑ ጣሪያ ከዋሻው ጋር አብሮ የተሠራ በመሆኑ የሚያሳየው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የተቀሩት ሦስት ክፍሎች በዋሻ የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ በተለይ

<u>ሁለተኛው የታሪኩ አስረጂዎች</u> ደግሞ እንዲህ ይላሉ ( ሰየትኛው ቤተመቅደስ እንደሆነ ባይታወቅም ) ዋሻው ለቅዱስ ቁርባን የሚሆነው ህብስት የሚዘጋጅበት ( ቤተልሔም ) ነው ብለው ያስረዳሉ።

<u>ሦስተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ</u> በበኩላቸው እንዲህ ይላሉ ስሚያስረዱት ታሪክም ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት በዋሻዋ መሀል ቆሞ የሚታየውን ምሰሶ ነው። በዚህም ምክንያት የተነሳ ይህ ቦታ የቅዱሱ ንጉሥ ላልይበላል የፈረስ ግርግም ነው። ምሰሶውም የፈረሱ ማሰሪያ ነው ብለው ያስረዳሉ። ነገር ግን ይህን ቦታ ስንመለከተው ከአቀማመጡ ጀምሮ ቦታው ለፈረስ መግቢያነት የተመቸ ሥፍራ አይመስልም። ነገር ግን ከታሪኮቹ በመነሳት ደብረ ሮሀን የረገጠ ሁሉ ቦታዋን ዓይቶ ሊደነቅባት የሚችልባት ቅዱስ ሥፍራ ናት ቤተልሔም።



## ቤተ ገብርኤል ወሩፋኤል

የእዚህ ቤተክርስቲያን መግቢያ የሚጀምረው ከቤተልሔም የጸሎት ቤት ፊት ለፊት በምሥራቅ በኩል ነው። ይህን መንገድ ይዘን ሦስት ደረጃዎች እንደ ተሻገርን በአክሱማውያን የእጅ ጥበብ አሠራር አምሳያ ከተሠራው በር እንደርሳለን። ዛሬ ዛሬ ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚገባው በምሥራቅ በኩል ከቤተ አማኑኤል አጠገብ በሚገኘው ድልድይ ሳይ ነው። ድልድዩ የባሕር ዛፍ ግንዶች ተረብርበው የተሠራ ሲሆን የድልድዩ ርዝመት ፲ ሜትር ነው። ይህን ፲ሜትር ርዝመት ያለውን ድልድይ እንደተሻገሩ በምሥራቅ አቅጣጫ የሚገኙ ዋሻዎች ውስጥ ይገቡና ዋሻውን አልፈው ከቅጥር ግቢው በላይ አልፈው ይደርሳሉ።

በሰሜናዊው አቅጣጫ ከውጭ ያለው ከዓለት የተሠራው መንገድ « የመንግሥተ ሰማየት መንገድ » የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ይህ መንገድ ወደ ቤተክርስቲያኑ ጣሪያ ቀስ በቀስ የሚያደርስን ነው። ከዚህ በኋላ ግን ወደ ሌላ ቦታ መግቢያ መንገድ አናገኝም። በሰሜን አቅጣጫ በኩል ያለው የቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ የሚገኘውን ስገነት እንደልብ መመልከት ይቻላል። ከቅጥር ግቢው ወደ ታች ዝቅ ሥንል የውኃ ጉድጓድ እና ውስጥ ውስጡን የሚፈሳ ውኃ እናገኛለን። አሁንም ደረጃዎቹን ይዘን ወደ ታች ስንወርድ ምሰሶዎቹ የሚገኙበት አዳራሽ ይጠብቀናል። እዚህ ጋር ስንደርስ ነው እንግዲህ ወኃው

ዝቅ ወይም ከፍ የሚለው:: የዚህ ውኃ እንቅስቃሴ እንደወራቱ ( በጋ/ ክረምት ) ይወሰናል::

የዚህ ቤተክርስቲያን የአሠራር ባህሪ እና ሁኔታ ከሌሎቹ ቤተክርስቲያናት ለይቶ ለመግለጽ በጣም ከበድ ይላል:: ቤተክርስቲያኑ ፎቅና ምድር እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ነገር ግን ምድር ቤት መሆን ይገባው የነበረው የታችኛው ወገኑ ቤት እንዲሆን ስላልተፈለፈለ ድፍን ሆኖ ቀርቷል::

<u>**የቤተክርስቲያኑ ውጫዊ ገጽታ**</u> የዚህ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊቱ ገጽ በሚገባ የሚታየው በተቃራኒው ለሜን አቅጠጫ ከሚገኘው ስገነት ላይ ሆኖ ነው:: በግድግዳዎቹ መስኮቶች ላይ ያሉት ቅርጻቅርጾች እስከ ዛሬ ድረስ ይዞታቸውን ሳይስውጡ እንደሉ ናቸው:: ሁለት ጌጣ ጌጦችን ለማስቀመጥ የተዘጋጁ ክፍተቶች በበሮቹ ላይ ተቦርቡረው ይገኛሉ:: ከእነዚህ በተጨማሪ ተማሳሳይ ሥራዎች በአምስት መስኮቶች ላይ ይታያሉ:: በሁለቱም በሮች ላይ ያለው ደረጃ ስፋት ያለው ነው:: ከደረጃው ጠርዝ እንስቶ በዓስት እስከ ተሸፈነው የግቢው ክልል ድረስ ያለው ርቀት ፲ ሜትር ርዝማኔ ያህል ነው::

<u>**የቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታ**</u> ቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታው ከውጫዊው የቤተክርስቲያኑ ገጽታ አንጻር ስንመለከተው አነስተኛ ሆኖ ነው የሚታየን:: የቤተክርስቲያኑ



ውስጣዊ ገጽታ ላይ እንደማዳመቂያ የሚታዩት ከግድግዳው ላይ የተለጠፉት ሦስት የላቲን መስቀሎች ብቻ ናቸው:: ውስጡ ሲታይ የተቦረቦሩ መስቀሎች እና ትናንሽ ጉድጓዶች እዚህም እዚያም ይታያሉ:: በአጠቃላይ በቤተክርስቲያኑ ውስጠኛ ክፍል ጌጣጌጦች የሚታዩበት አጋጣሚ የለም ማለት ይቻላል:: ለዚህ ችግር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በቂ መብራት እና ሥዕላ ሥዕሎች ያለመኖራቸውም አስተዋጽኦ አለው:: የቤተገብርኤል ወሩፋኤል ቤተክርስቲያን ከበዓላት ቀናት ውጪ የአምልኮ ሥፍራነቱ በጣሙን የተረሳ ነው:: ሌላው ቀርቶ ለማኅሌት አገልግሎት የሚውሉት መቋሚያ እና ከበሮዎች በአንድ ሥፍራ ላይ ተከማችተው ተደራርበውና ተጨናንቀው ይታያሉ:: በዚህም የተነሳ እነዚህ ንዋየ ቅድሳት ተጎሳቁለው ይታያሉ:: ከዚህም ባሻገር እነዚህ ቅርሶች ጥንታዊነታቸውና ክብራቸው ታውቆ በሚገባ ተጠብቀው የሚኖሩበት ሥፍራ ቢዘጋጅላቸው መልካም ነው እላለሁ::

**ዘስብሐት ለእግዚአብሔር::**

## ቤተ ጊዮርጊስ

ቤተ ጊዮርጊስ ቅዱስ ላልይበላ ካነጻቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል ከሁሉቱ የቤተክርስቲያን ስብስብ ፈንጠር ብሎ ከመንደሮች ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ሁለት ወንዞች ከሚገኙበት ሽንተረር አፋፍ ላይ ከሚገኘው ዓለታማ አካባቢ ነው የሚገኘው። ቤተመቅደሱ የመስቀል ቅርጽ ያለው ሆኖ አጅግ የሚያምር እና የሚያስደንቅ ነው።

ቅዱስ ላልይበላ በሁለቱ ስብስብ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉትን ህንጻ ቤተክርስቲያኖችን አንጾ እንደጨረሰ ይላሉ ስለቤተክርስትያኑ አሠራር ካህናቱ ሲገልጹ፤ ወዲያውኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሚያምረው ነጭ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ወደ ቅዱሱ ይመጣና በእርሱ ስም ቤተመቅደስ እንዳልተሠራ ይነግረዋል። ቅዱስ ላልይበላም ወዲያውኑ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ይህን ቃል እንደሰማ ወደ እዚህ ዓለታማ ቦታ በመምጣት ይህን አስደናቂ ሕንጻ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም አነጸስት።

ወደ እዚህ ቅዱስ ሥፍራ የሚደረሰው መሬት ለመሬት በተሠራ ቦይ የውስጥ ለውስጥ መንገድ አማካኝነት ሲሆ ነ ወደ ቤተክርስቲያኑ ግቢ ከገቡ በኋላ ትናንሽ ዋሻዎችን በግድግዳዋቹ ጥግና ጥግ ላይ ያያሉ። በዋሻዎቹ ውስጥም አጽሞችን ያያሉ። በእውነቱ ከሆነ ወደ ሥፍራው የሚጓዙት ምዕመናንም ሆኑ ጐብኝዎች ቅዱስ ላልይበላ ካነጻቸው ሕንጻ ቤተክርስቲያኖች ሁሉ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተክርስቲያን ህንጻ በንድፍ አወጣጡ እና



በድንጋይ አጠራረቡ ከሁሉም ቤተክርስቲያናት ያማረ እና የተጣራ እንደሆነ ሁሉም ይስማሙበታል። ሥራውም እንዲህ ሊያምር የቻለው ይላሉ ካህናቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ እራሱ በሰው አምሳል ተገልጾ ዕለት በዕለት ሥራውን ይከታተል ስለነበር ነው ይላሉ። እንዲያውም እስካሁን በዓለቱ ላይ ተቀርጾ የምናየውን የፈረስ ኮቴ በማሳየት የቅዱስ ጊዮርጊስን ከሥራው ያለመለየት ያስረዳሉ። በዚህ ፈረስ ኮቴ ላይ ያለውንም የቅዱስ ላልይበላንና የቅዱስ ጊዮርጊስን አሸቅድድምን የሚመለከተውን ታሪክም የሚነገረውን የሚያስረዱ ወገኖችም አሉ።

ቤተክርስቲያኑ በመስቀል ቅርጽ የተሠራ ሲሆን ወስሉም የተለየ ሞዴል ( ቅርጽ ) እንዳለበት ይታያል። አስገራሚው ነገር የቤተክርስቲያኑ ወለል እኩል ቅርጽ ባለው የመስቀል ቅርጽ (ምስል) የመሠራቱ ጉዳይ ነው። ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚገባው በምዕራብ በኩል ሲሆን ከሁሉም የበለጠውን በር የምናገኘው ግን በምሥራቅ በኩል ነው።

### የቤተክርስቲያኑ ውጫዊው ገጽታ

ቤተ ጊዮርጊስን ከውጭ ሆነን ስንመለከተው እንደ አንድ ግንብ በመስቀል ቅርጽ የወጣ ሆኖ ውስጡ ተቦርቡሮ ክፍል ያለው አይመስልም። ይህን ቤተክርስቲያን የተለየ የሚያስመስለው በምዕራብ ፤ በሰሜን እና በደቡብ አቅጣጫ በኩል በሚገኙት በሮች አካባቢ የሚታዩ የጥበብ ውጤቶች ናቸው። ይህ ቤተክርስቲያን ከውበቱ የተነሳ ስለ ላሊበላ ሲነሳ ቦታውን

የማያውቀው ሰው ሁሉ ቤተ ጊዮርጊስን በፎቶ ግራፍ በፖስትካርድ፣ በቲሸርቶችና በተለያዩ የማስታወቂያ ሥራዎች ሁሉ ላይ የሳሊበላን አብያተ ክርስቲያናት ወክሎ ስለሚቀርብ በሁሉም ሰው አእምሮ የሚታወቅ ነው። ቤተክርስቲያኑ በውጭ በኩል ያለው ጣሪያ ውበትን ከመላበሱ በተጨማሪ በጣሪያው በስተሰሜን፣ በስተ ደቡብና ምዕራብ አቅጣጫ ያሉት አሸንዳዎች የዝናብ ውኃው በተገቢው መንገድ እንዲፈስ ስለሚረዱ የቤተክርስቲያኑ ውጫዊ አካል በተለይ ጣሪያው ውኃ ስለማያቁር (ስለማይዝ) አይበላሽም አይጐዳም። በየበሮቹ እና መስኮቶቹ የታችኛው ጠርዝ ላይ ያሉት የቅርጽ አወጣጦችን ስንመለከት አክሱም የምናያቸው ጥበቦች እዚህም በጥበብ ሥራው ላይ ተጽዕኖ እንዳደረጉ እንመለከታለን። በተለይ በዋነኛው መግቢያ ላይ ያለው የፍሬም ቅርጽን ስንመለከት መልሱን እናገኛለን። ቤተጊዮርጊስን ዘመናዊ ጥበብ ያላበሰው ሌላው ገጽታው የግድግዳው ውፍረት ከጣሪያው ወደ መሠረቱ ሲወርድ ውፍረቱ እየጨመረ መምጣቱን በጣም ካልቀረቡት በስተቀር በርቀት ለዓይን ማዳገቱ ነው። በታችኛው የቤተክርስቲያኑ ክፍል ያሉትን ዘጠኙ መስኮቶች ጌጣቸው አንድ ዓይነት ሁኖ መጠነኛ ውበት ይኖራቸውና ወደላይ ያሉትን ዓስራ ሁለቱን መስኮቶች ስንመለከት ግን ከውበታቸው በላይ በመስቀል ቅርጽ የተዋቡ ሆነው እናገኛቸዋለን።



<u>የቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታ</u> የህንጻው ውስጠኛ ክፍል ጣሪያውንና ቅስት ያላቸውን አራቱ ዓምዶች በተስተካከለ ህብር ታንጸው እናገኛቸዋለን። በጥንቃቄና በእቅድ የተሠራ በመሆኑ ውስጥ ቆሞ ለሚመለከተው ሰው ቀለል የሚል ስሜት እንዲሰማው ያደረገዋል። ከውስጡም ያሉት የንድፍ ሥራዎች ረቂቅ መሆናቸው የውስጡ ቅርጽ ከውጭው ቅርጽ ጋር ተዘማጅነት እንዳለው በቀላሉ መገመት ይቻላል። እዚህ ውስጥ ራሱን የቻለ ምስል አይታይም። በምትኩ ሦስት ማዕዘን ያለው ቅርጽ ከግድግዳው ጋር ሆኖ ለቤተክርስቲያኑ ድጋፉን ሰጥቶ እናገኛለን። ከቤተ መቅደሱ በላይ በሚገኘው ጉልላት ላይ የሚገኘው ጌጣ ጌጥ የተዋበው በጅንጋይ ላይ በተቀረጹ ቅርጻ ቅርጾች ነው።

ለማጠቃለል ያህል ቅዱስ ላልይበላል እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ለማነጽ ከለማያውያን መሳእክት እርዳታ ጋር ፰፻ ዓመት ነው የፈጀበት። በአጠቃላይ እነዚህን ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት መሥራት ያስፈለገበት አብይ ምክንያት በዘመኑ የነበሩ ምዕመናን እንደ አሁኑ ዘመን የመገናኛው መንገድ ባልበለጸገበት ዘመን ከእምነታቸው ጽናት የተነሳ ስንቃቸውን ሰንቀው በእግራቸው የብዙ ወራትንና ዓመታትን አድካሚ ጉዞ አድርገው እየሩሳሌም በሚደረገው ጉዞ አቅጣጫን ከለማወቅ፣ በስንቅ ማለቅ ፣ በአውሬ በመበላት ፣ በፀሐይ ሀሩር ፣ በውኃ ሙላት ፣ በሽፍታ ወ.ዘ.ተ እየጠፉም መንገድ ላይ እንደወጡ

የሚቀሩ ስለነበሩ ከዚህ ኢየሩሳሌም በሚደረገው ጉዞ ፈንታ ዳግማዊት ኢየሩሳሌምን ኢትዮጵያ ውስጥ በመፍጠር ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ያለምንም አድካሚ ጉዞ ቅዱስ ላልይበላ ወደ እነዳቸው ቅዱሳን ሥፍራዎች በመሄድ በረከት እንዲያገኙ የእግዚአብሔርንም ድንቅ ሥራ እንዲመለከቱ የተደረገ ነው።

መቼም ቅዱስ ላልይበላ ሄደን የምንመለከተው ነገር ሁሉ እንኳን እኛን የታሪኩን ባለቤቶች ይቅርና የውጭ ሀገር እንግዶችንም እንኳን ባሉበት ፈዘው እንዲቀሩ የሚያደርግ ቅዱስ ሥፍራ ነው።

ምዕመናን ሆይ ቢቻለን በዓመት አንድ ጊዜ ለልደት በቦታው ተገኝተን የቢዛ ኩሉን ሥርዓት ለማየት እንሞክር ለማንኛውም ይህን ቅዱስ ሥፍራ ሳንረግጥ እንዳናልፍ እግዚአብሔር ዕድሜ ይስጠን አሜን ።



## ገነተ ማርያም

ገነተ ማርያም የምትገኘው በወሎ ክፍለ ሀገር ውስጥ ሲሆን ቤተክርስቲያኗ የተመሠረተችው በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ነው። ይህች ቤተክርስቲያን ቅዱስ ላሊበላ ካነጻቸው አብያተ ክርስቲያናት ራቅ ብላ የምትገኝ ናት። ከወልድያ ወደ ላሊበላ የሚሄድ ጉብኚ ከመኪና ወርዶ በ፲ ደቂቃ ውስጥ የሚያገኛት ሲሆን በአውሮኘላን ወይም በሌላ አቅጣጫ ደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ የሚገባ ሰው ደግሞ በበቅሎ ወይም በፈረስ ጀርባ የአራት ሰዓት ጉዞ ካደረገ በኋላ የሚያገኛት ቤተክርስቲያን ናት።

ይህች ቤተ መቅደስ ከግራጫ ድንጋይ ተፈልፍላ የተሠራች ናት። የቤተክርስቲያኒቱን አጠቃላይ ገጽታ ስንመለከት በቅዱስ ላሊበላ ከምናገኘው ቤተ መድኃኔ ዓለም ጋር በብዙ መልኩ ተመሳሳይነት ያላት ናት። የቤተክርስቲያኒቱ ምሰሶዎች ባለ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያላቸው ናቸው።

የገነተ ማርያም የላይኛው ጣራ ክፍል ልዩ ትኩረት ካልተሰጠው በቀር ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት የሚገኝ ነው። የውጪው ግድግዳዎች ልክ እንደ ቤተ መድኃኔ ዓለም ዓምዶች እና ምሰሶዎች ዙሪያውን የተከበቡ ናቸው። ነገር ግን የቤተመድኃኔ ዓለም ዓምዶችና ምሰሶዎች አብዛኛዎቹ የወደቁና የፈራረሱ ሲሆን የገነተ ማርያም ግን እንዳሉ ናቸው።

ውስጣዊው የቤተክርስቲያኒቱ ክፍል በድንቅ የቀለም ቅቦች ያሸበረቀ እና የሚያምር ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ የአሠራር ቴክኒክ በዓስራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ላይ እንደተገኘ ይነገራል፡፡ በግድግዳ ላይ የምናገኛቸው ሥዕሎች የቅዱሳን እና የመሳእክት ፣ የፀሐይና የጨረቃ በተለያዩ ቅርጾች የተሠሩ መለቀሎች ይገኛሉ፡፡

ገነተ ማርያም የብዙ ዘመናት ዕድሜን ያስቆጠረች የግራኝንና የሌሎችን መሰል የቤተክርስቲያን ጠላቶች አስቸጋሪና የጥፋት ዘመን አልፋ ለታሪክ ለመቆየት ብትበቃም አሁን ግን ካለችበት ደረጃ ዝቅ ከማለቷና ከመፈራረሷ በፊት የቤተክርስቲያን ልጆች የሆንን ሁላችን ልናስብበትና ፈጥነን ልንደርስላት የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ነው የምትገኘው፡፡



## <u>ነአኩቶ ለአብ</u>

ይህን የቅዱስ ነአኩቶ ለአብ አስደናቂ ህንጻ ቤተክርስቲያን የምናገኘው ከቅዱስ ላሊበላ ከተማ ደቡባዊ ምሥራቅ አቅጣጫ ፲ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው፡፡ ይህ ሕንጻ ቤተክርስቲያን በዋሻ ውስጥ መሠራቱ ከቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ንጉሥ ነአኩቶ ለአብ የቅዱስ ላሊበላ የወንድም ልጅ ማለትም የገብረማርያም የሐርበይ ልጅ ነው፡፡ ይህ ቅዱስ እና ጻድቅ ንጉሥ በኢትዮጵያ የነገሠው የቅዱስ ላልይበላል መንግሥት ከተፈጸመ በኋላ በዓስራ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ በዓስራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ የዚህን ጻድቅ ስም አወጣጥ ገድሉ ሲያስረዳን እንዲህ በማለት ነው፡፡ ወላጅ እናቱ በምጥ ተይዛ ሳለ በሥርዓተ ቅዳሴ ወቅት <u>**ዲያቆኑ ነአኩቶ**</u> ሲል በመወለዱ በዚሁ ምክንያት ነአኩቶ በሚለው ላይ <u>**ለአብ**</u> የሚል ቃል ተጨመረለት እና <u>**ነአኩቶ ለአብ**</u> የተባለ ስሙን አስገኘለት፡፡

ይህ ንጉሥ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ድንግል እንደ ነቢዩ ኤልያስ የተለወረ እና ሞትን ያለቀመሰ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ለዚሁም ይመስላል የአካባቢው ሕብረተሰብ መሐላን ሲፈጽም <u>**ሥውሩን**</u> ማለትን የሚያዘወትረው፡፡ ቅዱሱ ንጉሥ አፄ ነአኩቶ ለአብ ከመንፈሳዊ ተግባሩ ብቃት የተነሳ ከእግዚአብሔር አምላክ የሠረገላ መንኮራኩር ተሰጥቶት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይፋጠንበት እንደ ነበር የቅዱሱ ንጉሥ ገድል በሰፊው ይገልጽልናል፡፡

ንጉሥ ነአኩቶ ለአብ በሥርዓተ እግዚአብሔር የተጸመደ ጾመና ጸሎትን የሚወድ ከቤተክርስቲያን የማይለይ እንዲያውም በዕለተ ዓርብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተቀበለውን መከራ በማሰብ በቁመቱ ልክ ጉድጓድ በማስቆፈር በጉድጓዱ ውስጥም በኋላ በፊቱ በቀኝ በግራው ጦር በመስካት በነዚያ ጦሮች ሰውነቱን እየተወጋ በስግደት ፈጣሪ አምላኩን ይለምን የነበረ ጻድቅ ንጉሥ ነው።

ንጉሥ ነአኩቶ ለአብም እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ ክርስትናውን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛውን ሚና የተጫወተ ነው። ንጉሡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ የማምለኪያ ሥፍራን በማነጽም ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ የሚቆይ ቅርስ ለቤተክርስቲያን ሠርቶ ያለፈ ንጉሥ ነው። ከላይ በመግቢያዬ ላይ እንደገለጽኩት በዚህ ጻድቅ ንጉሥ ስም የታነጸውን ህንጻ ቤተክርስቲያን ከላሊበላ ፤ ኪሎ ሜትር ከተጓዙ በኋላ ያገኙታል። ወደ እዚህ ቅዱስ ገዳም በእግር፣ በበቅሎ ፣በፈረስ፣ በመኪናም ጥምር በተፈለገው የመጓጓዣ ዘዴ ተጠቅመው ሊደርሱበት ይችላሉ። ገዳሙ የታነጸው ተፈጥሮአዊ በሆነ ዋሻ መግቢያ ላይ ነው።

ወደ ዋሻው ከመዝለቃችን በፊት ከዋሻው የላይኛው ጣሪያ ክፍል ውስጥ ሰርጐ የሚወጣ እና ዓመት እስከ ዓመት



ሳይነጥፍ ንጽሕናው እንደተጠበቀ የሚፈስ ውኃን ይመለከታሉ። ይህ ውኃ በየቦታው ባሉት ብዛት ባላቸው የድንጋይ ገንዳዎች ውስጥ የሚገኝ ነው። የሚገርመው ነገር ከእነዚህ የድንጋይ ገንዳዎች ውስጥ የተፈለገውን ያህል ውኃ ቢቀዳ ገንዳዎቹ ሳይጉድሉ ሁል ጊዜ ሙሉ መሆናቸው ነው። ከእነዚህ ከጣሪያው ላይ ከሚገኘው ዓለት ላይ እየፈለቀ ከሚንጠባጠቡት ጠብታዎች መካከልም <u>ንጽ ይት</u> የተባለችው ጠበል ፈዋሽነቷ የተመሰከረላትና ወደር ያልተገኘላት ናት።

ወደ ዋሻው ውስጥ ስንዘልቅ ቅኔ ማኅሌቱም ሆነ ቅድስቱ ጣሪያቸው እንደ በሆነ ቋጥኝ ሥር ነው የሚገኙት በውስጣቸውም የሥዕል ጥበቦችን እናያለን። በዚህ ዋሻ ውስጥ ከአሸተን ማርያም ቤተክርስቲያን ጋር የሚያገናኝ ዋሻ እንዳለ ካህናቱ ሲናገሩ ይሰማል። ሌላው በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ነገሥታ በገጸ በረከትነት ለዚህ ገዳም ያበረከቷቸው ውድና ውብ ቅርሶች ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ረጅም ዘመንን ያስቆጠሩ የወርቅ ቅብ ክበርዎች ፣ የወርቅ ካባዎች ፣ የብር ከበሮ ፣ መስቀሎች፣ አክሊሎች እና ፲፻ ዓመትና ከዚያም በላይ ዕድሜ ያላቸው የብራና መጻሕፍት የገዳሙ ቅርስና የቤተክርስቲያኗ ውድ ሀብቶች ናቸው። በተለይ የጉብኝን ዓይን የሚማርከው እና የሚያስደንቀው።

አፄ ነአኩቶ ለአብ ከጦርነት መልስ ደዘውት እንደመጡ የሚነገርለት እና « **ለማ ጉንደር** » በሚል መጠሪያ የሚታወቀው ትልቁ ከበሮ ነው።

አፄ ነአኩቶ ለአብ መንግሥቱን ፺ ዓመት በሰላም በፍቅር እና በመንፈሳዊነት ከመራ በኋላ ተሸጦ የነበረውን የቅዱስ ላሊበላን ልጅ ይትባረክን ከተሸጠበት ቦታ አስመልሶ በክብር ካሳደገው በኋላ መንግሥቱን ለእርሱ አስረክቦ ከአምላኩ በደረሰው ጥሪ መሠረት ተሰውሯል። ቤተክርስቲያናችንም ቅዱስነቱን ተቀብላ ኅዳር ፲ ቀን ታከብረዋለች።



## አሸተን ማርያም

የአሸተን ማርያምን ውቅር ቤተክርስቲያን የምናገኘው ከቅዱስ ላሊባላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ላይ በሚገኝ ከፍተኛ ተራራ ላይ ነው። ወደ ቤተክርስቲያኗ ለመድረስ ያለው አማራጭ ለመኪና መግቢያ የሚሆን መንገድ ባለመሠራቱ ምክንያት በእግር ጉዞ ወይንም ደግሞ በበቅሎ በመጠቀም ብቻ ነው። እንዲያውም ወደ ቤተክርስቲያኗ ለመድረስ በበቅሎ ከመጠቀም ይልቅ በእግር ጉዞ መጠቀሙ ይመረጣል። ምክንያቱም ከተወሰነ ሥፍራ በስተቀር መንገዱ በአብዛኛው ገደል የበዛበት ነው።

ከዚህ ፩ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ከሚፈጀው የእግር ጉዞ በኋላ ተራራውን እየታከኩ በቀጥን የእግር መንገድ ተጉዘው ወደ ቤተክርስቲያኑ መግቢያ በር ይደርሳሉ። እስከ እዚህ የመግቢያ ሥፍራ ድረስ ያለው የአሸተን ማርያም አካባቢ መንገድ ዙሪያውን በነጭ በሐ መሬት የተከበበ በመሆኑ ይህንን አስደናቂ እና ነጭ ቀለም የተቀባ የሚመስለውን ተራራ ወጥተው ነው ከላይ ወደ ጠቀስኩት የቤተክርስቲያኗ መግቢያ በር የሚደርሱት። ከቤተክርስቲያኒቱ የመግቢያ በር በስተ ግራ በኩል በግሩም ሁኔታ የተሠራ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጸበል ሲገኝ በስተቀኝ በኩል ደግሞ ቅዱስ ላሊበላ ጀምሮት ከፍጻሜ ሳያደርሰው የቀረ እንደሆነ የሚነገር ዋሻ ይገኛል። ዋሻው ቅዱስ ላሊበላ ሊያንጸው በር እና መስኮት አበጀቶለት የነበረ ሲሆን ነገር

ግን በቅርቡ ዋሻው ተፈልፍሎ የተሠራበት ተራራ በድንገት ተንምሶ በመውደቁ ምክንያት በበጐ አድራጊዎች አማካኝነት በግንብ ተገንብቶ ቀሪው የዋሻው ክፍል በር ተሠርቶለት ይታያል:: እነዚህን ሁለት የጉብኝት ሥፍራዎች እንደአጠናቀቁ ወደ አሸተን ማርያም ቤተክርስቲያን መግቢያ በር ይደርሳሉ:: መግቢያ በሩ ለሁለት የተገመሰ እና ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ለሁለት የተሰነጠቀ ዓለታማ ተራራ ነው::

ይህ ሰንጥቅ ተራራ የታነጸው በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥስት አባ ደበሎ ( አባ ገብረሥላሴ ) በተባሉ መነኩሴ አማካኝነት ነው::ይህን መሿለኪያ መሥራት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ያነጸውን ቤተክርስቲያን እና ቅዱስ ላሊበላ ያነጸውን ዋሻ ለማገናኘት ሲሆን እግር መንገዱንም ወደ አሸተን ማርያም ለመድረስ የሚፈጀውን ረጅም የእግር ጉዞ ለማስቀረት ታስቦም ጭምር ነው:: እንግዲህ ይህን መንገድ አልፈው ነው ከዓለት ተዋቅራ ወደ ተሠራችው የአሸተን ማርያም ቤተክርስቲያን የሚደርሱት::

የአሸተን ማርያም ቤተክርስቲያን የታነጸችው በ[illegible] ዓ.ም በቅዱስ ነአኩቶ ለአብ አማካኝነት ነው:: የህንጻ ቤተክርስቲያኗን አወቃቀር ስንመለከት ህንጻው ሙሉ ለሙሉ ከዓለቱ ተላቆ የታነጸ አይደለም:: የህንጻው በስተ ምዕራብ እና ደቡብ ፣ እንዲሁም ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ድረስ የሚገኘው ክፍል ብቻ ነው እስከ መሬት ድረስ የዘለቀ ሥራ የሚታይበት::



በተረፈ በስተ ሰሜን እና ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ላይ ያለው የህንጻ ቤተክርስቲያኑ ክፍል ህንጻው ተጠርቦ ከወጣበት ዓለት ጋር የተያያዘ ሆኖ እናገኘዋለን::

የቤተክርስቲያኗ ቤተልሔም የታነጸው በስተምሥራቅ በኩል ከሚገኘው ዓለት ሥር ሲሆን ከፍ ብሎ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ላይ ለሱባኤ መግቢያነት የምታገለግል ዋሻም ትታያለች:: የአሸተን ማርያም ቤተክርስቲያን የጣራው ክፍል በማፍለሱ ምክንያት በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ቤተክርስቲያኒቱ ቆርቆሮ የለበሰች የነበረ ቢሆንም ያም ቆርቆሮ በማርጀቱ ምክንያት አሁን በቅርቡ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በዘመናዊ መልክ ለቤተክርስቲያኒቱ እና ከቤተክርስቲያኒቱ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ ላይ ለሚገኘውን ቅኔ ማኅሌት መጠለያ ሠርቶላቸው ይገኛል:: በዚህ አጋጣሚ የባህል ሚኒስቴር በቅዱስ ላሊበላ እና በአካባቢው በሚገኙ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት በማሥራት ላይ የሚገኘው መጠለያ ህንጻዎቹን ከዝናብ በመከላከል ዕድሜ እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ ይገኛል:: እናም የሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ሊመሰገን ይገባዋል እላለሁ::

ወደ ቤተክርስቲያኑ ውስጠኛ ክፍል ዘልቀን ስንገባ ደግሞ በስተ ደቡብ አቅጣጫ ላይ የሴቶች መቆሚያ ሲገኝ በሰተ ሰሜን አቅጣጫ ላይ ደግሞ የወንዶች እና የካህናት አባቶች የስዓታት መቆሚያ ሥፍራ ይገኛል:: በዚህ በደቡብ የሴቶች መቆሚያ በኩል በግድግዳዎቹ መካከል በጭቃና በድንጋይ የተሰሩ ግድግዳዎች

ይታያሉ:: በላይኛው በስዓታት መቆሚያው በኩል ደግሞ ዘመናዊ የሆኑ እና ብዛት ያላቸው የሥዕል ጥበቦች በመቅደሱ ግድግዳ ላይ ይታያሉ:: ይህ የስዓታት መቆሚያ ክፍል በመጠኑም ቢሆን ከቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ሥራ በኋላ በአባ ደበሉ ወይም በአባ ገብረሥላሴ አማካኝነት የማስፋፋት ሥራ እንደተደረገበት ይነገራል:: አባ ደበሉ ከዚህ በተጨማሪም ከቤተክርስቲያኑ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ ላይ የሚገኘውን የቅኔ ማኅሌትም አስፋፍተው አንጸዋል:: ይህ ቅኔ ማኅሌት የጠረያው ክፍል የመሰንጠቅ ምልክት ቢታይበትም ጠረያው በጠንካራ ምሰሶ ተደግፎ ቆሞ ይታያል::

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ከ፭፻ ዓመት በላይ ዕድሜን ያስቆጠሩ ውድ የብራና መጻሕፍት ይገኛሉ:: ከእነዚህም መካከል መጽሐፈ ሲኖዶስ ፣ ገድለ ሐዋርያት ፣ ወንጌል ፣ ገድለ ነአኩቶ ለአብ ፣ ተዓምረ ማርያም፣ አርጋኖን ፣ ግብረ ሕማማት ይገኛሉ::

አሸተን የሚለውን የቤተክርስቲያኗን መጠሪያ ስም አወጣጥም ታሪክ በተመለከተ ካህናቱ ገድለ ቅዱስ ነአኩቶ ለአብን በመጥቀስ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ:: « ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ይህችን ቤተመቅደስ መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፮ ዓ.ም ላይ ማነጽ ጀምሮ በ፵ኛው ቀን ህዳር ፫ ቀን የህንጻውን ሥራ ፈጽሞ የቤተክርስቲያኗንም ስም <u>**ደብረ ጽዮን**</u> በማለት ሰየመና ቤተመቅደሱን በማጠን ላይ ሳለ ቅዱሳን በምድር ላይ መላእክትም



በሰማይ በዚህች ቅድስት ሥፍራ ላይ ታዩ::-ነአኩቶ ለአብም ባያቸው ጊዜ « <u>**ምን ልትሠሩ መጣችሁ**</u> » ብሎ ቢጠይቃቸው « <u>**አንተ ያጠንከውን ዕጣን አሸተን**</u> » ብለው መለሱለት ከዚህ የመላእክት መልስ የተነሳም ቦታዋ <u>**አሸተን ማርያም**</u> ተብላ ቀረች በማለት ካህናቱ ያስረዳሉ:: ከዚህም ጋር ለመግለጽ የምፈልገው ከካህናት አባቶች እንደሰማሁት ከአሸተን ማርያም ተነስቶ እስከ ነአኩቶ ለአብ ድረስ ፩ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ የሚያስኬድ ዋሻም እንዳለ ካህናቱ ያስረዳሉ::

ከዚህ ሌላ ከቤተክርስቲያኒቱ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ላይ አንድ ከፍተኛ የሆነ ተራራ ይታያል:: በዚህ ተራራ ላይ ቅዱስ ላሊበላ ይጸልይበት የነበረ ዋሻም ይገኛል:: እዚህ ተራራ ላይ ሆነው ዙሪያ ገባውን በደንብ ለማየት ይቻላል:: ከሸምሸሀ አውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ እስከ ላሊበላ ከተማ ድረስ ያለውን ሥፍራ በሙሉ ማየት ይቻላል::

## ብልባላ ጊዮርጊስ

ይህ ደብር በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ በቡግና ወረዳ የሚገኝ ድንቅ ደብር ነው። ወደዚህ ደብር ለመውጣት ለበረታ ፲፭ ሰደከመ ፳፭ ደቂቃ የምትወስድ አነስተኛ ዳገት አለች። የቤተክርስቲያኑ አሠራር እንደ ሌሎቹ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የተለያዩ ጌጦች ያሉት ባይሆንም የቤተክርስቲያኑ አሠራር ግን አስደናቂ ነው። ስለ ቤተክርስትያኑ ጥንተ መሠረት የሚያብራራ ከዚሁ ደብር ተጽፎ ያገኘሁትን የጽሑፍ መረጃ እንዳለ አቅርቤዋለሁ።

ጥንት የዚህ ቦታ ስም መካነ ሉዛ ይባል ነበር። መካነ ሉዛ ማለት የረድኤት የበረከት ቦታ ማለት ነው። በዚህ ቦታ ላይ ዘጠኙ ቅዱሳን መጥተው ለ፯ ቀን ጸሎት አድርሰውበታል። ከነሱም በፊት እመቤታችን በስደቷ ወቅት አርፋበታለች። ልጇም ቦታውን ባርኮታል። በኋላም ጌታችን በዕለተ ዓርብ ሲሰቀል ከጐኑ የፈሰሰው ደሙን መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል በብርሃን ጽዋ ተቀብሎ በተለይ ይህን ቦታ ረጭቶታል። ከዚህ በኋላ በ፩፱፻፩ ዓ.ም የነገሡት አፄ ካሌብ ፊንሀስ የተባለው አይሁዳዊ ሀገረ ናግራንን ባጠፋ ጊዜ ንጉሡ ወደ ናግራን ዘምተው አይሁዳዊውን ድል አድርገው እሱን ገድለው ለማዕታተ ናግራንን አስቀብረው ሲመለሱ መጻሕፍተ ብሉያትን ታቦተ እግዚአብሔር አብን፣ ታቦተ አርባዕቱ እንስሳን፣ ታቦተ ማርያምን፣ ታቦተ ጊዮርጊስን፣ ታቦተ ሚካኤልን ፣ ታቦተ ቂርቆስን ማርከው ይዘው ሲመጡ አክሱም



ሲደርሱ ደብረ ሮሐ በተባለ ሥፍራ ላሊበላ የሚያንጻቸውን አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ታንጸው ለለታያቸው ሲገስግሱ ሮሀ ከተባለው ቦታ በሰላም ደረሱ። እንደደረሱም ክርስቶስ ለንጉሡ ተገልጾ እንዲህ አላቸው። ወዳጄ ካሌብ ሆይ! እየተከልክ ከዚህ ብትመጣም አንተ የምታንጻቸው ቤተመቅደሶች ከዚህ አይደሉም። ከዚህ ( በሮሐ ማለት ነው ) ቤተክርስቲያኔን የሚያንጸው ገና አልተወለደም። አንተ ቤተመቅደሴን የምታንጽበት ቦታ ግን ዓምደ ብርሃን ይመራሐል አላቸው። በዚህ ግዜ አፄ ካሌብ ይህ ምስጢር ከተገለጸላቸው በኋላ ከአራት ቦታ ላይ ወርቅ ቀብረው ሲመለሱ ዓምደ ብርሃን እየመራቸው ቡግና መካነ ሉዛ ሲደርሱ ዓምደ ብርሃኑ ቆመ። እንደምንጣፍም ተነጠፈ። በዚህን ግዜ ፈጣሪዬ ከዚህ ቦታ አንጽ ሲለኝ ነው ብለው መጀመሪያ ቤተ ጊዮርጊስን ከቋጥኝ ድንጋይ አንጹ። ቀጥለው ሳርዝና ሚካኤልን አነጹ። ከዚህ በኋላ ቤተ ቂርቆስን አነጹ። ከዚያም አርባዓቱ እንስሳን አነጹ ከዚያም ቤተ ሐራን አነጹ። ብርኳኳ ማርያምን። ማይ ምድር ማርያምን ሠሩ ከናግራን ያመጧቸውን ታቦቶች አግብተው ቅዳሴ ቤታቸውን በመካነ ሉዛ በቤተ ጊዮርጊስ ህዳር ፯ ቀን በ፲፱፻፳ ዓ.ም አከብረው ሲፈጽሙ ለፍር ቁጥር የሌለው ንብ መጥቶ ከቤተ መቅደስ ገብቶ ሰፈረ። በማግስቱ ህዳር ፰ ቀን ቤተ መቅደሱ በማር ተጥለቅልቆ ተገኝቷል። ይህንንም ማር በዚህ ግዜ በቦታው የተሰበሰቡት ሰዎች በየቤታቸው ለበረከት ብለው በወሰዱ ግዜ በየቤተሰባቸው ደዌ ያለባቸው ሰዎች

ድነዋል፡፡ ሕጋንንት ያደረባቸው ሰዎች ሁሉ እየጮኹ ከደረሰባቸው ስቃይ ድነዋል፡፡ ሰባት ቀንም በዚህ በመካነ ሉዛ ብርሃን እየታየ ቦታውን እጥለቅልቆታል ከዚህ በኋላ ይህ ዜና በአራቱ አህጉር ሁሉ ተሰማ፡፡ ደዌ ያለበት ሁሉ የቦታውን አፈር፣ ማር እየተቀባ ይፈወስ ጀመር፡፡ አፄ ካሌብም በዘመነ መንግሥታቸው ይህ ሁሉ ድንቅ ነገር በተፈጸመ ግዜ ለአምላካቸው ምስጋና አቀረቡ፡፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንም ተከለው እነዚህኑ አብያተ ክርስቲያናት ለዚሁ መካነ ሉዛ ለተባለው ለቤተ ጊዮርጊስ ርስት ጉልት አድርገው ሰጥተውታል፡፡ አፄ ካሌብ ግን መናኔ መንግሥት በመሆን መንኩሰዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በ፲፪፻፴፯ ዓ.ም የነገሡት የአፄ ካሌብ የልጅ ልጅ የአፄ ገ/መስቀል ልጅ ቆስጠንጢኖስ ስመ መንግሥቱ ይስሐቅ የተባለው ንጉሥ እንደነገሠ ወደ ቡግና መካነ ሉዛ ደረሰ፡፡ ከዚያም እንደደረሰ የአባቱ አባት አያቱ አፄ ካሌብ ካነጸበት ቤተመቅደስ መካነ ሉዛ ደረሰ፡፡ ይህም መካነ ሉዛ ለቤተጊዮርጊስ የተባለው ነው፡፡ ከዚህም ቤተመቅደስ ገብቶ ሰገደ፡፡ ሰግዶም እንደቆመ በተአምራት ግሩም የሆነ ነበልባል እሳት ከቤተመቅደሱ በር ሲንቦገቦግ ከነሠራዊቱ አየ፡፡ ንጉሡም ከነሠራዊቱ ሲደነቅ ለፍር ቁጥር የሌለው ንብ ከቤተመቅደሱ ወጥቶ ንጉሡ ያረፈበት ድንኳን ውስጥ ሰፈረ፡፡ ይህም ድንኳን በማር ተሞልቶ ተገኝቷል፡፡ የንቡም ሠራዊት ተመልሶ ቤተመቅደሰ ገብቷል፡፡ ንጉሡም ያን በድንኳን የተገኘ ማር ባርኮት ተከብሮ እንዲያዝ ሠራዊቱን አዘዘ፡፡ በዚህም ሁኔታ መሸና ፪ ሰዓት ሲሆን



የቤተመቅደሱ አፀድ እንደ ነደደ ሁኖ እሳተ ነበልባሉ ከሰማይ የሚደርስ መስሎ ሲንበለበል ሌሊቱን በሙሉ አደረ፡፡ ንጉሡና ሠራዊቱም ይህንኑ የእሳት ነበልባል ሁሉም እይነደደ አየ ሌሊቱን ሙሉ ይህ የእሳቱ ነበልባል አላቋረጠም ነበር ንጉሡ ይስሐቅም ሠራዊቱን እንዲህ አላቸው ይህን የአሳት ነበልባል ተመለከታችሁን ? አላቸው ሠራዊቱም ንጉሥ ሆይ አዎን እንመለከተዋለን አሉ፡፡ ይህን ነበልባል እሳት ያሳየን ልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ቡሩክ ነው አሉ፡፡ ወደፊትም ብዙ ተአምራት ይደረግበታል፡፡ አስ ይህን ነበልባል እሳት ያሳየን ልዑል እግዚአብሔርም ዳሩ እሳት መሀሉ ገነት ነው ብለህ ገድመው ሲለኝ ነው ብሉ ነገራቸው፡፡ ንጉሡም ቤተ አርባዓቱ እንስሳን እና ከላይ በመግቢያዬ ላይ የገለጽኳቸውን ገዳማትና አድባራት በሙሉ ለብልባላ ጊዮርጊስ ርስት ጉልት ሰጥቶ ዳሯ አሳት መሀሏ ገነት ትሁን፡፡ የሰገረ ቆቅ የበረረ ወፍ አይገደልበት ብሎ ገድሞ ፲፪ ካህናት መድቦ ሀገሩንም የእሳት ነበልባል ከቦት ስለታየ መካነ ነበልባል ዘቤተ ጊዮርጊስ ብሎ ሰየመ ከዚያ በኋላ ጥቂት በጥቂት አማርኛው እየተሰዋወጠ «**ከነበልባል**» **ብልባላ** ተብሏል ይለናል በገዳሙ ውስጥ ያገኘሁት የብራና ታሪክ፡፡ የብልባላ ጊዮርጊስን ታሪክ አበቃን፡፡

## ይምርሐነ ክርስቶስ

ይህን የንጉሥ ይምርሐነ ክርስቶስ ድንቅ የጥበብ ውጤት የሆነውን ህንጻ ቤተክርስቲያን የምናገኘው በወሎ ክፍለ ሀገር በቡግና ወረዳ ውስጥ ከላሊበላ ከተማ በስተ ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ላይ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ እዚህ ቅዱስ ሥፍራ ይኬድ የነበረው ደርሶ መልስ አንድ ቀን ይፈጅ በነበረ አድካሚ የእግር ጉዞ ነበር። ይህ መንገድ ከርቀቱ በተጨማሪ ረጃጅም የሆኑ ተራራዎችን መውጣት እና አደገኛ ቁልቁለቶችን መውረድን እንዲሁም አሰልቺ እና ሰፋፊ ሜዳዎችን ማቋረጥ የሚጠይቅ መንገድ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ከላሊበላ ከተማ ጀምሮ በብልባላ ጊዮርጊስ በኩል ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ድረስ የመኪና ጥርጊያ መንገድ በመሠራቱ ምክንያት ያንን አድካሚ እና አስቸጋሪ የእግር ጉዞ አስቀርቷል፡

የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ህንጻ ቤተክርስትያን የታነጸው ጥቁር ዓስታማ ከሆነ ተራራ ከታችኛው ክፍል ላይ በሚገኝ እጅግ ሰፊና ትልቅ በሆነ <u>ውግረ ስሄን</u> በተባለው ዋሻ ውስጥ ነው። ይህን አስደናቂ ህንጻ ያነጸው ቅዱሱ ንጉሥ አፄ ይምርሐነ ክርስቶስ ነው። ይምርሐነ ክርስቶስ ከሦስቱ የኢትዮጵያ ወንድማማች ነገሥታት መካከል የግርማ ሥዩም ልጅ ነው።



እነዚህም ወንድማማች ነገሥታት የሚባሉት።

1. ግርማ ሥዩም
2. ዣን ሥዩም
3. ጠንጠውድም ናቸው።

ቅዱስ ላሊበላ ከዣን ሥዩም የሚወለድ ሲሆን የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ የአጐት ልጅ ነው። ከቅዱስ ላሊበላ በፊት የነገሠውም ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ነው። የንግሥና ዘመኑም አርባ ዓመት ነው። ይኸውም / ፲፻፴፩-፲፻፸፩ / ዓ.ም ድረስ ነው።

የቅዱሱ ገድል እንደሚያስረዳው ንጉሥ ይምርሐነ ክርስቶስ « <u>ካህን ወንጉሥ</u> » ይሰኛል። ክህነትን ከንግሥና ጋር አስተባብሮ የያዘ ሰው ነበር። ይምርሐነ ክርስቶስ ከቅድስናው የተነሳ ቅዳሴ ገብቶ ሲቀድስ ሰማያዊ መና፣ ወይን ከነጽዋው የወረደለት አባት ነው።

ንጉሥ ይምርሐነ ክርስቶስ የዚህን ህንጻ ቤተክርስቲያን ግንባታ ለማሳካት እና ከፍጻሜ ለማድረስ የተጠቀሙበትን የአሠራር ጥበብ ስንመለከት በእጅጉ የሚደነቅ ነው። በዚህ ግዙፍ እና ያለ ምሰሶ እንደ ሰማይ በቆመ ድንቅ ዋሻ ውስጥ ቆመው በሁለት አበይት ነገሮች ከመጠን በላይ ይደነቃሉ።ይኸውም አንደኛ ነገር ያን የሚያህል ጥቁር ዓስታማ ድንጋይ ጠርቦ ዋሻ ውስጥ ቤተ መቅደስ ፣ ቤተ መንግሥት እና መካነ መቃብር በተወሰነ ሜትር ርቀት ውስጥ በዚያን ዘመን ይህን የመሰለ እጅግ የረቀቀ የህንጻ ሥራ መሥራት አባቶቻችን ምን ያህል የእምነት ጥንካሬና

የጥበብ ባለጸጋ እንደሆኑ በተግባር በዓይናችን እመልከተን የምንረዳበት ቅዱስ ሥፍራ ነው።

በመጀመርያ ደረጃ የምንጉበኘው ቤተክርስቲያኑን ነው። ይህ ቤተክርስቲያን አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ሲሆን የቤተመቅደሱም አሠራር ይህን ይመስላል። በመጀመሪያ የዚህን ህንጻ ቤተክርስቲያን አሠራር በአምላክ ፈቃድ ቅዱስ ሩፋኤል በቦታው የነበሩትን ርኩሳን መናፍስት ከአጣራለት በኋላ እግዚአብሔር አምላክ በግልጽ ተገልጾ ለይምርሐነ ክርስቶስ የአሠራሩን ሁኔታ ገለጸለት። ከዚህም በኋላ በአምላክ ፈቃድ ቅዱስ ይምርሐን ለቤተመቅደሱ ግንባታ የሚውሉ ቁሳቁሶችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በሠረገላ እያመጣ አከማቸ። በመቀጠልም በቀጥኑ የተጠረቡ እና የተፈለጡ ጥቃቅን ድንጋዮች በኖራ እየተጣበቁ በተወሰነ ሴንቲ ሜትር ከፍታ እንዲኖራቸው ተደርገው ከተገነቡ በኋላ በእያንዳንዱ ድንጋይ በተወሰነ ርቀት ላይ ጠንካራና ርዝመትን ከውበት ጋር በተላበሱ ጥርብ እንጨቶች የተረበረበ ሲሆን ፣ በየመስኮቶቹና በየበሮቹም ላይ እንደ ዓይነርግብ እየሆነ የጥንቶቹ የሐረግ ቅርጾች የተፈለፈሉ እንጨቶች እና ዕበነ በረዶች ተሰክተውበታል።

የቤተመቅደሱ ወለል እና የጣሪያው ክፍል በተለያዩ ሕብረ ቀለማት ያሸበረቀ እና እጅግ ረቂቅ በሆነ የእጅ ፍልፍል ሐረግና ሥዕላዊ ንድፎች የጌጠ ነው። በአጠቃላይ የዚህ ቤተመቅደስ የወለል ፣ ግድግዳ የጣሪያ ክፍል አሠራር በሙሉ በአሁኑ ዘመን



ለምናያቸው የሕንጻ ጥበብ ሥራዎች መሠረት ለመሆናቸው በቂ ምሥክሮች ናቸው።

የቤተክርስቲያኑን ውስጠኛ ክፍል መጉብኘት የሚቻለው በባትሪ ወይም በጧፍና በሻማ ብርሃን በመታገዝ ነው። ከመቅደሱ በላይ የሚገኘው የቤተክርስቲያኑ ጉልላት ላይ የሚገኙት ቅርጾች እና ቅቦች ሌላው የዚህ ቅዱስ ሥፍራ ልዩ ገጽታዎች ናቸው።

የቤተክርስቲያኑን ጉብኝት እንደጨረሱ በቀጥታ የሚያመሩት ከቤተክርስቲያኑ በቅርብ ርቀት ላይ ወደ ሚገኘው የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተ መንግሥት ነው። ቤተመንግሥቱ ዶሚገኘው በዚሁ ዋሻ ውስጥ ሲሆን አሠራሩም ባለ አንድ ፎቅ የሆነ ሕንጻ ሆኖ አብዛኛው አሠራሩ ከቤተክርስቲያኑ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ህንጻ ለቅኔ ማኅሌት መቆሚያነት የሚያገለግል ነው። የሚገርመው ቤተክርስቲያኑም ሆነ ቤተመንግሥቱ ከታነጹበት ከ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከማርጀታቸው በቀር የመፍረስና የመሰንጠቅ ሁኔታ ያለማሳየታቸው ነው። ጉብኝትዎ ይቀጥል እና በቤተክርስቲያኑ እና በቤተመንግሥቱ መሀል ለመሀል ባለው አቅጣጫ በስተ ምዕራብ በኩል ይጓዛሉ። ቦታውም የመቃብር ሥፍራ ሳይሆን አይቀርም።

በዚህ ሥፍራ ላይ የሚታዩት አስከሬኖች በአብዛኛው በፅማቸው ያልፈረሱ እና የተለያዩ ዓይነት የአገናነዝ ሥርዓቶችን የሚያሳዩ ናቸው። አስከሬኖቹ በ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ

እዚህ ቅዱስ ሥፍራ መጥተው ያረፉ ቅዱሳን አባቶች ዐፅም እንደሆነ ነው የሚነገረው:: ከዚህ የቅዱሳን ዐፅም ስብስብ በኋላ የሚገኝም ዋሻ ይታያል:: ይህ ዋሻ በጣም ረጅም እንደሆነም ካህናት አባቶች ይናገራሉ:: ከዚህ ሥፍራ ጉብኝት በኋላ በቀጥታ የሚያመራት የቅዱሉ ንጉሥ ይምርሐነ ክርስቶስ መካነ መቃብር ወደ ሚገኝበት ሥፍራ ነው:: መካነ መቃብሩ በጨርቅ የተሸፈነ ሲሆን ይህን ቦታ ስመሳለም የሚሄዱ ምዕመናን በሙሉ አንድ ሥርዓት ይፈጽማሉ:: ሥርዓቱም ምዕመናን የጻድቁን መካነ መቃብር « **ፍታኝ ይምርሐነ ክርስቶስ** » በማለት ሦስት ጊዜ በመዞር ከለባቸው የኃጢአት ደዌ እንዲፈቱ ይጸልያሉ፤ ከኃጢአታቸውም ይፈታሉ:: ይህ ደግሞ በአምነት የሚደረግ ታሳቅ መንፈሳዊ ሥርዓት በመሆኑ ይደረጋል:: መጽሐፍ ቅዱስም በነገሥት ካልዕ ፲፫÷ ፳ ላይ የጻድቀ ኤልሳ መካነ መቃብር ሙት እንዳስነሳ ይነግረን የለ::

**የጻድቁ በዓለ እረፍት የሚከበረው ጥቅምት ፲፱ ቀን ነው::**



## አብርሀ ወአጽብሐ ቤተክርስቲያን

በትግራይ ክፍለ ሀገር ከመቀሌ ከተማ በስተ ሰሜን በኩል በክስተ አውሳሉ አውራጃ ከውቅሮ ከተማ በስተ ምዕራብ ፳፭ ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ታሳቅ ደብር ነው:: የታነጸውም ፪፻፴፭ ሜትር ከፍታ ባለው ተራራ ሥር ነው ይህ ቤተክርስቲያን በጥንታዊና ታሪካዊነቱ ብቻ ሳይሆን በአሠራሩ በድንጋይ ቅርጽ ጌጡ እጅግ በጣም ግሩም የሆነ ሕንጻ ስለሆነ የውጭ ሀገር እንግዶች ንም ሆነ የሀገር ውስጥ ጉብኚዎችንና ታሪክ አጥኚዎችን ሁሉ የሚያስደስት፣ የሚማርክ ታሳቅ ደብር ነው::

የቤተክርስቲያን ጠላት ክርስትናን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ቆርጣ ተነስታ የነበረችው ዩዲት ( ጉዲት ) ይህንን ማራኪና አስደናቂ ከአንድ ወጥ ዓለት ተፈልፍሎ የተሠራውን የአብርሀ አጽብሐ ቤተክርስቲያንን ለማቃጠል ሞክራ ነበር:: ይኸውም የሰዓታት መቆሚያው ክፍል ፈርሶ ከግዜ በኋላ በጭቃ ግንብ ተቀጥሎ የተሠራ መሆኑ በቂ ማስረጃ ነው:: ቅኔ ማኅሌቱና ቅድስቱ እንዲሁም መንበረ ታቦቱ ማለት መቅደሱ ጣራና ግድግዳው አልፎ አልፎ ከአንዳንድ ቦታ ላይ በቀደመ ቃጠሎው ምክንያት በጥቀርሻ ከመጥቆሩ በስተቀር ምንም አልፍራረሰም:: ውስጡም እጅግ በጣም ሰፊ እንደመሆኑ መጠን በቀስት መልክ አምረውና ተጊጠው የተቀረጹ ፲፫ አዕማድ ( ምሰሶዎች ) አሉት::

የቅድስቱ ክፍል ጣራ በልዩ ልዩ ሐረግ የተጌጠ ነው። ቤተመቅደሱ ከሦስት የተከፈለ ነው። በቀኝ በኩል የሚካኤል ታቦት ያለበት ቤተ መቅደስ በግራ በኩል ደግሞ የቅዱስ ገብርኤል ታቦት ያለበት ቤተ መቅደስ ሆኖ መሃሉ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ መቅደስ ይገኛል። ሦስቱም መንበረ ታቦቶች ማለት ቤተ መቅደሶች ለየብቻቸው ሆነው በተራ የታነጹ ናቸው። የቅዱስ ሚካኤል እና የቅዱስ ገብርኤል ቤተመቅደሶች በር ያላቸው ሲሆን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ መቅደስ ግን በር የለውም ( በመንጦላዕት ) መጋረጃ ብቻ የተጋረደ ነው። የእነዚህ ሦስት ቤተ መቅደሶች መንበረ ታቦቶች ጣራቸው ክብ ሆኖ የተሠራና እጅግ በጣም ያማረ ሲሆን በተለይ የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን መቅደስ ግድግዳው ከመጥቀሩ በስተቀር በልዩ ልዩ ሐረግ የተቀረጸ በመሆኑ ደስ ያሰኛል ።

በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ውስጥ ስመ ጥር የሆኑትና ለክርስትና እምነት በኢትዮጵያ መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት የደጋጉቹ ነገሥታት የአብርሀና ወአጽብሐ ዐፅም ያረፈውም በዚሁ ታላቅ ደብር ውስጥ በተለየ ሁኔታ በተዘጋጀላቸው በቅዱስ ገብርኤል ቤተመቅደስ ውስጥ ነው።

በዚህ ድንቅ ቤተ መቅደስ ውስጥ እጅግ አስደናቂ ሆኖ የሚገኝ አንድ ተአምር አለ። ይኸውም ጥቅምት ፲ ለጥቅምት ፩



ዋዜማ ጀምሮ ለዋዜማ መቆሚያ ከበሮ መመታት ሲጀምር ቤተመቅደሱ ውስጥ በሚገኙት ዓምዶች ውስጥ ማርና ወተት የሚፈስ ሲሆን በቅኔ ማኅሌቱ ውስጥ የሚገኘው ዓምድ ላይ ደግሞ ንጹህ ውኃ ይፈሳል። ይህ ብቻ አይደለም በበዓለ ንግሡ ቀን ደግሞ ፩፰ ኪሎ ከሚመዝነው የወርቅ መስቀል ላይ ዲያቆኑ ጸልዩ በእንተ ወንጌል ብሎ ወጥቶ ምስባክ ሲሰብክ የወርቅ መስቀሉ ማንባት ይጀምራል። ከዚሁ የተነሳ መስቀሉ <u>አንብዓ</u> <u>**መስቀል**</u> ይባላል።

**የአብርሀ ወአጽብሐ በዓለ ንግሣቸው ጥቅምት ፬ ቀን በታላቅ ድምቀት ይከበራል የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን አሜን !**

## ሚካኤል ዐብይ ዓዲ

ከመቀሌ ተነስተው ወደ አዲግራት በሚወስደው መንገድ ላይ ውቅሮ ከተማ ሲደረስ በስተግራ ወደ አብርሀ አጽብሐ ቤተክርስቲያን በሚወስደው መንገድ ከአብርሀ ወአጽብሐ በ፲፪ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ድንቅ ቤተክርስቲያን ነው። ሚካኤል ዐብይ ዓዲ [illegible] ሜትር ከፍታ ባለው ተራራ ላይ የታነጸ ነው። የዚህ ቤተክርስቲያን የሰዓታቱ መቆሚያ በር እንዲሁም ከቅድስቱ በስተ ደቡብ በኩል የሚገኘው የዓምደ ወርቁ ሥራ ጥሩ መልክና ቅርጽ ይዞ ይገኛል።

ቤተክርስቲያኑ የታነጸው በአብርሀ አጽብሐ ዘመን ሲሆን እንዳሳነጹትም የሚነገረው አቡነ አብርሃም የተባሉ ጻድቅ ናቸው። ሚካኤል ዐብይ ዓዲ በስተ ውጭ ሆነው ሲመለከቱት ባለ ግርማ ሞገስ ዋሻ መስል ደብር ነው የቤተክርስቲያኑ ሕንጻ አሠራር አራት ማዕዘን ሆኖ ውስጡ በሦስት ታላላቅ ክፍሎች የተከፈለ ነው። የሰዓታት መቆሚያው ክፍል ስብቻው በስተ ምዕራብ በኩል በር ሲኖረው ቅኔ ማኅሌቱና ቅድስቱ ግን በተርታ ይገኛሉ። ውስጣዊ ቅርጻቸውም ደስ ይላል።

የቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ክፍሎች ጠበብ ያሉ ሆነው ቅርጻቸው ያማሩና የተዋቡ ዓምደ ወርቆች አሉት። ከቅድስቱ ጣሪያ ላይ በመስቀል መልክ የተቀረጸ ልዩ ጌጠኛ ሐረግ አለው ሚካኤል ዐብይ ዓዲ ውስጡ በንጽህና ስለተያዘና የዮዲትም



የቤተክርስቲያን ሕንጻ አቃጣይ ሠራዊቶች ያልደረሱበት በመሆኑ ጉዳት አልደረሰበትም። ሚካኤል ዐብይ ዓዲን ከወደ ውስጥ ስተመለከተው የ[illegible]ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መስሎ ይታያል።

## ደብረማርያም ቆርቆር

ከሐውዜን ከተማ በስተ ደቡብ ፪ ኪ.ሜ ርቃ የምትገኘውን መጋብ የተሰኘችውን መንደር አስፍ ብሎ በሚገኘውና ከባህር ወለል በላይ በግምት ፪፻፳፱ ሜ. ላይ በሚገኘው ተራራ አፋፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ከተራራው እግር እስከ ቤተክርስቲያኑ ድረስ የአንድ ሰዓት የእግር ጉዞን ይጠይቃል ፡፡

ተራራ መውጣትና ተፈጥሮን ማድነቅ ለሚያስደስታቸው ሰዎች ደብረማርያም ቆርቆር ተስማሚ ቦታ ናት፡፡ ከተራራው አናት ላይ ወጥተው በስተምዕራብ አምበደለሰነይቲንን፣ በስተደቡብ ተኮፍሰው የቆሙት ረጃጅሞቹ የጉሕ ተራሮችን፣ እንዲሁም በስተሰሜን የሐውዜን ሜዳ መመልከት ከፍተኛ እርካታን ይሰጣል፡፡ ማርያም ቆርቆር ትላልቅ ከሚባሉት የትግራይ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ጋር የሚፈረጅ ታላቅ ደብር ነው፡፡ የቤተክርስቲያኑ ፊት ለፊት በጥቃና በድንጋይ የተሠራ ግንብ ተሠርቶለት ይታያል፡፡

የውጭው አካሉ ጣራ በእንጨት የተሠራ ሲሆን አራት መስኮቶችና ወደ ውስጥ የሚያዘልቁ ሁለት በሮች አሉት፡፡ ስፋቱም ፳.፶ ሜትር X ፩.፲ ሜትር ነው፡፡ ከፊት ለፊት የተገነባውን አካል ሳይጨምር ከዓለት ተፈልፍሎ የተሠራው ሕንጻ ስፋት ፲፮ሜ X ፱.፶ ሜትር ሲሆን በውስጡ ስድስት ዓምዶች ይገኛሉ፡፡ የዓምዶቹ ቁመት ፩.፲ ሜትር ሲሆን በ፩.፲ ሜትር ተራርቀው ይገኛሉ፡፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በሚያስደንቅ ጥበብ የተቀረጹ የስንሰለት



ዲዛይን የጎስር መልክ ያላቸው ንድፎች በግድግዳው ላይ ይታያሉ ጣራውም በተለያዩ ንድፎች የተንቆጠቆጠ ነው፡፡ ይህ የዓምዶቹ አቀራረጽ ልዩና ከፍተኛ ጥበብ የተንጸባረቀበት ቤተክርስቲያን የተዋጣላቸው ፲፰ ሠረገላዎች አሉት፡፡ በትግራይ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የአዲስ ኪዳንን ታሪክ የሚያንጸባርቁ ሥዕሎች በብዛት አይታዩም፡፡ አብዛኞቹ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ ያዘሉ ናቸው፡፡ በደብረ ማርያም ቆርቆር ውስጥ ግን ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገን ጉዞ የሚያንጸባርቁ ሥዕሎች መኖራቸው የቤተክርስቲያኑን ጉብኝት ልዩ ያደርገዋል፡፡

ከደብረ ማረያም ቆርቆር በስተሰሜን ዳንኤል ቆርቆር ተብሎ የሚታወቅ ሌላ አንድ ትንሽ ቤተክርስቲያን ይገኛል፡፡ የመግቢያ በሩ ስፋት ዜሮ.፶ ሜትር ፩ X ፩ ሜትር ነው የቤተክርስቲያኑ ስፋት በጣም ጠባብ ቢሆንም ከቤተክርስቲያኑ በስተ ሰሜንና በስተ ምሥራቅ ጎልተው የሚታዩትን የተፈጥሮ ጸጋዎች ለመመልከት በጣም የተመቻቸ ቦታ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኑ በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቁ ሥዕሎች ባለቤት ነው፡፡ የአራቱ ወንጌላውያን የሐዋርያት የቅዱሳን መላእክቶች እንዲሁም ንጉሥ ዳዊት ከነበገናው የሚያሳይ ምስሎች ይታያሉ፡፡ የአቡነ ዳንኤል እንደነበረች የሚነገርላት ቤተ ጸሎትም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ትገኛለች፡፡

**የማርያም ቆርቆር በዓለ ንግሥ በየዓመቱ ህዳር ፮ ቀን ይከበራል፡፡**

## አቡነ ይምዓታ

እኚህ ጻድቅ በ፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመካከለኛው ምሥራቅ በስደት ምክንያት ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ወንጌልን ያስተምሩ ከነበሩት ዘጠኙ መነኮሳት መካከል አንዱ ናቸው። አቡነ ይምዓታ በተለይ ብዙ በቆየበት በትግራይ ውስጥ ገርዓልታ በሚገኘው ልዩ ስሙ ጉሕ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በስማቸው የታነጸ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ወደዚህ ቤተክርስቲያን ለመድረስ ከሐውዜን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ፲፫ ኪሎ ሜትር ከተጓዝን በኋላ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ የግማሽ ሰዓት የእግር ጉዞ ማድረግን ይጠይቃል።

ቤተክርስቲያኑ ሰማይን እንደ ምሰሶ ደግፈው የያዙ ከሚመስሉት ረዳጅም ተራሮች መካከል በአንዱ የሚገኝ ነው። የሚያስደንቀው የቤተክርስቲያኑ የመግቢያ በር አጠገቡ እስኪ ደረስ ድረስ ፈጽሞ አለመታየቱ ነው። ቤተክርስቲያኑ ከበህር ወለል በላይ በ፪፭፻፹ ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። በዚህ ከፍታ ላይ የሚገኘውን ቤተክርስቲያን ለመውጣት ከፊት ለፊት የተጋረጠውን የዓለት ተራራ መውጣት በጣም አስቸጋሪ ነው። ለእጅና ለእግር መቆንጠጫ የሚያገለግሉ ጉድጓዶች ብቻ ነው ያለው። ከ፲፱ - ፳፪ ሜትር ርዝመት ያለው ይህ ገደል ቁልቁል ሲመለከቱት የሚያስደነግጥና የሚያስፈራ ነው።



ወደ ተራራው ከተወጣ በኋላ በጣም በሚያስፈራ ገደል የተከበበችና ኃይለኛ የአየር ግፊት ያላት አንዲት ጠባብ መንገድ ትገኛለች። የመንገዷ ስፋት ከ፳ ሴንቲ ሜትር አይበልጥም። ቤተክርስቲያኑ ከዓለት ተፈልፍሎ የተሠራ ሲሆን ከውስጥ አራት ራሳቸውን ችለው የቆሙ ዓምዶች አሉት። ጠቅላላ ስፋቱ ፯ ሜትር X ፱ ሜትር ከወለሉ ወደ ጣሪያው ያለው ከፍታ ደግሞ ፫ ሜትር ነው። ቤተክርስቲያኑ የሚደነቀው በሕንጻው አሠራር ብቻ አይደለም በውስጡ በያዛቸው ደማቅ ሥዕሎች ጭምር እንጂ የሥዕሎቹን ድምቀት ያስተዋለ ሰው ሥዕሎቹ ጥንታዊ ናቸው ብሎ ለማሰብ መቸገሩ አይቀሬ ነው። አንዳንድ የሥነ ሥዕል ሊቃውንት እንደሚሉት ከሆነ ሥዕሎቹ በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን የተሣሉ ናቸው። ቤተክርስቲያኑም የታነጸው የክርስትና እምነት ወደ ሀገራችን እንደገባ ብዙ ሳይቆይ እንደሆነ ነው። ይህ ቤተክርስቲያን በተራራዎች ጉያ የተሸጉጠ በመሆኑ ከግራኝ እና ከጉዲት ጦር ጉዳት ሲያመልጥ ችሏል። በኢትዮጵያችን ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ በተዋሕዶ ጠላቶች ሲቃጠሉና ሲፈርሱ ግማሾቹም በተደጋጋሚ ዝርፊያዎች ሲቸገሩ የአቡነ ይምዓታ ቤተክርስቲያን ግን ይህ ችግር ብዙም የጉዳው አይመስልም። ሌላው ቤተክርስቲያኑን ልዩ ከሚያደርጉት መለያዎች አንዱ የሆነው ደግሞ የበርካታ ሰዎች ዐፅም የተቀበረበት እና ከዓለት ተፈልፍሎ የተሠራ የመቃብር ሥፍራ መኖሩ ነው። አስደናቂው የመቃብር ሥፍራው አይደለም ቀባሪዎቹም ጭምር

እንዷ:: ቀባሪዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው በመምጣት በተራራው ላይ እንደ ዝንጀሮ ተንጠልጥለው በቅዱሱ አባት በአቡነ ይምዓታ ስም ወደ ተሰየመው ሥፍራ አስከሬን ይዘው መጥተው መቅበር ምዕመናኑ ለቦታው ያላቸውን ትልቅ ክብር እና የእምነታቸውን ጽናት ያሳያል:: ለምሳሌ አስከሬን ተሸክመው ከዋጅራት ( ደቡብ ምሥራቅ ትግራይ ) ፩፻ ኪሎ ሜትር አቋርጠው ይቀብሩ ነበር:: የአቡነ ይምዓታ ቤተክርስቲያን ሀገራችንን በዓለም ደረጃ ከአሳወቋት የውቅር ዓለት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ ነው::

**የአቡነ ይምዓታ በዓለ ንግሥ ጥቅምት ፳፰ ቀን በታላቅ ድምቀት ይከበራል የአባታችን ጸሎትና አማላጅነት አይለየን አሜን::**



## ደብረ ጽዮን አቡነ አብርሃም

ደብረጽዮን ከድጉም በስተ ደቡብ ፩ ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝ አምባ ላይ ይገኛል:: ድጉም ከሐውዜን በስተ ደቡብ ፳፪ ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ ትንሽ መንደር ስትሆን ከሐውዜን የሚነሳው የመኪና መንገድ ደጉምን አቋርጦ ደብረጽዮን ወደ ሚገኝበት ተራራ ይጠጋል:: ከ፵፩ ደቂቃ ተጨማሪ የእግር ጉዞ በኋላ ቤተክርስቲያኑ ያለበት አምባ ላይ ይደረሳል:: አምባው በሁለት አቅጣጫዎች በሜዳ የተከበበ ሲሆን ምዕራባዊ አካሉ ግን ከገርአልታ የተራራ ሰንሰለት ጋር የተያያዘ ነው:: አምባው ከባሕር ወለል በላይ ፪፻፶፻፳፭ ሜትር ከፍታ ላይ በተለያዩ የዛፍ ዓይነቶች የተዋበና ለፊ ለምለም ቦታ ነው:: ቤተክርስቲያኑ በአምባው ለሜናዊ ጫፍ ላይ አስፈሪ ገደል አፋፍ ላይ የተሠራ ነው:: ሆኖም ግን አጥሩ ውስጥ ሆኖ ፊት ለፊትና በስተ ግራ የሐውዜን ሜዳ በስተ ቀኝ ዮሐንስ ማዕቁዲን ሚካኤል ዐብይ ዓዲ የተሰኙትን አብያተ ክርስቲያናት ያቀፈውን የተራራ ሰንሰለት መመልከት ልዩ መንፈሳዊ እርካታ ይሰጣል::

የደብረ ጽዮን አቡነ አብርሃም ቤተክርስቲያን በጥበባዊ አሠራሩም ሆነ በስፋቱ ትላልቅ ከሚባሉት የትግራይ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ይፈረጃል:: የቤተክርስቲያኑ ሥፋት ፲፪.፮ X ፲.፭ ሜትር ሲሆን ቁመቱም ፲.፰ ሜትር ነው:: የቤተክርስቲያኑ ፮ ዓምዶች ፭.፰ ሜትር ቁመት ያሉቸው ሲሆን በ፪.፳፭ ሜትር ተራርቀው የቆሙ ናቸው:: ዓምዶቹ ረዳጅም ብቻ ሳይሆኑ በሐረግ

ቅርጽና በሥዕል ያሸበረቁ ናቸው:: በአራቱ ዓምዶች ላይ የክሮፖቲ ( Croixpattee ) መስቀሎች ቅርጽ ተቀርጸውባቸዋል:: ከዓምዶቹ የሚነሱት ሠረገላዎች በተለያዩ ዲዛይኖች ተውበው ቤተክርስቲያኑን ግርማ ሞገስ አላብሰውታል:: የቤተክርስቲያኑ ጣራ በሠረገላዎች የተከፋፈለ እና አብዛኛው ጎድጎድ ያለ ( dome ) ሆኖ ሁለት ክፍልፋዮች ግን በአሞራ ክንፍ ያማረ ሥራ የተከተሉ ናቸው::ጣራውም እንደሠረገላዎች በተለያዩ ዲዛያኖች የተጌጠ ነው::

ቤተክርስቲያኑ ሦስት ቤተመቅደሶች አሉት:: እነሱም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የሚካኤል ወገብርኤልና የአርባእቱ እንስሳ ናቸው:: የቤተክርስቲያኑ አብዛኛዎቹ አካላት በመንፈሳዊ ሥዕሎች ያሸበረቁ ሲሆን በቤተመቅደሱ ግድግዳ ላይ የሚታየው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅ ሥዕል ግን ዕጹብ ድንቅ ከመሆኑም የተነሳ በዘመኑ የነበሩትን ሠዓሊዎች እንድናደንቅ ያስገድደናል::

ከቤተመቅደሱ በስተጀርባ ( በኮሪደሩ ምሥራቃዊ ጫፍ ) አንዲት አነስተኛ ክብ ክፍል ትገኛለች:: የአቡነ አብርሃም የጸሎት ቤት እንደነበረች ይነገርላታል:: በክፍሏ ግድግዳ ጣራ ላይ የተለያዩ ዲዛይን ያለባቸው መስቀሎችና እመቤታችንን ያጀቡ የቅዱሳን መላእክት ቅርጽ ተቀርጸውባታል:: አቡነ አብርሃም በዋናው ቤተክርስቲያን ውስጥ የምናያቸውን መስቀሎች ለማምረት እንደ



ሠርቶ ማሳያ አድርገው የተጠቀሙበት የድንጋይ ላይ ቅርጽ ጥበብ የሚታያበት ድንቅ ክፍል ናት::

ሌላው የደብረ ጽዮን ጸጋ የሚደነቅና ልዩ የሚያደርገው በሚተጣጠፋው የብራና የሥዕል አልበሙ ነው:: ይህ ዲያሜትሩ ፪ ሳንቲ ሜትር የሆነ ባለ አንጨት ፍሬም መደብል ሥዕል ፴፮ የተለያዩ የመላእክትና የሐዋርያት ሥዕሎችን ይዟል:: ፈረንጆች « ሲርሞን ያል ፋን » የሚሉት ይህ መድብል በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን እንደተሠራ ይነገርለታል:: የብራናው ሥዕል ትንሽ ከማርጀቱ በስተቀር የሥዕሎቹ ድምቀት አሁንም አልደበዘዘም::

**ይህ የተከበረ ቤተክርስቲያን በዓለ ንግሡ በየዓመቱ ህዳር ፳፩ ቀን በድምቀት ይከበራል::**

## ደብረ ዳሞ

ይህ ገዳም የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሀገር በአድዋ አውራጃ ውስጥ ነው። የደብረ ዳሞ ገዳም ከአክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን በ፳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ዙሪያው ፈጽሞ ገደል በሆነ ተራራ ላይ የሚገኝ ጥንታዊ ገዳም ነው። ገዳሙ ከሌሎች ገዳማት ለየት የሚያደርገው ወደ ገዳሙ የሚመጣ ሰው በሙሉ ወገቡን በገመድ እየታሰረ የሚወጣበት መሆኑ ነው።

ማንኛውም ሰው ወደ እዚህ ገዳም ለመግባት ቢፈልግ ከላይ ከተራራው ጫፍ በመነኮሳቱ መልካም ፈቃድ ወደ ገዳሙ የሚያስገባውን ገመድ ማግኘት ይኖርበታል። የተራራው ርዝመት በግምት ከ፲፭ - ፳ ሜትር ያህል ይሆናል። ይህ ግምት ከመሬት እስከ ተራራው መግቢያ በር ማለትም በገመድ መጐተቱ እስከሚያበቃበት የተራራው ግማሽ አካል ድረስ ያለው ቦታ የሚያመለክት ግምት እንጂ የተራራውን ሙሉ በሙሉ ርዝማኔ ያካተተ አለመሆኑ ነው።

ይህን ስመጥር ገዳም የመሠረቱት ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል አንዱ የሆኑት <u>አቡነ አረጋዊ</u> / ዘሚካኤል / ናቸው። ጻድቁ የደብረ ዳሞን ተራራ ለብሕትውና ከመረጡ በኋላ ወደ ተራራው ጫፍ ለመውጣት ተቸግረው ሳለ በተራራው ሥር ሆነው ወይኔ ምነው እንደ አሞራ ክንፍ በኖረኝ አለዚያም ምነው ገመድ በኖረኝ እያሉ ሱባኤ ገብተው ሲጸልዩ ሳለ ቅዱስ ሚካኤል ወደ እርሳቸው ቀርቦ « .... አትፍራ ሥልጣን ተሰጥቶሃል ፤ በቀኝ



በኩልም በዚህች ሰዓት ትንሽ አርፈህ ቆይ እግዚአብሔር በገመድ ፈንታ ትልቅ ዘንዶ ይልክልሃል » አላቸው። ወዲያውኑም እግዚአብሔር በቅዱስ ሚካኤል አማካኝነት ቁመቱ ለድባ ክንድ የሆነ ዘንዶ ልኮ በዘንዶው ጭራ አቡነ አረጋዊ ተቀምጠው ዘንዶውም እንዳይተናኮላቸው ቅዱስ ሚካኤል ሰይፉን መዞ እየጠበቀ ትንሽ ወደ ተራራው መውጣት እንደጀመረ ዘንዶው አቡነ አረጋዊን አወናጥፎ ከተራራው ጫፍ እንደወረወራቸውና በተራራው ላይ ሲደርሱ ሃሌ ሉያ አያሉ እግዚአብሔርን አመስግነው በዚያ መቀመጣቸውን ገድለ አቡነ አረጋዊ ይገልጻል።

በአሁኑ ግዜም የዚህ ዘንዶ ምሳሌ የሆነ የጠፍር ገመድ ይገኛል። ገመዱ ረጅም እድሜን ያስቆጠረ እና አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ያልተቀየረ መሆኑንም የገዳሙ መነኮሳት ይናገራሉ። ይህ ገመድ በእነዚህ ብዙ መቶ ዘመናት ውስጥ አንድ ጊዜም ሳይታደስና ሳይለወጥ በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች፣ ለስለት የሚገቡ በሬዎች ፣ በጐች ወ.ዘ.ተ በሙሉ ያለማቋረጥ በየጊዜው ሲወጡበትና ሲወርዱበት ይታያል።

ወደ ገዳሙ ለመውጣት መጀመሪያ ከላይ በሚላክልዎት ጠፍር ወገብዎን በሽምቀቅ ያስሩና ከዚያም ወፈር ያለውን እና በዘንዶው የተመሰለውን የጠፍር ገመድ በእጅዎ ይይዛሉ። ወገብዎ የታሰረበት ጠፍር ከላይ ባለ ሰው የሚጐተት ሲሆን በእጅዎ የሚይዙት ጠፍር ደግሞ ከላይ የሚጐትትዎትን ሰው ሳለማድከም በራስዎ ኃይል እየታገዙ የሚወጡበት ገመድ ነው። በዚህን ዓይነት

ጉዞ ውስጥ ፍርሀት ከታከሰበት በሰውነትም ሳይ ጉዳት አያደረሱ፣ እየተሳሳጡ እና እየተጋጋጡ ነው ከሳይ የሚደርሱት።

ወደ ገዳሙ እንዲወጡ የሚፈቀደው ለወንዶች ብቻ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ሴቶች ወደ እዚህ ገዳም ለመውጣት ካለመቻሳቸውም በላይ በገዳሙ የሚኖሩት ገዳማውያን ወንዶች በመሆናቸው ምክንያት ጾር እንዳይነሳባቸውም ጭምር ነው።

ወደ ገዳሙ የማይወጡት የሴት ጾታ ያላቸው እንስሳትም ጭምር ናቸው። ከዶሮ በቀር ሌሎች እንዲወጡ አይፈቀድላቸውም። በታሪክ ወደ ገዳሙ የወጡት የአቡነ አረጋዊ እናት ብቻ ናቸው። እሳቸውም ቢሆን በሕይወተ ሥጋቸው አያሱ ሳይሆን በሕይወት ዘመናቸው ከገዳሙ ግርጌ ሆነው በጾም በጸሎት ከቆዩ በኋላ የመጠራታቸው ጊዜ ደርሶ ከዚህች ዓለም በሞት ሲለዩ ነው አስከሬናቸው ወደ ተራራው ወጥቶ የተቀበረው።

ደብረ ዳሞ በገመድ ከመወጣቱ በፊት ለጥቂት ግዜ ወደ ተራራው የሚያስወጣ ደረጃ ከሥር ጀምሮ እስከ ተራራው ጫፍ ድረስ በአፄ ገብረመስቀል አማካኝነት ተሠርቶ ነበር። እንዲያውም አፄ ገብረመስቀል ሳሠሩት ቤተክርስቲያን ለህንጻው ግንባታ የሚውሉት ቁሳቁሶች በሙሉ በቀላሉ የወጡት በዚሁ ተሠርቶ በነበረ ደረጃ አማካኝነት ነበር። ደረጃው የፈረሰው ግን በጻድቁ አቡነ አረጋዊ ትዕዛዝ ቅዱስ ያሬድና አፄ ገብረመስቀል በአመቢታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የታነጸችውን



ቤተክርስቲያን መርቀው ቅዳሴ ቤቷ ከተከበረ በኋላ ነው። ዳሞ የሚሰው የተራራው ስምም የወጣው ከዚሁ ከደረጃው መፍረስ ጋር ተያይዞ ነው። ይኸውም ጻድቁ አቡነ አረጋዊ የተራራውን መውጫ ደረጃ በግእዝ « **ዳሕምሞ** » ማለትም አፍርሰው በማለት ስለተናገሩ ዳሕምሞ የሚለው ቃል ከግዜ ወደ ግዜ ከዘመን ብዛት **ዳሞ** የሚል ቃልን ፈጠረ። በዚህም ምክንያት የተራራው ስም **ደብረ ዳሞ** በመባል እየተጠራ ይገኛል።

ደብረ ዳሞ መሀል ተራራው ላይ እንደደረሱ በወገብዎ ላይ የታሰረውን ጠፍር አስረክበው በአንዲት ጠባብ መሿለኪያ ውስጥ ያልፉና ተራራው አናት እስኪደርሱ ድረስ በተራራው ጥግ የተሠሩ ደረጃዎችን በጥንቃቄ ይወጡና በስተ መጨረሻ በሚገርም ሁኔታ ሰፊ እና ለምለም ሜዳን ያገኛሉ። በዚህ አስገራሚ ሜዳ ላይ አንድ ቤተክርስቲያን ፣ ከ፹፱ በላይ የውኃ ጉድጓዶች፣ በሥስት የተከፈሉ የገዳማውያኑ መንደሮች እና የመቃብር ሥፍራዎችን ያገኛሉ።

እዚህ ሰፊ ሜዳ ላይ እንደወጡ የመጀመሪያው የጉብኝት ምዕራፍዎ የሚሆነው የወጡትን ደረጃ እንደጨረሱ ከሚያገኙት አንድ አነስተኛ እና ጠፍጣፋ ድንጋይ ይሆናል። ይህ ድንጋይ በላዩ ላይ አነስተኛ የመስቀል ቅርጽ ያለው ሲሆን አቡነ አረጋዊን ለመጎብኘት አፄ ገብረ መስቀል ወደ ተራራው በወጡ ጊዜ የንጉሡ ሠራዊት ከተራራው ግርጌ ሰፍሮ ስለነበር ይህንን ሠራዊት ሲባርኩ ጻድቁ ቆመውበት የነበረ ድንጋይ ነው።

ይህን ታሪካዊ ሥፍራ አይተው እንደጨረሱ ከፊት ለፊትዎ በሚያምር ጥርብ ድንጋይ የታነጸውንና ዙሪያውን በአረንጓዴ ዕፅዋት የተሸፈነውን ቤተክርስቲያን ያገኛሉ። የዚህ ቤተክርስቲያን አሠሪ አፄ ገብረመስቀል ናቸው። ንጉሡ የገዳሙን ቤተክርስቲያን ያሠሩት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ነው። ቤተክርስቲያኑ የታነጸው ጻድቁ ከመስወራቸው በፊት ስለነበር ቤተክርስቲያኒቱም የተሰየመችው በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ነበር።

የቤተክርስቲያኒቱ ውስጠኛ ክፍል ሰፊ ባይሆንም መጠነኛ ነው። በቤተመቅደሱ ውስጠኛ ክፍል የሚገኙት ሥዕሎች የቀለም ቅባቸው የሚያስደንቅ ነው። ሥዕሎቹ አብዛኛዎቹ ጥንታዊያን ባይሆኑም በቅድስቱ በኩል በስተ ምዕራብ አቅጣጫ በሚገኘው ግድግዳ ላይ የምትገኘው የእመቤታችን ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ብቻ ናት ፻፺ ዓመት በላይ እንደሆናት የተነገረኝ። በቤተመቅደሱ ውስጥ ወጥ የሆኑና የተሰበጣጠሩ የድንጋይ እና የእንጨት ምሰሶዎች የላይኛውን የጣሪያ ክፍል ደግፈው ቆመው ይታያሉ። በኮርኒስ መልክ የተሠራውን የጣራ ክፍል ያየን እንደሆነ ብዙ የረቀቁ የጥበብ ሥራዎች የሚታይበት ሌላው አስደናቂ ሥፍራ ነው። በዚህ የእንጨት ሥራ ጥበብ ተሰጥኦ እንዳላቸው የሚነገርላቸው አፄ ገብረመስቀል እራሳቸው ተሳታፊ እንደነበሩም ይነገራል።



ይህን የውስጠኛውን የጉብኝት መስመር እንደጨረሱ በቤተክርስቲያኒቱ ቅጽር ግቢ ውስጥ ወደሚገኘው የጸበል ቦታ ያመራሉ። ጸበሉ አራት ማዕዘን ባለው የድንጋይ ገንዳ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከብዙ በሽታዎችና ደዌዎች የመፈወስ ኃይልም አለው። ይህን ጸበል ጠጥተውና ተጠምቀው እንዳበቁ የቤተክርስቲያኑን ቅጽር ግቢ ለቀው ወደ ቀጣይ ጉብኝት መስመርዎ ሥፍራ ይሄዳሉ። መካነ መቃብሩን የሚያገኙት ከቤተክርስቲያኑ ምሥራቅ አቅጣጫ ላይ ያለውን ሰፊ እና ለምለም ሜዳ አቋርጠው አነስተኛ ደረጃዎች ከወረዱ በኋላ በዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ነው።

ከአቡነ አረጋዊ ቀጥለው ማኅበረ መነኮሳቱን ይመሩ የነበሩት __**አባ ማትያስም**__ የተቀበሩት በዚሁ የመካነ መቃብር ሥፍራ ነው። ለምልክትም እስከ አሁን ድረስ በመቃብራቸው ላይ የመስቀል ቅርጽ ያለበት ድንጋይ ከመቃብራቸው ላይ ተተክሎ እናያለን። የጻድቁን መካነ መቃብር እንዳለፍን ከበስተ ጀርባ አንዲት ጠበብ ያለችና ውስጧ በብዙ የአስክሬን ሳጥኖች የተሞላች ዋሻ ያያሉ። በቦታው በሳጥን የሚቀበር ባይኖርም አስከሬኑ ከስጋው አስኪረገፍ እና ዐፅም አስኪሆን ድረስ የሚያርፍበት ዋሻ ነው። ከዚህ ዋሻ ሌላም ስልጣነ ክህነት ያላቸው ሰዎች የሚቀበሩበት ዋሻ አለ።

በዚህ የመቃብር ሥፍራ ላይ የጻድቁ አባት የአባ ዮሐኒ መታሰቢያ የጸሎት ቤት ይገኛል። አባ ዮሐኒ የመንግሥት መደብ

ከሳስታ ወደ ሸዋ ገዥነት ከዛጉዌ ወገን ከነአኩቶ ለአብ ወደ ይኩኖ አምላክ በዞረበት ዘመን በደብረ ዳሞ የነበሩ አባት ናቸው። አባ ዮሐኒ ለሐይቅ እስጢፋኖሱ መምህር ለአባ ኢየሱስ ሞአ እና ለደብረ ሊባኖሱ እጨጌ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት አስኬማ ( ልብሰ ምንኩስና ) ሰጥተው ያመነኮሱ ጻድቅ ናቸው።

አቡነ ተ/ሃይማኖት የመጀመሪያውን አስኬማና ቀብ ቅናት ( መታጠቂያ ) ከአባ ኢየሱስ ሞአ በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ከተቀበሉ በኋላ እንደ ገና ወደ ደብረ ዳሞ ሄደው ሙሉውን የምንኩስና ልብስና ቀብ መታጠቂያውን ጥምር ከደብረ ዳሞው መምህር ከአባ ዮሐኒ እንደገና ተቀብለው ለአባ ኢየሱስ ሞአም ይዘውላቸው እንደመጡ የሁለቱም አበው ገድል ያስረዳል።

* የደብረ ዳሞ ገዳም ሥርዓተ ጳኩሚስ ተመስርቶበት ለዘመናት የኖረ ገዳም ነው።
* ደብረ ዳሞ ሥርዓተ መነኮሳት፣ሥነጽሑፍ፣ሥዕል፣ ቅርጽ ይሠራበት የነበረ ገዳም ነው።
* በመላው ኢትዮጵያ ለሚገኙ መነኮሳት አስኬማ ይሰጥ የነበረው በደብረ ዳሞ ብቻ ነው።

- **አስኬማ**፡- ማለት ምንኩስና ለመቀበል ወደ ገዳም የሚገቡ ወንዶች በአመክሮ ለሁለትና ለሦስት ዓመታት የጉልበት አገልግሎት ይሰጡና አመክሮ ጊዜያቸውን በትክክል የፈጸሙ እንዲመነኩሱ ይፈቀድላቸዋል። ከመነኮሱበት ዕለት አንስቶ ከ፭ - ፯ ለሚደርሱ ዓመታት ከገዳሙ የተመደበላቸውን



የሥራ ድርሻ ያለ ምንም ልግመኝነት ከማከናወን አልፈው ብዙ ትሩፋትን ለፈጸሙ የሚሰጥ ታላቅ የገዳማውያን መንፈሳውያን የአባትነት ማዕረግ ነው። ይህም አባት በሕይወተ ሥጋ እስካለ ድረስ እንደ ቅዱስ ይቆጠራል። በመንፈሳዊ ማዕረጉም ከማንም የበላይ ነው። ነገር ግን ለሴላ ሹመት አይታጭም።

በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ገዳማት ለዚሁ ማዕረግ የታጩውን መነኩሴ ከመካከላቸው መርጠውና ማስረጃ ሰጥተው ወደ ደብረ ዳሞ ይልኩ ነበር። የደብረ ዳሞ መነኮሳትም በክብር በመቀበል የሚገባውን ገዳማዊ መስተንግዶ ሰጥተው ሲያበቁ በማበረታታት በታላቅ መንፈሳዊ አደራ ወደ መጣበት ገዳም ይሸኙታል።

የዚህን መካነ መቃብር ሥፍራ ጉብኝትዎን እንደጨረሱ ቀጣይ የጉብኝት መስመርዎ የሚሆነውን ሥፍራ የሚያገኙት ከመካነ መቃብሩ በስተ ደቡብ አቅጣጫ ላይ ነው። የቦታው ስም <u>ለቂርቶ</u> ይባላል። ቦታው በተራራው ጫፍ በአንደኛው ወገን ላይ የሚገኝ እና በተፈጥሮ የተበላና ከሥር ካለው ዓለታማ ሥፍራ ጋር የሚያገናኝ ገደላማ ሥፍራ ነው። ስለዚህ ቦታ ገዳሙን ሲያስጎበኙኝ የነበሩት አባት ያጫወቱኝን ታሪክ ልንገራችሁ። በዚህ የመሬት ቀዳዳ ውስጥ ብዙ አረጋውያን አባቶች ሾልከው ከ፪ - ፭ ሚትር ያህል ጥልቀት ባለው ገደል ውስጥ ወድቀው በሚያሳዝን ሁኔታ ሞተዋል። እነዚህ አባቶች የሞቱትም በሌሊት

ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ላይ እያሉ ሰይጣን በሰው አምሳል እየተገለጸ የሚረዳቸው እና መንገድ የሚመራቸው በመምሰል ወደ እዚህ ገደል እንደከተታቸው ነው የተነገረኝ፡፡ ነገር ግን እኒህ የሚሞቱት አባቶች እግዚአብሔር ባወቀ የሰማዕትነትን ክብርም ከአምላካቸው ይቀበላሉ፡፡

እዚህ ገደል ጋር ቆመው ወደ ኋላዎት ሲዞሩ በምዕራብ አቅጣጫ በኩል አጅብ ያለና የገጠር ከተማ የሚመስል መንደር በቅርብ ርቀት ላይ ያያሉ፡፡ እነዚህ መንደሮች በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ አገልጋዮች የሚኖሩባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ መንደሮችም በሦስት ይከፈላሉ፡፡ ለእያንዳንዳቸውም መጠሪያ ስሞች አሏቸው፡፡ እነሱም፡-

፩. ምጽዳት አበው

፪. አፈ ጽዮን

፫. ታች ቤት በመባል ይጠራሉ፡፡

ወደ እነዚህ መንደሮች እየቀረቡ ሲመጡ ግን በዚያ ሰማይ ጥግ በደረሰ ተራራ ላይ በአእምሮዎት ይሆናል በዚኒ ሥፍራም ይገኛል ብሰው የማያስቡት ነገር ግን በአምላክ ቸርነትና ጥበብ የሆነ እና የተደረገ ነገር ያያሉ፡፡ ይኸውም ተዓምራት እዚያ ሰማይ ጥግ በደረሰ የድንጋይ ተራራ ላይ የውኃ ምንጭ መኖሩ ነው፡፡ የምንጭ ውኃው ጉድጓድ አንድ ብቻ ቢሆን ባልገረመም ባላስደነቀም ነበር፡፡ ነገር ግን የምንጮቹ ብዛት አንድ መቶ ሃምሳ ያህል መሆናቸው እንጂ፡፡ እነዚህ ምንጮች



ደግሞ በውጭ ከሚገኙት የምንጭ ውኃዎች በተጨማሪ በእያንዳንዳቸው መነኮሳት ቤት ውስጥ መገኘትም ሌላው ተዓምር ነው፡፡

በገዳሙ ውስጥ የሚገኝ አንድ መነኩሴ በቤቱ ውስጥ <u>እንደ የጸሎት ቤት</u> ፣ <u>እንደ እንግዳ መቀበያ ሳሎን</u> ፣ <u>እንደ ማዕድ ቤት ከነምንጭ ውኃው</u> ይኖረዋል፡፡ ይህ የምንጭ ውኃ የሌላቸው አንዳንድ ቤቶች የምንጭ ውኃ ካላቸው ጐረቤቶቻቸው በቀጥን ቦይ ስለሚላብላቸው የውኃ ችግር አያገኛቸውም፡፡ በተለይ ከበዓታቸው ለማይወጡና ሱባዔ በመግባት ለረጅም ጊዜ በዓታቸውን ዘግተው ለሚቀመጡ አባቶች ይህ የውኃ ምንጭ እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ አድርጐ ማዘጋጀቱ እንዴት ካለ ሥቃይ እንዳዳናቸው ነው የሚናገሩት፡፡

ከዚህ ቤት ውስጥ ከሚገኘው የውኃ ምንጭ የማይጠቀሙና በቤታቸው ውስጥ ምንጭ የሌላቸው፣ ከጐረቤትም ከቤታቸው አቀማመጥ የተነሳ ውኃው ሲላብላቸው ያልቻሉ መነኮሳትም የሚጠቀሙበት አንድ ሰፊ የውኃ ጉድጓድ ከመንደሮቹ ውጪ ለሦስቱም መንደሮች አማካይ በሆነ ሥፍራ ላይ የሚገኝ ጥልቀቱ ፲፭ ሚትር ያህል እንደሚደርስ በመነኮሳቱ የተገመተ ጉድጓድ ውስጥ የሚገኝ የውኃ ጉድጓድ ለላለ ከዚያ ይጠቀማሉ፡፡

እነዚህ በውጭ የሚገኙ የውኃ ጉድጓዶች አገልግሎት የሚሰጡት ለሦስት ነገሮች ነው፡፡ አንደኛውን ጉድጓድ ሰዎች ለመጠጥ የሚያውሉት ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ በገዳሙ ያሉ

ክብቶች የሚጠጡት ሲሆን ቀሪው እና ሦስተኛው ደግሞ ለልብስ ማጠቢያና ለቤት ሥራ አገልግሎት የሚውል ነው። የውኃ ጉድጓዱ በተፈጥሮ የራሱ መክደኛ የሆነ ልብስ ያለው እና በአረንጓዴ ዕጽዋት የተሸፈነ ነው። የሚገርመው ነገር ይህን በገዳሙ ውስጥ የሚገኝ ውኃ ከዝናብ በቀር ሌላ ከገዳሙ ውጭ ያለ ውኃ ቢደባለቅበት የውኃው ሽታ መጥፎ ጠረን አውጥቶ አካባቢውን እንደሚበክለው ነው ከመነኮሳቱ የተነገረኝ።

የጉብኝት መስመርዎ ይቀጥልና የደብረ ዳሞ ተራራን ጉብኝት በእንዲህ ዓይነት አስደናቂ ነገሮች ሲገረሙና ሲደሰቱ ከቆዩ በኋላ እያስቀሱና ጸጉሩዎን እየነጩ ደረትዎን እየደቁ ወደሚወጡበት ሥፍራ ያመራሉ። ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም መነኮሳቱ የፍንዳታ ድምፅ በመስማታችን ፤ የፍንዳታውን ድምፅ ወደ ሰማንበት ቦታ ሮጥን ፤ ሮጠንም ከቦታው ደረስን። እሳቱ በቤቱ ውስጥ የሚገኙት ጧፍና ዕጣኖች ኃይል እየሰጡት ወላፈኑ አሳስጠጋ እለን። ብንሯሯጥ ፣ ብንጮህ፣ ብናለቅስ የምናመጣው ነገር ባለመኖሩ ዓይናችን እያየ ብዙ ውድና ብርቅ ቅርሶችን የያዘው ዕቃቤት ነደደ ሐመድ ሆነ። ይላሉ መነኮሳቱ ወደኋላ ያንን ቀን በማስታወስ እያለቀሱ።

በዚህ ዕቃቤት ውስጥ የነበሩ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ውድ እና በአሁኑ ግዜ በምንም ዓይነት ዘዴ ለንተካቸው የማይቻሉን ቅርሶች ናቸው የወደሙት። ከነዚህ ካለመተኪያ ከወደሙት ቅርሶች መካከል፡፡



* ዜና ሕይወት የብራና መጽሐፍ፣
* ክበበ አክሱም የብራና መጽሐፍ፣
* የወርቅ ከበሮ እና ሁለት የወርቅ ዘውድ ለሁል ሚካኤል ስገዳሙ ያበረከትዋቸው፣

በተለይ **ክበበ አክሱም** የሚባለው መጽሐፍ በሌሎች ገዳማት የሌለ እና በደብረ ዳሞ ብቻ የነበረ ያስተተኪም የተቃጠለ መጽሐፍ ነው። ብቻ የደብረ ዳሞን ጉብኝትዎን በዚህ መልኩ ያጠናቅቁና በመጡበት አኳኋን ወገብዎትን በገመድ ይታሰሩና ተራራውን ይወርዳሉ።



ወደ ደብረዳሞ እስከሬን ሲወጣ ፎቶ ወንደሰን

## አባ ጰንጠሌዎን

አባ ጰንጠሌዎን ይህ ገዳም የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሀገር ውስጥ ነው። አክሱም አጠገብ በሚገኝ ተራራ ላይ በሚያስደንቅ አይታ ውስጥ የሚገኝ ቤተክርስቲያን ነው። አባ ጰንጠሌዎን ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ሲሆኑ የመሰረቱት ገዳም አሳቸው በህይወተ ስጋ እስካሉ ድረስ በማርያም መግደሳዊት ስም የሚጠራ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ነበር። ከአባ ጰንጠሌዎን በኋላ ግን **መካነ ፃማዕት** በመባል ታወቀ የሳቸው ስምም ተደራቢ በመሆን ይጠራ ጀመር። መካነፃማዕት ሰወንዶች ብቻ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥበት በማርያም መግደላዊት ሰም የተሠራው ደብር ሰሴቶች ብቻ ተወሰና እስከ አሁን ድረስ ይገኛል። ታዲያ የጻድቁና የቦታው ስም አንድ ላይ ሲጠቀስ አባ ጰንጠሌዎን ዘፃማዕት ይባላል። አንዳንዴም ገዳሙ መካነ ፃማዕት በመባል ይታወቃል። ፃማዕት ማለት ርዝመቱ ሦሰት ከንድ ሰፋቱ አንድ አሰኬር ሜትር ያህል ሆኖ የተዘጋጀ የጻድቁ መጸለያ ጉድጓድ ነው። በዚህች ጉድጓድ ውስጥ ቀን ቀን ሰብከተ ወንጌሳቸውን ሲያጣድፉ የሚውሉት ጻድቁ አባት ሌሊት ሌሊት እየጸለዩ ፵ ዓመት ሙሉ አሳልፈዋል።

ይህንን ቦታ በአካባቢው የሚኖሩት ምዕመናን **እንዳ አባ ጰንጠሌዎን** እያሉ የጠሩታል። **አፄ ካሌብ** ወደ የመን ከመዝመታቸው በፊት ከአባ ጰንጠሌዎን የጸሎት ተማጽኖን ያገኙበት፣ በድል አድራጊነት ሲመለሱ መንኩሰው የተቀመጡበትና



በኋላም **ዐፅማቸው ያረፈበት** ታላቅና ታሪካዊ ገዳም ነው። በዚህ ገዳም ቅዱስ ያሬድ የቅዱስ ኤፍሬምን የዜማ ትምህርት ተምሮበታል። ይህ ገዳም በከፍታማ ቦታ ላይ ስለነበር የፋሽስት ኢጣሊያ ወታደሮች የጦር ምሽግ በማድረግ በአምስቱ የወረራ ዓመታት ተጠቅመውበታል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከውጭ ቋንቋ ወደ ግዕዝ መገልበጥ ከተጀመረ አንስቶ **የመጻሕፍት ት/ቤት** ፤ ቅዱስ ያሬድ ከተነሳ ወዲህ ደግሞ **የዜማ ት/ቤት** ከአክሱም የራቀበት ጊዜ እንደሌለ ይታወቃል። መነሐሪያ ቦታውም ይኸው የአቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም ነበር። በዚሁ ገዳም ተስምዶ የኖረው የዜማ አይነት **ቆሜ** ይባላል። ሊቃውንቱ የዜማ መጻሕፍት ጾመ ድጓ፣ ድጓ ምዕራፍና ዝማሬ መዋሲት እስከ አሁን በገዳሙ በክብር እንደተጠበቁ ይገኛሉ። የአባ ጰንጠሌዎን ገድል ሙሉው የሚገኘው ግን በጣሊያን አገር ሲሆን አሁን የሚገኘው ገድል ግን ከሰንከሳር ከድጓና ከመሳሰሉት ተውጣጥቶ የተዘጋጀ ነው።

**የአባ ጰንጠሌዎን በዓለ ዕረፍታቸው ጥቅምት ፮ ቀን ይከበራል። የማርያም መግደላዊት ዕለተ ዕረፍትም ነሐሴ ፮ ቀን መሆኑ በሰንከሳር ሰለተመዘገበ የሁለቱ የጋር በዓል በአንድ ቀን ሲታሰብ ይኖራል።**

## ማኅበረ ዶጌ

ይህ ገዳም የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሐገር በአክሱም አውራጃ ከአክሱም ከተማ ወደ ደቡብ በሚወስደው መንገድ ፲፪ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው፡፡ ማኅበረ ዶጌ ማለት « እንስሳል » ማለት ነው፡፡ አቦታው ላይ በነበርሁ ግዜ ያገኘሁት መረጃ ትንሽ አጥጋቢ ባለመሆኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰበከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ በኩል እየተዘጋጀ በየወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ ከሚወጣው « <u>ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ</u> » ከሚለው የቤተክርስቲያናችን መጽሔት ላይ ያገኘሁትን በጥቂቱ ቀንጨብ አድርጌ አቅርቤዋለሁ፡፡

መጽሔቱም ዋቢ አድርጎ ለንባብ ያበቃው ከገዳሟ በተሳከለትና በመረ.ኤ.ኤም የተዘጋጀውን መጽሐፈ ሱባኤን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ታሪኩንም ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡፡ አቴ ዠን ሕንደኬ ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ሆና በነገሠች በ፴፱ ዓ.ም በአንደኛው ዓመተ መንግሥትዋ ወንጌላዊው ማቴዎስ መርዋ ከተማ ገብቶ ሲያስተምርና ሲያጠምቅ ሰምታ መኳንንቱን መሳፍንቱን አስከትላ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት ይዛ መረዋ ወረደች፡፡ በዚያም ንግሥቲቱ ቅዱስ ማቴዎስን አግኝታ «የኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር አብ የባህርይ ልጅ መሆኑን አውቃለሁ ይሁን እንጂ ዳግመኛ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መወለድን አላውቅም ነበር፡፡ አሁን ግን በትምህርትህ መንፈስ



ቅዱስ ስለገለጸልኝ አጥምቀኝ» አለችው፡፡ ማቴዎስም ንግሥቲቱን ካጠመቀ በኋላ መኳንንቱን መሳፍንቱንና የጦር ሠራዊቱንም ሁሉ አጥምቆአቸዋል ይላል፡፡ አያይዞም « ንግሥቲቱም ማቴዎስን ይዛው ወደ አክሱም ተመለሰች፡፡ ልጆችዋንና ቤተሰቦችዋንም አስጠመቀች <u>አክሱስ</u> የሚባል ባልዋም አምኖ ተጠመቀ በማለት ያትታል፡፡

ታሪኩን በማብራራት ሲቀጥል « ቅዱስ ማቴዎስ ከዚያ በፊት <u>የጉብንና የናግራንን</u> ሕዝቦች አጥምቆአል፡፡ ካለ በኋላ በዚሁ ጊዜ ሐዋርያው ማቴዎስ የማኅበረ ዶጌን አንድነት ማኅበር አቋቁሞ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በየወሩ በ፳፱ ቀን እየተሰበሰቡ ማኅበር እንዲጠጡ አድርጎአል ሲል ማኅበረ ዶጌን የመሠረተው ሐዋርያው ማቴዎስ መሆኑን ይነግረንና በመቀጠል በ፲፱፻፶ ዓ.ም በአሥፍሐ ወልደ አብርሃም ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመነ መንግሥት ርምያ ከምትባል መንደር ከርም

፩. ለለ ጽድቅ የሚለደዱ ብፁአን ናቸው፡፡ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና፡፡
፪. « አባቱን እናቱን ሚስቱን ልጆቹን ያልተወ ሲያገለግለኝ አይችልም » ብሎ የተናገረውን አንብበው ትርጉሙ የገባቸው እና የዚህችን አለም ጣዕም ጥቅም ንቀው ሀገራቸውን ወገናቸውንና ዘመዶቻቸውን ትተው መንነው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡

እነዚህም ከአክሱም ከተማ በስተ ሰሜን ከሐውልቱ በስተጀርባ « **ቤተቀጢን** » በሚበል ሥፍራ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ያህል እንደተጠቀመጡ ታሪኩ ያመለክትና በዚያም ምቾትና ድሎት ስለተሰማቸው ለዚህ ለዚህማ ከሀገራችን ለምን መጣን? ስለዚህ ሱባኤ ገብተን በጾም በጸሎት ተወስነን የምንሄድበትን ቦታ በረከተ ነፍስ የምናገኝበትን ሥፍራ እግዚአብሔር እንዲያሳየን እናመልክት ብለው ሱባዔ ገብተው ጾም ያዙ፡፡

ከሱባዔው በኋላ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጸ እያንዳንዳቸው የሚኖሩበትን በአት አመለከተቻቸው፡፡ በዚያውም በጾምና በጸሎት ጸንተው እንዲኖሩ ነገረቻቸው ሦስት ሺህ ያህሉ ደግሞ ከሳይ ወደጠቀለነው ሥፍራ ኼዱ፡፡ እዚያ ከነበሩት ጋርም ተደመሩ፡፡ ከዚያም የቅዱስ ጳውሎስንና የቅዱስ ዮሐንስን መመሪያ ተከትለው ማለት « ከሁሉ ፍቅር ይበልጣል » የሚለውን ጠብቀው በእምነት በፍቅር ጸንተው በየሳምንቱ እሑድ ተዝካረ ስንበትን ጠብቀው ማኅበር ሲጠጡ ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምሳለ ነዳይ ድሀ መስሎ በመካከላቸው ተገኘ ይላል ታሪኩ፡፡

መጽሐፉ ታሪኩን ሳያቋርጥ ይቀጥልና ከእነርሱ ጋርም እንደ ማኅበረተኛ ሆኖ እንዲታወቅ ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም ፈቀዱለት፡፡ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ያህልም ከእነርሱ ሳይለይ ቆየ በዚሁ ጊዜ ለኔም ተራ ስጡኝ እንደ አቅሜ ዝክር ሳውጣ



አላቸው፡፡ እነሱ ግን አይሆንም አንተ ድሀ ነህ ከእኛ ጋር ሁነህ በዓሉን አክብር እንጂ ምን አለህና ነው አሉት፡፡ እርሱም አይሆንም ስጡኝ እንጂ አላቸው፡፡ እነርሱም ካልክማ ብለው ቀን ወስነው ሰጡት፡፡ ከማኅበረተኞቹም መካከል « ሳይዳ » የሚባል ሰው ነበር፡፡ ይህም አሳሳፊ ( ሙሴ ) ማለት ነው፡፡ ይህም ሰው እንግዳና ድሀ ሰው ፈጽሞ አይወድም ነበር፡፡ ጌታችንም ከማኅበረተኞቹ መካከል ሲገኝ ድሀ መስሎ ስለነበር በጣም ይጠላው ነበር፡፡ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሲቀመጥም አንድ ቀንስ ስንኳ አንድ ዋንጫ የወይን ጠጅ ሰጥቶት አያውቅም ነበር፡፡

ሆኖም የጌታችን ማኅበር ለስ ደረስ እንደ ማኅበሩ ስርዓት አሳሳፊውን ጠርቶ ጋኖቹን አጠብልኝ አለው እርሱም አላጥብልህም ምን አለህና ነው! አንተ ማኅበር የምታደርገው? ብሎ አናንቆ ተመለከተው፡፡ ጌታም አንድ እረኛ ጠርቶ አንተ ልጅ ከብቶችህን እኔ እጠብቅልሃለሁና ውኃ አምጣልኝ አለው፡፡ ልጁም ገምቦውን ይዞ ትንሽ ወረድ እንዳለ ጌታ ዘወትር ከሚቀመጥበት ድንጋይ ላይ ሆኖ ዘንጉን ወደ ልጁ አቅጣጫ ወረወረው፡፡ ዘንጉም ከልጁ ፊት ሄዶ ተተከለ፡፡ ልጁንም ጠርቶ ዘንጉን ንቀለው አለው፡፡ ልጁም ዘንጉን ቢነቅለው ውኃ ፈለቀ፡፡ ከርሱ ቀድተህ አምጣልኝ አለው፡፡ ልጁም ከዚያ ውኃ ቀድቶ አመጣለት፡፡ ጌታም ውኃውን በጋኖቹ ውስጥ ጨምሮ እስከ በዓሉ ድረስ አቆየው፡፡

በበዓሉ ቀን ማኅበርተኞቹ ምን ሊያበሉን ነው ? ምን ሊያጠጡን ነው? ሳይሉ ሁሉም ተሰበሰቡ፡፡ ጌታችንም በፊታቸው ጋኖቹን ቢባርካቸው የወይን ጠጅ ተሞልተው ተገኙ፡፡ ቀድቶ ቢሰጣቸውና ቢቀምሱት በጣም ግሩም ለሰ ነበር እጅግ አደነቁ እነርሱም ጌታ ከጻድቃን አንዱ ለለመሰላቸው ከእግሩ ላይ ወድቀው እስካሁን ሳንበድልህ አልቀረንምና ይቅር በለን ብለው ለመኑት፡፡ ጌታም ተነሱ ብሎ ካስነሳቸው በኋላ እናንተ አልበደላችሁኝም የበደለኝ አሳላፊያችሁ ( ሙሴያችሁ ) ነው፡፡ አንድ ቀን እንኳን አንድ ዋንጫ ወይን ጠጅ አልሰጠኝምና አፈራርዱኝ አላቸው፡፡

ነገር ግን ሙሴው የማያፍር ደፋርና ርጉም ለስነበር ሊጠይቁት ይህ ሰው ( ጌታችንን ) በልቶ አልበላሁም ጠጥቶ አልጠጣሁም የሚል ለለ ሆነና ለለማይጠገብ ነው እንጂ እንዲያውም ለእናንተ አንዳንድ ዋንጫ ለለጥ ለእርሱ ሁለት ነበር የምሰጠውና የሚጠጣው ብሎ የሐሰት ቃል መሰለ፡፡ ጌታችንም እንግዲያስ እኔ የጠጣሁባት ዋንጫ ትቅረብና ትመስክርብኝ አለው፡፡ በዚሁ ተስማምተው አሳላፊው ( ሙሴው ) ኪዶ ዋንጫ አምጥቶ በዚህ ነበር የምሰጠውና የሚጠጣው ብሎ አቀረበ፡፡ ዋንጫዋም ከተቀመጠችበት አንድ ክንድ ከለንዝር ተነስታ እለማትን የፈጠረ ጌታ አምላክ በእጁ አልጠጣብኝም፡፡ እኔ የያዝኩትን የወይን ጠጅም አልቀመሰም ብላ መሰከረች፡፡ በዚያን ጊዜ ሳይዳን ( ሙሴ ) ከነልጆቹ እንደዳታትንና እቤርን ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው፡፡ ማኅበረ ጻድቃኑም ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ተረድተው እንደገና ከእግሩ ስር ወድቀው ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ለመኑት፡፡ ቀኑም ጥር ፳፩ ቀን ነበር፡፡

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስም ይቅርታ ካደረገላቸው በኋላ በስማችሁ ለድሀ የሰጠ ፣ በለማችሁ ተዝካር ያወጣ ፣ በስማችሁ ድሆችን የረዳ ፣ ያሰበሰ ፣ ያጐረሰ ፣ የሰጠ ፣ የመጸወተ ቤተክርስቲያናችሁን የሠራ ፣ ያሠራ እስከ ዓስራ ሁለት ትውልድ ድረስ ምሬላችኋለሁ ብሎ ቃል ኪዳኑን ሰጣቸው፡፡ ይኸንን ቃል ኪዳን ከሰጣቸው በኋላም የማኅበረ ጾጊ ጻድቃንን ከሞት ለውሯቸዋል ይኸም የሆነው በጥር ፳ቀን ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ይህ ታሳቅ በዓል ሆኖ ዛሬም በየዓመቱ ጥር ፳ ቀን በታላቅ ድምቀት ሊከበር ይኖራል፡፡



በዚህ ሥፍራ በታሪኩ ላይ የተጠቀሱት በዓይን የሚታዩት በእጅ የሚዳሰሱት ተዓምራት የታየባቸውና የተደረገባቸውም ሁሉ በቅርስነት ተጠብቀው ይገኛሉ፡፡

እነርሱም፡-

፩. ጌታችን የተቀመጠበትና የቆመበት ድንጋይ ከነ ምልክቱ፣
፪. « ምስዋርም » የሚባል ጻድቃኑ የተሠወሩበት ሥፍራ ፣
፫. ጌታ ከድንጋይ ላይ ሁኖ ዘንግ ወርውሮ ያፈለቀው ውኃ፣
፬. ቀመት ጨምሩ ከመሬት ተነስታ እንደሰው የመሰከረችው ዋንጫ፣
፭. ጻድቃኑ ሊወቅጡበት የነበረው የድንጋዩ ሙቀጫ፣

፮. በማኅበራቸው ጊዜ ሲደግሱባቸው የነበሩ የድንጋይ ገበታዎች፣

፯. ከሀገራቸው ከሮም ያመጡት ባለ መስታወት ቀዋሚ መስቀል፣

፰. ርዕስ ዮሐንስ የሚባሉ ነገሥታት ከነዘውዳቸው ጳጳሳት ከነአክሊሳቸውና ከነመስቀላቸው በዚያን ጊዜ የተሳለ ስዕል፣

፱. ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊው ማኅበረ ጻድቃን (ዶጊ) ውስጥ ሆኖ ያስተማረበትና የሚጠመቅበትንም የሚያሳይ ሥዕል፣

ይህ ገዳም በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት እንደተገደመና ገዳሙም ራሳቸው የገደሙት የራሳቸው መሆኑ በአክሱም መጽሐፍ ክብረ ነገሥት ተጽፎ እንደሚገኝ በታሪኩ ተረጋግጦ ተሳልፎልናል ለማየት የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሄዶ ለማየት የሚችል መሆኑን በዚሁ ጽሑፍ እንገልጻለን፡፡ በማለት የማኅበረ ዶጊን ገዳም ታሪክ ጽሑፍ ያበቃል፡፡



## <u>አክሱም ጽዮን</u>

አክሱም ከአሁኗ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ በ፲፻፶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ የጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት፡፡ አክሱም የሚባለው መጠሪያ ስሟንም የወረሰችው **<u>አክሱማዊ</u>** ከሚባለው የአክሱም ነገዶች አባት ነው፡፡ በአክሱም ከነገሡት ከቀደምቶቹ ነገሥታት አንድዋ ንግሥት ሳባ ናት፡፡ ንግሥት ሳባ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ጥበባት ሌላ የሰሎሞንን ጥበብ ለመመልከት ለትል እየሩሳሌም ሄዳ በነበረበ ጊዜ ለሀገርዋ የሚጠቅመውን ቅርስ ወርሳ ከመምጣቷም በላይ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር የሆነችውን ጽላት በልጅዋ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት ለኛ ለኢትዮጵያውያን በእግዚአብሔር ፈቃድ ተሰጥታናለች፡፡ ሌሎቹ ለምሳሌ እንደ ኢዛናና አይዛና ( አብርሀ ወአጽብሐ ) ያሉ ነገሥታት በዘመናቸው ለነበረው ስልጣኔ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች የተውባት እንደ **<u>ኤንዲበስና</u>** **<u>አፈላስ</u>** ያሉ ስማቸውና መልካቸው በወርቅና በብር ገንዘቦች ላይ ታትሞ የሚገኙ ነገሥታት መኖሪያ ነበረች፡፡ አክሱም ለኢትዮጵያ የክርስትና እምነት እናት ብቻ ሳትሆን የሥልጣኔም ዋና ለባህሏም መነሻ ምንጭ ናት፡፡ ከዚህ የተነሳ የአክሱም ታሪክ በሁለት ትላልቅ አበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

እነርሱም፡-
* ከክርስትና በፊት የነበረ ታሪኳና
* ከክርስትና በኋላ የነበረ ታሪክ ናቸው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተ ጽዮንን በማስመጣት ብቻ አልተወሰነም ከዓስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የተውጣጡ ፲፪ሺ ሕዝብም ይዞ ነበር የመጣው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ፲፫፻፷ ዘመን መካከል በ፵፭፻፳ ዓመተ ዓለም ነግሦ የነበረው ዘገዱር ይህ አሁን ፈርሶ የምናየው ቤተክርስቲያን በአብርሀ ወአጽብሐ ከመታነጹ በፊት ከከተማው ቦታ ላይ ታቦተ ጽዮን በሕገ ኦሪት ተጠብቃ በዘገዱር ጽዮንና ተከታዮችም በ፵፰፻፳፫ ዓመተ ዓለም ገደማ ከቤተ መንግሥቱ ተወስነው እስከ ፵፱፻ ዘመን ድረስ ቆየ።

እያሴ ዘመናት ካለፉ በኋላ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባዜን ዘመነ መንግሥት በ፶፭፻ ዓመተ ዓለም መጨረሻ ላይ ከድንግል ማርያም ተወለደ። ዓመተ ፍዳ አልፎ ዓመተ ምሕረት ተተካ። አብርሀ ወአጽብሐ በ፫፻፴ ዓ.ም በነገሡ ፫፻፵፬ ዓ.ም ላይ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፪ መቅደስ የተወሰነ አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተ። ታቦተ ጽዮን ከላይ እንደተነገረው በዘገዱር ብዙ ዘመናት ካሳለፈች በኃላ በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ወይም ፍሬ ምናጦስ በተባሉት ጳጳስ ጊዜ አዲስ በተሠራው ሕንጻ ለመኖር ቻለች። በተለይ ከዚህ በታች ለሚቀርበው ጽሑፍ ሙሉ በሙሉ መረጃ ለሰነወርቅ ገብረጊዮርጊስ ጥንታዊ ስርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ ከሚለው መጽሐፋቸው ያገኘሁትን እና ከሌሎችም በታዎች ያሰባሰብኳቸውን ስለ አክሱም ቤተክርስቲያን አሠራር ታሪክ



ለማቅረብ እሞክራለሁ።

ጻድቃን ነገሥታት አብርሀ ወአጽብሐ ትምህርተ ወንጌል እየሰጡ በአክሱም ቤተ መንግሥታቸው ሳሉ ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ መሳእክቱን አስከትሎ መጥቶ አክሱም ላይ ማይ ኰኵሖ በሚባለው ተራራ ላይ ቁሞ አብርሀ ወአጽብሐን ጠርቶ በዚህች ቦታ ቤተ መቅደሴን እንጹልኝ አላቸው። እነሱም ቦታው ባሕር ለለ ነበር በየት እንነጽልህ አሉት። ወዲያው ጌታ በጥበቡ ከገነት ጥቂት አፈር አምጥቶ ከበሕሩ ላይ ቢበትንበት ባሕሩ ደርቆ ሜዳ ሆነ። በዚህ ጊዜ ጌታ ቤተ መቅደሴን በዚሁ ሥሩ ብሎአቸው ወደ ሰማይ አረገ።
(ጌ በቆመበት ዓለት ላይ የእግሩ ጫማ ቅርጽ እስከ አሁን ሳይጠፋ በግልጽ ይታያል። ከዚያ ወዲህ ቦታው መከየደ እግዚእ እየተባለ ይጠራል።)

በነገታው አብርሀ ወአጽብሐ በትግሬ ትግረኚ ያሉ ብልሐተኞች አናጺዎችና ዕንጨት ጠራቢዎች አክሱም ላይ እንዲሰበሰቡ አዋጅ አስነገሩ። በአዋጁም መሠረት ፺፪ ጥበበኞች ተሰበሰቡ። እነርሱም ከተራራሮች ላይ ድንጋይ የሚጠርቡ ፷፪ ሰዎች መረጡ። ደሰሕ ላይ ሒደው ጥድና ዝግባ የሚጠርቡትን ደግሞ ፵፪ ሰዎች መርጠው ላኩ። ከእነዚህ ሌላ ከደሰሕ ወደ አክሱም የተጠረበውን ጥድና ዝግባ የሚያመላልሱትንም መቶ ሺህ ሕዝብ አዘዙ። ፺፪ ግንበኞችን መደቡ። ድንጋዩንም የሚያቀብሉ ፳፪ ጡቡን የሚያበስሉ ፲፪ ሲሚንቶውን ኖራውን

የሚያቦኩ ፺፱ ሠራተኞች አዘጋጁ፡፡ መልሰው ከአክሱም ጥበበኞች መረጡ፡፡ እነሱንም ሁለት ሁለት ክፍል አድርገው አዘጋጁ፡፡ መልሰው ከአክሱም ጥበበኞች መረጡ፡፡ እነሱንም አዛዥ አደረጉላቸው ለእነዚህም ሁሉ በየቀኑ ምግብ ፣መጠጥ፣ ገንዘብ አዘጋጁላቸው፡፡ የሥራው አከፋፈልም እንዲህ ነው፡፡ ሁለት ሁለት ሁነው ባንድ ቦታ ላይ የ፲፪ መቅደስ መሠረት መስከረም ፳፫ ቀን ለኛ ዕለት በዘመነ ማርቆስ በ፫፻፴፮ ዓመተ ምሕረት አስጀመሩ፡፡ አብርሀ ወአጽብሐም መሠረቱን እንዳስጀመሩ በምን ዓይነት ( መልክ ) እንደሚያሠሩት ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ፡፡ እግዚአብሔርም ወዲያው ጸሎታቸውን ሰምቶ የቤተመቅደሱን አሠራር ገለጸላቸው፡፡ በነገታው ዕንጨትና ድንጋይ የሚሸከሙትን ሕዝብ ሰብስበው ለእነዚያ ብልሐተኞች ( አናጺዎች ) የቤተ መቅደሱን ቅርጽ ሥለው አሳዩአቸው፡፡ ወዲያውኑ አናጺዎቹ የቤተ መቅደሱን ሥራ በጀመሩ ጊዜ እግዚአብሔር ቀድሞ ለእስራኤል መና ከደመና እንዳዘነመላቸው፡፡ ቤተመቅደሱን የሚያጌጡበት ወርቅና እንቁ ፳ ቀን ፳ ሌሊት አዘነበላቸው ፫ ቀን ፫ ሌሊትም ይላል፡፡

ቤተመቅደሱን እያሠሩ ውስጡን ዝግባ ሳንቃ አስለበጡት፡፡ ከመሠረቱ ጀምረው እስከ ጣራው ድረስ በዝግባ ጥርብ ለበጡት፡፡ ከዚያ በዘነመላቸው ወርቅና እንቁ ገበዘ አክሱምን አስጌጡአት፡፡ የምሰሶዎችዋ ቁጥር ፳ ናቸው፡፡



ለእያንዳንዱ ቤተ መቅደስ አምስት አምስት ምሰሶዎች አቁመው አብነ በረዱን እንደ መንበር ቀርጸው በወርቅና በዕንቁ ለብጠው ታቦተ ጽዮንን በዚያ ላይ አስቀመጡአት፡፡

የሕንጻው ሥራም እንደዚህ ነው፡፡ ወደታች መሠረቱ ፲፭ (ክንድ) ነው፡፡ የቤተ መቅደሱ ደረጃ ወይም ደፍ ርዝመት ከምድር እስከ አፈጽዮን ያለው ፲፭ ( ክንድ ) እመት ነው፡፡ የንድቀ ወርድ ፯ ( ክንድ ) እመት ነው፡፡ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ሞላልነቱ ፻፳፭ ክንድ ነው፡፡ ከድቡብ እስከ ሰሜን ስፋቱ ፺፪ ክንድ ነው፡፡ የውስጡ ወርድ ሥፋቱ ፺፫ ክንድ ነው፡፡ ከምድር እስከ ጉልላቱ ራስ ፴፪ ክንድ ነው፡፡ በድንጋይ ታንጸው የቆሙ ምሰሶዎች ፴፪ ናቸው፡፡ የሁሉም ድምር ፷፪ ነው፡፡ በስተ ምዕራብ በኩል በውጭ ያሉ ( የበር ) የደጃፎቹ ትላልቅ የዋንዛ መዝጊያዎች ፬ ናቸው፡፡ በውስጡም ያሉ ፬ ናቸው፡፡ ዋና መቅደሱ አንድ ነው ሰሜናዊ ፩፣ ደቡባዊ ፩፣ ዘቤተ ጊዮርጊስ ፩፣ ዘቤተ ዮሐንስ ፩፣ ዘቤተመዛግብት ፪፣ዘቤተ ገብርኤል ፪፣ ዘቤተ ማኅበር ፩፣ ዘቤተ ማርያም መግደላዊት ፩፣ ዘቤተ ሚካኤል ፩፣ በድምር ፲፪ ቤት መቅደስ ናቸው፡፡ በትላልቆች ደጃፎቹ ያሉ የዋንዛ መዝጊያዎች አራት መቶ ስልሳ አንድ ናቸው፡፡ መስኮቶችዋም ፩፻፳፪ ናቸው፡፡ ሠረገላዎችም ሰባት መቶ ስማንያ ናቸው፡፡ ቀስተ ደመናዋም ፲፱ ናቸው፡፡ ርእስ ሀብይ ( የአበባ ቅርጽ ) ፫፻፳፲፭ ናቸው፡፡ የውኃ መሸረብ ( አሸንዳ ) ዘጠና አንድ ናቸው፡፡ ይህን ሁሉ በወርቅና በዕንቁ ለብጠውታል፡፡

እናጺዎቹም ይህን በሙሉ ሥራ በትጋት እየሠሩ በዓሥራ አራት ዓመት በ፲፱፻፵፬ ዓ.ም ፈጸሙት። ቤተ መቅደስዋንም ስይጣናት እንዳይቀርቧት በአብርሀ ወአጽብሐ ትእዛዝ በትእምርተ መስቀል አምሳያ ሐውልት ጠርበው አቆሙላት። ከዚህ ሁሉ ሥራ ፍጻሜ በኋላ የሠሩትን ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን አስባርከው ከእስክንድርያ ያስመጡዋት ታቦተ ማርያምን አሸክመው ከዚህ ሁሉ ድርጅት አስቀደመው በዓሉን ስማክበር ከመላ ኢትዮጵያ በአዋጅ የሰበሰቡአቸውን ተሳልቆች ሹማምንትና አማግሊዎችን ካህናትን ሌዋውያንን አሰልፈው በከበሮ፣ በጸናጽል፣ በመሰንቆ፣ በመዝሙር ( በበገና ) በእንቢልታ፣ በነጋሪት፣ በመለከት፣ በእንዚራ ፣ በብእዛ ቀንድ፣ በነስር ቃና እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ታቦተ ሕጉን አስገብተው ቅዳሴ ቤቱን አከበሩ። ቀኑም ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓመተ ምሕረት ነው። ንዋየ ቅዱሳቱንም በሙሉ አዘጋጅተው ሰጡ። ከዚያ ብዛታቸው የማይቆጠሩትንና የማይመጥኑትን በጎችንና በሬዎችን አሳርደው ድኾችንም ሰብስበው ስምንት ቀን ሙሉ ሲያበሉ ሲያጠጡ ሰንብተው እንጀራው እንደ ቅጠል ፣ወይኑና ጠጁ እንደ ፈፋቱ ውኃ፣ ስጋው እንደ ጎመን በዝቶ ተርፎ አሳልቅም ስለ ቅዱስ ሚካኤል ባርኮ ያበረከተው ነው ብለው ስለ አመሠገኑ ቀኑን **ሚካኤል በረከቶ** አሉት። ከዚህ ሁሉ በኋላ እንደገና ሃይማኖት እየሰበኩ ጥምቀት በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን እያጠመቁ ቆይተዋል። ይህ የ፲፫ መቅደስ ሕንጻ ቤተክርስቲያን ፳፻፴፫ ዘመን



ቆይቶ በዮዲት « ጉዲት » ተብላ በምትጠራው የተቃጠለ መሆኑ ይታወሳል።

ከጉዲት በኋላ የነገሠው አንበሳ ውድም በ፲፪ ዓመት ዕድሜው እንደ ነገሠ ወዲያው ዮዲት ስለ አስለቀቀችው በስደት ፵ ዘመን ከተቀመጠ በኋላ በ፺፪ ዕድሜው በ፲፻፳፯ ዓመተ ምሕረት ሀገሩ አክሱም ተመልሶ በአባቱ ዙፋን ተቀምጦ ኢትዮጵያን በጸጥታ ማስተዳደር በጀመረ ጊዜ አስቀድሞ የክርስቲያን ሃይማኖት እንዲስፋፋና እንደ ጥንቱ ያሬዳዊ ዜማ ፣ ብሉይና ሐዲስ በትምህርት ቤቱ ተዘርግተው እንዲነገሩ አወጀ። ቀጥሎ ሕዝቡን እየሰበሰበ የተቃጠለውን የአክሱም ቤተ ክርስቲያንን አስጠረገ። ከአበው ካህናት ጋርም ሱባኤ ገባ። ሱባኤውን እንደፈጸመ የሰሙኑትን የማይነሳ የነገሩትን የማይረሳ እግዚአብሔር በቸርነቱ ስአባቶቹ አብርሀ ወአጽብሐ እንዳዘነመላቸው ፫ ቀን ፫ ሌሊት ወርቅና እንቁ አዘነመለት። በዚህ እግዚአብሔርን እያመሰገነ የሕንጻ ባለሙያችን ሰበሰበ። ቀለብና ልብስ ደመወዝ አቀረበላቸው።

በዚህ ጊዜ የተቃጠለውን ቤተክርስቲያን መሠረት አስቆፍሮ ከዓስራ ሁለቱ ቤተመቅደስ አምስቱን ቀንሶ አቅሙ በሚፈቅድለት ፯ ቤተ መቅደስ አድርጐ በከበረ እብነ በረድ አሠርቶ በወርቅና በእንቁ ለበጠው እንደ ፀሐይም አንጸባረቀው።

እንደዚሁም ለጽላተ ሙሴም በወርቅ ያጌጠ ቤተ መቅደስ አሠራላት። በዚህ ጊዜ ሰጊዜው ጳጳስ ለለአልነበረ

በአክሱም ሲቀ ካህናት አሰባርኮ ቅዳሴ ቤቱን አከበረ። ንዋየ ቅድሳቱን በሙሉ ለቤተክርስቲያኑ ሰጠ። የጥንት ጉልት ጽዮንን እየመለሰና እያሳደሰ እንደገና ሐዲስ ጉልት ጕሰተሳት መዘምራንና መምህራን ካህናት እና ዲያቆናትን ሁሉ ለአገልግሎት መደበላት። ብዙ ቅርሶችንም አቆመላት።

ይህንንም ድንቅ የሆነ መቅደስ በቤተክርስቲያን ፣ በክርስትና እምነት አና በ፲፭፻፳፯ ዓ.ም በነገሡት በአፄ ልብነ ድንግል ሳይ ተነስቶ የነበረው በግራኝ መሐመድ ምክንያት በ፲፭፻፳፱ ዓ.ም መካከል ፻፲፯ ዓመታት ያህል በአገልግሎት ከቆየ በኋላ ተቃጠለ። ከዮዲት ተሰውረው የቀሩት ቅርሶችም ጠፉ።

ከዚህ በኋላ በ፲፮፻፵፬ ዓ.ም ነግሠው በነበሩት በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ለ፹ ዘመን ያህል ፈርሶ ከቆየ በኋላ አሁን የሚታየውን ቤተ ክርስቲያን በ፫ መቅደስ መሠረቱ። አፄ ፋሲል በ፲፮፻፶፱ ዓ.ም ማረፋቸው ስለሚታወቅ የቤተክርስቲያኑ ዕድሜ አሁን ፫፻፴፫ ዘመን ይሆነዋል።እስካሁን ድረስም በማንም ሳይፈርስና ሳይጠፋ አገልግሎት በመስጠት ሳይ ይገኛል።

በመጨረሻም ታቦተ ጽዮን ወደ አስችበት ቤተ መቅደስ ሴቶች ስለማይገቡ ለሴቶች ብለው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፶፭ ዓ.ም መሠረቱን ጣሉና በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም ሥራው ሙሉ በሙሉ በመጠናቀቁ በዚሁ ዘመን የታላቋ እንግሊዝ ንግሥት ኤልሣቤጥ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት መጥተው በነበረ ጊዜ ተመርቆ ይኸው እስከ ዛሬ ድረስ አገልግሎት ሳይ ይገኛል።



የአክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን አመሠራረት ይህን ይመስላል። ነገር ግን አቦታው ሲኬድ ደግሞ በዘመናዊ መልክ በተሠራው ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ እና ከሙዚየሙ ውጭ የሚገኙ ቋሚ ሐውልቶች የነገሥታቱ መቃብሮች እና ሌሎችም ድንቅ ድንቅ ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙበት ቅድስት ሥፍራ በመሆኗ ለጊዜው ከመጻሕፍትና ከቤተ ክርስቲያን አበቶች ያገኘሁትን የአክሱምን ታሪክ እዚህ ላይ አበቃለሁ።

**ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ።**

## ዙር አምባ

ዙር አምባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም ከአዲስ አበ
ተነስተው ፮፻፺ ኪሎ ሜትር ከተጓዙ በኋላ በደቡብ ጐንደር ጋይን
ወረዳ በሳይ ጋይንት አውራጃ የምትገኝ ገዳም ናት። ቤ
ክርስቲያኗ ያለችበት ተራራ ሰማይ ጠቀስ ሁና በደመና ተሸፍ
ክርቀት ትታያለች። ይህን ተራራ ለመውጣት አሁን ዘመናዊ ደረ
ከመሠራቱ በፊት የበረታ ተንጠልጥሎ የደከመ በመጫኛ ተጐት
ወንዶችም ሴቶችም የሚወጡበት ዘመናትን ያስቆጠረች ጥንታ
ገዳም ናት።

ገዳሟ የተመሠረተችው በአምስኛው መቶ ክፍለ ዘመ
ሲሆን ገዳሟን የመሠረቷት አባ ገ/መስቀል ናቸው። ከእርሳቸውም
ጋር በመንግሥተ አልአሜዳ ዘመን በ፬፻፸ ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ
ከመጡት ዘጠኙ መነኮሳት አንዱ የሆኑት አባ አረጋዊና የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የዜማ ደራሲ የሆነው ቅዱስ
ያሬድ ነበሩ። እነዚህ ቅዱሳን በጣና ደሴት በሚገኘው ጣና
ቂርቆስ ገዳም ሲጸልዩ ቅዱስ ዑራኤል ተገልጦ « <u>ሑሩ ኀበ ሀገረ</u>
<u>በጌምድር ወበህየ አእየከሙ ደብረ ንፅለተ</u> » ትርጉም ወደ
በጌምድር ሂዱ ከዚያ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም
የባረከኋት የማሳያችሁ አነስተኛ ተራራ አለችና በርስዋ ላይ
አምላክን በወለደች በድንግል ማርያም ስም ቤተክርስቲያን ሥሩ
አላቸው። እነርሱም ወዲያው ተነስተው ከባሕረ ጣና ወደ
በጌምድር ሄደው በተራራው ምዕራብ በሚሆን በደቡብ በኩል



ተቀምጠው ላስ ገደሏ ተረተሯ ከምድር ፫፻ ሜትር ከፍታ በላይ
የሆነች ተራራ ሽቅብ ያያሉ። ወዲያው ያቺ ተራራ ጉና ታየችን
በማለት ተናገሩ። ዛሬም ድረስ የዚያ ሥፍራ ስም <u>ጉና ተራራ</u>
በመባል ይወታወቃል።

ከተራራው ጥግ በስተምዕራብ ሲደርሱ ተራራው
ተሰወረባቸው፤ በሁኔታውም ግራ ተጋቡ። ጊዜውም መሸቶ ነበርና
በዚያም ባሉበት ቦታ ላይ በጽኑዕ ሐሳብ አደሩ። አባ አረጋዊም
እንዲህ ብለው ጸለዩ « ቀድሞ ወደ ደብረ ደሞ ያወጣኝ ዘንዶ
ዛሬም በዚህ ቦታ ተገኝቶ ወደዚች ተራራ ላይ ባወጣኝ እንዴት
መልካም ነበር እያሉ ጸለዩ። » ምክንያቱም ወደ ተራራው
መውጫ ስላልነበረ ነው። በዚህን ጊዜ ዑራኤል መልአክ ተገልጾ
«<u>ዑድ አባ መንገለ ምሥራቅ ውዑድ ለዛቲ ደብር</u>» ዙር አባ
በእርሱዋም ትወጣ ዘንድ በምሥራቅ በኩል ዙር አላቸውና ወደ
ምሥራቅ ሲዞሩ ወደ ተራራው መውጫ የሌለው በመሆኑ መልአኩ
ቅዱስ ዑራኤል ዕፀ ሳቤቅ ( ነጭ ሀረግ ) ዘረጋላቸውና እሱን
ይዘው ወደ ተራራው ጫፍ ወጡ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ቦታ
እስከ ዛሬ ድረስ <u>ዙር አምባ</u> በመባል ይታወቃል።

አባ አረጋዊና ካህኑ ያሬድም ከተራራው አናት እንደደረሱ
ከሰሜን ወደ ደቡብ ስፋቱ ፫፻ ሜትር የሆነ ሰፊ መሬት አገኙና
አረፍ አሉ። በቦታው ላይ ምንም የሚመገቡት ስላልነበረ ዑራኤል
መልአክ ኅብስት ሰማያዊ እያወረደ ይመግባቸው ነበር። ሁለቱም
ቅዱሳን ምስጢሩ እንዲገለጽላቸው ሱባኤ ገቡ በሦስተኛው ሱባኤ

በ፳፩ኛው ቀን አባ ገ/መስቀል ከአክሱም ተነስተው በዚሁ ዕለ
ተራራው ሥር ሰፈሩ። አባ ገ/መስቀል ወደ ተራራው መውጫ
አጥተው ሲጨነቁ ቅዱስ አረጋዊ ከተራራው ጫፍ ላይ ሆነ
ገደሉን በትምዕርተ መስቀል ቢባርኩት ከሁለት ተከፈለላቸው
ስፋቱ ፱ ሴንቲ ሜትር በሚሆን ቀጭን መንገድ ወጥተው ከአበ
አረጋዊ ጋር ሲገናኙ መስሕኩ የሐር ድንኳን ዘረጋላቸው፣ በዚ
ድንኳን **አቡነ አረጋዊ ካህን**፣ **ቅዱስ ያሬድ ዲያቆን** ሆነ
ሥጋወ ደሙን አቀበሏቸው።

ከዚህ በኋላ አቡነ አረጋዊ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን
ሥርዓተ ምንኩስናን ሲያስተምሩ ቅዱስ ያሬድ ደግሞ **ከር**
**አይደርቅ** በምትባል ዛፍ ሥር ተቀምጦ ዝማሬ መዋስዕትን
ፀዋትወ ዜማ በሙሉ በመንፈሰ ቅዱስ እየተቃኘ አደረሰ። ያ
ዛፍ ቅጠሉ ሳይደርቅ ለብዙ ዘመን ቆይቶ አሁን በቅርብ እንጨ
ከታች እስከ ላይ በሰው እጅ የተፈለፈለ መስሉ እንደ ዋሻ ሆ
ይገኛል። አባ ገ/መስቀል ከጨጨሆ እስከ ጉለዩ ፣ ከአሽደብ እስ
ጉና ጋይንት በሙሉ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል። የዙ
አምባን ቤተክርስቲያን ለመሥራትም ሦስት ዓመት ተቀመጡ
የሚገርመው የቤተክርስቲያኑ ቆመ ብዕሲ በመቅደሱና በቅድስ
መካከል ጣራውን የሚሸከሙ ቋሚ ምሰሶዎች አሉ። ርዝመታቸ
፳ ሜትር ነው። ብዛታቸውም ከትንንሾቹ ሌላ ፳፩ ነው
የእንጨቶቹ ስም ግን እስካሁን አይታወቅም። የቋሚዎ
ምሰሶዎችም ስም **አርድዕት** ይባላል። የመቅደሱ ውስጥ አስደናቂ



በሆኑ ጥንታዊያን ሥዕሎች የተዋበ ነው። ከእነዚህም መካከልአብዛኛቹ በአርጅና ምክንያት ደብዛዛ ሆነዋል። ክእነዚህ ሥዕሎች መካከል አንዲት አስደናቂ የሆነች የእመቤታችን ሥዕልም ትገኛለች።

ይህችም ሥዕል ማንኛውም ሰው በየትኛውም አቅጣጫ ሆኖ ሲመለከታት ፊት ለፊት አተኩራ የምትመለከትና ዓይን ወዳለበት የምትንከባለል ናት። ሥዕሏም በሐር መጋረጃ ተጋርዳ ለመግለጥ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ ሦስት መነኮሳት ጸሎት አደርሰው ማዕጠንት አያጠኑ በዝማሬ ይገልጧታል። በሥዕሏም የተማፀነ የጠየቀው ሁሉ ይፈጸምለታል።

አባ ገብረ መስቀል ከተራራው ስሥር ከተማ መስርተው ህንፃ ቤተ ክርስቲያን አያሠሩ ፫ ዓመት ቆይተዋል ያም ቦታ እስካሁን ድረስ **አባ ከተማ** እየተባለ ይጠራል። ንጉሥቲቱ ባለቤታቸውም ተቀምጠውበት ከነበረው ከጥንጫው መሬት ውኃ ስለፈለቀላቸው **እቴጌ ውኃ** እየተባለ ይጠራል። እስከ አሁን ድረስም በመፍሰስ ላይ ይገኛል። በዚህ ገዳም ውስጥ ከሠላሳ የማያንሱ የመሳእክት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት ጽላቶች ይገኛሉ። የታቦተ ማርያም ጽላት ግን በልዩ ከርሰ ሐመር ውስጥ ሆና አቡነ አረጋዊ ባዘጋጁት የዝሆን ጥርስ መንበር ላይ ተቀብሩ ትኖራለች። ይህችም ጽላት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በተፈቀደላቸው በአራት መነኮሳት ከአራት ወገን ተሸክመዋት ትወጣና ከክብረ በዓሉ በኋላ ተመልሳ ትገባለች። ጽላቷን ባርከው ያስገቧት አቡነ አረጋዊ

ናቸው፡፡ ቅዳሴውም ስብሐተ ነግሁም ዓመት እስከ ዓ
በድንግሳዊያን መነኮሳት ይቀደሳል ፤ ይወደሳል፡፡

በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በዘመኑ የነበሩት ዕ
ቴዎፍሎስ በድፍረት ቀልፏን ከፍቼ ጽሳቷን አያለሁ ብ
መንበሩን ሲዳስሱ እጃቸው ተኮማትሮ አፅምሮአቸውን ስ
ከመሬት ይወድቃሉ ፡፡ በዚህን ጊዜ መነኮሳቱ ጸሎተ ም
አድርሰው አፅምሮአቸው ተመለሰ፡፡ በሁኔታው የተደናገጡት ዕ
ቴዎፍሎስ ልብሰ ተክህናአቸውንና ያላቸውንም ገንዘብ በመ
አውጥተው ሰጥተዋል፡፡ ይህችን ቦታ የሚያስተዳድሩት ድንግ
መነኩሴ ሲሆኑ በውስጡ ፻፪ ያህል አገልጋዮች ይገኛሉ፡፡ ይህ
ሥፍራ ከቤሉቹ ገዳማት ልዩ የሚያደርጋት እንደ ታሳ
ዩንቨርስቲዎች የዝማሬ መዋሲዕት ማስመስከሪያ ቦታ መ
ነው፡፡ ለዚህም ትምህርት በቋሚነት ወንበር ዘርግ
የሚያስተምሩ በቂ ሊቃውንት አሏት፡፡ ሦስት የዝማሬ መዋሲ
መምህራን ፤ ሁለት የድጓ ፤ አንድ የቅኔ፣ አንድ የታሪክ
ሁለት የአቋቋም ፤ ሁለት የመጽሐፍ ፤ ሁለት የንባብ መምህ
ይገኙባታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ መምህራንና ተማሪዎች በአ
ወቅት ከችግር ፅናት የተነሳ በሐገራችን ወዳሉ ትላልቅ ከተ
እየተሰደዱ ነው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሊቃው
ከቦታው ድረስ በመሄድ ተምረዋል እስከዚያም ከቦታው በተ
ሰዎች ተምረዋል፡፡ ስለዚህ በየትኛውም ክፍለ ዓለም የምን



ክርስቲያኖች ይህችን ታላቅ ገዳም እስከ አሁን ድረስ የብዙ ሊቃውንት መፍለቂያ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ፈሳሽ ውኃ የማይደርቅ ንጹሕ ምንጭ በመሆኗ ለኢትዮጵያ ሊቃውንት የመጨረሻውን የእውቀት ማረጋገጫ ዲግሪ በመስጠት ላይ የምትገኘውን ገዳም በአፋጣኝ ልንደርስላት ይገባናል፡፡

በመጨረሻም በዚህች ታላቅ ገዳም ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ቦታዎችን አስታዋውቃችሁና ጽሑፌን እቋጫለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አቡነ ተክለሃይማኖት የጸለዩበት፣ የተክለ ሃይማኖት ዋሻ፣ የበቁ ቅዱሳን የልደታን ታቦተ ህግ ይዘው የተሰወሩበት ልደታ ዋሻ፣ ዓባይ ንቃት ሠንቃጣጤ በጠሳት ጊዜ ብዙ ንዋየ ቅድሳት የተደበቁበት የምስጢር ቦታ ከተራራው ራስ ላይ የሚገኝ ገሲሳ ( ገለሳይት ) የሚባል በስደት ጊዜ እመቤታችን ከልጇ ጋር ያረፈችበት ቅዱስ ሥፍራ ይገኝበታል፡፡

ቅዱስ ያሬድ ከዚህች ገዳም ተነስቶ ወደ ትግራይ ማለት ወደ አክሱም ሲሄድ በሰሜን በኩል በምትገኝ ደብረ ሐዊ ከምትባል አገር ደረሰ፡፡ በዚህች <u>በደብረ ሐዊም ቅዱስ ያሬድ ከሰው ዓይን ተሰወረና</u> አኗኗሩ ከሰማይ መላእክት ጋር ሆነ፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡**

## ዋሻ እንድርያስ

ከአዲስ ዘመን ተነስተው ወደ ጎንደር የሚወስደው
መንገድ በመከተል ጥቂት ደቂቃዎች እንደተጓዙ ጣራ ገዳ
ተብሎ በሚታወቀው ቦታ እንደደረሱ ወደ ቀኝ በመታጠፍ ከ፪
ኪሎ ሜትር ርቀት ያህል ከተጓዙ በኋላ የሚያገኙት ጥንታ
ገዳም ነው። ይህ ዋሻ በገዳምነት መታወቅ ከጀመረ የ፺፻ ዓመ
ዕድሜ ያህል አስቆጥሯል።

ገዳሙ የተገደመው በዓስራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመ
በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ነው። ይህ ዋሻ በገዳምነ
ከመታወቁ በፊት በዘመነ ኦሪት የጣዖት አምልኮ ይከናወንበ
እንደነበር እና በወቅቱም የአካባቢው ነዋሪዎች በዘንዶ አያመለ
ለእርሱም እየሰገዱ ከእንጨት በተፈለፈለ ገንዳ ወተት ያቀርቡለ
እንደነበር አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህንን ሥርዓ
አምልኮ በመሻር ነበር ከላይ በተጠቀሰው ዘመን አቡነ እንድርያ
የክርስትናን ሃይማኖት በማስተማር በዋሻው ውስጥ ይገበርለ
የነበረውን ዘንዶ በማጥፋት በዋሻው የኢየሱስን ታቦት በማስገባ
ቅዳሴ ቤቱን በማክበር ገዳሙን የመሠረቱት። ከዚያን ጊ
ጀምሮ ዋሻው በስማቸው <u>ዋሻ እንድርያስ</u> ተባለ።

በዓይን ከሚታዩትና ሊጎበኙ ከሚችሉት ቅርሶች መካከል፣

* ለዘንዶው ወተት ይቀርብበት የነበረው ከእንጨት የተፈለፈለ ገንዳ፣
* የሰው ቅርጽ ያለው የእንጨት ጣዖት



* ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት
* የብር መስቀሎችና አልባሳት
* ሳይበሰብስ ለረጅም ዘመን የኖሩ የሰው አስከሬኖች

በእነዚሁ የተለያዩ አስከሬኖች ላይ የተለያዩ የአገናነዝ ሥርዓቶች በጉልህ የሚታዩበት ነው። በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ይህ ሥፍራ በምዕመናንም ሆነ በውጭ ሀገር እንግዶች ቢጎበኝ ልዩ መስህብነት ያለው ሥፍራ ነው ።

## ወይን ዋሻ ተክለሃይማኖት

ይህ ቤተክርስቲያን ከአዲስ ዘመን ወደ ጉንደር በሚወስደው መንገድ አቅራቢያ የሚገኝ ታሪካዊ ቤተክርስቲያን ነው፡ የአካባቢው መጠሪያ ስምም ጣራ ገዳም እየተባለ የሚጠራው ነው። ይህንን ገዳም የአካባቢው ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ልዩ ውበት ሰጥቶታል። በተሰደ ገዳሟ ያለችው ዙሪያው ገደላማ ሆኖ ጥቅጥቅ ባለ ደን በተሸፈነ ቋጥኝ ስር ነው። ገና ወደ ዋሻው ውስጥ ሳይገባ በጥቃና በድንጋይ ውብ ሆኖ የተሠራውን የተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያንን ያገኙታል። የዚህን ቤተክርስቲያን አመሠራረት እንደ ተረዳነው ከሆነ የገዳሙ ሥራ በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ በአፄ ሰይፈ አርዕድ ነው የተጠናቀቀው። ዋሻው የውስጥ ለውስጥ መንገድ አለው። በዚህ የውስጥ ለውስጥ መንገድ አቡነ እንድረያስ እና አቡነ ተክለሃይማኖት ከየበዓታቸው ተነስተው ዛና ማርያም ድረስ በመሄድ ጸሎት ያደርጉ እንደነበር የቤተክርስቲያኗ አበው ይናገራሉ። በዋሻው ውስጥ ከመንገዱ ሌላ ባህርም እንዳለ ነው የሚነገረው። ከባህሩም በኋላም ጥንታዊ የሆኑ ከወርቅና ከብር የተሠሩ ቅርሶችና መጽሐፎች እንደሚገኙም ነው የተነገረን። ወራሪው የኢጣሊያ መንግሥት የዚህን ቤተክርስቲያን ቅርስ ያስምንም ከልካይ ግፍ በተሞላበት ጭካኔ ያለ ርህራሔ ብዙ ቅርሶችን እንደ ዘረፉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አበው እስከ ዛሬ **በቁጭት የሚናገሩት** ነው።



## የጣና ሐይቅ

ጣና በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ሐይቆች ሁሉ በትልቅነቱ ቀዳሚውን ሥፍራ የያዘ ሐይቅ ነው። ጣና ሐይቅ ፫፻፷፯፫ ስኩር ኪሎ ሜትር አጠቃላይ ስፋት ሲኖረው አቀማመጡም ከሰሜን ወደ ደቡብ ፹፬ ኪሎ ሜትር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ደግሞ ፷ ኪ.ሜ ርዝመት ያለው ነው። የጣና ሐይቅ ከባሕር ወለል በላይ በ፩ሺ፯፻፹፰ ሜትር ( ፮ሺ ጫማ) ከፍታ ላይ ይገኛል። የሐየቁ የውኃ ይዘት በዚህ ክልል ብቻ አራት ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ነው። ከ፮ሺ ጫማ ከፍታ በታች ያለውን መሬት በሐይቁ ውኃ በቀላሉ ለመስኖ ማዋል ይቻላል።

ከሐየቁ ይዘት አራት ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውኃ በአባይ ወንዝ ፈሰስ ላይ ለመስኖ ፍጆታ ለማዋል ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፺፭ በተደረገው ተደጋጋሚ ጥናት መሠረት ከ፲-፲፭ ሚሊዮን ዶላር እንደሚፈጅ ተገምቷል።

ጣና በክረምት ወቅት ማብቂያ መስከረም ሲጠባ ከሐይቁ የሚወጣው ውኃ ከፍተኛ መጠን በሰከንድ አራት መቶ ሜትር ኪዩብ ያህል የሚከላል። በታህሣሥ በሰከንድ ወደ መቶ ሜትር ኪዩብ ያህል ያማክልና ወዲያው በሚቀጥሉት ወራት እየቀነሰ ይሄድና ክረምት ከመግባቱ አስቀድሞ በግንቦት ወር በሰከንድ ፲ ሜትር ኪዩብ እስኪደርስ ድረስ እያነሰ ይሄዳል።

ጣና በኢትዮጵያ ሰሜን ምዕራብ ታላቅ የተራራ ሰንሰለት በጣም ቅርብ ስለሆነ ከበስተ ሱዳን በኩል ወደ <u>በለሳ</u> ወይም ወደ

**ዲንደርባር** ወንዞች የውኃ መሿለኪያ ቢቀደድ በአካባቢው የሚኖሩ ሕዝቦች ሸለቆዎቻቸውን በመስኖ ለማልማት ይችላሉ። አባይ ከጣና የሚወስደው ከወንዙ ጠቅላላ ወራጅ ፯.፭ መቶኛውን ብቻ ሲሆን ቀሪውን ውኃ የሚመግቡት ወደ ወንዙ የሚገቡ ከ፴ የማያንሱ ገባር ወንዞች ናቸው።

በዚህ በጣና ሐይቅ ላይ በመሀሉ እና በሐይቁ ዳርቻ በአጠቃላይ ከ፴ በላይ የሚሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብት የሆኑ በብዙ ቢሊዮን ከሚገመቱ ውድና ክቡር ቅርሶቻቸው ጋር ይገኛሉ። ስለ ጣና ማለት የፈለኩትን እዚህ ላይ አቆምና ገዳማቱን ለሚጐበኝ ሰው ይረዳው ዘንድ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በጣና ሐይቅ ላይ ሰውና ዕቃ ስለሚያመላልሱ ጀልባዎች ጥቂት ልበላችሁ።

**ጣና ነሽ** ይህች ጀልባ በአሁኑ ጊዜ በጣና ሐይቅ ላይ ከሚንሳፈፉት ጀልባዎች ሁሉ በመጠኗ ሰፊና ትልቅ የሆነች ጀልባ ነች። ጣናነሽ ሁለት ትላልቅ ሞተሮች ያሏት ስትሆን አንደኛው በስተ ቀኝ በኩል ያለው ሞተር በአሁኑ ሰዓት ከመለዋወጫ እጦት የተነሳ ባይሠራም በስተ ግራ በኩል ያለው ሞተር ግን በአስተማማኝ ሁኔታ በመሥራት ላይ ይገኛል። ይህች ጀልባ በ፲፻ ሊትር ነዳጅ ዘይት አንድ ሺህ ኩንታል ጭነትና ፪፻ ያህል ሰው በአንድ ጊዜ ጭና መጓዝ ትችላለች።

ጣና ነሽ ከባሕርዳር ተነስታ ጐርጐራ ለመድረስ ሁለት ቀን ያህል ይፈጅባታል። ይኸውም ቀጥታ ጉዞ ስለማታደርግ ነው።



ከባሕርዳር ስትነሳ ዘጌ ፣ ጉረር፣ ቁንዝል ፣ እሰፋደብር ፣ ደልጊ ደርሳ ነው ጐርጐራ የምትገባው። ጀልባዋ በማኅበር ተሰብስበው ለሚመጡ እና በሰዓት አየከፈሉ በጣና ላይ የሚገኙ ገዳማትን ለሚጐበኙ ብዙ ሰው ሳይጨናነቅ ስለምትይዝ አመቺ ናት። በአጠቃላይ በጣና ሐይቅ ላይ የሚመላለሱ ጀልባዎች ፲ ያህል ሲሆኑ የሚይዙት የሰው ብዛት ፍጥነታቸው የፈረስ ጉልበታቸው እና አገልግሎታቸው በሙሉ አንዱ ከአንዱ ይለያል።

**አይሻ** እና **ድል ብትግል** ፣ ከ፲-፲፭ ሰው በአንዴ ሲያመላልሱ ከእሁድና ከሰኞ በስተቀር ከባሕር ዳር ሕዝብና ዕቃ እንዲያመላልሱ እንዲሁም ልዩ ልዩ ጐብኚዎችን ከባሕር ዳር ዑራ ኪዳነ ምሕረት ፣ ክብራን ገብርኤል ያመላልሳሉ።

**የካቲት** እና **ዳህላክ** ባለ ሁለት ሞተር ፈጣን ጀልባዎች ናቸው። የካቲት ከሆላንድ ተገዝታ ስትመጣ ባለሁለት ሞተር ነበረች። አሁን ግን አንዱ ሞተር በመለዋወጫ እጥረት ምክንያት በመበላሸቱ በአንዱ ሞተር ብቻ አያገለገለች ትገኛለች። እንዲያውም ከ፴ - ፺፭ ሰው ይዛ ጣናን መሀል ለመሀል ሰንጥቃ በሰዓት ፴ ኪሎ ሜትር ትጓዛለች። ዳህላክ የመጣችው ከሀንጋሪ ሲሆን በአንድ ጊዜ ጉዞ ፲፭ ሰው ብቻ ነው የምትይዘው። ያላት የፈረስ ጉልበት ፴፭ ሲሆን በግማሽ ፍጥነት ወደ ፳፫ ኪሎ ሜትር ወይም ፲፪.፯ የባሕር ማይል ትጓዛለች። በዚህ የፍጥነት ጉዞ ውስጥ ፲፪.፭ የፈረስ ጉልበትንም ትጠቀማለች።

**አንድነት፣ታጠቅ፣ህብረት፣ሲማሊሞ** እነዚህ ጀልባዎች

ከህብረት በስተቀር ሦስቱ ጀልባዎች ፋሽስት ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ሲባረር በእንጋራ ደሴት አስጥሟቸው በጥቀማ ተፈልገው የወጡ ጀልባዎች ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውም በአሁኑ ወቅት ለባሕርዳርና ለጉጃም ነዋሪዎች ከደልጊ ግራና ቀኝ በመጓዝ ከጨንቂና መስቀለ ክርስቶስ አሸዋ የሚያመላልሱ ናቸው፡፡

<u>ደቅ</u> እና <u>ጣና ቂርቆስ</u> ደቅ በጣና ላይ ከሚገኙ ጀልባዎች በሙሉ በጣም ፈጣን ናት፡፡ ለምሳሌ ከጉርጉራ ተነስታ ባሕርዳር ለመድረስ አንድ ሰዓት ተኩል ብቻ ነው የሚፈጅባት፡፡ ብዙውን ጊዜ አገልግሎት የምትሰጠው ባሕር ዳርን ወይም ጉርጉራን ለቀው ባሕር ላይ ወይም አንዱ ወደብ ላይ ተበላሽተው ለሚቆሙ ጀልባዎች ቴክንሽያናችን በመያዝ በፍጥነት ደርሳ እርዳታ የምትሰጥ እና በተገልጋዮቿ ዘንድ « <u>ፈጥኖ ደራሽ</u> » ተብላ የምትታወቅ ጀልባ ናት፡፡ <u>ጣና ቂርቆስ</u> በመባል የምትጠራው ጀልባ ደግሞ ለአሁኑ ብዙም ሳትርቅ በባሕር ዳር አካባቢ ወደሚገኙ ገዳማት በመጓዝ አገልግሎት እየሰጠች ትገኛለች፡፡ አገልግሎት አልጀመረችም እንጂ ወደ ፊት ይህች ጀልባ ጣና ቂርቆስን ሱለንዮስ ግንብንና ምፅሌ ፋሲል ደሴን በመሳሰሉት የጣና ዳርቻዎች ለመጓጓዝ በባሕር ትራንስፖርት ድርጅት ዕቅድ ውስጥ ትገኛለች፡፡ቢሆንም ግን ጣናን እና የጣናን መርከቦች ምን እንደሚመስሉ ካየን ዘንድ አሁን ደግሞ ከዚህ በመቀጠል ከብዙ በጥቂቱ በጣና ሐይቅ ላይ ያሉትን ቅዱሳን ገዳማት ተራ በተራ ለማየት እንሞክራለን፡፡ በመጀመሪያም ከደብረ ማርያም እንነሳ፡፡




## <u>ደብረ ማርያም</u>

በሀገራችን በትልቅነቱ እና በስፋቱ በሚታወቀው የጣና ሐይቅ ላይ በደቡብ ምሥራቃዊ ጫፍ በኩል የምትገኝ ውብና የረጅም ግዜ ዕድሜ ያላት ድንቅ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ ደብረ ማርያምን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙዋት አባት አቡነ ታዲዎስ ናቸው፡፡ በጊዜው አቡነ ታዲዎስ ወደ ደሴቷ በቀረቡ ጊዜ የጣና ሐይቅን ውኃ ለሁለት ከፍለው ያለምንም ችግር ልክ እስራኤላውያን ባሕረ ኤርትራን እንደተሻገሩት በየብስ ላይ ተራምደው ነው የደረሱት፡፡ ቤተክርስቲያኗ የተሠራችው በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ ከዚያም በኋላ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ከነገሡ በኋላ እንደገና ተሠርታለች፡፡ የዚህች ቤተ ክርስቲያን አሠራር በዚያው በጣና ሀይቅ ላይ የሚገኘውን የክብራን ገብርኤልን ይመስላል፡፡ ደብረ ማርያም በጊዜዋ ሥፌ ዕውቅና የነበራት እና ወደ ፱ የሚደርሱ አድባራት በዙሪያዋ የሚገኙባት ነበረች፡፡

ደብረ ማርያምን በትላልቅ ጀልባ ላይ ሆኖ ለመጐብኘት ውኃው ዝቅተኛ ይዘት ስላለውና ለስማይመች በትናንሽ ጀልባዎች ከባሕር ትራንስፖርት ድርጅት በደንከል ወይም ከላር በተሠሩ ጀልባዎች ወደ ጉንደር በሚወስደው የአባይ ድልድይ በኩል በእግር ተጉዘው፣ በላር ጀልባዎች ወደ ቤተክርስቲያኗ መግባት ይቻላል፡፡ የዚህች ቤተክርስቲያን ዙሪያ ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ሲሆን በአጠቃላይ የአካባቢው ተፈጥሮአዊ ውበት ልዩ ግምት

የሚሰጠው ነው፡፡ <u>**አባይ በጣና ሳይ ዋኝቶ በገዛ አካሉ መፍሰስ የሚጀምረው**</u> ከዚሁ ታሪካዊ ቦታ መግቢያ ሳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ቤተክርስቲያኗ በተጐሳቀለ ሁኔታ ሳይ ብትገኝም ባሳት ታሪካዊነትና ጥንታዊያን የግድግዳ ሳይ ሥዕሉች፣ ረጅም ዕድሜ ያሳቸው የብራና መጻሕፍት ታሳሳቅ ጥበባዊ ሥራዎችና ንዋየ ቅድሳት የሚገኙባት ማራኪ በመሆኗ የቱሪስት መስህብ ናት፡፡



*ደብረ ማርያም* (ፎቶ ወንደሰን)



## <u>ክብራን ገብርኤል</u>

በጣና ሐይቅ ደቡባዊ ዳርቻ ሳይ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ታሳቅ ገዳም ነው፡፡ ይህ ገዳም ከባሕር ዳር ተነስተው የሚመጡ ጀልባዎች በአጭር ግዜ የሚደርሱበት ነው፡፡ ስዣን የሚበለው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን የፈረንሳይ ቆንስል የነበረው ስለ ክብራን በመጽሐፉ ሲጽፍ እንዲህ ነበር ያለው፡፡

> « እነ ክብራን እነ ምፅራሐ ያሉበት ደሴቶች በሩቅ መሬት ሳይ ሆነው ሲታዩ ለም ሆነው ልምላሜ የለበሉና የሚዋኙ ሕይወት ያሳቸው ቅርጫቶች ይመስሳሉ፣ ቀረብ ብለው ሲመለከቱዋቸው ልምሳሜያቸው የበዛ ዕቅፍ አበባ ሆነው በውስጣቸው በሚገኘው ቋጥኝ ሳይ የተከበሩትን ገዳማት እንዳቀፉ ሆነው ይገኛሉ....» ብሏል፡፡

ጸሐፊው እውነቱን ነው፡፡ ክብራን ገና ከሩቅ ሲታይ ህሊናን የሚማርክ እና ልቦናን የሚመስጥ ውበት ያለው ጥንታዊ ገዳም ነው፡፡

ገና ከጀልባ ወርደው ይህንን የመጀመሪያ የባሕር ሳይ የጉብኝት ምዕራፍ የሆነውን እና በሊቀ መሳእክት ቅዱስ ገብርኤል ስም የታነጸውን የክብራን ገብርኤልን ደሴት እንደረገጡ ዓይን ማረፊያ ያጣል፡፡ የደኑን ጥቅጥቅ ብሉ ማደግ እያዩ የአእዋፋቱን ዝማሬ እያደመጡ ያን በዝምታ የተዋጠ ቅዱስ ሥፍራ ለመጐብኘት ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ገና ጥቂት እንደተራመዱ የዳገትነት ስም ያሳት ነገር ግን እንደሌሎቹ ጉልበትን የማታደክም ስውነትን

የማታዝል ስቀበት ከወጡ በኋላ ሰማየት ወደ ተናፈቀው የክብራን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ይደርሳሉ።

ክብራን ገብርኤል በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የተተከለና በአጨጌ ፊሊጶስ አመንኳሽነት አባ ዘዮሐንስ የገደሙት ገዳም ነው ። አባ ዘዮሐንስ የመጡት ከሸዋ ክፍለ ሀገር ከደብረ ሊባኖስ ሲሆን ወደዚህ ሥፍራ ያደረሱዋቸው ተክለገብርኤልና አና መስቀል ክብራ የተባሉ ባልና ሚስት ናቸው። በጊዜው እርኩስ መንፈስ ያደረበትን ዘንዶ አማትበው ይገድሉትና የአካባቢውን ሕዝብ አጥምቀው ክርስትናን ስብከው አሻግረው ያመጧቸውን ሰዎች ስም ለማዘከር ሲሉ ገዳሙን በባልና ሚስት ጥምር ስም ክብራን ገብርኤል በማለት ( ዓ.ም.ም.፲፫፻፲፬ - ፲፫፻፵፬ ) ቤተክርስቲያን ሠርተዋል።

ይህ ቤተክርስቲያን በዳግማዊ አፄ ዳዊትና በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥትም እንደገና ታንጿል። ቤተክርስቲያኑ በወጉ ከተጠረቡ ቀያይ ደንጋይ የታነጸ ነው። በቤተ መቅደሱ ዙርያ የተተከሉት ዓምዶች ከድንጋይ የተጠረቡ ሲሆን በረቂቅ ጥበበዊ ችሎታ የተሠሩ የግድግዳ ሥዕሎች ከግራኝ አህመድ ወረራ አምልጠው የመጡትን ጨምሮ ብዛት ያላቸው የብራና መጻሕፍት የሚገኙት በዚሁ ገዳም ነው። ዘዮሐንስ ይውሉበት ከነበረው ዋሻ ውስጥም አንዳንድ መጻሕፍት እና ሌሎች ልዩ ልዩ የታሪክ ቅርሶች ይገኛሉ። እንደውም የአንዳንዶቹ መጻሕፍት ቅጅዎች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርትና የሳይንስ



ክፍል (UNESCO) ቤተ መዘከር እንደሚገኙ ከተሰያዩ ጥናቶች መገንዘብ ተችሏል።

ክብራን በጸሎት ተወስነው በትህርምት ያሉና ከዚህች ዓለም ርቀው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ያስገዙ ወንድ መናንያን መነኮሳት የሚኖሩበት ስለሆነ፣ በወንዶች እንጂ በሴቶች የማይጐበኝ አጅግ ማራኪ የሆነ ድንቅ ገዳም ነው።



ክብራን ገብርኤል (ፎቶ ወንደሰን)

## ዑራ ኪዳነ ምሕረት

ዑራ ኪዳነምሕረት ከባሕር ትራንስፖርት ድርጅት ተነስተው ከአንድ ሰዓት የጀልባ ላይ ጉዞ በኋላ ከባሕር ዳር ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ በአንድ ጐኑ ከዩብስ ጋር በሌላው ጐኑ ደግሞ ከሐይቁ ጋራ የተገናኘ አና በተፈጥሮአዊ ልምላሜው ማራኪ በሆነ ደሴት ላይ የምትገኝ ከብ ቅርፅ የሆነች አና የሳር ክዳን ያለት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ቤተክርስቲያኗ የተመሠረተችው በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን በገዳምነት የጸናችው ግን በአፄ አድያም ሰገድ እያሱ ዘመነ መንግሥት በ፲፰፻፹፪ - ፲፱፻፲፭ዓ.ም ነው፡፡ መስራቾቹም አቡነ ዮሐንስ አና አቡነ ፋሲል ይባላሉ፡፡

አቡነ ዮሐንስ የተወለዱት በሸዋ ክፍለ ሀገር ነው፡፡ አባታቸው የማነ ብርሃን አናታቸው ሐመረወርቅ ይባላሉ፡፡ ሥርዓተ መንግሥትና ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በሚገባ አጠናቀው ከተማሩ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሰምነና ይጠራሉ፡፡ አምስት ዓመት ሙሉ ሥርዓተ መነኮሳትን ከአባ ጸጋ ኢየሱስ ዘንድ ከተማሩ በኋላ በእኝሁ አባት እጅ መንኩሰው ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመሄድ ሰባት ዓመት ሙሉ አባቶችን በትጋት በማገልገል በረድነት ከቆዩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም አንዲሄዱ በእግዚአብሔር ስለታዘዙ ጉዞአቸውን በመቀጠል ኢየሩሳሌም ደርሰው ቅዱሳን መካናትን ጐብኝተው በባሕረ ዮርዳኖስ ተጠምቀው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ አግረ መንገዳቸውን ግብጽ ገዳመ አስቀጤስ ይገባሉ፡፡ አዚያም አድሜያቸው አምስት መቶ የሆነውን ዳግማዊ አንጦስ የሚባሉትን



ደገኛ አባት ያገኛሉ፡፡ አኝህም አባት ከ፭፻ ዘመን በፊት አመቤታችን በደብረ ቁስቋም ተገልጻ አራት ታቦቶችን በአጇ ይዛ በኋለኛው ዘመን አባ ዮሐንስ የሚባል ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ይመጣልና ስጠው ብላ አዛኛለችና እንካ ተቀበለኝ ብለው የተሠጧቸውን አራት ታቦታት ማለትም፡-

- ታቦተ ሥላሴ • ታቦተ ኢየሱስ • ታቦተ ደብረ ምጥማቅ እና
- ታቦተ ኪዳነ ምሕረትን ይሰጡቸዋል፡፡

እሳቸውም እነዚህን ታቦታት በመያዝ የአምላካቸውን ሥራ በማድነቅ ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ በዑራኤል መልአክ መሪነት ይደርሳሉ፡፡ እንደደረሱም በጐጃም ክፍለ ሀገር ልዩ ስሙ ሜጫ ከተባለው አካባቢ ጉታ በሚባል ሥፍራ ሄደው ውሮ የተባለውን ባላባት አግኝተው የቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ቦታ ይቀበላሉ፡፡ አቡነ ዮሐንስም የባላባቱ ስምና ቦጐ አድራጐቱ ከትውልድ ትውልድ ሲጠራ ሲታወስ እንዲኖር በማሰብ በቦታው የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን <u>ውራ ኢየሱስ</u> ብለው ሰየሙት፡፡

ውራ ኢየሱስ ሆነው ሲጸልዩ ገዳመ ዘጌ ላይ ዓምደ ብርሃን ተተክሎ ስለታያቸው አቡነ ሩፋኤል አና ሦስት መቶ መነኮሳት ከቀሪዎቹ ፫ ታቦታት ጋር ዘጌ ይገባሉ፡፡ ከዚያም በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን አምደ ብርሃን ተተክሎ ካዩበት ሥፍራ ላይ ቤተክርስቲያን ሠርተው ታቦተ ኪዳነ ምሕረትን ያስገባሉ፡፡አሁንም የዚያን ቀን ባላባት ስም ለማዘከር ሲሉ ውራ ኪዳነ ምሕረት ብለው ይሰይሙና፡፡ በአቡነ ናሆም መቃብር ላይ ደግሞ የሥላሴን

ቤተክርስቲያን ሠርተው እንደጨረሱ የቀረችውን የደብረ ምጥማቅ ማርያምን ታቦት ደግሞ ጣና አጠገብ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው አዘዞ ማርያም በማለት ሰይመው በክብር አርፈዋል፡፡

ዑራ በአሁኑ ጊዜ ወደ ገዳሟ የሚያስገባ ወደብ ስለተሠራላት ያለምንም ችግር ከ፳-፴ ደቂቃ የእግር መንገድ በኋላ በግራና በቀኝ የተተከሉትን የሎሚ ፣ የብርቱካን የቡና እና የተለያዩ ዕጽዋትን መዓዛ እያሸተቱ ከተጓዙ በኋላ የሚያገኟት ገዳም ናት፡፡ ዑራ በጣና ሐይቅ ውስጥ ከሚገኙት ሴቶች ሲገቡ ከሚፈቀድላቸው ገዳማት ውስጥ አንዷ ናት፡፡

ዑራ ኪዳነምሕረት ከ፰፻ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላት ሲሆን ከመግቢያዋ ላይ እንደጠቀስኩት ክብ ቅርፅ ያላት፤ ከትላልቅ እንጨቶች ተጠርበው በወጡ አምዶች፣ በሮች፣ መስኮቶች በሸንበቆና በጠፈር ተጠልፎ በተሠራ የሳር ክዳን ግድግዳው በእንጨትና በጭቃ ባማረ በህላዊ አሠራር ያማረች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ከውጭ ወደ ውስጥ ሲታይ በመጀመሪያ የመከታ ክፍል በመካከልም የመቅደስ ክፍል ይገኛል፡፡ ቅድስት ክፍሉ ስምንት በሮች እና ስምንት መስኮቶች ያሉት ሲሆን ቅድስቱ ደግሞ ሦስት በሮችና አንድ መስኮት አለው፡፡ ከቅኔ ማኅሌቱ ፊት ለፊት ባለው ግድግዳ ላይ በ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን የተሣሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ታሪኮችን በሚያሳዩና ጥንታዊ ሠዓሊያን ከሰልን ዕጽዋትን ውኃን ቀላቅለው ቀለም በጥብጠው በሣሏቸው ሥዕሎች ያሸበረቀ ነው፡፡ ይህንና ይህን



የመሳሰለውን የቤተክርሰቲያኗን የውስጥ ጉብኝት ጨርሰው ከገዳሙ ብዙም ሳይርቅ በተሠራው አሳት በማይገባው የሳር ክዳን ያለው የቅርስ ማስቀመጫ ቤት ውስጥ ተቀምጠው በመጉብኘት ላይ ያሉ ቅርሶችን ያገኛሉ፡፡ ከቅርሶቹም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል

- ከአፄ አድያም ሰገድ እያሱ የተሰጠ የወርቅ ካባ
- በአፄ ዮሐንስ ዘመን የተሰጠ የብር ዘውድ
- የብር መስቀል ፣ የወርቅ ቀብ መፃር
- ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተሰጠ የወርቅ ዘውድ የወርቅና የብር ጉብጉብ ሲሆኑ ከዚህም ሌላ በብራና የተጻፉ ትላልቅ መጽሐፍትም ይገኛሉ፡፡ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ከተሣሉት ሥዕሎች ውስጥም ለመጥቀስ ያህል፡፡
- የጌታን ፅንሰት ( ልደት ) እስከ እርገቱ
- እመቤታችን ያደረገቻቸው ተዓምራት ( ከተዓምረ ማርያም የተወሰዱ ሥዕሎች )
- የሐዋርያትን፣ የመላእክትን፣ የሰማዕታትን ታሪክና የተለያዩ ገድሎችን የሚያመለክቱ የሐረግ ሥዕሎች በመቅደሱ ዙሪያ ይገኛሉ ፡፡

ይህችን ታሪካዊት ገዳም ለመጐብኘት ሁለት ዓይነት መንገድ መጠቀም ይቻላል፡፡ አንዱ ከባሕር ዳር ፳፫ ኪሎ ሜትር በሚርቀው የየብስ መገናኛ ሲሆን ሌላው በኮንትራት ወይም በቋሚነት በሚመላለሰው ጀልባ ነው፡፡


## መሀል ዘጌ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን የመሠረቱትም አቡነ በትረ ማርያም የተባሉ ጻድቅ በገዳሙ ከነበሩ አንዳንድ መነኮሳት ጋር ነው። (፲፪፻፺፮-፲፫፻፺፯) ዓ.ም። ከታሪክ እንደተረዳነው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሳንቃ ( መዝጊያ ) በፈቃደ እግዚአብሔር ተገኝ ይባላል። ቤተ ክርስቲያኑም የተመሠረተው በጭቃ እና በድንጋይ ነው። አቡነ በትረ ማርያም እና በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ቤተክርስቲያኑን ሲሠሩ በጾም እና በጸሎት በመትጋት ነው። ይኸው ቤተክርስቲያን እንደገና ፈርሶ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም የእደሳው ሥራ ተጀምሮ ስረጅም ጊዜ ከቆየ በኋላ በቅርብ ጊዜ ተጠናቋል። ይህ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በጣም የሚያምር እና የሚደንቅ ነው። ቤተክርስቲያኑ ክብ ቅርጽ ያለው ሲሆን መቅደስ እና ቅድስት ተብሎ በሁለት ትላልቅ ክፍሎች የተከፈለ ነው። መቅደሱ የታቦት ( የጽላት ) መቀመጫ ሲሆን የሚገኘውም በቅድስቱ ተከቦ በመካከል ነው። ቅድስቱ ስምንት በሮች ሲኖሩት ስድስቱ ባለ ትላልቅ ዓምድ ናቸው። ከዚህም ሌላ ስምንት መስኮቶች ያሉት ሲሆን ስድስቱ ባለ ስድስት ዓምድ ናቸው። እያንዳንዱ ዓምድ የሚያምሩ ባለ ሦስት በሮች እና አንድ መስኮት አሉት። ከዚህም ሌላ እንደ ምሰሶ የሚያገለግል ትልቅ ዓምድ ያለው ሲሆን ከዓምዱ በላይ አንድ ትልቅ እና ክብ ዋልታ አለ።



በቤተ ክርስቲያኑ መስኮቶች እና በሮች አገጣጠም በጣም የሚያስገርም እና የሚያምር ነው።

የቤተ ክርስቲያኑ ግቢ የጊዮርጊስ ፈረስ ኮቴ ያረፈበት ነው የሚባልበት ድንጋይ ቆሞ የሚታይ ሲሆን የፈረስ ኮቴ ቅርጽ ተቀርጾበት ይታያል። በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥንታዊ የነገሥታት የዘውድ አልባሳት ዘውዶች ከሴቻ ከታብ ወርቅ.... ወዘተ ይገኙበታል። በተለይም አቡነ በትረማርያም በአፀደ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ሲጸልዩ ይለብሱት የነበረ የብረት ልብስም በዚሁ ገዳም ይገኛል።



መሀል ዘጌ ጊዮርጊስ (ፎቶ ወንደሰን)

## አቡነ በትረ ማርያም

የአቡነ በትረ ማርያምን ቤተክርስቲያን የምናገኘው የመሐል ዘጌ ቅዱስ ጊዮርጊስን የጉብኝት መስመር አጠናቅቀን ትንሽ ሄድ እንዳልን ነው። ይህ ገዳም በተለያዩ አረንጓዴ ዕጽዋት ከመሸፈኑም በላይ ጸጥታ የሠፈነበት እና ለመናንያን አመቺ የሆነ ቅዱስ ሥፍራ ነው። ቤተክርስቲያኑ የታነጸው ከድንጋይ ከጭድ እና ከዋንዛ እንጨቶች በተለያዩ ዓይነት ቅርጾች ተቀርጸው በሚያስደንቅ ሁኔታ ከወጡ እንጨቶች ነው። ቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ክብ ሲሆን የመቅደሱ እና የቅድስቱ ክፍሎች ስፌ ሆነው በተጨማሪም በቅድስቱ ዙሪያ በሸምበቆ የታጠረ የመከታ ክፍል አለው። አሠራሩም ከውጭ ከመከታው ክፍል ወደ ቅድስቱ የሚወስድ ስምንት በሮች እና ስምንት መስኮቶች አሉት።

አቡነ በትረ ማርያም በጣና ሐይቅ ላይ የሉትን ገዳማት ካቀኑትና ስባቱ ከዋክብት እየተባሉ ከሚጠሩት አበው መካከል አንዱ ናቸው። ጻድቁ አቡነ በትረ ማርያም በ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እግዚአብሔር መርጦአቸው በመልአከ እግዚአብሔር መሪነት በጣና ሐይቅ ላይ አጽፋቸውን አንጥፈው በመቋሚያቸው እየቀዘፉ በድንቅ ተዓምራት ሐይቁን ተሻግረው ወደ ገዳመ ዘጌ ገብተዋል። እኚህ ጻድቅ መጀመሪያ ጣና ሐይቅ እንደደረሱ በጣና ባሕር ዳር አዝዋ ማርያም ተብላ የተሰየመችውን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ቤተክርስቲያን የጸሎትና የሥዕል ቦታ አድርገው



ስረጅም ዓመታት ተቀምጠዋል። ገድላቸውም ይህን ታሪክ ሲያጠናክር እንዲህ ይላል።
« አንተ ይእቲ ምቅዋመ ጸሎቱ ለበትረ ማርያም መንበር ብርሃን አዝዋ ማርያም። »

አቡነ በትረ ማርያም በጾም በጸሎት ተወስነው ፈጣሪያቸውን እያገለገሉ ብዙ ዘመን እንደ ቆዩ ከተጋድሎአቸው ብዛት የተነሳ ከቆሙበት ከእግራቸው ሥር ድውይ የሚፈውስ፣ ሙት የሚያስነሳ ፣ ዕውር የሚያበራ ፣ ለምጽ የሚያነጻ ፣ አጋንንት የሚያወጣ፣ ብዙ ተዓምራት የሚሠራ ቅዱስ ጸበል ፈልቆላቸዋል። በዚህ ጸበልም ብዙ ሰዎችን ካደረባቸው ደዌሥጋ ሁሉ በተሰጣቸው ጸጋ እየፈወሱ ይቆያሉ። በኋላ ላይ አቡነ በትረ ማርያም ከዕለታት በአንደኛው ቀን በጸሎት ላይ እንዳሉ ከገዳመ ዘጌ በስተምሥራቅ አቅጣጫ ላይ ዛሬ ( መሃል ዘጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ) ተብሎ የሚጠራው ሥፍራ ላይ ዓምደ ብርሃን ተተክሎ ስለታያቸው ወደ እዚያው ዓምደ ብርሃኑ ወዳየበት ሥፍራ ይሄዳሉ። እዚያም እንደ ደረሱ ዛሬ <u>ሰባ በጸሎት</u> ከሚባለው ሥፍራ ላይ ቆመው ጸሎት ሲያደርሱ ሳለ ሲቀ ሰማዕታት ቅዱስ ጊዮርጊስ በነጭ ፈረሱ ተቀምጦ ታያቸው። በዚያም ቦታ ላይ የዛሬውን መሃል ዘጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አንጸዋል። አቡነ በትረ ማርያም ገዳመ ዘጌን ካቀኑ በኋላ ብዙ ዘመን በዚሁ ገዳም በብዙ ተጋድሎ ቆይተው ከአምላካቸው ዘንድ ቃል ኪዳን ተቀብለዋል።

ቃለ ኪዳኑም፣

፩. በዚህ በገዳመ ዘጌ ውስጥ መብረቅ ሰው ሆነ እንስሳ እንዳይመታ፣

፪. እባብ ማንንም እንዳይነድፍ፣

፫. ዘንዶም ማንንም እንዳይበላ፣

ከእንዚህም ሌላ ነብር እና የመሳሰሉት ልዩ ልዩ እንስሳት የሰው ልጆች በገዳመ ዘጌ ውስጥ ማንንም አይተናኮሉም፤ በማንም ላይ አይደርሱም:: ይህም ሁሉ የሆነው በአቡነ በትረ ማርያም መንፈሳዊ ተጋድሎ ብዛት ከእምሳካችን ከልዑል እግዚአብሔር የተሰጠን የቸርነት ሥራ ነው::

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አቡነ በትረ ማርያም በገዳመ ዘጌ ላይ ያነጹት መሃል ዘጌ ቅዱስ ጊዮርጊስን ብቻ ሲሆን ለመታሰቢያቸው ይሆን ዘንድ በርሳቸው ስም ተሰይሞ የሚገኘው ህንጻ ቤተክርስቲያን ግን የታነጻው እርሳቸው ካለፉ በኋላ በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነው::

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንደ ሌሎቹ የጣና ሐይቅ ደሴቶች ሁሉ በልዩ ጥበብ በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የተሣሉ ቅዱሳን ሥዕሳት ይገኛሉ:: እነዚህን ሥዕሳት የሣሉ ሠዓልያን ምንጫቸው ቅዱስ ወንጌል ሲሆን ሠዓሊያኑ በሥዕሉቹ ላይ የተጠቀሙት የሥዕል ሥራ ከንድፍ አወጣጡ ጀምሮ እስከ ቅብ ሥራው ድረስ ያሰው ጥበብ ኢትዮጵያዊያኑ ሠዓሊያን ምን ያህል መንፈሳውያን እንደሆኑ የውስጥ መንፈሳዊ ስሜታቸውን የገለጹበት ሥፍራ



እንደሆነ የምናደንቅበትን ሥዕሉች በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ እናገኛለን::

በቅርስ ረገድም ያየን እንደሆን የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ቅርሶች ማለትም የመሃል ዘጌ ጊዮርጊስ እና የጻድቁ የአቡነ በትረ ማርያም ቤተክርስቲያን ቅርሶች በአንድነት ተሰብስበው በአንድ ዕቃ ቤት ውስጥ በአስተማማኝ ሁኔታ በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ:: በዚህ ገዳም ውስጥ ያሉትን ቅርሶች በሙሉ በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ መጻፍ ባይቻልም ከብዙ በጥቂቱ እንደሚከተለው አድርጌ አቀርባለሁ::

የወርቅ የእጅ መስቀል ፣ የወርቅ ከሊቻ፣ የብር ከሊቻ፣ የብር ከበሮ ፣ የወርቅ እና የብር አክሊልና የብር ጉባጉቦ ፣ በነሐስ የተለበጠ ነጋሪት ፣ ከብረት የተሠራ የአቡነ በትረ ማርያም ቀሚስ ፣ የብር ዘውዶች እና የነሐስ ከበሮዎች ሲሆኑ ከመጻሕፍት ደግሞ መጽሐፈ ሐዊ ፣ መጽሐፈ ሲኖዶስ ፣ ገድለ ሐዋርያት ፣ ገድለ ጊዮርጊስ ፣ ገድለ አቡነ በትረ ማርያም ፣ ትርጓሜ ወንጌል ወ.ዘ.ተ የሆኑ ቁጥራቸው እና እርእሰታቸው የበዙ ንዋየ ቅድሳት በዚህ ገዳም ውስጥ ይገኛሉ::

**የጻድቁ ረድኤትና በረከት አይለየን:: አሜን !**

## አዝዋ ማርያም

የአዝዋ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በአ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው። ይህች ቤተክርስቲያን ረጅ ዘመን እንዳሳለፈች ዙሪያውን በቅጽረ ቤተክርስቲያኒቱ የተተከሉ እና ረጅም ዕድሜን ያሳለፉት አፀዶች ምሥክሮች ናቸው የቤተክርስቲያኒቱ አሠራር ዙሪያ ክብ ሆኖ በሦስት ክፍሎ የተከፈለ ነው። ከመከታው ክፍል ወደ ቅድስቱ የሚወስ ስምንት በሮች ዙሪያውን ከስምንት መስኮቶች ጋር ያሉት ሲሆ የመቅደሱ ክፍልም ሦስት በሮችና አንድ መስኮት አለው።

የአዝዋ ማርያምን ቤተክርስቲያን የግድግዳው አ የጣርያ ማገር ለማስተሳሰር ይረዳ ዘንድ እንደገመድ የተጠቀሙ የአራት መቶ ክብቶችን ቀዳ በመተልተል እንደነበር ነ የተነገረኝ። የአዝዋ ማርያም ቤተክርስቲያን በር የመዝጊ ቁልፍም ከታቦተ ሕጓ ጋር ከቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በአ ዮሐንስ እጅ እንደመጣ ይነገራል።

መቼም በእያንዳንዱ የጣና ሐይቅ ገዳማት ውስ ጥበብን ማየት የተለመደ እንደሆነ ግልጽ ነው። በዚሁ ምክንያ የአዝዋ ማርያምም የዚሁ የሥነ ሥዕል ጥበብ የሚገኝባት አ የሚታይባት ናት። በተለይ ከቅድስቱ ክፍል ሆነው አንገትዎ አቅንተው ሲመለከቱ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ታሪኮች በአበው ሠዓሊያን ተሥሉ ያይዋቸዋል።



እነዚህ ድንቅ ሥዕሎች የተሣሉት በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ እንደሆነም ይነገራል። እነዚህን የግድግዳ ላይ ሥዕሎች ከቅብ ሥራቸው ጀምሮ እስከ ቀለም አመራረጣቸው ያየን እንደሆን እጅግ የረቀቁና በልዩ ተሰጥኦ የተሣሉ መሆናቸውን እናያለን። ሥዕሎቹ የተሣሉት ደግሞ በሸማኔዎች በተሠሩ ሸማ ከተባለ የጥጥ ልብስ ላይ ነው። ሠዓሊያኑ ሥዕሎቹን ለማሳመሪያነት ይጠቀሙበት የነበረውም የተለያዩ ዕፀዋቶችን በመጭመቅ ሲሆን እነዚህ የቀለም ውጤቶች በዘመን ብዛት እንኳን ምንም ዓይነት ለውጥ ያለማምጣታቸው በራሱ ሌላው ተዓምር ነው።

ሌላው ደግሞ በወቅቱ የነበሩ ሠዓሊያን የሚሰባሰቡባትና የሌሎች አድባራት እና ገዳማት ሥዕሎች ይሣሉባት የነበረችና ለሥነ ሥዕል ጥበብ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገች ቅድስት ሥፍራ ናት። ቤተክርስቲያኒቱ ውስጥም ትላልቅ የብራና መጻሕፍትና ጥንታውያን ቅርሶችም ይገኛሉ።

## ዳጋ እስጢፋኖስ

የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ከባሕር ዳር ከተ
በስተምዕራብ አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ታሳቅ ገዳም ነው።
ለመድረስ ፈጣን ባልሆኑ ጀልባዎች እንኳ ቢጠቀሙ ሁለት ሰ
ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የሚደርሱበት ገዳም ነው። ዳጋን እየቀረበ
ሲመጡ እንዲ በርቀት ሲታይ ሜዳ የሌለውና በውኃ ላይ የቀ
ቀጥ ያለ ተራራ ነው የሚመስለው። ዳጋን እየቀረብን ስናየ
ግን ተራራው በስተ ምዕራብ አቅጣጫ እንዳለ ሆኖ በስተምሥራ
አቅጣጫ ያለው ቦታ ግን ሜዳማ ሆኖ በአረንጓዴ ዕፀዋት የተሸ
ሥፍራ ነው። የዚህን ሥፍራ አቀማመጥ ልብ ብለን ስናየ
ከገዳሙ በቅርብ ርቀት ላይ ከሚገኘው ከደቅ ደሴት ጋ
የሚያመሳስል የተፈጥሮ አቀማመጥ አለው። የዳጋ እስጢፋኖ
ገዳም የመሬቱ አቀማመጥ ከራስጌው ሰፋ ብሎ ይታይና ከወደታ
ከግርጌው በኩል ደግሞ ጠበብ እያለ የሚሄድ ነው። ቁመ
ከደቡብ እስከ ሰሜን በግምት ፫ ኪሎ ሜትር ያህል ይረዝማል።

ወደ ገዳሙ ለመግባት ከጀልባ ወርደው ከወደቡ ወ
ገዳሙ የምታስገባዋን ድልድይ ይሻገሩና በግራና በቀኝ የበቀሉት
የዕፀዋት አይነቶች በዓይንዎ እየቃኙ እስከ ቤተክርስቲያኑ ድረ
የሚያደርስዎትን ቀጥ ያለ ዳገት የሚወጡበትን ቀጭን መንገ
ይዘው ተራራውን መውጣት ይጀምራሉ። ዳገቱን እየወጡ ሳ
ከተራራው መሀል እንደደረሱ **የጻድቃን ማረፊያ** ከተባለ ሥፍ
ይደርሳሉ። ከዚህ ቦታ ሲደረስ ማንም ሰው ጥቂት ደቂቃዎች



ሳያርፍ አይሄድም። በዚህ ቦታ ላይ ጉድጉድ ያለ እና ትንሽ ሰፋ ያለ ድንጋይ ይገኛል። ይህ ድንጋይ የገዳሙ መስራች የነበሩት አቡነ ኂሩተ አምላክ አስቀድመው ወደ ገዳሙ ሲመጡ በጣና ውኃ ላይ እንደ ጀልባ አድርገው በተዓምራት በላዩ ላይ ተቀምጠው የመጡበት ድንጋይ ነው። ይህን ቦታ አልፈው አቀበቱን ከወጡ በኋላ በተራራው አናት ላይ በስማዕቱ በቅዱስ እስጢፋኖስ ስም የታነጸውን ቤተክርስቲያን ያገኙታል።

ገዳመ እስጢፋኖስ የተመሠረተው በ፲፪፻፷ ዓ.ም በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ነው። ገዳሙን ያቀኑት አባት አቡነ ኂሩተ አምላክ የተባሉ የአፄ ይኩኖ አምላክ የወንድም ልጅ ናቸው። እኚህ አባት ከደብረ ሊባኖሱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር ከሐይቅ እስጢፋኖሱ መምህር ከአባ እየሱስ ሞአ ዘንድ መንፈሳዊ ትምህርት የተከታተሉ አባት ናቸው። አፄ ይኩኖ አምላክ አባ ኢየሱስ ሞአን ለመጉብኘት ሐይቅ በነበሩት ወቅት አቡነ ተክለሃይማኖት እና አባ ኂሩተ አምላክ ሥርዓተ ምንኩስናን እየተማሩ ሐይቅ እስጢፋኖስ ስለነበሩ ንጉሡ አፄ ይኩኖ አምላክ አባ ኢየሱስ ሞአን አቡነ ተክለሃይማኖት በመላ ኢትዮጵያ ሲቀ ካህናት እንዲሆኑ አባ ሂሩተ አምላክ ደግሞ ፀቃቤ ሰዓት አድርገው እንዲሾሙዋቸው ነገሯቸው። በትዕዛዙም መሠረት የእግዚአብሔርም መልካም ፈቃድ ታክሎበት ሁለቱም በፈቃደ እግዚአብሔር ሹመቱን ተቀብለው አገልግሎታቸውን በስፋው መስጠታቸውን ቀጡሉ።

በዚህ አገልግሎት አቡነ ተክለሃይማኖት ሲቀጥሉ አቡነ ኊሩተ አምላክ ግን ጥቂት ጊዜ በተሰጣቸው ማዕረግ ካገለገሉ በኋላ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቀው ከሰው ተለይተው እግዚአብሔርን በገዳም ለማገልገል ከአንዱ ገዳም ወደ አንዱ ገዳም ታቦተ እስጢፋኖስን ይዘው ሲዘዋወሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ዳጋ ደሴት ደርሰዋል። ወደ ገዳሙ እንደገቡ በገዳሙ ውስጥ በአብርሀ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት በአመቢታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስም የታነጸችውን ቤተክርስቲያን ስላገኙ ታቦቲቷን እያጠኑ የተባሕትዎ ሥራን እየሠሩ እስከ አፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ድረስ ቆይተዋል።

በኋላ በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በራሳቸው በንጉሡ ፈቃድ ታቦተ ማርያም በደቅ ደሴት ውስጥ ኮታ ወደተባለ ሥፍራ ስለሄደች በቦታውም ላይ ታቦተ እስጢፋኖስ ስለ ገባ የገዳሙ ስም ዳጋ እስጢፋኖስ ተባለ። ይህ ቤተክርስቲያን ምንም እንኳን በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ቢታነጽም በተለያዩ ዘመናት የእድሳት ሥራዎች ተደርገውለታል። የእድሳት ሥራውን ካደረጉት ነገሥታት መካከልም አፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ አፄ ሉስንዮስ፣ አፄ ፋሲል ይገኙበታል። የቤተክርስቲያኑ አሠራር በጣና ሐይቅ ውስጥ ከሚገኘው ከጣና ቂርቆስ ጋር ይመሳሰላል። የቤተ ክርስቲያኑ ጣራ እስከ አሁን ድረስ የሳር መሆኑ በራሱ የተለየ ውበትን ለቦታው አጕናጽፎ ይገኛል።ወደ ቤተክርስቲያኑ እንደ ቀረቡ ከቤተክርስቲያኑ ምሥራቅ ደጃፍ ላይ የተቀበሩትን



የጻድቃን አባት የአቡነ ኊሩተ አምላክን መካነ መቃብር ያገኛሉ። የጻድቁ በዓለ እረፍት የሚከበረውም ነሐሴ ፳ ቀን ነው።

የዳጋ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን የሳንቃ መዝጊያዎች አንድ ወጥ ሆነው ረጅምና ሰፋፊ ናቸው። የአንዱ ሳንቃ ርዝመት የአምስት ሜትር ቁመትና የሦስት ሜትር ወርድ ስፋት አለው። እነዚህ በሮች ከ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያልተነኩ መሆናቸውን መነኮሳቱ ይናገራሉ። ይህ ቤተክርስቲያን አሁን በቅርቡ እንኳን ከ[illegible] እስከ [illegible] ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ጊዜያት እድሳት የተደረገለት ቢሆንም በጥንታዊው የቤተክርስቲያኑ አሠራር ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አላመጣበትም።

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያሉት ሥዕሎችም ቢሆኑ የተሣሉት በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ሲሆን በጥንታዊነታቸው ቀዳሚውን ሥፍራ ከሚይዙት ጉራ የሚያስለፋቸው ነው። የቤተክርስቲያኑን ጉብኝትዎን ካጠናቀቁ በኋላ በእነስተኛ ቤት ውስጥ ዕፁፍ እዕላፋት ታሪክ ወደ ሚገኝበት ታሪካዊ ሥፍራ ያመራሉ።

ቤቷ ለገዳሙ እንደ ቅርስ ማስቀመጫ ሙዝየምነት የምታገለግል ናት። በዚህ ቤት ውስጥ ታሪክ እና የታሪኩ ሠሪዎች ጥምር ይገኛሉ።

* አፄ ዳዊት ([illegible] - [illegible])
* አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ([illegible] - [illegible])
* አፄ ሉስንዮስ ( [illegible] - [illegible] )

* አፄ ፋሲል ( ፲፮፻፴፪ - ፲፮፻፶፯ ) እኒህ ነገሥታት በሕይወት ዘመናቸው በገዳሙ ከፍተኛ ፍቅር የተነደፉ ሰለ ነበር ከዚህች ዓለም በሞት ሲለዩም አስከሬናቸው ሳይፈርስ በሳጥን ውስጥ እንዳሉ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ ነገሥታቱ ከጥንት ጀምሮ የነበሩበት እና ዐፅማቸው ያረፈበትን ሳጥን በአሁኑ ወቅት የአየሩሳሌም ድርጅት ባሠራው ባለመስታወት ሳጥን ውስጥ ሁሉ ሰው እንዲያያቸው ተደርገው ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡

በዳጋ ገዳም ውስጥ ከነገሥታቱ ዐፅም ሌላ ለዓይን የሚያታክቱ የብራና መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡ የነገሥታቱ የወግ ዕቃዎች ንዋየ ቅድሳት በሙሉ በወጉ ተደርድረው ይታያሉ፡፡ ነገሥታቱ ለገዳሙ ካበረከቱት ቅርሶች መካከል አፄ ዳዊት የሚዘጉና የሚከፈቱ የነሐስ መሰቀሎች ፣ **የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ** የወርቅና የነሐስ መሰቀሎች ፣ በሕይወት ዘመናቸው ከእጃቸው የማይለየው እና « **ወንቦ ከመያንዝር** » የሚል ጽሑፍ ያለበት ጉራዲያቸው እና በርከት ያሉ የወርቅና የብር ቅርሶች በዚህችው ዕቃ ቤት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ሁሉ አስደናቂ ጉብኝት በኋላ ሌላው የጉብኝት ምዕራፍ የሚሆነው ደግሞ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በሚገኘው ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ ያሉት የአዝርዕትና የዕፀዋት ዓይነቶች ናቸው፡፡ በዚህ ገዳም ውስጥ የሌሉ የዕፀዋት ዓይነቶች የሉም፡፡ ከሚበሉ አንስቶ እስከማይበሉት ድረስ ያሉት የማከስኛ ፍጥረታት በሙሉ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ብቻ ያሉ ነው የሚመስሉት፡፡



በዚህ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ከ፷ - ፸ የሚደርሱ ባሕታውያን፣ መነኮሳት ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ መካከል አብዛኛዎቹ በጫካ ውስጥ ዘግተው በጾም በጸሎት የሚተጉ አባቶች ይገኙበታል፡፡ የሚያስደንቀው ደግሞ በገዳሙ ውስጥ ይህን ያህል ሰው እየኖረ የአንድም ሰው ድምጽ አይሰማም፡፡ ከአዕዋፋት ዝማሬ በቀር፡፡ መነኮሳቱ የሚመገቡት ከዳጉሣ እህል የሚዘጋጅ ዳቦ የሚመስል __መኩሬታ__ የሚባል ምግብ ነው፡፡ ይህንንም ምግብ የሚመገቡት ውስው በ፱ እና በ፲፪ ሰዓት ብቻ ነው፡፡

እነዚህ መነኮሳት መተዳደሪያቸው የአትክልት ልማት ሲሆን ገዳሙ ውስጥ ሙዝ፣ሸንኮራ፣ ሉሚ፣ ትርንጉ፣ ፓፓዬ፣ ማሽላ እያመረቱ እራሳቸውን እያረዱ ይኖራሉ፡፡ ገዳማውያኑ በአሁኑ ወቅት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርክ አንድ የሞተር ወፍጮ፣ አንድ የውኃ ሞተር ከብፁዕ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ አንድ ታሳቅ የውኃ ሞተር እና ሁለት የአሳ ማጥመጃ ጀልባዎች ስለተሰጡዋቸው በነሱ በመጠቀም የገቢ ምንጭ በመፍጠር እና በመፈለግ ቦታውን በማደራጀት ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ገዳም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ በየጊዜው በተነሱ ጠላቶች ጉዳቲ እንዳልደረሰበት ይነገራል፡፡ አሁን ድረስ ከየገዳማቱና ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ መናንያን በዚህ ገዳም ውስጥ መኖር ቢችሉም የሚኖሩት ግን በገዳሙ ሕግ መሠረት

ተፈትነው የፈተናውንም መመዘኛ ያስፉ እንደሆን ብቻ ነው። የዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም መነኮሳቶች የሚገኙት እንደ መላእክት እግዚአብሔርን እያመሰገኑና በሥራቸውም ተግተው ነው ሲኖሩ የሚታዩት።

የጻድቁ አባት የአቡነ ጎሬተ አምላክ ረድኤትና በረከት አይለየን አሜን ።



ዳጋ እስጢፋኖስ



## ደጋንደ ተክለሃይማኖት

ይህ ቤተክርስቲያን የተመሠረተው በአፄ አድያም ሰገድ እያሱ ዘመነ መንግሥት ነው። ገዳሙ የሚገኘው በዘጌ አፋፍ ላይ ሲሆን አሁን የምናየው ሕንጻ ቤተክርስቲያን በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም በእሳት ተቃጥሎ እንደገና የተሠራ ነው።

በወቅቱ ቤተክርስቲያኑ በምን ምክንያት እንደተቃጠለ ባይታወቅም እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሱ አንዳንድ አፈታሪኮች ግን አሉ። አንድ የገዳሙ አገልጋይ ካህንና አንድ ክርስትያን ያልሆነ ሰው ታመው ሆስፒታል ይገባሉ። ሁለቱም ይሞታሉ። በአስከሬን ርክክብ ወቅትም የገዳማዊው አስከሬን በስሕተት ለማያምኑት ወገን የማያምኑት ወገን አስከሬን ደግሞ ለገዳማውያኑ ይሰጥና በቅጽረ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ይቀበራል በማግስቱ ግን ያልታሰበ እሳት ተነስቶ ቤተክርስቲያኑን አቃጠለው። የቃጠሎውም ምክንያት የኢ-አማኛዊው ሰው አስከሬን በቤተክርስቲያን መቀበር ነው ይላሉ የገደሙ ካህናት። የሚያስደንቀው ነገር በወቅቱ ቤተክርስቲያኑ ሲቃጠል የታቦቱ አብሮ አለመቃጠል ነው። ነገር ግን ይህን በተዓምር እና በሚያስደንቅ ሁኔታ ከቤተክርስቲያኑ ፍርስራሽ ሥር የተገኘውን ታቦት ( ጽላት ) ሌቦች ሰርቀው ከሄዱ በኋላ አሁንም በሚያስገርም ሁኔታ ወደ ቦታው ተመልሷል።

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ብዙ ብርቅ እና ድንቅ የሆኑ ቅርሶች በመኖራቸው የተነሳ አብዛኛውን ግዜ ሌቦች ቢያጠቁትም

እግዚአብሔር ግን በተዓምራት የተሰረቁትን ዕቃዎች ሲያስመልስ ይታያል፡፡ ለምሳሌ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም አንድ የወርቅ ቅብ የመጾር መስቀል ፣ አንድ የነሐስ መስቀል ጠፍቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰራቂዎቹ እግዚአብሔር ከዚህ በፊት በገዳሙ ያደረገውን ተዓምራት እያወቁ በድፍረት ይህን ክቡር ቅርስ ቢዘርፉም ቅርሶቹ በተወሰዱ በዓመቱ ማለትም ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ተገኝተው ተመልሰዋል፡፡ የተገኘው የወርቅ መስቀል ፩ ኪሎ ግራም የሚመዝን ነው፡፡

በዚህ ምክንያት የቤተክርስቲያኑ የቅርስ ቀበኞች በመብዛታቸው ምክንያት የተነሳ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ቅርሶቹን እንደሌሳው የጣና ገዳማት ማየት አይቻልም፡፡ ይህም ማለት ቤተክርስቲያኑ ቅርስ የለውም ማለትም አይደለም፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ ቅርሶቹ ከቤተክርስቲያን ወጥተው በአንድ ግለሰብ ቤት ውስጥ ነው የሚገኙት፡፡ አንባቢ ሆይ ተመልከት የእግዚአብሔርን ዕቃ በቤቱ ተከብሮ እንዳይቀመጥ ያስፈሩት ዘራፊዎች አንድን ተራ ፍጡር በመፍራታቸው ምክንያት እስካሁን ድረስ ቅርሱ በግለሰቡ ቤት ውስጥ ተቀምጦ እንደተከበረ ይገኛል፡፡ **የሚገርም ዘመን ነው**፡፡




## ናርጋ ሥላሴ

ይህን ቤተ ክርስቲያን ያሳነጹት ከ ፲፮፻፸፪ - ፲፮፻፺፯ ዓ.ም ነግሠው የነበሩት አፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድና እናትየው ንግሥት ምንትዋብ ናቸው፡፡ የቤተክርስቲያኑ አሠራር ከዳጋ እስጢፋኖስ እና ከክብራን ቅዱስ ገብርኤል ህንጻ ቤተክርስቲያን ተለየ ሲሆን የአውሮፓውያንን ሕንጻ ሥራ የሚያንጸባርቅ መሆኑ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ በፖርቹጋሎች የተሠራ ሳይሆን ይቀርም የሚል መላ ምት ይነገራል፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያኑ የተሠራበት ዘመን ጋር የማይጣጣም በመሆኑ እውነትነት ያለው አይመስልም፡፡ ይልቁንም የቤተክርስቲያኑን ሕንጻ የገነቡት ኢትዮጵያዊያን አባቶች ቀደም ሲል በሀገራችን ከነበሩት ፖርቹጋሎች ያልተናነሰ ጥበብ እና እውቀት እንደነበራቸው ያመለክራል፡፡

ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲገባ በምሥራቅና በምዕራብ ትይዩ ነው የተሠሩ የጐንደሩን የአፄ አፄ ፋሲልን የቤተ መንግሥት አሠራር ተከትለው የታነጹ ባለ አንድ ፎቅ ሕንጻዎች ሲኖሩ ሥራቸው ሁለት ቀጫጭን መንገዶች አሏቸው፡፡ በዚህ ገዳም ውስጥ በአሁኑ ወቅት እንደሌሎቹ ገዳማት ለትውልድ ተላልፎ ዓይን የሚታይ ቅርስ እንዳይኖር ፋሽስቱ የኢጣሊያ ጦር ሀገራችን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ በገዳሙ ውስጥ የነበሩትን እያሌ ባዕዳንን ልብ የሚያማልሉና የእኛነታችን አሻራ የሆኑ ድንቅ ቅርሶችን በሚያሳዝን መልኩ በመዝረፉ ነው፡፡ የናርጋ

ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከተሠራበት ዘመን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥገና የተደረገለት በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ሲሆን አሁን በቅርብ ግዜ ደግሞ በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር የጣሪያ ቆርቆሮ ለውጥ ተደርጉለታል :: ናርጋ ሥላሴ በሚገኝበት ደቅ ደሴት ውስጥ በግማሽ ሰዓት የእግር ጉዞ የሚራራቁ እጅግ ጥንታዊና ውብ የሆኑ የብራና መጻሕፍት የሚገኙበት አርሴማ ፣ ኮታ ማርያምና ጋደና ጊዮርጊስ አብያተክርስቲያናት ይገኛሉ:



ናርጋ ስላሴ (ፎቶ መንደሰን)



## ደብረ ሲና ማርያም

የደብረ ሲና ማርያም የምትገኘው በጣና ሐይቅ ሰሜናዊ ቅጣጫ ከባሕሩ የመጨረሻ ጫፍ ላይ በጉርጉራ ወደብ ላይ ው:: ወደ ደብረ ሲና ማርያም ቤተክርስቲያን በሁለት አይነት ንገድ ተጉዘው መድረስ ይችላሉ:: አንደኛው መንገድ ከባሕር ር ተነስተው በሚመጡ ጀልባዎች አማካኝነት በባሕር ላይ ሚደረግ ጉዞ ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ከጉንደር ከተማ መኪና ትራንስፖርት የ፳ ኪሎ ሜትር ርቅት ያለውን መንገድ ተጓዙ በኋላ የሚያገኟት ጥንታዊ ቤተክርስቲያን ናት::

የደብረ ሲና ማርያም ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ባ ኤስዲሮስ በተባሉ ጻድቅ መነኩሴ አማካኝነት ነው:: አባ ስዲሮስ የትውልድ ሀገራቸው በሸዋ ክፍለ ሀገር ደብረ ሲና ው:: ለዚህም ነው የቤተክርስቲያኒቱ ስም በአባ ኤስዲሮስ ትውልድ ሀገር ስም **ደብረ ሲና ማርያም** የተባለችው::

የቤተክርስቲያኒቱ አሠራር ዙሪያ ክብ ሆና በጥቃ ምርጊት ማረ ግድግዳ ያላት ናት:: የቤተክርስቲያኒቱ ጣሪያ እስከ አሁን ረስ ጥንታዊ ውበቱን እንደጠበቀ ቆርቆሮ ሳይለብስ በሚያምር ሳር ክፍክፍ የተከደነ ነው:: በቤተክርስቲያኒቱ ዙሪያ በውጪም ውስጥም ብዛታቸው የተለያዩ ምሰሶዎች ቆመው የላይኛውን ጣሪያውን ክፍል ደግፈው ይታያሉ:: ምሰሶዎቹ አንድ ወጥ ሆነው መሳሳይ ውፍረት ያላቸው ናቸው::

በውስጠኛው የቤተክርስቲያኑ ክፍል ውስጥ ከሚገኙት ምሰሶዎች መካከል አንደኛው ምሰሶ የተለየ ታሪክ እንዳለው ነው የተነገረኝ፡፡ ታሪኩም እንዲህ ነው፡፡ የደብረሲና ማርያም ቤተክርስቲያን ገና ስትሠራ በውጭ ከሚገኙት ወደ ፬ ከሚጠጉት ምሰሶዎች በተጨማሪ በውስጠኛው ክፍል ውስጥ ከሚገኙት ፲፪ ምሰሶዎች መካከል አንደኛው ምሰሶ ከዘጌ ሲገዛ ገዢዎቹ በሌሎቹ ምሰሶዎች ዋጋ ይስማሙና በዚህ በአንደኛው ሳይስማሙ ቀርተው ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ፡፡ ነገር ግን ሀገራቸው እንደገቡ ያንን በዋጋ ያልተስማሙበትን ምሰሶ ማዕበል እየገፋ አምጥቶ ደብረ ሲና ይጥለዋል፡፡ ሰዎቹም በእመቤታችን ተዓምራት እየተደነቁ ከዓስራ አንዱ ምሰሶዎች ጋር ቀላቅለው ለቤተክርስቲያኒቱ ሥራ ያውሉታል፡፡ ዛሬም ካህናቶች ያ በማዕበል እየተገፋ የመጣው ምሰሶ ይህ ነው በማለት ለምዕመናን ያሳያሉ፡፡

በደብረ ሲና ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ ረጅም ዕድሜን ያስቆጠሩ የብራና መጻሕፍት እና በቤተመቅደሱ ዙሪያ የተሣሉ ጥንታዊ መንፈሳዊ ሥዕሳት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሥዕሳት የተሣሉት በ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በአፄ ፋሲል እህት **<u>በወ/ሮ መለኮታዊት</u>** አማካኝነት እንደሆነ የቤተክርስቲያኒቱ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ እነዚህን ሥዕሎች በ፲፱፻ዎቹ አካባቢ የበህል ሚኒስቴር ባለሙያዎችን ልኮ ሥዕሎቹ የቀደሞ ገጽታቸውን ሳይለቁ በሳይንሳዊ መንገድ መጠነኛ ጥገና እንደተደረገላቸው ይነገራል፡፡ እንዲያውም በለተምሥራቅ በኩል



ያለችው የእመቤታችን ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ከተለያዩ በሽታዎች ፈዋሽ በመሆኗ ምክንያት ምዕመናን ሥዕሏን በማሻሸትና አንዳንዶቹም እየቆረጡ መውሰድ በመጀመራቸው ምክንያት የባህል ሚኒስቴር ሥዕሏን በባለመስታወት ፍሬም ውስጥ እንድትቀመጥ አድርጓል፡፡

ሌላው ደግሞ ለደብረ ሲና ማርያም ቤተክርስቲያን ልዩ ውበትን ከሚሰጧት መካከል የጐርጐራ ወደብና በአካባቢው ያሉት የተለያዩ ዕጽዋቶች ናቸው፡፡ የጐርጐራ ከተማ በ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ እና በ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በፖርቱጋሎች አማካኝነት እንደተመሠረተች ይነገራል፡፡ በተለይ የጣና ትራንስፖርት ድርጅት ንብረት የሆነው የጐርጐራ ወደብ ከበብ ለአካባቢው ልዩ ውበትን ሰጥቶ እናያለን፡፡

## የማንዳባ መድኃኔ ዓለም


የማንዳባ መድኃኔ ዓለም ገደም በጣና ሐይቅ ውስጥ ከሚገኙ ገዳማት መካከል አንደኛው ነው። ይህ ገዳም የሚገኘው በጉርጉራ ወደብ አካባቢ በሚገኝ ቦታ ሳይ ሲሆን ግማሽ ጉኑ በውኃ የተከበበ እና ቀሪው የገዳሙ ክፍል ደግሞ ከየብስ ጋር ተያይዞ የሚገኝ ገዳም ነው።

ገዳሙ የተመሠረተው በ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን የገደሙ አቅኚ አባ አሳይ የተባሉ መንፈሳዊ አባት ናቸው። እንዲያውም እኚህ ጻድቅ አባት  የጣና ሐይቅ ገዳማትን ካቀኑት ሰባቱ ከዋክብት ከሚባሉት አባቶች መካከል አንደኛው ናቸው። አቡነ አሳይ ወደ ገዳሙ የመጡት በድንጋይ ሳይ ቀመው ከእምነታቸው ጽናት የተነሳ ድንጋዩን እንደ ጀልባ ተጠቅመውበት እንደ ነበር መነኮሳቱ የጻድቁን ገድል በመጥቀስ ያስረዳሉ።

ይህ የድንጋይ ጀልባ አሁን ድረስ ከገዳሙ ግቢ በስተምዕራብ በኩል በክብር ምዕመናን እንዲያዩት ተደርጐ ተቀምጦ ይገኛል። የገዳሙ መጠሪያ ስምም የተገኘው ከእኚሁ ጻድቅ ግሩም ሥራ የተነሳ ነው። አባ አሳይ በድንጋይ ጀልባ ተቀምጠው በውኃ ላይ በሚያስደንቅ ሁኔታ በመመላለሳቸው ምክንያት የተነሳ <u>ማን እንደ አባ አሳይ</u> እንደርሳቸው ያለ የለም ተባለ ። ከዚህም ጋር የገዳሙ ስም <u>**ማንዳባ መድኃኔዓለም**</u> ገዳም ተብሎ ተሰየመ።



የማንዳባ መድኃኔዓለም ገዳም መነኮሳት የሚተዳደሩት ሙ ባለው የእርሻ መሬት ሳይ እያረሱ ከሚያገኙት ምርት መጠቀም ነው። ቤተክርስቲያኑ አሁን በቅርቡ ቆርቆሮ ከመልበሱ ቅር በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ያሉት መስኮቶች አንዳዶቹ በሸንበቆ ተከደኑ ናቸው። በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙ ሥዕሎችም ውበታቸው ተወዳዳሪ የላቸውም። ነገር ግን ሥዕሎቹ የጥንቶቹ ቀዳደው በማለቃቸው ምክንያት አሁን የምናያቸው ሥዕሎች ቅርቡ የተቀየሩ ሥዕሎች ናቸው።



*ማንዳባ መድሀኒዓለም* (ፎቶ ወንደሰን)

## ጣና ቂርቆስ

ይህ ታሳቅ ገዳም ስትልቁ የጣና ሐይቅ እንኳ መጠሪያ ስሙ የተገኘበት፣ በምሥራቃዊው የጣና ሐይቅ ጫፍ ሳይ በጐንደር ክፍለ ሀገር በደራ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ እምነት ለሆነችው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት የትውፊት ማህደር ለምዕመናኑም የታሪኩ መግለጫ የአባቶች የቅርሶቻቸው ሚዝየም የሆነ ታሳቅ ገዳም ነው። ወደ ገዳሙ ለመግባት ሁለት ዓይነት መንገዶችን መጠቀም የግድ እና አማራጭ የሌለው ነው።

**<u>አንደኛው መንገድ</u>** ከባሕር ዳር ተነስተው በሚመጡ የኪራይ ጀልባዎች ሲሆን ነገር ግን ይኸኛው አማራጭ ከገደሙ መራቅ እና ለጀልባዎች መቆሚያ ወደብ ያለመኖርም ተደምሮ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ወደእዚህ ገዳም ለመምጣት አቅም ስለሚያንሳቸው ከቱሪስት እንኳን ከለንት አንዱ ነው ይህን ቦታ በጀልባ የሚጐበኘው። በዚህ ችግር የተነሳ ገዳማውያኑ እንደሌሎቹ የጣና ሐይቅ ገዳማት እንኳን ሲረዱ አልቻሉም።

**<u>ሁለተኛው መንገድ</u>** ደግሞ በየብስ የሚደረግ ጉዞ ሲሆን ከባሕር ዳር ተነስተው በመኪና ትራንስፖርት ወደ ሐሙሲት ከተማ ድረስ በመሔድ ወደ ናብጋ የሚወስደውን መንገድ በመከተል ክርስቶስ ሠምራን በለሚናዊው አቅጣጫ ሳይ በመተው የጉመራን ወንዝ ተሻግረው የሚያገኙት ጥንታዊ እና ታሪካዊ ገዳም ነው። ይህም መንገድ ቢሆን አስቸጋሪ ነው። ከ፲፩ - ፲፮



ኪሎ ሜትር ያህል የእግር መንገድን በመጓዝ ፈታኝና አዳካሚ እግር ጉዞን ካደረጉ በኋላ የሚደርሱበት ነው።

የገዳሙ አንደኛው ጫፍ ከጣና ሐይቅ ጋር የተገናኘ ሲሆን ሌሳው ወገኑ ደግሞ ከየብስ ጋር የተገናኘ ነው። ከገዳሙ ስተምምሥራቅ በኩል በዚሁ ገዳም ውስጥ በሴቶች ገዳም ታገለግል ነበረችው የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ገዳም ሲያዋስነው ምዕራብ በኩል ደግሞ በርቀት የታሳቁ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ዋስኑታል። ገዳሙ በተለይ በምሥራቃዊ ጐኑ በኩል ከውኃው ውስጥ በጥሩ መሐንዲስ ተገንብቶ የወጣ ግሩም ሕንጻ ሚመስለው የድንጋይ ጉብታ ለተመልካች አይታ አጹብ የአንተ ሥራ የሚያሰኝ ድንቅ ተፈጥሮ ነው። ይህ ገዳም ከዘመነ መሳፍንት ወዲህ **<u>በደርቡሽ ጦርነት</u>** እና በአካባቢው ሕዝብ ጽዕና **<u>ከ፫፻</u>** ዓመት በሳይ ጠፍቶ / ጠፋ / ሆና ቆይቶ አሁን ቅርብ ግዜ በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ሳይ በጥቂት መነኮሳት ገና መቋቋሙ ስለሆነ የመነኮሳተ የልፋት ውጤት የሆኑ እና ከምስጥ ተረፋትን የጓሮ አትክልቶች በዓይንዎ እየቃኙ በምዕራባዊው ገዳሙ አቅጣጫ በኩል ከዓለት ጋር የሚጋጨውን እና በግጭቱም ሚፈጠረውን የማዕበል ድምጽ እና በገዳሙ ደን ውስጥ ሆነው ሚዘምሩትን የአዕዋፋቱን ዝማሬ እያዳመጡ ቀጭኗን መንገድ ከትለው ወደ ገዳሙ ይገባሉ።

የጣና ቂርቆስ ቤተክርስቲያን በቅርብ ቆርቆር የለበሰ ሆና ሠራሩ ከደጋው ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ጋር ተመሳሳይነት

ያለው ነው፡፡ የቤተክርስቲያኑ በሮች እና መስኮቶች እንኳ እዚያው ባሉበት ቆመው እድሜ የጠገቡ ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የተሣሉት ሥዕሎች ጥንታዊነታቸውና ብዙ ዘመን መቆየታቸው ሳያንሳቸው በገዳሙ ውስጥ ብዙ ቅርሶችን በማጥፋት ላይ የሚገኘው እና ገዳማውያኑ እንኳ መፍትሔ ያጡለት ምስጥ ብዙ ጉዳት እያደረሰባቸው ይገኛል፡፡ በተለይ የቅድስት ሥላሴን ሥዕል ከጥቅም ውጭ አውጥቶታል፡፡ ይህ ምስጥ ሥዕሎቹን ብቻ ሳይደለም እያወደመ የሚገኘው የገዳሙ መነኮሳት በስንት መከራ የተከሏቸውን የፖፖዬ ዛፎች ከሥራቸው በመጣል፣ ድንች፣ ካሮት፣ ጉማን፣ ቲማቲም ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን የጓሮ አትክልቶች እንደተተከሉ ስለሚያጠፋቸው መነኮሳቱን ለምሬት ዳርጉአቸዋል፡፡ የገዳሙን ችግርና የገዳማውያኑን አስቃቂ ኑሮ ወደ ኋላ ለስምመለስበት አሁን ወደ ገዳሙ ጥንተ አመሠራረት ልውሰዳችሁ፡፡

ገዳሙ የተመሠረተው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ**፱፻፹፪** ዓመት ገደማ ወይም ዓለም ከተፈጠረች በ**፵፭፻፲፰** ዓመተ ዓለም ላይ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡የእስራኤሉ ንጉሥ ዳዊት ልጅ የሆነው የንጉሥ ሰሎሞንና የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ ልጅ የሆነው ቀዳማዊ ምኒልክ አባቱ ሀገር ኢየሩሳሌም ሄዶ ታቦተ ጽዮንን፣ ከሀገሪቱ የበኩር የበኩር ልጅ የሆኑትንና በዘመኑ በምድረ እስራኤል የነበሩትን ካህናተ ኦሪት የሆኑትን <u>ስዛሬያሰና ዘዲክን</u>፣ / ሳዶቅን / ከነቤተሰቦቻቸው ይዞ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ



ይመጣል፡፡ በወቅቱ ካህናተ ኦሪት የነበሩት እነ አዛሪያስ ታቦተ ጽዮን ከእነሱ እንዳትነጠል በመፈለጋቸው ታቦተ ጽዮንን ማንንም ሳያስፈቅዱ በድብቅ ይዘዋት በመምጣታቸው የተነሳ ንጉሥ ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥም ታቧቷ መጥፋቷ ሲታወቅ እስራኤላውያኑ በግድ ጦርነት አንስተው ታቦተ ጽዮንን ይመልሷቷል የሚለው ፍራቻ በማየሉ የግድ ታቦተ ጽዮንን መደበቅ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለዚህም ሲባል ጦርነት እንኳ ቢነሳ ታቦቷን ለመጠበቅም ሆነ ለመከላከል አመቺ ሥፍራ ሆኖ የተመረጠው በጣና ሐይቅ ውስጥ ካሉት ደሴቶች መካከል ይህን ዛሬ ጣና ቂርቆስ ብለን የምንጠራውን ሥፍራ በመምረጥ በታቦተ ጽዮን መሪነትና በፈቃደ እግዚአብሔር አማካኝነት እስራኤላውያኑ ወደዚህ ሥፍራ ይመጣሉ፡፡ የቦታውንም ስም « <u>ሳፍ ጽዮን መካነ ሳህል</u> » በማለት ይሰይሙና ታቦተ ጽዮንን ከገዳሙ ሲያስቀምጡ አብሮ የመጣውን ሕዝብ ደግሞ ከባህሩ ውጭ ባለው ሥፍራ ያሰፍሩታል፡፡ የሰፋሪዎቹ ዝርያዎች እስከ ዛሬ ድረስ ሳይጠፉ ደቡብ ጐንደር ውስጥ <u>ነገደ እስራኤል</u> እየተባሉ እየተጠሩ ይገኛሉ፡፡

በዘመነ ኦሪት ኢትዮጵያ ውስጥ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለአልተስፋፋ እነ ካህኑ አዛርያስና ዘዲክ / ሳዶቅ / አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማስፋፋት ብዙ ይጥሩ ነበር፡፡ በተለይ አባቶቻችን ጠብቀው አሁን ድረስ ያቆዩልን አምስት ዓይነት የኦሪት መሰዊያ በገዳሙ ውስጥ በክብር ተጠብቆ መገኘቱ አንዱ ምሥክር ነው፡፡

የዚህ ገዳም ታሪክ በዘመነ ብሉይ ብቻ ሳይሆን በዘመነ ሐዲስም ድንቅ ታሪክ አለው:: ክርስቶስ መድኃኒታችን ሲወለድ ሕፃኑን ለመግደል ሄሮዶስ ሲፈልገው እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ግብጽ ሀገር ስትሰደድ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያም መምጣቷንና በዚህ ገዳም ውስጥ ለስመቆየቷ ድርሳነ ዑራኤል በሰፊው ጽፎታል:: ለዚሁ ምሥክር ይሆን ዘንድ በዚህ ገዳም ውስጥ ብቻ በሚገኘው <u>ድርሳነ ማርያም</u> በተባለ መጽሐፍ ውስጥ የጌታችን ስደትና የእመቤታችን ቆይታ ሙሉ ታሪክ ተጽፎ ይገኛል:: እመቤታችን በዚህ ሥፍራ ፫ወር ከ፲ ቀን ቆይታለች::

የገዳሙ ስም የተሰየመው በዛኔ ግዜ ነው:: እመቤታችን በዚህ ገዳም ሳለች ይመራት የነበረው መልአክ እግዚአብሔር ለዮሴፍ በሕልም ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ሀገራችሁ ሂዱ ብሎ ስለ ነገረው ዮሴፍም ወደ ሕፃኑ በመቅረብ « <u>ፀአና በደመና</u> » በደመና ጫናት በማለቱ የገዳሙን ስም <u>ጣና ቂርቆስ</u> የሐይቁም ስም <u>ጣና</u> ተብሎ እንደቀረ አንድ ያገኘሁት ጽሑፋዊ መረጃ ያስረዳል::

በተለይ በጣና ቂርቆስ ገዳም ከ፫፻፳፰ - ፫፻፵፰ ዓ.ም በነገሡት ኢዛናና ሳይዛና ( አብርሀ ወአጽብሐ ) ዘመነ መንግሥት ከፍተኛ የክርስትና ማስፋፊያ ማዕከል ሆና ተገኝታ ነበር:: አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ( ፍሬምናጦስ ) ከሁለቱ ነገሥታት ጋር ወደ እዚህ ቅዱስ ሥፍራ በመምጣት የመጀመሪያውን የኦሪት እምነት ግዝረትን ሽረው አማናዊውን የክርስቶስን ሥጋና ደም በመሠዋት



የክርስትናን እምነት አስተምረውበታል::

አቡነ ሰላማ ጥምቀትን ብቻ ሳይሆን አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምባቸውን ጽላቶችን በታቦተ ጽዮን አምሳል በመቅረጽ በዚያን ጊዜ ክርስትና እምነት ይስፋፋባቸው ወደ ነበሩት ጣና ቂርቆስን ጨምር በትግራይ <u>አክሱም ጽዮን</u> በጐጃም <u>መርጦ ለማርያም</u> በወሎ <u>ተድባበ ማርያም</u> በመሳከ አራቱን አንድ አይነት ጽላቶች ታቦተ ጽዮን በማለት ሰይመው ይበካሉ:: አሁን አክሱም የምትገኘው የሙሴ ጽላት የሆነችው ታቦተ ጽዮን በዚህ ገዳም ውስጥ በተሰያዩ የከበሩ ድንጋዮችና ጌጣጌጦች ባሸበረቀ ህንጻ ውስጥ ለ፮፻ (ለድስት መቶ) ዓመታት ያህል መቆየቷን የሚያስረዱ መረጃዎችም አሉ::

በዚህ ገዳም ውስጥ ቅዱሳን ኖረውበታል:: በኦርአቸውም ክርስትናን ሰብከውበታል:: ጣና ቂርቆስ ገዳም ውስጥ ቅዱስ ያሬድ ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር ተቀምጧል:: በዚህ ቆይታ ውስጥም ለገዳሙ ትልቅ ቅርስ አውርሶ ነው ያለፈው:: ስጦታውም በሐገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኝ እና በራሱ የእጅ ጽሑፍ የተሰያዩ ዕጽዋትን በመጥመቅና በመቀመም በብራና ላይ የጻፈው ምልክት አልባ <u>የድጓ መጽሐፍ</u> ነው:: የእጅ መስቀሉ፣ ከሐር የተሠራ ካባው እስከ አሁን ድረስ ምንም የማስቀመጫ ቦታ በማጣታቸው ከወድያ ወዲህ ቢንገላቱም መቹም እስካሁን ድረስ አሉ::

በዚህ ገዳም ውስጥ ከ፪፻ - ፫፻ መናንያን ወንድና ሴት

መነኮሳት ይኖሩበት ነበር፡፡ ዛሬ ግን ያሁሉ በነበር ተተክቶ በትዝታ ብቻ ሲታወስ ይኖራል፡፡ ጽላት የተቀረጸላቸው፣ ቤተክርስቲያን በስማቸው የታነጸላቸው፣ ገድል የተጻፈላቸው እነ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ፥ ወለተ ጴጥሮስ ፣ ፍቅርተ ክርስቶስ ክብር የተቀበሉት በዚሁ ገዳም ውስጥ በሚገኝ የሴቶች ገዳም ውስጥ ነው፡፡

የቀድሞውን ህንጻ ቤተክርስቲያን አብርሀ ወአጽብሐ ናቸው ያነጹት፡፡ ነገር ግን አሁን የሚታየው ቤተ ክርስቲያን የታነጸው በደብረ ታቦሩ ራስ ጉግሳ ጊዜ በዳግማዊ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ ከላይ እንደገለጽኩት ቤተ ክርስቲያኑ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ሆኖ የፊተኛው ክፍል በስተ ምሥራቅ ሲሆን መግቢያው ደግሞ በስተ ምዕራብ በኩል ነው፡፡ በዚህ ጥንታዊ ገዳም ዕቃ ቤት ውስጥ የመግባት ዕድልም አጋጥሞኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ያየሁት ትዕይንት በሙሉ በቆምኩበት ደንዝዤ እንድቀር ነው ያደረገኝ፡፡

ከዚህ በታች ዘርዝሬ የማቀርባቸው ከ፭፻ - ፮፻ ዓመት ዕድሜ ያስቆጠሩ ቅርሶች በሙሉ በዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ካልደረሱላቸው በስተቀር ከጥቂት ዓመታት በኋላ ይህ ሁሉ ቅርስ በእይታ ፣ በብልና ፣ በምስጥ እንደሚጠፉ ከወዲሁ አስረግጬ ልናገር እወዳለሁ፡፡

<u>ከቅርሶቹ መካከል</u>፡- አምስት ዓይነት የኦሪት ሥርዓት የሚፈጸምባቸው እና የመሥዋዕት ማቅረቢያ ቁሳቁሶች ፣ የአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ካባ ፣ የእጅ መስቀል፣ የመጀመሪያው የአባ



ሰላማ ትርጉም የሆነው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፈ ሔኖክ ፣ መጽሐፈ ሐዊ ፣ የቅዱስ ያሬድ የእጅ መስቀል፣ ካባው፣ በራሱ እጅ የጻፈው ምልክት አልባው የደጓ መጽሐፍ፣ የወርቅና የብር መስቀሎች ጽዋዎች ፣ አንድ ሺህ ዘመን የሚሆናቸው ቅዱሳን ሥዕሎች፣ የስይፈ ሥላሴ ደራሲ የሆኑት የአባ ስብሐት ለአብ እና የሌሎች ቅዱሳንን ዐፅም የያዘ ከግንድ ተፈልፍሎ የተሠራ የእንጨት ሳጥን ወ.ዘ.ተ፡፡

እነዚህ በቅርብ ያውም ከላይ ተቀምጠው ያየኋቸው ናቸው፡፡ ከስር ሆነው በምስጥና በብል እየተበሉ ያሉትንማ ማንነታቸውም እየጠፋ ስለሆነ እንዲህ ሆኖአል ብሎ መናገሩ ትርፉ ከመቆጨት በቀር የሚመጣ ነገር ባለ መኖሩ ምን ይደረጋል፡፡

በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በኢያቄም ወሐና መንፈሳዊ የጉዞ ማኅበር አማካኝነት የተጓዙ ሁለት ወጣቶች እነዚያ ውድና ክቡር የሆኑ በሰው ሕይወት እንኳን ሲተኩ የማይችሉ ቅርሶች መሬቱን እንኳን ለሚነቶ የሚያደርግ በመጥፋቱ የተነሳ እንደ እዚያ ተጉሳቁለው በማየታቸው እራሳቸውን ለሥራ በማነሳሳት ሁለት ትላልቅ ቁምሳጥናች በራሳቸው ወጪ በመሸፈን <u>በብፁዕ አቡነ ኤልሳ የደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ</u> አማካኝነት ተመርቆ የተወሰኑ ያውም ካሉት ቅርሶች አንድ አራተኛ የሚሆኑት እንዲሰባሰቡ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን አሁንም ይቀራል፡፡ በተለይ በአንደኛው ክፍል ውስጥ ያሉት ቅርሶች ከመጨናነቃቸው የተነሳ ከእይታ ለመከላከል ሲሉ ከጣሪያው ማገር ጋር መጻሕፍቶችን

በሐንድ ሳይ በማድረግ በአየር ሳይ አንጠልጥለው ቢያስሩትም አይጡ በማገሩ ሳይ በመሄድ ገመዱን እየበጠሰ ቅርሶቹን በማውደም ሳይ ይገኛል፡፡ እናም በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም ያሳችሁ ምዕመናን በዚሁ ጉዳይ ሳይ ተነጋግራችሁ አንድ መፍትሔ ልትሰጡት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ሳይ ገዳሙን የሚያገለግሉት መነኮሳት አንዳንድ ምዕመናን ለረሀባቸው ማስታገሻ የሚሆን እህል ከባሕር ዳር ቢገዙሳቸውም ወደ ገዳሙ የሚወስዱበትን ጀልባ ስለማያገኙ እየተጉዱ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ብቻም ሳይወሰኑ መነኮሳቱ በጓሮአቸው እና በበጋ ደረቅ ከሚሆነው እና በጉመራ ወንዝ አካባቢ በሚገኘው መሬት ሳይ የሚዘሩትን እህል በሰንት መከራ ተንከባክበው ከአሣማና ከወፎች ሌት ተቀን ጠብቀው ለፍሬ ደረሰልን የሚሉት እህል በጓሮአቸው የሚገኘውን ምስጥ በሐይቀ ዳር ያሰውን ደግሞ በሐይቁ ውኃ ድንገት መሙሳት የተነሳ ስለሚጠፋባቸው የሰው ልጅ ሲያገኘው በማይገባ መከራ ውስጥ ወድቀው ይገኛሉ፡፡

ያም ሆነ ይህ መነኮሳቱ ይህ ሁሉ መከራ ቢደርስባቸውም እግዚአብሔር የፈቀደ እለት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅርስ የሚቆረቆር ሰው እንደሚልክላቸው እና ካሉባቸው ችግሮች በሙሉ እንደሚላቀቁ ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ግን መቼ እና ማን እንደሆነ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡



## ክርስቶስ ሠምራ ገዳም

ደብረ ኅንጉት ተብሳ የምትጠራውና በቅድስት እናታችን ክርስቶስ ሠምራ ስም የታነጸችው ቤተክርስቲያን የምትገኘው በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን በፎገራ ወረዳ ውስጥ በጣና ሐይቅ ዳርቻ ከጉማራ ወንዝ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ሳይ በሚገኝ ጉብታ ሳይ ነው፡፡

ወደ እዚህች ገዳም ለመምጣት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሁለት አማራጭ መንገዶችን መጠቀም የግድ ይሆናል፡፡

አንደኛው መንገድ በመኪና ትራንስፖርት ከባሕር ዳር ከተማ ተነስተው ወደ ጎንደር ከተማ በሚወስደው መንገድ ሳይ ከባሕር ዳር ከተማ በ፴፮ ኪሎ ሜትር ርቀት ሳይ ወደ ምትገኘው ሐሙሲት ከተማ ከሄዱ በኋላ የከተማዋን ምዕራባዊ አቅጣጫ ይዘው ጥንታዊውን የዛራ ሚካኤልን ወደ ቀኝ በመተው የጣና ሐይቅን ሳይርቁ በተራራ ሳይ ያሰውን የአባ እፍቅረነ እግዚእን ቤተክርስቲያን አልፈው የጉማራ ወንዝን ተሻግረው የሚደርሱበት ሲሆን፡፡

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በጀልባ ትራንስፖርት ከባህር ዳር ትራንስፖርት ድርጅት ተነስተው ጣና ቂርቆስ ወደብ ይወርዱና ወጣ ገባ በበዛበት ሸንተረር ከተጓዙ በኋላ ሰፊ ሜዳ ያገኛሉ፡፡ ይህ ሜዳ በክረምት ወራት በጣና ሐይቅ የውኃ ሙሳት የሚጥለቀለቅ ሲሆን በበጋ ወራት ግን የጣና ሐይቅ ስለሚጎድል ለእርሻ አገልግሎት እና ለከብቶች መሰማሪያነት የሚያገለግል ሥፍራ ነው፡፡

በሜዳው መሀል እንደደረሱ ግን በክርስቶስ ሠምራ ገዳም እና በጣና ቂርቆስ መካከል የሚገኘው የጉማራን ወንዝ ያገኙታል፡፡ የጉማራን ወንዝ መሻገር ደግሞ በቀላሉ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ወንዙ በላዩ ላይ ድልድይ ስላልተሠራለት በዋና ወይም በክርስቶስ ሠምራ በዓለ ንግስ ዕለት ከሣር በሚሠሩ ጀልባዎች /ድልድዮች/ ላይ በሚያስገርም ሁኔታ እየተረማመዱ ካለፉ በኋላ ቀሪውን ሜዳ አቋርጠው ይጓዛሉ፡፡

ወንዙን ተሻግረው ሜዳውንም አጋመሱት እንጂ ያሰቡት ቦታ አልደረሱም፡፡ ነገር ግን ወደ ገዳሙ መቃረብዎትን በቅርብ ርቀት ላይ የሚያዩት የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ያሸበረቀውን የቤተክርስቲያኒቱን ጣራ አያዩ ልብዎ በሐሴት እየተሞላ ገዳሙ ከሚገኝበት ጉብታ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ጉብታውን እንደወጡ በቀጥታ የሚገቡት አስፈላጊው እንክብካቤ ሳይደረግላቸው በበቀሉ የቡና ተክል ውስጥ ይሆናል፡፡ ይህንን የቡና ተክል እንኳን በዘመናዊ መልኩ የሚያዘጋጀውና የሚያበጅላቸው ሰው ቢያገኙ እነዚህ ገዳማውያን ችግር ባይም ባልወደቁ ነበር፡፡ ይህን የቡና ተክል እንዳለፉ እስካሁን ድረስ ከሩቅ ጀምሮ ሲመለከቱት የነበረውን የቅድስት ክርስቶስ ሠምራን ቤተክርስቲያን ያገኛሉ፡፡

የዚህች ቤተክርስቲያን ታሪካዊነት የተመሠረተው በ«**ገድለ ክርስቶስ ሠምራ**» ላይ ተጽፎ በምናገኘው ታሪክም ጥምር ነው፡፡ ገድሏ እንደሚያስረዳው ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ



በአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግሥት በሸዋ ክፍለ ሀገር በቡልጋ አውራጃ <u>**ቅዱስ ጌዮ**</u> በተባለ ቦታ ላይ በሀብት ከከበሩ ሁለት ደጋግ ባልና ሚስቶች የተወለደች ናት፡፡ የአባቷ ስም <u>**ደረሳኒ**</u> የእናቷ ስምም <u>**ዕሌኒ**</u> ይባላሉ፡፡ ክርስቶስ ሠምራ ከሕፃንነቷ ጀምሮ የደምግባት ያላት ቆንጆ ፣ አስተዋይ ፣ ደግ ሆና የእግዚአብሔርን ሕግጋት ተምራ ያደገች ናት፡፡ ገድለ ክርስቶስ ሠምራ በመቀጠል ባደገች ግዜ እና ለአቅመ ሔዋን በደረሰች ግዜ የንጉሡ ባለሟልና ነገዱ የአባ <u>**ፃሠርጋ**</u> ወገን የሆነውንና <u>**የአባ ኢየሱስ ሞአ**</u> ወገን ለሆነው <u>**ሠመረ ጊዮርጊስ**</u> ለሚባል ሰው በሕግ እንደተዳረች ይናገራል፡፡ ባሏም ሠምረ ጊዮርጊስ በምድራዊ ሀብት የበለጸገ ስለነበር ለሕጋዊው ባሏ አስራ አንድ ልጆችን ወልዳለታለች ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ግን ምንም ሳይጉድልባት እግዚአብሔርን ማገልገልዋን ቀጠለች፡፡ በዘመኑ የነበሩት ንጉሥ አፄ ገብረ መስቀል ግን በእሷ ላይ ያደረውን ኃይለ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለገለጸላቸው በጸሎት ታስባቸው ዘንድ በማለት በራሳቸው ቤተመንግሥት ውስጥ የሚያገለግሉትን አገልጋዮች አደባበይ በወጣች ግዜ በቀኝ በግራዋ ሆነው እንዲያጅቧት ፣ በቤቷም ውስጥ በትጋት ያገለግሏት ዘንድ ፲፪ አገልጋዮችን ይልኩላታል፡፡ ከእነዚህ አገልጋዮችም በተጨማሪ ፈረስ እና በቅሎ ከነስራታቸው እንዲሁም ለነገሥታት ሚስቶች የሚገባ ከሐርና ከወርቅ የተሠራ ልብስ እና የወርቅ ጫማ ይልኩላታል፡፡ እሷም ይህን የተላከላትን ሁሉ ምድራዊ ሀብት አልፈለገችም፡፡

ይሰቀሉም ለዓሳማዋ አንቅፋት እንደሚሆንባት በመገመት ሁሉን ነገር በመተው ለምነና መውጣቷንና ብዙ ተጋድሎ ማድረጓን በተለይ በጣና ባህር ውስጥ ቆማ ፲፪ ዓመት ሙሉ መጸለይዋን እና ወደ ሲዓል በመውረድም ለዲያብሎስ እንኳ ሳይቀር ምሕረት መለመኗን ገድሏ በሚገባ ያስረዳናል።

የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ሕንጻ ቤተክርስቲያን የታነጸው በራሷ በቅድስት ክርስቶስ ሠምራ እና በመነኮሳቱ ትብብር ድንጋዩን ፣ አፈሩን ቆፍረው ጭቃውን አቡክተው እንጨቱን ጠርበው በአባ ይስሐቅ መሪነት የታነጸ ነው። ቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ክብ ሆኖ ጠንካራ የጭቃ ምርጊት ያረፈበት ግድግዳ ያለው ነው። የሳር ክዳን የነበረው ጣሪያው እንኳ በቅርብ ግዜ ነው ወደ ቆርቆሮ ክዳንነት የተለወጠው። በውስጠኛው ክፍል ያለው ግድግዳ እድሳት ካለማግኘቱ የተነሳ የበሩ ማጠፊያ ያረፈበት የግድግዳ ክፍል በመሰንጠቁ ምክንያት በሩ ተገንጥሎ በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነው ያለው።

ታቦተ ሕጉ የሚያርፍበት መንበር እነ አባ ይስሐቅ እንዳሠሩት ነው እስከዛሬ ድረስ ያለው። ከዚሁ ከታቦተ ሕጉ ማስቀመጫ መንበር ጋር አብሮ ረጅም እድሜን ያስቆጠረ የሻማ ማብሪያ እና ከእንጨት የተሠራ መቅረዝም ይገኛል። የመንበሩን የላይኛውን ክፍል እየተመለከተ የሚገኘው ዓይናችን ዝቅ ብሎ ከመንበሩ ሥር ባለው ሥፍራ ላይ ሲመለከት ብፅዕናን የምንገኝበትና ያንንም በማየታችን ታላቅ መንፈሳዊ እርካታን



የምናገኝበትን የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ አስከሬኗ ያለበትን ሳጥን በመጐናጸፊያ ተሸፍኖ እናየዋለን። እዚህ ጋር ሆነው በደልዎንና ኃጢአትዎን ከማስፋቅ አንስቶ የፈለጉትን ነገር ሁሉ በአካል እንዳገኟዋት ቆጥረው እንደታማልድዎ ጸሎትዎን በንጹሕ ህሊና ማቅረብ ይችላሉ። ገዳሙን ያስጐበኙኝ አባት አባ ኪሮስ እንደነገሩኝ ከሆነ ከእግዚአብሔር ከተፈቀደለት ካህን በቀር አስከሬኗ ያረፈበትን ሳጥን ማንም ሲነካው አይችልም። ቢነካ እንኳ ጥሩ ሁኔታ እንደማይፈጠርለት ነው የነገሩኝ። ብዙ ምዕመናን አስከሬኗ ያረፈበትን ሳጥን ለመቀየር ብሉም በወርቅ እና በእንቁ ለመለወጥ ቢፈልጉም እስካሁን ድረስ ፈቃደ እግዚአብሔር ባለመሆኑ የተነሳ ሀሳቡ ሲፈጸም አልቻለም ነው የሚሉት አባ ኪሮስ የገዳሙ አስተዳዳሪ።

ከቤተክርስቲያኗ የውስጥ ጉብኝት በኋላ ያቀናሁት ከገዳሟ አስተዳዳሪ ከአባ ኪሮስ ጋር በመሆን ወደ ገዳሙ ዕቃ ቤት ነበር። ዕቃ ቤቱ የሚገኘው ከቤተክርስቲያኑ በስተ ደቡብ አቅጣጫ ላይ ነው። በዚህ ዕቃ ቤት ውስጥ የሚገኙት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ቅርሶች ከፍተኛ ውድመት ነው የገጠማቸው። በአብዛኛው ቅርሶቹ የተጐዱት መሬቱ አፈር በመሆኑ እና ቅርሶቹም በመሬት ላይ ያለምንም ንጣፍ በመቀመጣቸው ምክንያት ለአይጥና ለምስጥ በመጋለጣቸው ነው። በዚያች ጠባብ የምድር ቤት ውስጥ ፲፭ ያህል መጻሕፍትን የምትይዝ መደርደሪያ

ብትኖርም ከቅርሶች ብዛት የተነሣ መፍትሔ ሁና ቀሪዎቹን ቅርሶች ከመጥፋት ሊያድናቸው አልቻለም፡፡

እነዚህን በሰው ሕይወት እንኳ ሲተኩ የማይችሉ ቅርሶች የጻድቋ ወዳጅ የሆኑ ምዕመናን በፍጥነት ካልደረሱላቸው በቀር ከጥቂት ዓመታት በኋላ እነዚህ ውድና ብርቅ የሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ውድ ሀብቶች በቀላሉ ሲጠፉ እንደሚችሉ ላሳስብ እፈልጋለሁ፡፡

<u>ከእነዚህ ቅርሶች መካከልም</u>

« <u>ለተክለሃይማኖት በጻማሁ ወለአፈወርቅ ብፁዕ እስእለኪ ክርስተስ ሠምረ ማዕከለ ገቡእን ለብ እምወይን ለባልኪ ለጸታየርከ ነፍስኪ ጽሙዕ ወረደ ለኪ ሰኮነ በእደ ሚካኤል ጽዋዕ ጽዋዕኪ ውዕቱ ጽንእት</u> » ተብሎ በገድሏ ላይ የተጻፈ ማስረጃ ያለው እና <u>ከሰማይ የወረደ ጽዋ</u>፡፡ ይህ ፅዋ በግራኝ መሐመድ ወረራ ወቅት ግራኝ ወደ ገዳሙ መጥቶ ጥቃት ፈጽሞ ስለነበር ይህ ጽዋ ከሰማይ የወረደ መሆኑን ስለሰማ <u>ከሰማይ ከመጣ ወደ ሰማይ ይመለስ</u> ብሎ ወደ ሰማይ ቢወረውረው ከመሬት ሰሰወደቀ በአንድ ወገኑ የተሰበረ ነው፡፡

- ከብረት የተሠራው የእናታችን የቅድስት ክርስቶስ ሠምረ <u>በትረ መስቀል</u>፣
- የጻድቋ እባት የአባ ደስሐቅ <u>በትረ መስቀል</u> ፣
- በአባ ደስሐቅ ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሠራ <u>ቀንዲል</u>፡፡



- መደባቸው ያልተለየ <u>አሬት ለክሊሳት</u>፡፡
- የአጼ አድያም ሰገድ እያሱ የክብር ዕቃዎች እና ከንጉሡ የማይለየው <u>የቅዱስ ገላውዲዎስ ታቦት</u>፡፡
- የአንበሳ ምልክት ያለበት ካባ <u>ቀንደ መለከት</u>፡፡
- ቁጥራቸው በርከት ያሉ የብራና መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቋቁሞ ምዕመናንን ገዳማትን በማስጐብኘት ላይ የሚገኘው የኢያቄም ወሐና መንፈሳዊ የጉዞ ማኅበር ወደ እዚህች የተቀደሰች ሥፍራ ምዕመናን እንዲሄዱ በማድረግ ቦታው በዓመት አንድ ጊዜ ግንቦት ፲፪ ቀን የሚከበረውን በዓሏን በታላቅ ድምቀት እንዲከበር ከማድረጉም ባሻገር ለገዳሟ አገልግሎት እና በዓመት አንድ ጊዜ የሚወሰዳቸው ምዕመናን የሚያርፉበት ሁለት ትላልቅ አዳራሾችን ሠርቶ አስረክቧል፡፡ ከዚህም ሌላ መኪና ወደ ገዳሟ እንዲገባ ለማስደረግ ለተጀመረው የመንገድ ሥራም የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተረፈ ይህች ገዳም በዓመት አንድ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር የሚጐበኟት ባለመኖሩ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለመንገድ ሥራዋ የእርዳታ እጁን እንዲዘረጋ የገዳሟ አባቶች የድረሱልን ጥሪያቸውን ያሰማሉ፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

## ሪማ መድኃኔ ዓለም

ሪማ መድኃኔ ዓለም ገዳም የተመሠረተው በአፄ ይስሐቅ ዘመን መንግሥት ከደብረ ሊባኖስ በመጡ አባ ኖም በተባሉ መነኩሴ አማካኝነት ነው:: ገደሙ የሚገኘው በደራ ወረዳ በምዕራፊት ማርያም ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ በጣና ሐይቅ ደቡባዊ ምሥራቅ አቅጣጫ ነው:: የሪማ መድኃኔ ዓለም ገዳምን በደቡብ አቅጣጫ የምዕራፊት ማርያም ቀበሌ ገበሬ ማኅበር በስተ ሰሜን እና ምዕራብ አቅጣጫ የጣና ሐይቅ ያዋስኑታል:: የጣና ሐይቅ ከምዕራፊት ማርያም እስከ ገደሙ ድረስ በመሃከላቸው በግምት [illegible] ሜትር ያህል ተንጣሉ ይገኛል::

ዛሬ ሪማ የሚባለው ስሙ የወጣው የገደሙ መሥራች አባ ኖም አፄ ይስሐቅን ቀርበው « **ንጉስ ሆይ የምሰግድበትን ሪም ታህል መሬት ስጠኝ** » በማለታቸው ምክንያት ሪም / ትንሽ / የሚለውን ቃል ከግዜ ብዛት ሪማ የሚለውን ቃለ ፈጥሮ አሁን ሪማ በመባል ገዳሙ እየተጠራ ይገኛል::

ገዳሙን ታሪካዊ የሚያደርገው የገዳሙ መሥራች የአባ ኖም እና የሌሎቹ አንዳንድ ሰዎች ዐፅም ሳይፈርስ በቤተመቅደሱ ውስጥ ይገኛል:: በዚህ ገዳም ውስጥ አቡነ በርቶሎሜዎስ ፣ አፄ ሰርፀ ድንግል ተቀብረዋል:: ብዙውን ግዜ ይህ ገዳም ራቅ ያለ ስለ ሆነ እርዳታ የማግኘቱ ነገር ከሌሎቹ ገዳማት ጋር ስናወዳድርው ምንም የለውም ማለት ይቻላል:: ገዳሙ የ[illegible] ዓመት ባለጸጋ ከመሆኑም ባሻገር የታሪክ ማህደርም ጥምር ነው::



## ደብረ ወርቅ ማርያም

ቤተክርስቲያኒቱ ከአዲስ አበባ በስተሰሜን በሞጣ ባሕርዳር በሚወስደው መንገድ ከአ.አ [illegible] ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የእናርጅ እናውጋ ወረዳ ማዕከል በሆነችው ደብረወርቅ ከተማ ውስጥ ትገኛለች:: ይህች ቤተክርስቲያን ከከተማዋ በስተ ምሥራቅ መሶበ ወርቅ በመሰለው ተራራ ቁንጮ ላይ ሕሊናን በሚመስጥ ሁኔታ ቀልጥ ብላ ትገኛለች:: ከመንገዱ እስከ ተራራው ጫፍ ደረጃ ለለተሠራበት የግድ [illegible] ደረጃዎችን እየቆጠሩ መውጣት ነው እንጂ ተራራ ላይ ለለሆነች ብቻ ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ለመግባት ጋራ አያስቢጥጥም:: ዋናው የግቢ በር እንደ ሌሎቹ ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በስገነት መልክ በተሠራ ፎቅ ቤት ሥር የሚያልፍ ነው:: ቤተክርስቲያንዋ የቤተ ንጉሥ ( ክብ ) ቅርጽ ኖሯት ዙሪያዋን በዓርባ አራት ዓምድ የተዋቀረች ናት:: ውስጥዋ በጥንታውያን ሥዕሎች የተሞላ ነው:: ከመቅደሱ በር ግራና ቀኝ ሁለት ጥንታውያን አልጋዎች ከነመደገፊያቸው ( ትራስ ) ይገኛሉ:: እነዚህ አልጋዎች ከቀደምት አባቶች የተበረከቱ ሲሆኑበአሁኑ ግዜ ግን ለንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫነት ይረዳሉ::

ደብረ ወርቅ በዘመነ ኦሪት በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ምኩራባት አንዱ ተሠርቶባት እንዲያውም የዕቆብ የተባለ ምሁረ ኦሪት ሕገ ኦሪትን ሲያስተምርባት የቆየች ቦታ ናት:: ቅዱሳን ነገስታት አብርሀ ወአጽብሐ ከአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን

ክርስትናን ተምረው ከተጠመቁ በኋላ በመሳው ኢትዮጵያ ስለብኩት ሲወጡ ከመርጡ ለማርያም ቀጥለው የመጡት ወደ ደብርወርቅ ነበር። አብርሀና አጽብሐም መርጡ ለመርያምን ካነጹ በኋላ ደብረወርቅን ለመቀጠል ሲያስቡ ሳለ ዕረፍተ ዘመን ስለገታቸው አደራውን ለልጃቸው ለአስፍሃ ትተው አለፉ።

ንጉሥ አስፍሃም አደራውን ጠብቆ በ፲፯፻፳ዎቹ ዓ.ም ውስጥ ቤተክርስቲያኗን በወርቅ አስጌጦ በመሥራት ታቦተ ቅድስት ማርያምን አስገብቶላታል። ደብረ ወርቅ የተባለው ስም የተሰጣትም በሁለት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል። የመጀመሪያው ንጉሥ አስፍሃ ቤተክርስቲያኗን ሲያሠራ ሲመጣ በዚህች ቦታ ላይ የወርቅ መሰሳል ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሎ በራዕይ ስላየ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሸዋ ወደ ጐጃም ሲጓዙ ግንቦት ፲፪ ቀን በ፲፯፻፺፮ ዓ.ም በድንገት ሞተው ደብረ ወርቅ የተቀበሩት የአፄ እስክንድር ልጅ ልዕልት ማርታ የአባቷን መቃብር ለትጎበኝ በመጣችበት ወቅት በቤተ ክርስቲያኒቷ ውስጥ በብዙ ሕዝብ ተከባ መንቀሳቀሻ ስላጣች በአንድ አቅጣጫ ገንዘብ ወይም ወርቅ በመበተን መንገድ እንዲለቀቅላት ስላደረገች በዚህ የተነሳ ደብረ ወርቅ ተባለች የሚሉ አሉ። ደብረወርቅ ማርያም ከመርጡ ለማርያም ጋር ለአካባቢዋ የክርስትና ማዕከል በመሆን ብዙ ሲቃውንትና ምዕመናን እያፈራች ለ፲፪ ዓመታት ያህል እንደቆየች የዮዲት የመከራ ዘመን ደረሰ።



የደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም ከተመሠረተ ከ፩፻ ዓመታት በኋላ በ፰፻፶ ዓ.ም ዮዲት ጉዲት ክርስትናን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት ስትነሳ ካቃጠለቻቸው አድባራት አንድዋ ደብርወርቅ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ናት። አገልጋዮቿ ታቦቷን ይዘው ለ፵ ዓመታት ያህል በየበረሃውና በየዋሻው ተንከራተዋል። በኋላም ዮዲት ጉዲት ስትሞት ወደ በታዋ በመመለስ ጥንታዊው ቤተክርስቲያን ስለተቃጠለ ለ፰፻፹፱ ዓ.ም መቃኛ ሠርተውላት እስከ ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ተቀምጣለች ።

በ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን አባ ሠርፀ ጴጥሮስ የተባሉ አባት ከአነብሴ አካባቢ ተነሱ። በምሥራቅ ጐጃምም በዘመነ ዮዲት ተዳክሞ የነበረውን የክርስትና ትምህርት ይበልጥ አስፋፉት የደብረ ወርቅም ዝና በርሳቸው የተነሳ እየገነነ መጣ በዚያን ጊዜ የነበሩትም አፄ ዳዊት አባ ሠርፀ ጴጥሮስን አስጠርተው ካማከሩዋቸው በኋላ ደብረወርቅ ማርያም እንደገና እንድትታነፅና ከመቃኛ እንድትወጣ አድርገዋል። አፄ ዘርዓ ያዕቆብም በዘመናቸው ከአረማውያን ጋር ሲዋጉ ጦር ቢያይልባቸው የአባሠርፀ ጴጥሮስን ዝና ሰምተው ስለነበር እግዚአብሔር ይረዳቸው ዘንድ እንዲጸልዩላቸው ሳኩባቸው እግዚአብሔርም የቅዱሱን ምልጃ ተቀብሎ ለአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኃይለ መዊዕ ( የማሸነፍ ኃይል ) ስለሰጣቸው ከድል መልስ የጦር ልብሳቸውን በሙሉ ለመታሰቢያነት ለደብረ ወርቅ ማርያም ለከውላት እስከዛሬ ድረስ በዕቃ ቤትዋ ይገኛል። በአፄ ዳዊት ዘመን በጥቃ

የተሠራችው ደብረወርቅ የግራኝን የመከራ ዘመን አልፋ በአፄ ገላውዴዎስ ጊዜ በኖራ ታድሳለች::

በቤተክርስቲያኗ ታሪክ ሲባው የሚታወሱት ሰው ደጉ ዮሐንስ ናቸው:: ደጉ ( ጻድቁ ) በጸሎት ሳይ እንዳሉ እመቤታችን በራዕይ ተገልጣ የደብረወርቅ ማርያምን ሰዓታት ቋሚ ስታመስክታቸው ያያሉ:: እሳቸውም ባዩት ነገር ተገርመው ሳይውሉ ሳያድሩ ወደ ደብረወርቅ መጡ:: እንደደረሱም ሰዓታት ቋሚውን ጠርተው « **በል እግርህ እስከቻለ በዙሪያህ ወዳለው ምድር ውጣ** » አሉዋቸው እኝህ አባትም እስከቻሉት ድረስ ተጓዙ ደጉ ዮሐንስም ያንን መሬት ለአገልጋይዋ ርስት አድርገው ሰጥተዋል ከዚህም ሌላ እኚሁ ንጉሥ በ፲፯፻፳ ዓ.ም ወይኑቱ ለተባለችው የእመቤታችን ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ማስቀመጫ ይሆን ዘንድ በጉንደሩ አብያተ መንግሥታት የሕንጻ አሠራር ጥበብ ያሳነጹትን ባለ አንድ ደርብ ዕቃ ቤትም ሠርተው አበርክተውላታል:: ታዲያ ይህ ለ፲፱፻፴፮ ዓ.ም የቆየው ዕቃ ቤት እሳት ከሳ ሆኖ አሁን ድረስ ብዙ ነዋየ ቅድሳት እንደያዘ ይገኛል::

የደብረወርቅ ማርያም ቤተክርስቲያን ከዚህ በኋላ የእድሳት እድል የገጠማት ሁለት ጊዜ ነው:: የመጀመሪያው በጉንደሩ ንጉሥ በአፄ ተክለ ጊዮርጊስ ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ግዜ ነው:: አፄ ተክለ ጊዮርጊስ በዘመናቸው የገዳሟን ቅኔ ማኅሌትና ቀመ



ብእሲዋችን አሰተከሰዋል:: አፄ ኃይለ ሥላሴም የቤተክርስቲያኗን ቅኔ ማኅሌት በሰሚንቶ አሠርተው አሁን በምትገኝበት ሁኔታ ያሳደሷት እሳቸው ናቸው::

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜም ጠላት በገዳሟ ላይ ተደጋጋሚ የቦምብ ጥቃት ቢያደርስም ቤተ ክርስቲያኗ ምንም ችግር ሳይደርስባት መቅረቷንና ከተተኮሱባት የመድፍ ጥይቶች አንዱ በቅኔ ማኅሌቱ ህንጻ ውስጥ ተሰክቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይታይ እንደነበር የአገሬው ተወላጆችና የደብሯ መነኮሳት የሚናገሩት ሀቅ ነው::

ለዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ያደሉ ነበር የሚባሉት የጐጃምና የከፋ ንጉሥ የነበሩት ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከገዳሟ ጋር የተያያዘ ታሪክ አላቸው:: ታሪኩም እንዲህ ነው:: ንጉሡ በመጨረሻ ዘመናቸው በጠና ታመው ዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ቢጠመቁም መፍትሔ ሰላላገኙ ወደ ደብረወርቅ ያመራሉ:: ካህናቱንም ጠርተው በድያታለሁ እና ይቅርታ እንድጠይቃት የሉቃስን ሥዕለ ማርያም አምጡልኝ ብለው ይጠይቃሉ:: ካህናቱም አበው በደነገጉት መሠረት በዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜ በሚከበሩ በዓላት ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ጊዜ ሥዕለ ማርያምን ማውጣት እንደማይቻል ካህናቱ ቢገልጹላቸውም ንጉሡ « እሷስ ያለ እኔ ተከበረች ? » « እኔስ ያለ እሷ መኖር እችላለሁ? » በማለት በጣም ተቆጥተው በኃይለ ቃል ሲስተናገሩ ሥዕለ ማርያሟ ወጥታ ወደ አረፉበት ድንኳን ተወሰደችላቸው:: ንጉሡም ዓይናቸውን

በምትፍለቀለው ሥዕለ ማርያም ላይ እንዳሳረፉ ከመቅጽበት ህይወታቸው ታልፋለች። ቀደም ሲል በሰጡት የኑዛዜ ቃል መሰረትም አስከሬናቸው ወደ ደብረማርቆስ ተወሰዶ በክብር ሲያርፍ የራሳቸው የወርቅ ዘውድ፣ የባለቤታቸው የወርቅ ካባና የተለያዩ የክብር ዕቃዎች በገዳሚ ዕቃ ቤት በቅርስነት ተቀምጠው ይገኛሉ።

በመጨረሻም ለመግለጽ የምፈልገው ደብረወርቅ ደርሰው ገዳሟን የመጐብኘት ዕድል ከገጠመዎት በዕቃ ቤቱ ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ንዋየ ቅድሳትና የታሪክ ቅርሶችን ያያሉ።

* ከ፳፻ በላይ የሆኑ ከተለያዩ እንስሳት በተገኙ ቆዳዎች ላይ የተጻፉ የብራና መጻሕፍት፣
* የብር ካበሮ እና በወንጌላዊው ሉቃስ እጅ የተሣለችውን « ወይኒቱ » የተባለችውን የእመቤታችንን ሥዕል፣
* ዘጠኝ ክንድ ያህል ርዝመት ያለውና ከካህናት በቀር ማንም የማይነካው የአባ ሰርፀ ጴጥሮስ መቋሚያና ከዕፅ የተሠራ የእጅ መስቀላቸው።
* ራስ በዛብህ ያበረከቱተት ወርቅ የራስ ቁር፣
* አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመናቸው በጦርነት ጊዜ የማረኩት ከብረት የተሠራ ልብስ እና ሌሎችንም ብርቅና ድንቅ ቅርሶች የማየት እድል ያገኛሞታል ። የሚያስደንቀው ዕቃቤቱንም ሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱን ንብረት የሚጠብቀው የንብ ሠራዊት መሆኑ ነው። ጣሊያኖች ያን የተሰመደውን የቅርስ ዘረፋ ለማካሄድ ወደ



ቤተክርስቲያኒቱ በመጡ ግዜ ባሳሰቡት ሰዓት ቅርሱን ሳይነኩ በንብ ሠራዊት ተነድፈው ሰወሬ ነጋሪ እንኳን ሳይተርፉ ማለቃቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ከምዕመናን ከፍተኛ ድጋፍ ካልተገኘላቸው በስተቀር ከገዳሟ በስተደቡብ የምትገኘው የእናቴ ሐና ገዳም እንኳን አሰታዋሽ በማጣቷ እየፈራረሰች ትገኛለች። ሌላው ከቤተክርስቲያኑ በስተሰሜን ከተራራው ግርጌ ወደ ሞጣ በሚወስደው መንገድ በስተምሥራቅ የሚገኝ ብልየ ልዩ የውስጥ ደዌ የተያዙትን ማንኛውንም ዓይነት በሽታዎች መነቅሎ በማውጣት የሚታወቅም የአባ ሠርፀ ጴጥሮስ ጸበልም የሚገኘው እዚሁ ነው።

**የጻድቁ በረከት አይለየን ጥቅምት ፲፪ ቀንም የአባ ሠርፀ ጴጥሮስ በዓል በታላቅ ድምቀት ይከበራል።**

## መርጡ ለማርያም

መርጡ ለማርያም ቤተክርስቲያን የምትገኘው በምሥራቅ ጐጃም ዞን በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ መርጡለ ማርያም የገጠር ከተማ ውስጥ ነው:: ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸውና ከምትደነቅባቸው ጥንታዊያን ሰብያተ ክርስቲያናት መካከልም አንዷ ናት:: ስለዚህች ቤተክርስቲያን አቦታዋ ድረስ በመሄድ በቦታው የሚገኙትን ሰበው ስለቦታው እንዲያስረዱኝ በጠየቅኳቸው መሠረት በቃል አስረድተውኝ ነበረ:: ነገር ግን በተሻለ መልኩ ከተለያዩ መጽሔቶችም ያገኘሁትን ታሪካዊ መረጃ ጨምሮ ከራሷ ከመርጡለ ማርያም ገዳም ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ያገኘሁት የበለጠ ለጽሑፌ ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘሁት ሰፋ አሰፍ አያልኩ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ::

መጽሐፉ ስለ ገዳሟ አመሠራረት ከመጀመሩ በፊት ከአበው፣ በቃልና ፣ በጽሑፍ ትውውቅ ያገኘሁት ነው ብሎ ከቃረበው ታሪክ በመነሳት ከአንዳንድ ቦታዎች በስተቀር ሙሉ ስሙሉ ማለት ይቻላል ጽሑን እንዳለ ለቅርቤዋልሁ ::

« የአባይን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ልዩ ልዩ ነገዶች በልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ቦታዎች ነዋሪ መሆናቸው እንደማያጠያይቅ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ::

በዚህም ጥንታዊያን የሰፈሩ አካባቢዎች በቀድሞ አጠራር በጎጃም ክፍለ ሀገር በሞጣ አውራጃ በእነብሴ ወረዳ ከአባይ ወንዝ በግምት ፴፭ ኪሎ ሜትር ርቃ በወይና ደጋ የአየር ንብረት



ክልል የተቆረቆረችው በዓረፍተ ዘመን ሂደት የስም መለዋወጥ የተሰጣት ጥንታዊቷ ቦታ መርጡለ ማርያም ናት::

ከሁለተኛው ሺህ ዓመተ ዓለም ጀምሮ ነገደ ካም የኩሽ ልጆች አባይን ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በመርጡለ ማርያም ቦታ መንደራቸውን መስርተው ከ፲፯፻፵ ዓመታት ያላነሰ ጊዜ እግዚአብሔርን በሕገ ልቦና ሲያመልኩ ኑረዋል:: ወደ ቦታው ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት ችግር ሳይደርስባቸው በሰላም ስለኖሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ቦታውን « **ሀገረ ሰላም** » ብለውታል::

አያይዘም ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ በጆሮዋ ትሰማ የነበረውን የሰሎሞንን ጥበብ በዐይኗ ለማየት ወደ አየሩሳሌም ደርሳ ተመልሳለች:: በዚህም ጊዜ ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳ ኖሮ ኢትዮጵያ እንደደረሰች ሃማሴን ( ማአበል ) ከተባለው ቦታ ወልዳዋለች:: አሳድጋም የ፳፪ ዓመት ወጣት ሲሆን ወደ አባቱ ሀገር ወደ ሰሎሞን መልሳ ላከችው:: ሰሎሞንም ቀዳማዊ ምኒልክን ተቀብሎ የአብራይስጥን ቋንቋ የኦሪትን ሕግና ሥርዓት ለ፫ ዓመታት ካስተማረው በኋላ ከዓሰራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ፲፪፻ ሕዝብ ማለት ፫፻ ሌዋውያን ካህናት ፣ ፫፻ ጠበብተ ኪራሞስ ፫ ፻ ከበኩረ እስራኤል እንዲሁም ከእስራኤል ፈረሰኞች፣ ፫፻ ጨምሮ ከታቦተ ጽዮን ጋር ወደ ኢትዮጵያ ላከው::

ቀዳማዊ ምኒልክም ኢትዮጵያ እንደደረሰ መንግሥትን ከእናቱ ማክዳ ተቀብሎ በኢትዮጵያ ነገሠ:: አብረውት የመጡ

ነገደ እስራኤልንም በየሙያቸው ደልድሎ በየግዛት ሀገሩ ሳካቸው:: ፈረሰኞችን በአስተዳደር ሌዋውያን ካህናትንና ጠበብተ እስራኤልን ደግሞ ስመናር የሚያስችሳቸውን መሣሪያ ከማምረት ባሻገር ምኹራበ ኦሪትን እንዲሠሩና እንዲያገለግሉ መደባቸው::

በጊዜው ጎጃምን እንዲያስተዳድር ከጭፍሮቹና ከሌዋውያን ካህናት ጋር ወደ ጎጃም የተሳከው አለቃ ኤፍሬም ነበር:: ኤፍሬም ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ጎጃም ምድር እንደገባ ርእስ ከተማውን ነገደ ካም ቀደም ሲል ስፍረውበት በነበረችው **<u>ሀገረ ሰላም</u>** (**<u>መርጡለ ማርያም</u>**) አደረገ:: አብረውት የመጡት ስለቆችንም በመላው ጎጃም አየደለደለ ሳከ:: ለምሳሌ በከተማው ዙሪያ ከደለደሳቸው ብንጠቅስ ለነብሬ ፣ እነብሴ ሲሶ እነሴ፣ ሁለት እጁ እነብሴ ተብለው የሚጠሩትን በአካባቢው ደልድሎ ሥራውን ሲሠራ ኖረ:: ይህ አካባቢ እስካሁን የሚጠራው ተደልድለውበት በነበሩት ነገዶች ስም ሆኖ እስካሁን ድረስ መለያ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል::

ጠበብተ እስራኤልና ሌዋውያን ደግሞ የኦሪትን ሕግና ሥርዓት ጠብቀው በሐገረ ሰላም ( መርጡለ ማርያም ) ቤተ ምኹራብ እንዲሠሩ አደረገ:: በአካባቢው በሰፈሩ ለለቆች ትብብር ቤተ ምኹራብን ሠርተው ሲጨርሱ ለሁለተኛ ጊዜ የቦታወን ስም « **ጽርኃ አርያም** » ብለው ሰይመውታል::

ከዚህ ዓረፍተ ዘመን ጀምሮ ሕገ ኦሪትን በመፈጸም የእግዚአብሔርን ስም ሲያመሰግኑ ሲያስተምሩ እስከ ዘመነ ሐዲስ



( አብርሀ ወአጽብሐ ) እስከተነሱበት ጊዜ ድረስ በቤተ ምኹራብ ሲያገለግሉ ኖረዋል::

በቀለምንጥንያ መንግሥት ቀንለጣ በኢትዮጵያ ደግሞ አብርሀ ወአጽብሐ ነግሠው በነበረበት ፫፻፴ ዓ.ም በከሳቴ ብርሃን ሰላማ ትምህርት በአክሱም ጽዮን ፣ በተድባበ ማርያምና በመርጡለ ማርያም እንዲሁም በጣና ሚካኤል ( ጣና ቂርቆስ ) በነዚህ ሕገ ኦሪት ሲፈጸምባቸው በነበሩት የኦሪት ምኹራባት ላይ ሐዲስ ወንጌልም ተሰበከ:: በኋላም ቤተ ምኹራባት ተሠርቶባቸው በነበሩ ቦታዎች የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መሠረት በፍቁራን አበው አብርሀ ወአጽብሐ ዘምስለ ሰላማ ቡራኬ ተጣለ:: በዚህ አጋጣሚ ተአበው « ፈለገ ግዮን አብርሀ ወአጽብሐ ዘምስለ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ወበጽሁ ምድረ ጎጃም ወሐንጽዋ ለመርጡለ ማርያም በወርቅ ወበእንቁ » « አብርሀና አጽብሐ » ከሰላማ ከሳቴ ብርሃን ጋር በአባይ ወንዝ ተሻግረው ጎጃም ምድር ደረሱ:: የማርያምን ቤተመቅደስ ዓምዶችና ዓረፍቶች በወርቅ በእንቁ ሠሩ በማለት የመርጡለ ማርያም የታሪክ መጻሕፍት ገድለ አብርሀና አጽብሐ እንዲሁም ገድለ ሰላማ ያስረዳሉ::መጻሕፍቱም በዚህች ደብርና በአክሱም ጽዮን ይገኛሉ::

ከታሪኩ እንደምንረዳው ነገሥታቱን ጳጳሱ ሰላማ ጽርኃ አርያም ለምባ እንደደረሱ የስምባውን አቀማመጥ እና የቤተ - ምኩራቡን ውበት ዙረው ተመልከተው ሲጨርሱ ቤተ መቅደሱ ቦታውን እንደያዘ ለታሪክ መዘከር እንዲቆይ ወሰኑ::

ስለዚህም ከጽርሃ አርያም አምባ በስተምሥራቅ አሻጋሪ አብርሀ ኮረብታ ላይ ቤተክርስቲያን ለመሥራት መሠረት ጀመሩ በሥራ ተጀምሮ እንዳለ መሬቱ በሚቆፈርበት ላይ እሳት በመትፋት አሳስቆፍር በማስቱና የተሠራው በመስጠሙ ቤተክርስቲያኑን ከዚህ ቦታ መሥራቱ ፈቃደ እግዚአብሔር አለመሆኑን እኒህ ቅዱሳን ነገሥትና አቡነ ሰላማ ስለተረዱ ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ በሚከተሉት የተለያዩ ቦታዎች ሱባኤ ገቡ፡፡

የኦሪቱ ሊቀ ካህናት <u>አብኒ</u> በተባለው ቦታ <u>የሐዲሱ ሹም ሐዲስጌ</u> ጻጳሱ <u>ከሳቴ ብርሃን ሰላማ</u> <u>ሰሳምጌ</u> ንጉሥ <u>አብርሀ አብርሂ</u> ንጉሥ <u>አጽብሐ</u> <u>ዜነም</u> ከተባሉት ቦታዎች ለሦስት ዕለታት በየበአታቸው ጸንተው እንዳሉ በሦስተኛው ሌሊት ሁሉንም እግዚአብሔር በራዕይ አሳያቸው፡፡ ራዕዩም ዓሰራ ሁለት በሮች ያሳት አንድ ዓምደ ብርሃን የቤተ መቅደሱን መሠረት ከጀመሩበት አብርሃሀኮረብታ ተነስታ አያበራች ከኦሪቱ ቤተመቅደስ ጋር ተያይዛ ከጽርኃ አርያም አምባ ላይ አረፈች፡፡ ንጉሥ አጽብሐም ቀደሞ ወደ አባ ሰላማ በመሄድ ያየውን ራዕይ ተናገረ ሌሎቹም መጥተው ያዩትን ተናገሩ፡፡ አባ ሰላማም ይህንን ራዕይ ያዩ መሆናቸውን ነገሯቸው ሁሉም በአንዲት ሌሊት አንድ ዓይነት ራዕይ አዩ፡፡

በዚሁ ምክንያት አጽብሐ በመጀመሪያ መጥቶ ራዕዩን ስለተናገረ ሱባኤ የገቡባቸው ቦታ <u>ዜና /ዜነም</u> ተባለ፡፡ ሌሎቹ አባቶችም ሱባኤ የገቡባቸው ቦታዎች በየስማቸው በመጠራት



ማረ መዘከሮች ሁነው ሕያውና ታሪካዊ ሥራቸውን ለትውልድ ታውቁ ይኖራሉ፡፡ ተጀምሮ የቀረው የመሠረት ሕንጻም ባቢው ህዝብ ግንቡ <u>ወሬ ግንብ</u> ይባላል፡፡ ማስትም ሳይሠራ ምሮ በወሬ የቀረ ግንብ ለማለት ነው፡፡

ቀጥሎም አምላካችን እግዚአብሔር በአመለከታቸው ደ ብርሃን መለቀል ቅርጽ <u>ቢታኒያ</u>፤ <u>ሰሳምጌ</u>፤ <u>ሐድስጌ</u>፤ <u>ጅ</u>፤ <u>አብኒ</u>፤ <u>ዜነም</u>፤ አብርሂ በተባሉት ታሪካውያን ቦዎች መካከል እንደመሶብ ተከባ በምትገኝ ጽርኃ አርያም ላይ ከኦሪቱ መቅደስ ጋር አያይዘው ከግራና ከቀኝ ፊትም አስፍተው መሠረቱን በመጣል የሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን ጀምሩ፡፡ ሥራውም በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ቀን ተሠርቶ ሰው በሦስት እጥፍ አያደገ አድሮ በመገኘቱ ፲፪ ቤተ መቅደስ በጥራትና በፍጥነት ተሠራ፡፡

ዓመዶቹንና ዓረፍተ ቤተመቅደሱን ግን አጅግ በተዋበ ንጋይ ሐረግ ቅርጽ አስጊጠው በወርቅና በዕንቁ አነጹት፡፡ ፍሩ ግራና ቀኝ ደግሞ ከድንጋይ የተቀረጹ የካህናተ ሰማይ ል መንበረ ጸባዖትን ሲያጥኑ በሚያሳይ ሁኔታ ጽና ጽናቸውን ው ከሕንፃው ጋር በቅርጽ ታንጸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ በሕንጻው ልዩ ልዩ አካል የሚገኙ ከድንጋይ ቀረጹ የመላእክት ሌሎችም ውብና አስደናቂ የሆኑ መልካችን ህሊና የሚስቡ ተዓምራዊ የሐረግና የአበባ ቅርጾች ኙበታል፡፡ እነዚህም በልዩ ልዩ ሕብር ከድንጋይ የተቀረጹ

የሐረግ ቅርጾች የቀደምት አበውን የፈጠራ ችሎታና ሙያን ለመግለጽ ሆን ተብሎ በልዩ መሣሪያ እንደተ ያስቀረጸው የጣት አሻራ እንዲ የሰው እጅ የደከመበት ነው ለማለት ከርቀቱ የተነሳ ያዳግታል።

መምህራን የሚሆኑ ሐጌና ዘካሪያስ ትንቢት የተናገሩላቸው የተለየ ቤተመቅደስ ሥራ ተብሎ « በከልዕ ዕዝራ » እንደተነገረ በፍቅራን አሃው አብርሀና አጽብሐ ትጋት በነገሡ በ፲፮ኛው ዓመት በከሳቱ ብርሃን ሰላማ ቡራኬ ጳጳስ በሆኑ በሦስተኛው ዓመት በእግዚአብሔር ረድኤት በልዩ ብርቅና ድንቅ ሁኔታ ዓለራ ሁለቱ ቤተ መቅደስ ተሠርቶ አለቀ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ጥር ፳፩ ቀን በጳጳሱ አቡነ ሰላማ የእመቤታችን ጽላትና ቤተ ክርስቲያኑ ታባርኮ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። በዚህ ጊዜ ካህናቱ « ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሀ ዘተሰብሀ » እያሉ ከታቦተ ሕጉ ፊት ሲያሸበሽቡ መላእክት በዝማሬ እመቤታችንን አጅበው ጌታ በሊቀ ካህናትነት ከብር ተቀምጦ ወዳለበት መንበረ ስብሐት ስትገባ ነገሥታቱና አባቶች ይህ ድንቅ ምሥጢር ተገልጾላቸዋል።

የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጠናቆ እንዳለቀና የአናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ እረፍት ተከብሮ በዋለበት ጥር ፳፩ ቀን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚች ቅድስት ቦታ ላይ በአመሳለ ሊቀካህናት አምሞ በመታየት ይችን ቦታ ለአንች የድንግልናሽ መታሰቢያ ሰጥቻለሁ በዚህም ቦታ የሚያገለግሉ በንጽህና



ድንግልና የጸኑ መነኮሳት ይሁኑ። በዚህም ዓለት ባንች ተማጽኖ ዚህ ቦታ ደርሶ የጸለዩ በለምሽ እጣንና መብራት የሰጠውን ቅር ብፁልሻለሁ በማለት በማይታበል ቃሉ ለእናቱ ቅድስት ንግል ማርያም ይችን ቦታ በደናግል መነኮሳት ስትገለገል ንድትኖር ለድንግልናዋ መታሰቢያ ሰጥቷታል።

በዚሁ ጊዜ ጳጳሱ ሰላማ እመቤታችን ከልጇ ይህን ደግ ል ኪዳን ተቀብላ በግልጽ ወደ ቤተ መቅደሱ ስትገባ ስላዩ ተሰበሰበው ህዝብ ሁኔታውን አስረድተውና ገልጸው ጽርሀ ለውን መርጡል - አርያም ያለውን ማርያም በማለት አያይዘው ርጡለ ማርያም ( የማርያም አዳራሽ ) ብለዋታል። ቀጥሎም

* « አንተ ይእቲ ርእሰ ርኡሳን መርጡለ ማርያም »

የደብሯ መጠሪያ እንዲሆን ለየሙ። የአስተዳዳሪው

ማእረግ ደግሞ ርእሰ ርኡሳን ይበላል ብለው ወሰኑ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ኤፍሬም ደምት የነበረ ስም ለታሪክ ተቀምጦ መርጡለ ማርያም ጠሪያዋ ሆነ። አብርሀና አጽብሐም በርከት ያሉ አልባሳትን ዋየ ቅድሳትንና ውድ የወግ ዕቃዎችን ዘውዳቻውንና ህለተ ርቃቸውን የተሰያየ የወርቅ አክሊላትን በወርቅ የተገበገቡ ጽሐፍትን ሰጥተው ቤተክርስቲያኗን ገዳምና ደብር አድረገው ርዓት ሠርተወዋል። እንደ ደብርነቷ ሺህ መዘምራን በማኅሌት ክለውላታል። እንደ ገዳምነቷ ደግሞ ሰማንያ ዲያቆናት ድንግልና የጸኑ ንጽሕ ጠብቀው የሚኖሩ በቤተ መቅደስ በቅዳሴ

እንዲያገለግሉ ወሰነዋል። የሚያስተዳድራቸው በንፅህና በድንግልና የጸና ቆሞስ እንዲሆን ደንግገውላታል። ስለ ደብሯ መከበርም በድሉ ወይም ተበድሎ በቤተክርስቲያኗ በመማጸን ገብቶ ደውል ከደወለ ወንጀለኛም ቢሆን እንዳይታደንባት አንዳች ክፉ ነገርም እንዳይደርስበት አውጀዋል። ይልቁንም ካህናት ሥዕል፣ መስቀል ይዘው ከባለ ጋራው እንዲያስታርቁት አዝዘዋል።

ጳጳሱ ከሳቴ ብርሃን ሰላማ የኦሪትና የሐዲስ ምሁር የሆነ ሚናስን በአንብሮተዕድ ቅሰናና ቁምስና ሹመው ወደ አብርሀና አጽብሐ በማቅረብ <u>ርእሰ ርኡሳን ዘመርጡለ ማርያም</u> ብለው ለመጀመሪያ ጊዜ አሹመውታል። የሚያስተዳድረውም ቦታው <u>ከእናውጋ</u> እስከ <u>ዘንጓን</u>፣ <u>ከሰማ</u> እስከ <u>ቀማ</u> ብለው ከልለውላታል።

ጳጳሱም በመንፈሳዊ ስልጣናቸው በሰበካዋ ውስጥ አባብ ቢነድፍ መርዙ ሰው እንዳይጎዳ አራዊት ሰውና እንስሳን እንዳይቃወሙ ቃል አሳድረውበታል። እስካሁን ድረስ በግና ፍየሉ ከውጭ ሲያድር አራዊት ሳይተናኮሉት በሰላም እስካሁን ይኖራል ምክንያቱም በረድኤተ እግዚአብሔር ተጠብቃ እንድትኖር ባርከዋታልና ወደዚህች ቦታ አምና የተጠጋ ችግረኛም ጾም እንዳያድርባት ቀድሰዋታል።

ነገሥታቱም በግራና በቀኝ የቅዱስ ሚካኤል በመካከል የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ያሉበት የብር መጾር መስቀል ሠጥተዋል። ይህ መስቀል የተጣላ የማስታረቅ



የታመመ የመፈወስ መንፈሳዊ ኃይል ያለውና ለወጣበት ጉዳይሁሉ መፍትሄና ፈውስ የሚሰጥ በመሆኑ <u>አፍር አይገባ</u> የሚል ቅጽል ስም ተሠጥቶታል። ውዳሴና ቅዳሴ ያለማሰለስ አዘውትሮ ከዓመት እስከ ዓመት እንዲገለገል ነገሥታቱ በስልጣነ መንግሥት ጳጳሱ በስልጣነ ክህነት ሥርዓትና ሕግ ሠርተውላታል።

ይህ ሥርዓት ከክርስቶስ ልደት ከ፫፻፴፫ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፰፻፷፰ ዓ.ም ጸንቶ በዓስራ ሁለት ቤተመቅደስ ዘወትር በእግዚአብሔር ስም ሲቀደስ ይኖራል።

በኋላ ግን ዮዲት ጉዲት በመነሳት መሥዋእተ ኦሪት ሲሰዋባቸው ኑረው በአብርሀና አጽብሐ በመታደስ በሰላማ ተቀድሰው የመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም የተሠዋባቸውንና ወንጌል የተሰበከባቸውን ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ለማጥፋት ሆን ብላ ተነሳች። ወዲያውኑ የአብርሀ ወአጽብሐን ቤተ መቅደስ ለማቃጠል ወደ መርጡለ ማርያም ገሰገሰች። የጉዲትን መምጣት የሰሙ ካህናት የእመቤታችንን ጽላተ ሕግና የከበሩ የወግ ዕቃዎችን በጠቅላላ አልባሳትንና ንዋየ ቅድሳትን ይዘው በግምት ፲፭ ኪሎ ሜትር ርቆ ወደሚገኘው <u>ሸብር አምባ</u> ዋሻ ገቡ። በዚህ ጊዜ የሚመራው ለጥቶ ከሕንጻ ቤተክርስቲያኑ ሥር ተሸጉጦ የቀረ አንድ ዓይነ ስውር ተማሪ በወራሪው ወታደር ተይዞ ወደ ጉዲት ወሰዱት። ዮዲት ጉዲትም ወዲያው ከደብሯ እንደደረሰች ለማቃጠል ሞክራ አቅቷት ቀርቶ ነበርና የሚቃጠልበትን ሁኔታ እንዲነግራት ጠየቀችው።

ዓይነስውሩም የቤተክርስቲያኗን መቃጠል ለአልወደደ አላውቅም በማለቱ ወታደሮቿን ጡርታ እስኪናገር ድረስ እንዲገርፉት አዘዘች፡፡ ወታደሮቹም ለውየውን በጅራፍ እየገረፉ በእሳት እየለበለቡ ሰቃይ አበዙበት፡፡ ከመከራው ጽናት የተነሳም ፣ አባቶቻችን **በሰም** ካልሆነ በስተቀር በእሳት ሲቃጠል አይችልም ሲሉ ሰምቻለሁ ሰም ለብጠሽ ለማቃጠል ሞክሪ አላት፡፡ እርሷም ሰም ተዘርፎ እንዲመጣ አዝዛ ተዘርፎ በመጣው ሰም አለስብጣ በወርቅና በእንቁ የተሠራውን ፲፪ ቤተ መቅደስ በእሳት እንዳልነበረ አደረገችው፡፡

በልዩ ልዩ ቅርጽ በወርቅና በእንቁ ተሸልሞ የነበረ የአስራ ሁለቱ ቤተመቅደስ አካል ሥጋ የተለየው ዐፅም መሰለ፡፡ የድንጋዩ ሐረግ ቅርጽ ብቻውን አርቃኑን ቆሞ ቀረ፡፡ ሙሴ ኢትዮጵያን ሲጎበኝ ያመጣውን ባለ ፮ ማዕዘን ድንጋይ ለባብራ ጣለችው፡፡ ይህ ባለ ስድስት ማዕዘን ገጽ ድንጋይ የሙሴ ድንጋይ እስካሁን ድረስ በአደባባዩ የመስቀል ቅርጽ ተደርጎለት ቆሞ ይገኛል፡፡

ጉዲትም ለ፵ ዓመታት ያህል እየተዘዋወረች አብያተ ክርስቲያናትን ስታቃጥል ካህናትን ስታስገድል ኖራ ሞተች፡፡ የመርጡ ለማርያም ጽላትም ለ፵ ዘመናት ከተቃጠለው ታላቅ ቤተክርስቲያን አጠገብ በድንኳን አድርገው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ኖረዋል፡፡ ጉዲት ከሞተች በኋላ በ፱፻፷፰ ዓ.ም አንበሳ ውድም በኢትዮጵያ ተመልሶ ነገሠ፡፡ በጉዲት የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ አቋቋመ፡፡ የመርጡስ ማርያም



ቤተክርስቲያን ግን በጣም ታላቅና ሰፊ ከመሆኑም በላይ አሠራሩ ልዩ ባለሙያና ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ መልሶ እንደነበር ለመሥራት አልተቻለም፡፡ በአንጻሩ ግን ከተቃጠለው መቅደስ መካከል በራሱ ስም ዛሬ በአገልግሎት ላይ የሚገኘውን ቤተክርስቲያን አንድ መቅደስ አድርጎ ሠራ፡፡ ሙሉ ንዋየ ቅድሳትንና መጻሕፍትን ሰጥቶ በቀድሞው አብርሀ ወአጽብሃ ሥርዓት እንድትተዳደር አዘዘ፡፡ በተጨማሪም በቤተመቅደሱ የሚያገለግሉ ካህናት እንደቀድሞው ደናግልና መነኮሳት እንዲሆኑ ሥርዓት ሠራ፡፡ ከእርሱ በኋላ የተነሱ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ ገዳሚን ሲንከባከቧት ኖረዋል፡፡

አፄ በእደማርያም በ፲፬፻፷ ዓ.ም ቤተክርስቲያኗን አድሰዋታል፡፡ ባለቤታቸው ንግሥት እሌኒም አራት በሮች ትታ በአንባው ዙሪያ የእሌኒ ውድም የተባለውን ቅጽር አሳንጻዋለች፡፡ ወደ አንባው የሚያስገቡት በሮችም አበው ( አቦ ) በር ዘገብርኤል በር ዘለሚን በርና ምዕራብ ( ደጀሰላም ) በር የተባሉት ከእግረ ቤተ ክርስቲያኑ የሚያስገቡ ናቸው፡፡ በመጨረሻም ንግሥት እሌኒ የከበር ልብሷን ጨምራ ሰጥታለች፡፡

በዚህ ሁኔታ እስከ አፄ ልብነ ድንግል ድረስ ልዩ እንክብካቤ ሲደረግለት ቆይቶ የግራኝ መሐመድ ወረራ ሆነ፡፡ በዚህ ዘመን አፄ ልብነ ድንግል እንደሞቱ ልጃቸው ገላውዲዎስ ንግሥ ከግራኝ ጋር ለመዋጋት ሰልፍ አድርጎ ሳለ ግራኝ ድል እንዲሆንላቸው ከጎንደር ተነስተው ጥር ፳፭ ቀን ፲፭፻፴፭ ዓ.ም

መርጡስ ማርያም መጥተው ብፅአት ገቡ:: ብፅአቱም የግራኝ መሐመድን ሽንፈት ያሳየሽኝ እንደሆነ የልጁን የገላውዲዎስን የክብር ልብስና የኔን የክብር ልብስ አስጣስሁ ብለው እንደተመለሱ ጎንደር ውስጥ ፎገራ ዘንተራ ከተባለው ቦታ ጦርነት ተደርጎ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፭፻፴፭ ዓ.ም ግራኝ መሐመድ በጥይት ተመትቶ ሞተ:: አፄ ገላውዲዎስ በእናታቸው ብፅአት መሠረት የግራኝ መሐመድን የክብር ቀሚስ፣ የእናቲቱንና የራሱን የክብር ልብስ፣ የራሱን የብራና ዳዊት ለድርጎ ለመርጡስ ማርያም በብፅቱ መሠረት ሰጠ:: በዚህም መሠረት በእመቤታችን ኃይል ግራኝን ድል ስለተመታና ሠራዊቱ ስለተማረከ **<u>የግራኝ እመቤት</u>** እየተባለች እስካሁን ድረስ ትጠራለች::

በአሁኑ ወቅት በአንባዋ ላይ በአንድ ቅጽር ውስጥ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: እነዚህም የሥላሴና የገብርኤል፣ የእመቤታችንና የአብርሀ ወአጽብሐ ቤተመቅደስ የነበረው ግንብ ናቸው::

በዚህች ቅድስት ቦታ በርካታ ውብና ብርቅ የሆኑ ቅርሶች ይገኙባታል::

ለአስረጅ ያህል ብንጠቅስ ኦሪትንና ወንጌልን በአንድነት የሚያስቀጥር ረጅም አድሜ ያለው ቤተ መቅደስ በዐይን ለዓየው የአበውን ዐፅም በአንባ የሚያዘክር የትዝታ ዓምድ ነው:: ሙሴ ያመጣው ባለ ፮ ገጽ የድንጋይ ሐውልት ከኦሪት ሌዋውያን ጀምሮ እስከ ራዕይ ዮሐንስ በህብረ ቀለማት የተጻፉና በወርቅ የተንበገቡ



በርካታ ቅርስነት ያላቸው መጻሕፍት በ፫፻ ዓ.ም የነበረ የአብርሀ ወአጽብሐ የወርቅ መስቀል በ፲፪፻፸፭ ዓ.ም የተጻፈ ግእዙን በግእዝ የሚተረጉም ሰርባአቱ ወንጌል የአፄ ገላውዲዎስ ዳዊት፣

- የአፄ በእደ ማርያም የራስ ቁርና የብር ዋንጫ
- የንግሥት እሌኒ የክብር የወርቅ መስቀሎች
- ልዩ ልዩ የብርና የወርቅ አክሊሎች
- የወርቅና የብር ከበሮ
- የብር መነሳንሶች
- የግራኝ መሐመድ የክብር ቀሚስ
- የአብርሀ አጽብሐ የብር ዘውድ
- የእቴጌ ምንትዋብ ( የአፄ ቴዎድሮስ ባለቤት )

የክብር ልብስና እንዲሁም የመሳፍንቶችና የመኳንቶች በወርቅና በብር የአጌጡ የአጌጡ የክብር ልብሶችና የጻድቁ ዮሐንስ የክብር ልብስ ሲሆኑ ለቁጥርና ለጽሑፍ በርካታ የሆኑ የሀገር ቅርሶች የሚገኙበት የታሪክ ቦታ ናት::

በማኅሌትና በሰዓታት እንዲሁም በቅዳሴ ከዓመት እስከ ዓመት ያለማቋረጥ እግዚአብሔር ይመስገንበታል ቀዳስያኑም ሆኑ መምህራን በድንግልና የጸኑ ደናግል መነኮሳት ናቸው::

ለዚህም በዋቢነት የምንጠቅሳቸው አብርሀ ወአጽብሐ የአቡነ ሰላማ ገድል ለኢትዮጵያ አድባራት ርእስ ለመሆኗ ድርሳነ ዑራኤል ዘሰኔ ምዕ. ፪ ቁ. ፲፭ ላይ አሐተኒ ርእሰ አድባራት ዘኢትዮጵያ በማለት ቀደምትነቷን ያስረዳል::

## ዋቢ መጻሕፍት


- ምንታዌ ምርዓተ ማኅሌት ዘቅዱስ ያሬድ ሊቅ
  በመሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ
  አዲስ አበባ /መቀሌ
- የግራኝ አህመድ ወረራ
  በተክለ ጻዲቅ መኩሪያ
  አዲስ አበባ [illegible]
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ
  በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ጠ/ጽ/ቤት የተዘጋጀ
  መስከረም [illegible] አዲስ አበባ
- ዋዜማ
  በብላቴ ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴ
- የመጻሕፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት
  አዲስ አበባ [illegible]
- ፈለግ መጽሔት
  ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፩ የካቲት [illegible]
- መለከት መጽሔት
  ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲ ነሐሴ [illegible]
- መለከት መጽሔት
  ፩ተኛ ዓመት ቁጥር ፩ ነሐሴ [illegible]
- ሐመር መጽሔት
  ፩ተኛ ዓመት ቁጥር ፩ ሚያዝያ [illegible]






- ሐመር መጽሔት
  ፩ተኛ ዓመት ቁጥር ፫ ጥቅምት/ህዳር [illegible]
- የትግራይ ቱሪዝም ቢሮ ካዘጋጀው ፖንፍሌት
- ሐዋርያ ጋዜጣ
- ገድለ አቡነ አረጋዊ
- ስዒ ዘርዓ ያዕቆብና ቀደምት አበው ጻድቃት
  ስለ ግሸን ደብረ ከርቤ የተናገሩት ሕያው ቃል
  በግሸን ደብረ ከርቤ ማርያምና አካባቢዋ
  መንፈሳዊ ልማታዊ ሥራ ኮሚቴ የተዘጋጀ
  አዲስ አበባ መስከረም [illegible]
- ድርሳነ ዑራኤል
- የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የታሪካዊ ቅርስ
  አስተዳደር
  አንኛው ሞሬ መጽሐፍ
- ሐመር መጽሔት
  ፩ተኛ ዓመት ቁጥር ፪ መጋቢት [illegible]
- መለከት መጽሔት
  ፩ተኛ ዓመት ቁጥር ፩ ነሐሴ [illegible]
- ሐመር መጽሔት
  ፩ተኛ ዓመት ቁጥር ፪ ግንቦት [illegible]
- ዲ.ኪዳኑ ከየካ ሚካኤል ካዘጋጀው ፖንፍሌት

- ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ
  ቁጥር ፩ [illegible] አዲስ አበባ
- ገድለ ክርስቶስ ሠምራ
- ገድለ ስባ እየሱስ ሞአ
- *By vast Expense and hideous pain, The Rock a Church become, " ( Hob loudly new History of Ethiopia " 1684 ).*
- የመርጦ ለማርያም ገዳም ታሪክ
  በመ/ማ/ገ/ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት
- ታሪክ ነው ገበያ የሁሉ መዋያ
  በአለቃ አያሌው ታምሩ
- ክርስትና በኢትዮጵያ ክፍል አንድ
  በገ/የሐንስ ገ/ማርይም
  M.A
  አዲስ አበባ የካቲት [illegible]
- መጽሐፈ ምክር በኪሰ
  በዶ/ር ሊሳይያስ ስለሜ
  አዲስ አበባ [illegible]
- መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ
  ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ
  በኪዳነ ወልድ ክፍሌ
  አዲስ አበባ [illegible]


# ወሎ




ስፈርት 1:71·6 ኪ.ሜ

## ጎንደር




**መግለጫ**

- ኢንተርናሽናል ወሰን
- የክፍለ ሀገር ወሰን
- ትልልቅ ከተማ
- ሌላ ከተማ
- የዘወትር መንገድ
- ሐይቅ

መስፈርት 1፡71·6 ኪ.ሜ

## ትግራይ





**መግለጫ**

- ኢንተርናሽናል ወሰን
- የክፍለ ሀገር ወሰን
- ዋና ከተማ
- ትልልቅ ከተማ
- ሌላ ከተማ
- የዘወትር መንገድ
- ሐይቅ

መስፈርት 1፡71·6 ኪ.ሜ

## በጣና ሐይቅ ደሴቶች የሚገኙ ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያናት ካርታ




| | |
|---|---|
| 1 | ደብረ ሲና (ጎርጎራ) |
| 2 | [illegible] ማርያም |
| 3 | መንዳባ ገዳም |
| 4 | [illegible] |
| 5 | ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም |
| 6 | ደቅ ደሴት |
| 7 | ናርጋ ሥላሴ |
| 8 | [illegible] |
| 9 | [illegible] |
| 10 | ክብራን ገብርኤል እና እንጦንስ ደሴቶች |
| 11 | ደብረ ማርያም |
| 12 | ዑራ ኪዳነ ምሕረት፣ መሐል ዘጌ ጊዮርጊስ፣ አዝዋ ማርያም፣ ይጋንዳ ተክለ ሃይማኖት፣ [illegible] በትረ ማርያም |
| 13 | ገሊላ |
| 14 | ምጽርሃ |
| 15 | [illegible] ማርያም |
| 16 | ክርስቶስ ሠምራ |

መደበኛ መስመር ——— የጉብኝት መስመር ------------